# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ገላትያ ሰዎች

*አስተዋፅኦ*

*መግቢያ* (1፥1-10)
- (ሀ) *ሰላምታ* (1፥1-5)
- (ለ) *ከጸጋው ወንጌል ፈቀቅ ማለታቸው እንዳስደነቀው* (1፥6-10)

I. *ጳውሎስ የወንጌሉና የጥሪው ሥልጣን ከማን እንደ ሆነ በመግለጽ እውነተኛነቱን ደግፎ መቆሙ* (1፥11—2፥21)
- (ሀ) *ወንጌሉን የገለጠለት ክርስቶስ እንደ ሆነ* (1፥11-24)
- (ለ) *ያዕቆብ፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ ይህን እንደ ተገነዘቡና የትብብር ቀኝ እጃቸውን እንደ ሰጡ* (2፥1-10)
- (ሐ) *ጳውሎስ ጴጥሮስን በተቃወመው ጊዜ የዚህን እውነተኛነት እንደ አስረዳ* (2፥11-21)

II. *ጳውሎስ ለወንጌሉ መልእክት መቆሙ (አስተምህሮን በሚመለከት)* (3፥1—4፥31)
- (ሀ) *መንፈስ ቅዱስንና አዲስ ሕይወትን መቀበል የሚቻለው በእምነት እንጂ በሥራ እንዳልሆነ* (3፥1-14)
- (ለ) *ድነት በተስፋ ቃል እንጂ ሕግን በመጠበቅ እንዳልሆነ* (3፥15-24)
- (ሐ) *በክርስቶስ የሚያምኑት የእግዚአብሔር ልጆች እንጂ ባሮች እንዳልሆኑ* (3፥25—4፥7)
- (መ) *ድርጊታቸውን ቆም ብለው እንዲመረምሩ፤ ሐዋርያው ጳውሎስ የገላትያ ሰዎችን አጥብቆ ማሳሰቡ* (4፥8-20)
- (ሠ) *ከሕግ በታች የሚኖሩ ባሮች እንጂ የእግዚአብሔር ልጆች አለመሆናቸው* (4፥21-31)

III. *ጳውሎስ፣ ወንጌሉ ለሚሰጠው ነጻነት (በተግባር የሚገለጽ) መቆሙ* (5፥1—6፥10)
- (ሀ) *የክርስቲያን ነጻነት በጸጋ ከመዳኑ ጋር የተያያዘ እንደ መሆኑ* (5፥1-12)
  1. *ክርስቲያን ነጻነቱን ጠብቆ መኖር እንዳለበት* (5፥1)
  2. *በሙሴ ሕግ መሠረት መገረዝ የሚያስከትለው ውጤት* (5፥2-12)
- (ለ) *ክርስቲያን ነጻነቱን የሥጋ ምኞት መፈጸሚያ መንገድ ማድረግ እንደሌለበት* (5፥13-26)
  1. *የፍቅር ሕግ* (5፥13-15)
  2. *የሥጋን ምኞት በመፈጸም ሳይሆን፣ በመንፈስ መመላለስ* (5፥16-26)
- (ሐ) *የክርስቲያን ነጻነት የክርስቶስን ሕግ በመፈጸም መገለጽ እንደ አለበት* (6፥1-10)
  1. *አንዱ የሌላውን ከባድ ሸክም መሸከሙ* (6፥1-5)
  2. *ቃሉን የሚያስተምሩትን አገልጋዮች መርዳት* (6፥7)
  3. *በጎ ነገር ከማድረግ አለመታከት* (6፥7-10)

*መደምደሚያ* (6፥11-18)

**ጸሐፊው፤** *ጳውሎስ*

**ዋና ሐሳብ፤** *በእምነት አማካይነት በጸጋው መዳን*

**የተጻፈበት ጊዜ፤** *በ49 ዓመተ ምሕረት ሳይሆን አይቀርም*

### ታሪካዊ ዳራ

ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው (1፥1፤ 5፥2፤ 6፥11)፣ "በገላትያ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት" ነው (1፥2)። አንዳንዶች፣ የገላትያ ሰዎች በሰሜን ገላትያ ይኖሩ የነበሩት ጎሎች የተባሉ ነገዶች ናቸው ብለው ያምናሉ። ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው፣ እርሱና በርናባስ የመጀመሪያውን ሐዋርያዊ ጉዞ ባደረጉበት ጊዜ (ሐሥ 13—14)፣ ወንጌልን ሰብከው አብያተ ክርስቲያናትን ለመሠረቱባቸው በደቡብ የገላትያ አውራጃ ክልል ለሚገኙ ከተሞች ማለትም ለጲስድያ አንጾኪያ፣ ለኢቆንዮን፣ ለልስጥራና ለደርቤ መሆኑ ይበልጥ አሳማኝ ነው። ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው፣ በሶርያ ወደምትገኘው ወደ ላከችው ወደ አንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ከተመለሰ ከጥቂት ጊዜ በኋላና ከኢየሩሳሌም ጉባኤ (ሐሥ 15) ቀደም ብሎ ባለው ጊዜ ነው ማለቱ ይበልጥ ተቀባይነት አለው።

በገላትያ ምእመናን ዘንድ የተፈጠረው ዋና ችግር፣ ለኢየሩሳሌም ጉባኤ ቀርቦ ውይይት ከተደረገበትና ውሳኔ ከተሰጠበት ጉዳይ ጋር አንድ ነው (ምናልባት በ49 ዓ.ም፤ ከሐሥ 15 ጋር ያነጻጽሩ)። ዋናው ጉዳይ የሚከተሉትን ሁለት ጥያቄዎች ይዞአል፤ (1) ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታና አዳኝ እንደ ሆነ ማመን፣ ለድነት የሚያስፈልግ ብቸኛ ጉዳይ ነውን? (2) ወይስ በክርስቶስ ድነትን ለማግኘት፣ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ለሚገኙ አንዳንድ የአይሁድ ልምምዶችና ሕጎች መታዘዝ ያስፈልጋልን? ጳውሎስ የገላትያን መልእክት የጻፈው፣ ሕጉን በሚመለከት የተነሣው አከራካሪ ጉዳይ ለኢየሩሳሌም ጉባኤ ቀርቦ በተገቢው ሁኔታ ውይይት ከመደረጉና ቤተ ክርስቲያን ውሳኔዋን በግልጽ ከማሳወቋ በፊት ሳይሆን አይቀርም። ይህም ሐዋርያው ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች የጻፈው መልእክት የመጀመሪያው መልእክቱ ነው ማለት ነው።

### ዐላማ

አንዳንድ አይሁዳውያን አስተማሪዎች መገረዝንና የሙሴን የሕግ ቀንበር ለድነትና ወደ ቤተ ክርስቲያን በአባልነት ለመጨመር አስፈላጊ ነገር አድርገው በእነርሱ ላይ በመጫን፣ በቅርብ ጌታን የተቀበሉትን የገላትያ ክርስቲያኖች እያናወጡና እያወኩ እንደ ሆነ ጳውሎስ ተገንዝቦአል። ጳውሎስ ይህን ሰምቶ መልእክቱን የጻፈው፣ (1) መገረዝና የመሳሰሉት ሕጉ የሚጠይቃቸው የብሉይ ኪዳን ሥርዐቶች፣ በአዲስ ኪዳን በክርስቶስ በኩል ድነትን በሰጠው በእግዚአብሔር የጸጋ ሥራ ውስጥ ምንም ቦታ እንደሌላቸው በመግለጽ አጥብቆ ለመቃወም እና (2) መንፈስ ቅዱስንና መንፈሳዊ ሕይወትን የምንቀበለው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንጂ፣ የብሉይ ኪዳንን ሕግ በመፈጸም እንዳልሆነ እንደ ገና በግልጽ ለማረጋገጥ ነው።

### ቅኝት

ከዚህ መልእክት ይዘት መረዳት እንደሚቻለው፣ በገላትያ የነበሩ የጳውሎስ አይሁድ ባላንጣዎች፣ ጳውሎስ በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የነበረውን ተቀባይነት ለማሳጣት (ዝቅ ለማድረግ) በግል ይቃወሙት የነበረ ይመስላል። የጳውሎስ ተቃዋሚዎች እርሱን የሚከሱት በሚከተሉት ጉዳዮች ነበር፤ (1) ከመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት መካከል ስላልሆነ እውነተኛ ሥልጣን የለውም በማለት (ከ1፥1:7:12፤ 2፥8-9 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (2) የእርሱ መልእክት በኢየሩሳሌም ከተሰበከው ወንጌል የተለየ ነው በማለት (ከ1፥9፤ 2፥2-10 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (3) በጸጋ ላይ የተመሠረተ መልእክቱ፣ ሕግ የለሽ ኑሮን ያስከትላል በማለት (ከ5፥1:13:16:19-21 ጋር ያነጻጽሩ)።

ጳውሎስ በእርሱ ላይ ለቀረቡት ለሦስቱም ክሶች በቀጥታ መልስ ሰጥቶአል። (1) የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ይሆን ዘንድ የተሰጠው ሥልጣን፣ በቀጥታ ከእግዚአብሔር የተቀበለው፣ ያዕቆብ፣ ጴጥሮስና ዮሐንስም ያጸደቁት ሥልጣን መሆኑን በመግለጽ የሥልጣኑን እውነተኛነት በጽናት አስረድቶአል (ምዕ 1—2)። (2) የድነት ወንጌል በክርስቶስ በማመን በጸጋው የተገኘ መሆኑን ጥልቅ በሆነ ስሜት በመግለጽ በጽናት ቆሞአል (ምዕ 3—4)። (3) በመጨረሻም ሐዋርያው ጳውሎስ እውነተኛው የክርስቶስ ወንጌል በአንድ በኩል ከአይሁድ ሕግ ባርነት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከኀጢአትና ከሥጋ ሥራ ሁሉ ነጻ የሚያወጣ መሆኑን በጽናት ይናገራል። እውነተኛ የክርስቲያን ነጻነት፣ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መመላለስንና የክርስቶስን ሕግ መፈጸምን ያካትታል (ምዕ 5—6)።

የገላትያ መልእክት በገላትያ፣ በአንጾኪያና በኢየሩሳሌም (ሐሥ 15፥1-2:5) እንዲሁም በአብዛኞቹ ጳውሎስ ባገለገለባቸው ቦታዎች ሁሉ ጳውሎስን የተቃወሙትን ከአይሁድ ወገን የሆኑትን አማኞች ባሕርይ በዝርዝር ያመለክታል። ጳውሎስ እነዚህን አማኞች አደናጋሪዎች፣ አጣማሚዎችና (1፥7) አሰናካዮች (5፥7) እንደ ሆኑ ይናገራል፤ በተጨማሪም ውጫዊ በሆነ ነገር ለመታየት የሚፈልጉና የክርስቶስ መስቀል ሲሰበክ ከሚመጣው ቍጣ የተነሣ

የሚመጣውን ስደት የሚሸሹ ሰዎች መሆናቸውን ያስገነዝባል (6፥12)። በተዘዋዋሪ መንገድ ጳውሎስ እነዚህ ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰዎችን ደስ የሚያሰኙ (1፥10)፤ ሐሰተኛ ወንድሞች (2፥4)፣ መገረዝን ከሚደግፉ ወገን የሆኑና (2፥12) ለራሳቸው ጥቅም እውነተኛ የሆነውን ነገር የሚያደበዝዙ (3፥1) መሆናቸውን ይገልጻል።

### ልዩ ገጽታ

ይህን መልእክት አራት ገጽታዎች ልዩ ያደርጉታል፤ (1) ወንጌል የቱን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ የሚገልጽና በዚህ እውነት የቆመ፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ እጅግ ጠንካራ ማስረጃን የያዘ መልእክት ነው። ጳውሎስ ሐሰተኛ አስተማሪዎችን ለመቃወምና (1፥8-9፤ 5፥12) በቀላሉ የተታለሉትን የገላትያ ምእመናን ለመገሠጽ (1፥6፤ 3፥1፣ 4፥19-20) የጻፈው በመሆኑ፣ የመልእክቱ ድምፀት ኀይለኛ፣ የጋለ ስሜትና አስቸኳይነት ያለው ነው። (2) ከሁለተኛ ቆሮንቶስ ቀጥሎ ስለ ግል የሕይወት ታሪክ የሚያወሱ ማገለጫዎችን በመያዝ በሁለተኛ ደረጃ ይገኛል። (3) ከጳውሎስ መልእክቶች መካከል ይህ ለብዙ አብያተ ክርስቲያናት ይደርስ ዘንድ በግልጽ የተጻፈ ብቸኛ መልእክት ነው (ወደ ኤፌሶን ሰዎች የተጻፈውን መልእክት መግቢያ ይመ)። (4) የመንፈስን ፍሬ ዝርዝርና (5፥22-23) በአዲስ ኪዳን ውስጥ አያሌ የሆነውን የኀጢአተኛ ተፈጥሮን ድርጊት ዝርዝር ይዞአል (5፥19-21)።

### ገላትያን ማንበብ

ሙሉውን አዲስ ኪዳን መጽሐፍ በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ የገላትያ መልእክት ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በስምንት ቀን መነበብ ይኖርበታል፦

❑ 1 ❑ 2 ❑ 3፥1-14 ❑ 3፥15-25 ❑ 3፥26—4፥20 ❑ 4፥21—5፥15 ❑ 5፥16-26 ❑ 6

*ማስታወሻ*

# 1

1 ከሰዎች ወይም በሰው ከተላከው ሳይሆን፣
በኢየሱስ ክርስቶስና ከሙታን ባስነሣው
በእግዚአብሔር አብ ሐዋርያ ከሆነው ከጳውሎስ፤
2 አብረውኝም ካሉት ወንድሞች ሁሉ፤
በገላትያ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት
3 ከአባታችን ከእግዚአብሔር፣ ከጌታም
ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ
ይሁን። 4 እንደ አምላካችንና እንደ አባታችን
ፈቃድ፣ ከዚህ ክፉ ዓለም ያድነን ዘንድ ስለ
ኀጢአታችን ራሱን ሰጠ፤ 5 ከዘላለም እስከ
ዘላለም ለእርሱ ክብር ይሁን፤ አሜን።

## ወንጌል አንዲት ናት

6 በክርስቶስ ጸጋ የጠራችሁን እርሱን
ትታችሁ፣ ወደ ተለየ ወንጌል እንዲህ ፈጥናችሁ
መዞራችሁ ደንቆኛል፤ 7 እንደ እውነቱ ከሆነ
ሌላ ወንጌል የለም። የሚያደናግሯችሁና
የክርስቶስን ወንጌል ለማጣመም ጥረት
የሚያደርጉ አንዳንድ ሰዎች አሉ። 8 ነገር
ግን እኛም ብንሆን ወይም የሰማይ መልአክ፣
ከሰበክንላችሁ ወንጌል የተለየ ወንጌል
ቢሰብክላችሁ እርሱ ለዘላለም የተረገመ
ይሁን። 9 ቀደም ብለን እንዳልነው፣ አሁንም
ደግሜ እላለሁ፤ ማንም ከተቀበላችሁት
ሌላ የተለየ ወንጌል ቢሰብክላችሁ፣

1፥1 ቍ 11፡12፡15፡16፤ ሐሥ 24፥9፤ 15፥20፥24፤ 1ቆሮ 1፥1
1፥2 ሐሥ 16፥6፤ ፊል 4፥21
1፥3 ሮሜ 1፥7
1፥4 ማቴ 20፥28፤ ሮሜ 4፥25፤ 1ቆሮ 1፥20፤ 15፥3፤ ገላ 2፥20፤ ፊል 4፥20
1፥5 ሮሜ 11፥36
1፥6 ቍ 15፤ ሮሜ 8፥28፤ 2ቆሮ 11፥4
1፥7 ኤር 23፥16፡36፤ ሐሥ 15፥24፤ ገላ 5፥10
1፥8 ቍ 11፡16፤ ሮሜ 9፥3፤ 1ቆሮ 15፥1፤ 2ቆሮ 11፥4፤ ገላ 2፥2 1፥9 ሮሜ 16፥17

**1፥4 ከዚህ ክፉ ዓለም ያድነን ዘንድ፤** ምናልባት ይህ ጥቅስ በአዲስ ኪዳን አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በሚገባ የታወቀ የጥንት የእምነት መግለጫ ሊሆን ይችላል:: የክርስቶስን ሞት የኀጢአት ይቅርታን ከማግኘትና “ከዚህ ክፉ ዓለም” ነጻ ከመሆን ጋር ያያይዘዋል:: የክርስቶስ የማዳን ዐላማ አስፈላጊነት የዚህን ዓለም ኀብረተ ሰቦች ከሚገዛው ከክፋው አማኞችን ነጻ ማውጣት ነው:: መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ኀምሳ ቀን ከወረደ በኋላ የተሰበከው የመጀመሪያው የወንጌል መልእክት፣ “ከዚህ ጠማማ ትውልድ ራሳችሁን አድኑ” (ሐሥ 2፥40) የሚለውን የያዘ ነው:: አማኞች እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መኖር እንጂ በዓለም ሕዝብ ዘንድ በስሩት ተሠራጭቶ በሚገኘው ፋይዳ፣ ጥበብ፣ ሐሳብ፣ የተበላሸ ምኞትና ሥጋዊ ደስታ መገዛት የለባቸውም (ከሮሜ 12፥2 እና ማብ፤ ከቲቶ 2፥14 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 2022 ላይ፣ *“ክርስቲያን ከዓለም ጋር ያለው ግንኙነት”* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

**1፥6 ወደ ተለየ ወንጌል፤** የገላትያ ምእመናን ሐዋርያው ጳውሎስ ያስተማረውን ትምህርት ትተው “የተለየ ወንጌል” እንዲቀበሉ ለማድረግ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ወደ ገላትያ መጥተው ነበር:: የወንጌል ትምህርታቸውም ድነት በክርስቶስ በማመን ብቻ የሚገኝ ሳይሆን፣ በአይሁድ እምነት መሠረት መገረዝን (5፥2)፣ ሕግ መጠበቅንና (3፥5) የአይሁድ በዓላትን ማክበርን (4፥10) የሚያካትት እንደ ሆነ ይገልጻል:: (1) አንድ ወንጌል ብቻ እንዳለ፣ ይኸውም “የክርስቶስ ወንጌል” (ቍ 7) እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያረጋግጣል:: ይህ ወንጌል ወደ እኛ የመጣውም፣ “በመገለጥ ከኢየሱስ ክርስቶስ” (ቍ 12) እና በመንፈስ ቅዱስ የተለየ ምሪት ነው (በገጽ 1941 ላይ፣ *“መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ መሆኑና ያለው ሥልጣን”* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ):: ይህ ወንጌል፣ የእግዚአብሔር ቃል በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚገባ ተገልጾአል፤ ተብራርቶአልም:: (2) በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ያልተገለጸ ወይም ያልተጠቀሰ ከሰዎች፣ ከአብያተ ክርስቲያናት ወይም ከባህል የመጣ ማንኛውም ትምህርት፣ አስተምህሮ ወይም ሐሳብ በክርስቶስ ወንጌል ውስጥ ሊካተት አይችልም (ቍ 11):: እነዚህን ከመጀመሪያው የወንጌል ዋና ሐሳብ ጋር ማደባለቅ፣ “የክርስቶስን ወንጌል ማጣመም” (ቍ 7) ነው::

**1፥9 ለዘላለም የተረገመ ይሁን፤** “ለዘላለም የተረገመ” (በግሪክ አናቴማ) የሚለው ቃል (ሐረግ) በእግዚአብሔር የቍጣ ፍርድ እርግማን ሥር ሆኖ ለጥፋት የተጠበቀና ወደፊት የእግዚአብሔርን ቍጣና የፍርድ ውሳኔ የሚቀበል ማለት ነው:: (1) ሐዋርያው ጳውሎስ የመጀመሪያውን የክርስቶስን ወንጌል ለማጣመምና (ቍ 7) በሐዋርያት ምስክርነት የተላለፈውን እውነት ለመለወጥ በሚሞክሩት ላይ የሚነሣሣውን የመንፈስ ቅዱስን የፍርድና የቍጣ ሐሳብ ይገልጻል:: ይህ ተመሳሳይ ሐሳብ በኢየሱስ ክርስቶስ (ማቴ 23፥13 እና ማብ ይመ)፣ በጴጥሮስ (2ጴጥ 1፥2)፣ በዮሐንስና (2ዮሐ 1፥7-11) በይሁዳ (1፥3-4፡12-19) ትምህርት ውስጥ በግልጽ ይታይ ነበር፤ እንደዚሁም በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እንደ ተገለጠው፣ የክርስቶስን ወንጌል በሚወድና በኀጢአት የጠፋው ዓለም (ሮሜ 10፥14-15) ወንጌሉ ድነት የሚያገኝበት እጅግ አስፈላጊ የሆነ የምሥራች መሆኑን በሚያምን በማንኛውም የክርስቶስ ተከታይ ልብ ውስጥ ይገኛል::

(2) በክርስቶስ ተገልጦለት (ቍ 11-12፤ ቍ 6 እና ማብ ይመ) ጳውሎስ ከሰበከው ወንጌል የተለየ ወንጌል የሚሰብኩ ሁሉ የተረገሙ ናቸው:: ከመጀመሪያ በተሰበከውና መሠረታዊ በሆነው በክርስቶስና በሐዋርያት ወንጌል ላይ አንዳች የሚጨምር ወይም የሚቀንስ ማንኛውም ሰው ከእግዚአብሔር የቍጣ ፍርድ በታች ይሆናል፤ “እግዚአብሔር ... ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ ዕድሉን ያጐድልበታል” (ራእ 22፥18-19)::

(3) አማኞች ለእምነታቸው እንዲቆሙ (ይሁ 1፥3 እና ማብ ይመ)፣ በፍቅር እንዲያቃኑ (2ጢሞ 2፥25-26) እንደዚሁም ኢየሱስ ክርስቶስና ሐዋርያት ያስተማሩትን መሠረታዊ የሆነውን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ከሚቃወሙት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚገኙ አስተማሪዎች፣ አገልጋዮችና ሌሎች ሰዎች ራሳቸውን እንዲለዩ እግዚአብሔር ያዛል (ቍ 8-9፤ ሮሜ 16፥17-18፤ 2ቆሮ 6፥17):: ይህ እውነት ቀጥሎ ያሉትን ያካትታል:-

(ሀ) የክርስቶስን አምላክነትና ከድንግል መወለድ (ማቴ 1፥23፤ ዮሐ 20፥28 እና ማብ ይመ)፤

(ለ) የእግዚአብሔር ቃል በሚያስተምረው ትምህርት ሁሉ ሙሉ እስትንፋስ እግዚአብሔርና ሥልጣን ያለው መሆኑን (በገጽ 1941 ላይ፣ *“መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ መሆኑና ያለው ሥልጣን”* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፤

(ሐ) የአዳምን ውድቀት ታሪካዊነትና እውነተኛነት (ሮሜ 5፥12-19)፤

(መ) ሰው በተፈጥሮው ክፋትን የማድረግ ባሕርይ ያለው መሆኑን (ዘፍ 6፥5፤ 8፥21፤ ሮሜ 1፥21-32፤ 3፥10-18፤ 7፥14፡21)፤

(ሠ) ሰው በክርስቶስ አምኖ ካልዳነ በቀር የጠፋ መሆኑን (ሐሥ 4፥12 እና ማብ፤ ሮሜ 1፥16-32፤ 10፥13-15)፤

እርሱ ለዘላለም የተረገመ ይሁን።
10አሁን እኔ ጉሽ ለመባል የምሻው በሰ
ዎች ዘንድ ነው ወይስ በእግዚአብሔር ዘንድ?
ወይስ ሰዎችን ደስ ለማሰኘት እየተጣጣርሁ
ነው? ሰዎችን ደስ ለማሰኘት የምጥር ብሆን
ኖሮ፣ የክርስቶስ አገልጋይ ባልሆንሁ ነበር።

**ጳውሎስ በእግዚአብሔር መጠራቱ**

11ወንድሞች ሆይ፤ የሰበክሁላችሁ
ወንጌል ሰው ሠራሽ አለመሆኑን
እንድታውቁ እፈልጋለሁ፤ 12ከማንም
ሰው አልተቀበልሁትም፤ ከማንም
አልተማርሁትም፤ ይልቁንስ በመገለጥ
ከኢየሱስ ክርስቶስ ተቀበልሁት።
13ቀድሞ በአይሁድ ሃይማኖት እንዴት
እንደኖርሁ፣ የእግዚአብሔርንም ቤተ ክርስቲያን
እንዴት በእጅጉ እንዳሳደድሁ፣ ለማጥ ፋትም
እንዴት እንደጣርሁ ሰምታችኋል፤ 14በእኔ
ዕድሜ ዘመን ከነበሩት ከብዙዎቹ አይሁድ
ይበልጥ በአይሁድ ሃይማኖት እልቅ ነበር፤
ስለ አባቶቼም ወግ እጅግ ቀናተኛ ነበርሁ።
15ነገር ግን፣ ከእናቴ ማሕፀን[ሀ] ጀምሮ የለየኝና
በጸጋው የጠራኝ እግዚአብሔር፣ 16በአሕዛብ
መካከል ስለ እርሱ እንድሰብክ ልጁን በእኔ
ሊገልጥ በወደደ ጊዜ፣ ከማንም ሥጋ ለባሽ ጋር
አልተማከርሁም፤ 17ከእኔ በፊት ሐዋርያት
ወደ ሆኑትም ወደ ኢየሩሳሌም አልወጣሁም፤
ነገር ግን ወዲያው ወደ ዐረብ አገር ሄድሁ፤
በኋላም ወደ ደማስቆ ተመለስሁ።
18ከዚያም ከሦስት ዓመት በኋላ፣
ጴጥሮስን[ለ] አገኘው ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም
ወጣሁ፤ ከእርሱም ጋር ዐሥራ አምስት ቀን
ተቀመ ጥሁ። 19ነገር ግን ከጌታ ወንድም
ከያዕቆብ በቀር፣ ከሐዋርያት ማንንም
አላየሁም። 20በምጽፍላችሁ ነገር በእግዚአብሔር
ፊት ሐሰት እንደማልናገር አረጋግጬ
እነግራችኋለሁ። 21ከዚያም በኋላ፣ ወደ ሶርያና
ወደ ኪልቅያ አገር ሄድሁ። 22በክርስቶስ
ያሉት የይሁዳ አብያተ ክርስቲያናትም
ፊቴን አይተው አያውቁም ነበር፤ 23እነርሱ
ግን፣ "ቀድሞ እኛን ሲያሳድድ የነበረ ሰው፣
ከዚህ በፊት ሊያጠፋው ይፈልግ የነበረውን
እምነት አሁን እየሰበከ ነው" የሚለውን ወሬ
ብቻ ሰምተው ነበር፤ 24በእኔም ምክንያት
እግዚአብሔርን አመሰገኑ።

**ጳውሎስን ሐዋርያት ተቀበሉት**

2 ከዐሥራ አራት ዓመት በኋላም፣
ዳግመኛ ወደ ኢየሩሳሌም ወጣሁ፤
በዚህ ጊዜ ከበርናባስ ጋር ነበርሁ፤
ቲቶንም ይዤው ሄጀ ነበር። 2ካገኘሁትም
መገለጥ የተነሣ ወደዚያ ሄድሁ፤ በአሕዛብ
መካከል የምሰብከውን ወንጌል ለእነርሱም
ገለጥሁላቸው። ይሁን እንጂ፣ ምናልባት
በከንቱ እየሮጥሁ ወይም ሮጬ እንዳይሆን
በመሥጋት፣ ዋነኞች ለሚመስሉት ብቻ
በግል ይህን አስታወቅኋቸው። 3ከእኔ ጋር
የነበረው ቲቶ እንኳ የግሪክ ሰው ቢሆንም፣
እንዲገረዝ አልተገደደም ነበር። 4ይህ ጉዳይ
የተነሣው አንዳንድ ሐሰተኞች ወንድሞች
በክርስቶስ ኢየሱስ ያገኘነውን ነጻነት
ሊሰልሉና ባሪያዎች ሊያደርጉን ወደ እኛ
ሾልከው በመግባታቸው ነው።
5ለእነዚህ ሰዎች ለአንድ አፍታ

1፥10 ሮሜ2፥29
1፥11 ቆላ8፤
1ቆሮ15፥1
1፥12 ቆላ1፥16፤
1ቆሮ2፥10፤
11፥23፤ 15፥3
1፥13 ሐሥ8፥3፤
26፥4፡5፤
1ቆሮ10፥32
1፥14 ማቴ15፥2፤
ሐሥ21፥20፤
1፥15 ኢሳ49፥1፡5፤
ኤር1፥5፤
ሐሥ9፥15፤
ሮሜ8፥28፤
1፥16 ማቴ16፥17፤
ሐሥ9፥15፤
ገላ2፥9፤
1፥17 ሐሥ9፥21፤
9፥22
1፥18
ሐሥ9፥22፡23፤
26፡27፤
1፥19 ማቴ13፥55፤
ሐሥ15፥13
1፥20 ሮሜ1፥9፤
9፥1
1፥21 ሉቃ2፥2፤
ሐሥ6፥9
1፥22 ሮሜ16፥3፤
1ተሰ2፥14
1፥23 ሐሥ6፥7፤
8፥3
1፥24 ማቴ9፥8
2፥1 ሐሥ4፥36፤
15፥2፤ 2ቆሮ2፥13
2፥2
ሐሥ15፥4፡12፤
1ቆሮ2፥10፤ 9፥24
2፥3 ቆላ1፤
ሐሥ16፥3፤
1ቆሮ 9፥21፤
2፥3 2ቆሮ2፥13 2፥4 ሐሥ1፥16፤ 2ቆሮ11፥26፤
ገላ5፥1፡13፤ ይሁ1፥4 2፥5 ቆላ14

ሀ1፥15 ወይም ከመወለዴ

(ረ) ድነት፣ ክርስቶስ ጌታና አዳኝ መሆኑን በማመን በጸጋ የሚገኝ መሆኑን፣ በሞቱና በደሙ ማስተስረያነት መፈጸሙን (ሮሜ 3፥24-25፤ 5፥10 ይመ፤ በገጽ 1746 ላይ፣ *«እምነትና ጸጋ»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፤

(ሰ) የክርስቶስን ትንሣኤ (ማቴ 28፥6 እና ማብ፤ 1ቆሮ 15፥3-4 ይመ)፤

(ሸ) በሁለቱ ኪዳኖች ማለትም በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን የታምራት መፈጸም ታሪካዊ እውነት መሆኑን (1ቆሮ 10፥1)፤

(ቀ) ሰይጣንና አጋንንት መንፈሳውያን ፍጥረታት መሆናቸው እውነት መሆኑን (ማቴ 4፥1፤ 8፥28፤ 2ቆሮ 4፥4፤ ኤፌ 2፥2፤ 6፥11-18፤ 1ጴጥ 5፥8)፤

(በ) መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ገሃነም የሚያስተምረው ነገር እውነት መሆኑን (ማቴ 10፥28 እና ማብ ይመ)፤

(ተ) ክርስቶስ እንደተናገረው ወደ ምድር ተመልሶ የሚመጣ መሆኑ (ዮሐ 14፥3 እና ማብ፤ ሐሥ 1፥11፤ 1ቆሮ 1፥7 እና ማብ፤ ራእ 19፥11 እና ማብ ይመ)።

(4) ስለ ሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች የሚያስጠነቅቁ ሐሳቦችን የያዙ ተመሳሳይ ምንባቦች በሮሜ 16፥17፤ በ2ጴጥ 2፥17-22፤ በ2ዮሐ 1፥9-11፤ በይሁ 1፥12-13 ላይ ይገኛሉ፤ 2ቆሮ 11፥13 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ፤ በገጽ 1519 ላይ፣ *«የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከተ።

**1፥10 ሰዎችን ደስ ለማሰኘት የምጥር ብሆን ኖሮ፤** አንድ ሰው በወንጌል እውነት ላይ በማመቻመች ሰዎችን ደስ ለማሰኘት የሚጥር ከሆነ፣ እውነተኛ የወንጌል አገልጋይ ሊሆን አይችልም (1ቆሮ 4፥3-6)። ሰዎችን ሳይሆን፣ «ልባችንን የሚመረምረውን እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት» (1ተሰ 2፥4 እና ማብ ይመ) መናገር የእርሱ ኀላፊነት መሆኑን ጳውሎስ ተረድቶአል። የክርስቶስ ወንጌል ተከታዮች የሆኑ ሁሉ፣ አንዳንድ ሰዎችን የሚያሳዝን ቢሆንም እንኳ፣ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት ዐላማቸው መሆን አለበት (ከሐሥ 5፥29፤ ከኤፌ 6፥6፤ ከቈላ 3፥22 ጋር ያነጻጽሩ)።

**1፥15 የለየኝና ... እግዚአብሔር፤** ከዚህ ላይ ጳውሎስ የሚናገረው ሐዋርያዊ አገልግሎቱን አስመልክቶ ቢሆንም፣ እግዚአብሔር በእርሷ ወይም በእርሱ ልጁን ይገልጽ ዘንድ እያንዳንዱ አማኝ በጸጋ የተለየ መሆኑን የማመልከት ሐሳብ አለው። ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት በማድረግ እንድንኖርና በዓለም ፊት ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስክሮች እንድንሆን፣ ከኀጢአትና ከዚህ ክፉ ዓለም እንድንለይ ተደረግን (ቍ 4 እና ማብ ይመ)። መለየት ማለት እግዚአብሔርን ለማክበርና ልጁን ለማሳየት፣ በእምነትና በመታዘዝ እየኖሩ ከእግዚአብሔር ጋር መሆን፣ የእግዚአብሔር መሆንና ለእግዚአብሔር ቅርብ መሆን ማለት ነው (በገጽ 1826 ላይ፣ *«የአማኞች መለየት»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**2፥5 ለእነዚህ ሰዎች ለአንድ አፍታ እንኳ**

እንኳ አልተገዛንላቸውም፤ ይኸውም፣
የወንጌል እውነት ከእናንተ ጋር ጸንቶ
እንዲኖር ነው።
6ዋነኛ መስለው ስለሚታዩት ሰዎች
ማንነት እኔን አይገደኝም፤ እግዚአብሔር
የሰውን ፊት አይቶ አያደላም፤ እነዚህም
ሰዎች ለመልእክቴ የጨመሩልኝ ነገር
የለም። 7ነገር ግን ጴጥሮስ ለተገረዙት
ወንጌልን እንዲሰብክ ዐደራ እንደ ተሰጠው፣
እኔም ላልተገረዙት ወንጌልን እንድሰብክ
አደራ እንደ ተሰጠኝ ተገነዘቡ፤ 8ጴጥሮስን
ለአይሁድ ሐዋርያ እንዲሆን የሠራ
እግዚአብሔር፣ በእኔ የአሕዛብ ሐዋርያዊ
አገልግሎትም ሠርቶአል። 9እንደ አዕማድ
የሚቈጠሩት ያዕቆብ፣ ጴጥሮስና ዮሐንስም
የተሰጠኝን ጸጋ ባስተዋሉ ጊዜ፣ ለእኔና
ለበርናባስ የትብብር ቀኝ እጃቸውን ሰጡን፤
ከዚያም እኛ ወደ አሕዛብ፣ እነርሱ ደግሞ
ወደ አይሁድ እንድሄድ ተስማሙ።
10አጥብቀው ዐደራ ያሉን ድኾችን
ማሰባችንን እንዳናቋርጥ ብቻ ነው፤ እኔም

2፥6 ቍ2፡ ሐሥ10፥34፡ 1ቆሮ15፥11፡ ራእ2፥23
2፥7 ቍ9፡11፡14 ሐሥ9፥15፡ 1ተሰ2፥4፡ 1ጢሞ1፥11
2፥8 ሐሥ1፥25፡ 1ቆሮ1፥1
2፥9 ቍ1፡7፡11፡14፡ ሐሥ4፥36፡ 9፥15፡ 15፥13፡ ሮሜ12፥3፡ 1ጢሞ3፥15 ራእ3፥12
2፥10 ሐሥ24፥17
2፥11 ቍ7፡9፡14፡ ሐሥ11፥19
2፥12 ሐሥ10፥45 11፥2፡ 11፥3፡ 15፥13
2፥13 ቍ1፡ ሐሥ4፥36

ይህንኑ ለማድረግ ጕጕቴ ነበር።

### ጳውሎስ ጴጥሮስን ተቃወመው

11ጴጥሮስ ወደ አንጾኪያ በመጣ
ጊዜ፣ በግልጥ ስቶ ስለነበር ፊት ለፊት
ተቃወምሁት። 12አንዳንድ ሰዎች ከያዕቆብ
ዘንድ ከመምጣታቸው በፊት፣ ከአሕዛብ
ጋር ይበላ ነበር፤ እነርሱ በመጡ ጊዜ ግን
የተገረዙትን ወገኖች ፈርቶ ከአሕዛብ ራሱን
በመለየት ገሸሽ ማለት ጀመረ፤ 13በርናባስም
እንኳ በእነርሱ ግብዝነት እስኪወሰድ ድረስ፣
ሌሎቹም አይሁድ በግብዝነቱ ተባበሩት።
14ተግባራቸው እንደ ወንጌል እውነት
አለመሆኑን በተረዳሁ ጊዜ፣ በሁሉም
ፊት ጴጥሮስን እንዲህ አልሁት፤ "አንተ
አይሁዳዊ ነህ፤ ሆኖም በአሕዛብ ሥርዐት
እንጂ በአይሁድ ሥርዐት አትኖርም፤
ታዲያ አሕዛብ የአይሁድን ሥርዐት
እንዲከተሉ እንዴት ታስገድዳቸዋለህ?

2፥14 ቍ5፡7፡9፡ 11፡12፡ ሐሥ10፥28

**አልተገዛንላቸውም፤** ጳውሎስ በብዙ ነገር ቻይና ታጋሽ ነበር (ከ1ቆሮ 13፥4-7 ጋር ያነጻጽሩ)፡ "የወንጌልን እውነት" የሚቃወም ነገር ሲመጣ ግን በፍጹም አልተበገረም:: ጳውሎስ ከክርስቶስ የተቀበለው መገለጥ (1፥12)፣ ለሚያምኑት ሁሉ ለድነት የሚያበቃ ኀይል ያለው (ሮሜ 1፥16) አንድና ብቸኛ ወንጌል ነው:: ከሌሎች ጋር በሰላምና በአንድነት ለመኖር ወይም በወቅቱ ተቀባይነት ባለው ሐሳብ ላይ ለመስማማት ተብሎ በዚህ ወንጌል ላይ መደራደር ክፉ እንደማያስፈልግ ጳውሎስ ተረድቶአል:: እንዲህ ባይሆን ኖሮ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲከበርና የጠፉት እንዲድኑ የማድረጉ ተግባር አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ በወደቀ ነበር:: ዛሬ በአዲስ ኪዳን መገለጥ መሠረት የተጻፈውን ማንኛውንም የወንጌል እውነት ብንለቅ፣ ከዘላለም ጥፋት የሚያድነንን ብቸኛ የወንጌል መልእክት ማፍረሳችን ነው (ከማቴ 18፥6 ጋር ያነጻጽሩ)::

**2፥6 እግዚአብሔር የሰውን ፊት አይቶ አያደላም፤** ማንም ሰው ካለው ሀብት፣ ካለው ዝናና ሥልጣን ወይም ካከናወነው ሥራ የተነሣ እግዚአብሔር አድልዎ አያደርግም (ከዘሌ 19፥15፤ ከዘዳ 10፥17፤ ከኢዮ 34፥19፤ ከሐሥ 10፥34፤ ከኤፌ 6፥9 ጋር ያነጻጽሩ):: (1) እግዚአብሔር ልብን ያያል፤ ይመዝናልም፤ ይኸውም እግዚአብሔር የሰውን የውስጥ ማንነት ይመዝናል፤ በፍቅር፣ በእምነትና በንጽሕና ልባቸውን ወደ እርሱ በሚመልሱት ሰዎች እጅግ ደስ ይሰኛል ማለት ነው (ከ1ሳሙ 16፥7፤ ከማቴ 23፥28፤ ከሉቃ 16፥15፤ ከዮሐ 7፥24፤ ከ2ቆሮ 10፥7 ጋር ያነጻጽሩ፤ 1ቆሮ 13፥1 እና ማብ ይመ):: (2) እግዚአብሔር ካልተማረው ይልቅ የተማረውን፣ ከድኻው ይልቅ የሀብታሙን፣ ከደካማው ይልቅ ኀይለኛ የሆነውን ሰው ፍቅር፣ ኅብረትና ጸሎት አይመርጥም:: "ነገር ግን እርሱን የሚፈሩትንና ጽድቅን የሚያደርጉትን ሁሉ ከየትኛውም ወገን ቢሆኑ" መቀበል (ሐሥ 10፥35) የእግዚአብሔር ዘላለማዊ መርሕ ነው::

**2፥10 ድኾችን ማሰባችንን፤** ድኾችን መርዳት እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተደጋግሞ የተጠቀሰ ዋና ሐሳብ ነው (ዘፀ 23፥10-11፤ ዘዳ 15፥7-11፤ ኤር 22፥16፤ አሞ 2፥6-7፤ ማቴ 6፥2-4፤ ዮሐ 13፥29):: የእኛን ርዳታ የሚፈልጉ ሁልጊዜ በዙሪያችን ይኖራሉ:: ድኾች በተለይም ከእምነት ቤተ ሰብ የሆኑት (6፥10) የእኛን የገንዘብና የጸሎት ድጋፍ ይፈልጋሉ (በገጽ 1327 ላይ፣ "ድኾችንና ችግረኞችን መርዳት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

**2፥11 ፊት ለፊት ተቃወምሁት፤** ማንኛውም አገልጋይ ወይም መንፈሳዊ መሪ ስሕተት በመፈጸምና በግብዝነት በመመላለስ (ቍ 13) በደለኛ ሆኖ ከተገኘ፣ እርሱን መቃወምና መገሠጽ ይገባል (ከ1ጢሞ 5፥20 ጋር ያነጻጽሩ):: ይህ የሰዎችን ማንነት ሳይመለከቱ ተግባራዊ መሆን አለበት፤ እግዚአብሔር በድንቅ ሁኔታ የተጠቀመበት እንደ ሐዋርያው ጴጥሮስ ያለ ታላቅ ሰው እንኳ ቢሆን፣ ስሕተቱን እንዲያርም መገሠጽ ይገባል (ቍ 11-17 ይመ፤ ከ1ጢሞ 5፥20-21 ጋር ያነጻጽሩ):: ጴጥሮስ ስሕተቱን ተገንዝቦ ስለ ጥፋቱ በትሕትናና በመጸጸት መንፈስ የጳውሎስን ግሣጼ እንደ ተቀበለው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል:: በኋላም ጴጥሮስ በመልእክቱ ስለ ጳውሎስ በመጥቀስ፣ "የተወደደው ወንድማችን ጳውሎስ" (2ጴጥ 3፥15) በማለት ይናገራል::

**2፥12 የተገረዙትን ወገኖች ፈርቶ፤** እነዚህ፣ "የተገረዙት ወገኖች" የተባሉት፣ የብሉይ ኪዳን የመገረዝ ሥርዐት ለአዲስ ኪዳን አማኞች ሁሉ አስፈላጊ እንደ ሆነ የሚያምኑ፣ በተለይ በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን የነበሩና ከአይሁድ ወገን የሆኑ ክርስቲያኖች ናቸው:: እነዚህም ክርስቲያኖች፣ ከአይሁድ ወገን የሆኑ አማኞች ሁሉ፣ የአይሁድን ባህልና የአመጋገብ ደንብ ከማይከተሉት ከአሕዛብ ወገን ከሆኑት ካልተገረዙት ክርስቲያኖች ጋር አብሮ መብላት እንደሌለባቸው ያስተምሩ ነበር:: እግዚአብሔር ከአሕዛብ ወገን የሆኑ አማኞችን ምንም ልዩነት ሳያደርግ እንደ ተቀበላቸው ጴጥሮስ ቢያውቅም (ሐሥ 10፥34-35)፣ ነቀፌታ እንዳይደርስበት በመፍራትና በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን የነበረውን ሥልጣን ሊያጣ እንደሚችል በመሥጋት፣ ለሚያምንበት ነገር ከመቆም ወደ ኋላ አለ:: ጴጥሮስ ከአሕዛብ ወገን ከሆኑ ክርስቲያኖች ጋር አብሮ መብላትን ማቆሙ፣ "የአይሁድና የአሕዛብ" በማለት ሁለት የክርስቶስ አካል እንዳለ የሚያስተምረውን የስሕተት አስተሳሰብ የሚያጠናክር ነው::

[15]"እኛ በትውልዳችን አይሁድ እንጂ፣
'ኀጢአተኞች አሕዛብ' ያልሆን፣ [16]ሰው
በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንጂ፣ ሕግን
በመጠበቅ እንደማይጸድቅ እናውቃለን።
ስለዚህ ሕግን በመጠበቅ ሳይሆን፣
በክርስቶስ በማመን እንጸድቅ ዘንድ እኛም
ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል፤ ሕግን
በመጠበቅ ማንም አይጸድቅምና።

ኤፌ. 2፥4-9

[17]"በክርስቶስ ለመጽደቅ ስንፈልግ፣
እኛ ራሳችን ኀጢአተኞች መሆናችን
ግልጽ ነው፤ ታዲያ ክርስቶስ ኀጢአት
እንዲስፋፋ ያደርጋልን? ፈጽሞ አይደለም!
[18]ያፈረስሁትን መልሼ የምገነባ ከሆነማ ሕግ
ተላላፊ መሆኔን አረጋግጣለሁ። [19]ለእግዚአብሔር
እኖር ዘንድ፣ በሕግ በኩል ለሕግ ሞቻለሁና።
[20]ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ፤ ከእንግዲህ
እኔ አልኖርም፤ ነገር ግን ክርስቶስ በውስጤ
ይኖራል። አሁንም በሥጋ የምኖረው ኑሮ
በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን አሳልፎ በሰ ጠው
በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለኝ እምነት ነው።
[21]የእግዚአብሔርን ጸጋ አላቃልልም፤ ጽድቅ
በሕግ በኩል የሚገኝ ከሆነማ፣ ክርስቶስ
እንዲያው በከንቱ ሞተ ማለት ነዋ!"[b]

2፥15 1ሳሙ 15፥18፤ ሉቃ 24፥7፤ ፊል 3፥3፡5
2፥16 ሮሜ 3፥28፤ 4፥25፤ 9፥30
2፥17 ቍ 15፤ ገላ 3፥21
2፥19 ሮሜ 6፥10፡ 11፡14፤ 7፥4፤ 2ቆሮ 5፥15
2፥20 ማቴ 4፥3፤ ሮሜ 6፥6፤ 8፥10፤ 8፥37፤ ገላ 1፥4፤ 1ጴጥ 4፥2
2፥21 ገላ 3፥21
3፥1 ሉቃ 24፥25፤ ሐሥ 16፥6፤ 1ቆሮ 1፥23፤ ገላ 5፥7
3፥2 ቍ 5፡10፤ ዮሐ 20፥22፤ ሮሜ 10፥17፤ ገላ 2፥16፤ ዕብ 4፥2
3፥5 ቍ 2፡10፤ 1ቆሮ 12፥10፤ ገላ 2፥16

## እምነት ወይስ የኦሪትን ሕግ መጠበቅ

3 እናንተ የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች
ሆይ! ለመሆኑ ማን መተት አደረገባችሁ?
ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ
በፊት ለፊታችሁ በግልጥ ተሥሎ ነበር።
[2]ከእናንተ ዘንድ አንድ ነገር ብቻ ማወቅ
እፈልጋለሁ፤ መንፈስን የተቀበላችሁት
ሕግን በመጠበቅ ነው ወይስ የተሰበከላችሁን
በማመን? [3]ይህን ያህል የማታስተውሉ ናች
ሁን? በመንፈስ ጀምራችሁ በሥጋ ፍጹም
ለመሆን ትጥራላችሁን? [4]በርግጥ ለከንቱ
ከሆነ፣ ይህን ያህል መከራ የተቀበላችሁት
እንዲያው ነውን? [5]እግዚአብሔር መንፈሱን

[a]2፥18 ግሪኩ ኬፋ ይለዋል።
[b]2፥21 አንዳንድ ተርጓሚዎች ትእምርተ ጥቅሱን ከቍ 14 በኋላ ይዘጋሉ።

**2፥16 በክርስቶስ በማመን እንጸድቅ ዘንድ፤** እዚህ ላይ ጳውሎስ ኀጢአተኞች እንዴት ሊጸድቁ ይችላሉ? ማለትም፣ የኀጢአት ይቅርታን እንዴት ያገኛሉ? በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አግኝተው ከእርሱ ጋር ትክክለኛ ኅብረት እንዴት ሊኖራቸው ይችላል? የሚሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል። ይህ ሊሆን የሚችለው "ሕግን በመጠበቅ" ሳይሆን፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በሚኖረን ሕያው እምነት ነው (በገጽ 1735 ላይ፣ *"ድነትን የሚገልጹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**2፥19 ለሕግ ሞቻለሁና፤** ሮሜ 7፥4 እና *"ለሕግ መሞት ምን ማለት ነው?"* በሚለው ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ እንዲሁም ማቴ 5፥17 እና ኋአማኝ ከሕጉ ጋር ያለው ግንኙነትኝ በሚለው ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ፤ በገጽ 144 ላይ፣ *"የብሉይ ኪዳን ሕግ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**2፥20 ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ፤** ጳወሎስ ከክርስቶስ ጋር ያለውን ግንኙነት፣ በግል ከጌታው ጋር ካለው ጥልቅ የሆነ ቅርበትና በእርሱም ላይ ካለው መታመን ጋር በማያያዝ ይገልጸዋል። በክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች በሞቱና በትንሣኤው ሕይወታቸውን ከእርሱ ጋር አንድ በማድረግ ይኖራሉ። (1) አማኞች ሁሉ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅለዋል፤ ይድኑ ዘንድ ለሕግ ሞተዋል፤ አሁን ግን በክርስቶስ በኩል ለእግዚአብሔ ር ሕያው ሆነው ይኖራሉ (ቍ 19)። በክርስቶስ አምነው ስለ ዳኑ፣ ከእንግዲህ ኀጢአት አይገዛቸውም (ሮሜ 6፥11 እና ማብ ይመ፤ ከሮሜ 6፥4፡8፡14፤ ገላ 5፥24፤ 6፥14፤ ቈላ 2፥12፡20)።

(2) ከክርስቶስ ጋር የተሰቀልን እኛ በትንሣኤ ሕይወቱ ከእርሱ ጋር እንኖራለን። የሕይወት ሁሉ ምንጭ፣ የሐሳባችን፣ የቋንቋችንና የተግባራችንም ሁሉ ማእከል በመሆን (ዮሐ 15፥1-6፤ ኤፌ 3፥17)፣ ክርስቶስና ኀይሉ በእኛ ውስጥ ይኖራሉ። የክርስቶስ የትንሣኤ ሕይወት ለእኛ ሳይቋረጥ የሚተላለፍልን በመንፈስ ቅዱስ በኩል ነው (ዮሐ 16፥13-14፤ ሮሜ 8፥10-11)።

(3) የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ተካፋዮች ለመሆን የቻልነው በእምነት ነው፤ ይኸውም በወደደንና ራሱን ስለ እኛ አሳልፎ በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለን ጽኑ እምነት፣ ፍቅር፣ ለእርሱም ታማኝና ታዛዥ በመሆን ላይ የተመሠረተ ነው (ከዮሐ 3፥16 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1746 ላይ፣ *"እምነትና ጸጋ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። "በእምነት መኖር"፣ "በመንፈስ መኖር" ማለት ሊሆን ይችላል (3፥3፤ 5፥25 ይመ፤ ከሮሜ 8፥9-11 ጋር ያነጻጽሩ)።

**2፥21 ጽድቅ፤** ጳውሎስ ስለ መጽደቅና (ቍ 16-17) ስለ ጽድቅ ያለው መረዳት፣ እግዚአብሔር በሕግ መልክ ከሰጠው በላይ የሚያልፍ ነው። በእምነት የሚገኘው ጽድቅ ግብረ ገባዊ ለውጥን (ቍ 19)፣ የእግዚአብሔርን ጸጋ (ቍ 21)፣ የክርስቶስን የትንሣኤ ሕይወት የምንካፈልበትን ከእርሱ ጋር ያለንን ኅብረት (ቍ 20) ያካተተ ነው። ይህም ክርስቶስን በማመን የሚገኘው ጽድቅ፣ መንፈስ ቅዱስን በምንቀበልበት ጊዜ የሚኖረንን ዐይነት ሕይወት እንደሚሰጠን ጳውሎስ ግልጽ አድርጎ በሚናገርበት በ3፥21 ላይ ተረጋግጦአል (3፥2-3፡14 ይመ፤ (በገጽ 1735 ላይ፣ *"ድነትን የሚገልጹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**3፥2 መንፈስን የተቀበላችሁት ... በማመን?** ክርስቶስን በማመን በጸጋው የሚገኘው ድነት፣ ለሕጉ በመታዘዝ ድነትን ለማግኘት ከሚደረገው ጥረት እጅግ የላቀ እንደ ሆነ ጳውሎስ ይገልጻል። በክርስቶስ በማመን፣ መንፈስ ቅዱስን እንደዚሁም የዘላለምን ሕይወት ጨምሮ እርሱ የሚሰጠውን በረከት ሁሉ እንቀበላለን (ቍ 2-3፡5፡14፡21፤ 4፥6)፤ ይሁን እንጂ ድነትን ለማግኘት በሕጉ ላይ የሚደገፍ ሰው፣ መንፈስ ቅዱስንና ሕይወትን አያገኝም፤ ሕግ በራሱ ሕይወትን አይሰጥምና (ቍ 21)።

**3፥5 መንፈሱን፤** ጳውሎስ ስለ መንፈስ ከዚህ ላይ የሚናገረው (ቍ 2፡5፡14፤ 4፥6)፣ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅንና ከዚያም ቀጥሎ የሚመጣውን የተለየ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ያካትታል (ከሐሥ 1፥4-5፤ ከ2፥4፤ ከ8፥14-17፤ ከ10፥44-47፤ ከ11፥16-17፤ ከ19፥1-6፤ ከ1ቆሮ 12፥4-11 ጋር ያነጻጽሩ)፤ የሚከተሉትም ይህን ያመለክታሉ፤ (1) በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው "ታምራት" (በግሪክ ቋንቋ፣ ዱናሚስ) የሚለው ቃል ይህን ያመለክታል፤ ይህ ቃል፣ ሐዋርያው የተናገረው በበዓለ

የሚሰጣችሁ፣ በእናንተም ዘንድ ታምራትን
የሚሠራው ሕግን ስለ ጠበቃችሁ ነው ወይስ
የሰማችሁትን ስላመናችሁ?
[6]እስቲ አብርሃምን አስቡ፤ "እርሱ
እግዚአብሔርን አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ
ተቈጠረለት።"[7]እንግዲህእነዚያየሚያምኑት
የአብርሃም ልጆች እንደሆኑ አስተውሉ።
[8]መጽሐፍ፣ እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት
እንደሚያጸድቅአስቀድሞበማየት፣"አሕዛብ
ሁሉ በአንተ ይባረካሉ" በማለት ወንጌልን
ለአብርሃም አስቀድሞ አስታወቀው።
[9]ስለዚህ በእምነት የሆኑት፣ የእምነት ሰው
ከሆነው ከአብርሃም ጋር ቡሩካን ናቸው።
[10]ሕግን በመጠበቅ የሚተማመኑ ሁሉ
ከርግማን በታች ናቸው፤ "በሕግ መጻሕፍት
የተጻፈውን ሁሉ የማያደርግ የተረገመ ነው"
ተብሎ ተጽፎአልና።
[11]"ጻድቅ በእምነት ይኖራል" ስለ ተባለ፣
ማንም በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እንደማይጸድቅ
ግልጽ ነው። [12]ሕግ በእምነት ላይ የተመሠረተ
አይደለም፤ ነገር ግን "ሕጋጋትን የሚፈጽም
ሰው በእነርሱ በሕይወት ይኖ ራል"
ተብሎአል። [13]"በዕንጨት ላይ የሚሰቀል
ሁሉ የተረገመ ነው" ተብሎ ስለ ተጻፈ፣
ክርስቶስ ስለ እኛ ርግማን ሆኖ ከሕግ ርግማን
ዋጅቶናል፤ [14]ለአብርሃም የተሰጠው በረከት፣
በክርስቶስ ኢየሱስ ለአሕዛብ እንዲደርስ
ዋጅቶናል፤ ይኸውም በእምነት የመንፈስን
ተስፋ እንድንቀበል ነው።

3፥6 ዘፍ15፥6፤ ሮሜ4፥3
3፥7 ቍ9፤ ሉቃ3፥8
3፥8 ዘፍ12፥3፤ 18፥18፤ 22፥18፤ 26፥4፤ ሐሥ3፥25
3፥9 ቍ7፤ ሮሜ4፥16፤ 4፥18-22
3፥10 ቍ2፡5፡13፤ ዘዳ27፥26፤ ኤር11፥3፤ ሮሜ4፥15፤ ገላ2፥16
3፥11 ዕብ2፥4፤ ሮሜ3፥28፤ 9፥30፤ ዕብ10፥38
3፥12 ዘሌ18፥5፤ ሮሜ10፥5
3፥13 ዘዳ21፥23፤ ሐሥ5፥30፤ ገላ4፥5
3፥14 ቍ2፤ ኢል2፥28፤ ዮሐ20፥22፤ ሐሥ2፥33፤ ሮሜ4፥9፡16
3፥15 ሮሜ7፥1
3፥16 ዘፍ12፥7፤ 13፥15፤ 17፥7፡8፡10፤ 17፥19፤ 24፥7፤ መዝ132፥11፤ ሚክ7፥20፤

## የአሪት ሕግና የተስፋ ቃል

[15]ወንድሞች ሆይ፤ ከሰው ዕለታዊ ሕይወት
የተለመደውን ምሳሌ አድርጌ ላቅርብ፤ የሰው
ኪዳን እንኳ አንድ ጊዜ ከጸደቀ በኋላ ማንም
ሊሽረው ወይም በእርሱ ላይ ሊጨምርበት
እንደማይችል ሁሉ፣ በዚህም ጕዳይ ቢሆን
እንደዚሁ ነው። [16]የተስፋውም ቃል የተነገረው
ለአብርሃምና ለዘሩ ነበር፤ መጽሐፍ፣ ለብዙ
ሰዎች እንደሚነገር፣ "ለዘሮቹ" አይልም፤
ነገር ግን ለአንድ ሰው እንደሚነገር፣ "ለዘርህ"
ይላል፤ እርሱም ክርስቶስ ነው። [17]የምለው
እንዲህ ነው፤ ከአራት መቶ ሠላሳ ዓመት
በኋላ የተሰጠው ሕግ፣ አስቀድሞ በእግዚአብሔር
የጸናውን ኪዳን አፍርሶ የተስፋውን ቃል
አይሽርም። [18]ርስትን መውረስ በሕግ ቢሆን
ኖሮ፣ በተስፋ ቃል ባልተ ገኘ ነበርና፤
እግዚአብሔር ግን በጸጋው በተስፋ ቃል
አማካይነት ለአብርሃም ሰጥቶታል።
[19]ታዲያ ሕግ የተሰጠበት ምክንያት
ምንድን ነው? ሕግ የተጨመረው ከመተላለፍ

3፥16 ሉቃ1፥55፤ ሮሜ4፥13፡16፤ 9፥4፡8፤ ገላ3፥29፤ 4፥28
3፥17 ዘፍ15፥13፡14፤ ዘፀ12፥40፤ ሐሥ7፥6
3፥18 ሮሜ4፥14 3፥19 ቍ16፤ ዘፀ20፥19፤ ዘዳ5፥5፤ 33፥2፤ ሐሥ7፥53፤ ሮሜ5፥20

*ⁿ3፥7 ወይም ለአይሁድ*
*ⁿ3፥7 ወይም ለአረማዊያን እንዲሁም ቍ 8 እና 9 ይመ*
*ⁿ3፥9 ግሪኩ ኬፋ ይላል፤ እንዲሁም ቍ 11 እና 14 ይመ*

ኀምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ በአስደናቂ ሁኔታ መገለጥንና «በኀይል» መምጣቱን (በግሪክ ቋንቋ፣ ዱናሚስ) (ሐሥ 1፥8 ይመ፤ ከ2፥1-4 ጋር ያነጻጽሩ) በማሰብ እንደ ሆነ ማሳየቱ፥ (2) የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሳያቋርጡ እንደሚገለጡ የሚያመለክቱት «የሚሰጣችሁ»፣ «የሚሠራው» የሚሉት የአሁን ጊዜያት ግሶች መጠቀሳቸው፤ (3) በሐሥ 2፥33 ላይ ጴጥሮስ ከተናገረው ቃል ጋር የሚመሳሰለውን፣ «የመንፈስን ተስፋ» የሚለውን አገላለጽ መጠቀሙ (ከሉቃ 24፥49፤ ከሐሥ 1፥4 ጋር ያጻጽሩ)፤ (4) የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችን፣ መንፈስ ቅዱስ ወደ እኛ ከመላኩ በፊት እንደ ተፈጸመና እርሱም ወደ አማኞች ልብ ለመምጣቱ መሠረት እንደ ሆነ በ4፥6 ላይ የተጠቀሰው ሐሳብ ማረጋገጡ::

3፥5 **መንፈሱን ... ታምራትን የሚሠራው፤** በገላትያ አብያተ ክርስቲያናት እየተካሄደ የነበረው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ታምራት ማድረግን ያካተተ ነበር:: ለሐዋርያው ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስን መቀበል ሲባል፣ የማይታይ ውስጣዊ ሥራን መሥራት ብቻ ሳይሆን፣ በአማኞች መካከል በመለኮታዊ ኀይል ራሱን የሚገልጽ ውጫዊ ልምምድም ነው:: የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች፣ የመንፈስ ፈቅዱስን ህልዎትና ሥልጣን የሚገልጹ መመዘኛዎች ናቸው (ከ1ቆሮ 12-14 ጋር ያነጻጽሩ):: መለወጥና በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ፣ ብዙ ጊዜ ታምራትና ሌሎች የመንፈስ ቅዱስ መገለጦች የሚከተሏቸው ሊሆኑ ይገባል::

3፥6 **ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት፤** ሮሜ 4፥3፡5፡22 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

3፥11 **ጻድቅ በእምነት ይኖራል፤** ጳውሎስ በእምነት ስለ መጽደቅ በሚናገርበት ጊዜ በዕብራውያን 2፥4 ላይ ያለውን ሐሳብ ይጠቅሳል (ከሮሜ 1፥17 ጋር ያነጻጽሩ):: ዕንባቆም፣ ጻድቅ ሰውን ምኞቱ ቅን ካልሆነውና (ዕብ 2፥4 እና ማብ ይመ) ከክፉው ሰው ጋር ስለሚያነጻጽር፣ በእምነት የጸደቀ ሰው ውስጣዊ ጽድቅ እንዳለው በአጽንዖት ይገልጻል:: ስለዚህ መጽደቅ፣ በውስጣችን በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እውነተኛ ውስጣዊ ጽድቅን ያካተተ እንደ ሆነ ጳውሎስ ተረድቶአል (በገጽ 1735 ላይ፣ «*ድነትን የሚገልጹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

3፥14 **ለአብርሃም የተሰጠው በረከት፤** እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ (ቍ 8) ዋና ሐሳብ፣ «የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ» እንደ ሆነ ተገልጾአል (ከሉቃ 24፥49፤ ከሐሥ 1፥4-5 ጋር ያነጻጽሩ):: መንፈስ ቅዱስን መቀበል ጽድቅን፣ ሕይወትንና ሌሎችንም መንፈሳዊ በረከቶች ሁሉ ማግኘት ነው (ቍ 5 እና ማብ 4፥6 እና ማብ ይመ)::

3፥19 **ታዲያ ሕግ የተሰጠበት ምክንያት ምንድን ነው?** በግሪክ «ኖሞስ» በዕብራይስጥ ደግሞ «ቶራህ» የተባለው «ሕግ» የሚለው ቃል ትርጕሙ «ትምህርት» ወይም «መመሪያ» ማለት ነው:: ይህ ሕግ ዐሥርቱ ትእዛዛትን፣ አምስቱን የሙሴ መጻሕፍት ወይም በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኝ ማንኛውንም ትእዛዝ ሊያመለክት ይችላል፤ ጳውሎስ እዚህ ላይ ሕግ ብሎ የሚገልጸው፣ የሙሴን ኪዳን የመሥዋዕት አቀራረብ ሥርዐትም ይጨምራል:: ሕጉን በሚመለከት ጳውሎስ የሚከተሉትን አያሌ ነገሮች ይናገራል፤ (1) ሕጉ በሰው መተላለፍ ምክንያት ከእግዚአብሔር እንደ ተሰጠ፣ ይኸውም ኀጢአት የእግዚአብሔርን ፈቃድ መጣስ እንደ ሆነ ለማሳየትና በክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ምሕረት፣ ጸጋና ድነት እንደሚያስፈልግ የሰውን ሰብአዊ ስሜቱን ለመቀስቀስ ነው (ቍ 24 ይመ፤

የተነገ ተስፋው ያመለከተው ዘር እስኪመጣ
ድረስ ነበር፤ ሕጉም የመጣው በመላእክት
በኩል፣ በአንድ መካከለኛ እጅ ነበር።
20ሆኖም መካከለኛው አንድን ወገን ብቻ
የሚወክል አይደለም፤ እግዚአብሔር ግን አንድ
ነው። 21ታዲያ ሕግ የእግዚአብሔርን የተስፋ
ቃል የሚቃወም ነውን? ከቶ አይደለም፤
ሕግ የተሰጠው ሕይወትን ለማስገኘት ቢሆን
ኖሮ፣ በርግጥም ጽድቅ በሕግ በኩል በተገኘ
ነበር። 22መጽሐፍ ግን ዓለም ሁሉ የኀጢአት
እስረኛ መሆኑን ያውጃል፤ ይኸውም
በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው ተስፋ
ለሚያምኑት ሁሉ ይሰጥ ዘንድ ነው።
23ይህ እምነት ከመምጣቱ በፊት በሕግ
አማካይነት እስረኞች ሆነን፣ እምነት እስ
ከሚገለጥ ድረስ ተዘግቶብን ነበርን። 24ስለ
ዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ
ክርስቶስ የሚያደርሰን[ሀ] ሞግዚታችን ሆነ።
25አሁን ግን ያ እምነት ስለመጣ፣ ከእንግዲህ
በሕግ ሞግዚትነት ሥር አይደለንም።

## የእግዚአብሔር ልጆች

26ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን
የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ፤ 27ከክርስቶስ ጋር
አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁላችሁ
ክርስቶስን ለብሳችሁታልና።
28በአይሁድና በግሪክ፣ በባሪያና በነጻ
ሰው፣ በወንድና በሴት መካከል ልዩነት
የለም፤ ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ
ናችሁ። 29የክርስቶስ ከሆናችሁ፣ እናንተ
የአብርሃም ዘር ናችሁ፤ እንደ ተስፋውም
ቃል ወራሾች ናችሁ።

4 እኔ የምለው ይህ ነው፤ ወራሹ ሕፃን እስከ
ሆነ ድረስ፣ ሀብት ሁሉ የእርሱ ቢሆንም
እንኳ፣ ከባሪያ የተለየ አይደለም። 2አባቱ
እስከ ወሰነለት ጊዜ ድረስ በጠባቂዎችና
በሞግዚቶች ሥር ነው። 3እኛም እንዲሁ ገና
ልጆች በነበርንበት ጊዜ ከዓለም መሠረታዊ
ትምህርት ሥር በመሆን በባርነት ተገዝተን
ነበር። 4ነገር ግን የተወሰነው ዘመን በደረሰ
ጊዜ፣ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን፣
ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤
5ይህም የሆነው የልጅነትን መብት እናገኝ
ዘንድ ከሕግ በታች ያሉትን ለመዋጀት ነው።
6ልጆችም ስለ ሆናችሁ እግዚአብሔር፣ "አባ[ለ]

3፥20 1ጢሞ2፥5፤ ዕብ8፥6፤ 9፥15፤ 12፥24
3፥21 ሮሜ7፥12፤ ገላ2፥17፤ 2፥21
3፥22 ሮሜ3፥9-19፤ 11፥3
3፥23 ቍ 25፤ ሮሜ11፥32
3፥24 ቍ 19፤ ሮሜ 4፥15፤ 10፥4፤ ገላ2፥16
3፥25 ሮሜ7፥4
3፥26 ሮሜ8፥14
3፥27 ማቴ28፥19፤ ሮሜ13፥14
3፥28 ዘፍ1፥27፤ 5፥2፤ ኢል2፥29፤ ዮሐ10፥16፤ 17፥11፤ 1ቆሮ12፥13፤ ኤፌ2፥14:15፤ ቈላ3፥11
3፥29 ቍ 16፤ ሉቃ3፥8፤ ሮሜ8፥17፤ 1ቆሮ3፥23፤ ገላ3፥16
4፥3 ቍ8:9:24:25፤ ገላ2፥4፤ ቈላ2፥8:20
4፥4 ማር1፥15፤ ሉቃ2፥27፤ ዮሐ1፥14፤ 3፥17፤ ሮሜ5፥6፤ ኤፌ1፥10 4፥5 ዮሐ1፥12፤ ሮሜ3፥24፤ 8፥14
4፥6 ሐሥ16፥7፤ ሮሜ 5፥58፥15፥16

*ሀ 3፥24 ወይም ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ*
*ለ 4፥6 በአረማይኩ አባት ማለት ነው።*

ከሮሜ 5፥20፤ 8፥2 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) የብሉይ ኪዳኑ ሕግ በራሱ ቅዱስ፣ መልካምና ጻድቅ ቢሆንም እንኳ (ሮሜ 7፥12)፣ መንፈሳዊ ሕይወትን ወይም ግብረ ገባዊ ብርታትን ለመስጠት ብቃት አልነበረውም (ቍ 21፤ ሮሜ 8፥3፤ ዕብ 7፥18-19)።

(3) በክርስቶስ በማመን የሚገኘው ድነት እስኪ መጣ ድረስ፣ ሕግ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ጊዜያዊ ሞግዚት ሆኖ አገልግሎአል (ቍ 22-26)። በዚህም፣ ሕዝቡ ምን ማድረግና እንዴት መኖር እንደሚገባቸው ለማመልከት ሕጉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይገልጻል (ዘፀ 19፥4-6፤ 20፥1-17፤ 21፥1-24፥8)፤ የሕዝቡ ኀጢአት ይሸፈን ዘንድ የደም መሥዋዕት እንዲቀርብ አደረገ (ዘሌ 1፥5፤ 16፥33)፤ ኀጢአትን ወደሚያስተሰረየው ወደ ክርስቶስ ሞት አመለከተ (ዕብ 9፥14፤ 10፥12-14)።

(4) ሕግ የተሰጠው በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ወደ ክርስቶስ እንዲያደርሰን ነው (ቍ 24)። አሁን ግን ክርስቶስ ስለ መጣ፣ በሕግ ቍጥጥር (ሞግዚትነት) ሥር መሆን አብቅቶአል (ቍ 25)። ስለዚህ ከእንግዲህ ለሕጉ መታዘዝና መሥዋዕት ማቅረብን ጨምሮ የብሉይ ኪዳንን ሥርዐት በመፈጸም ድነትን እናገኛለን ብለን አንጠብቅም። አሁን ግን ድነት የሚገኘው በአዲስ ኪዳን መግቦቶች መሠረት ሲሆን፣ በተለይም ኢየሱስ ኀጢአትን ለማስተሰረይ በሞተው ሞት፣ በታላቅ ትንሣኤውና የእርሱ በመሆን በቀጣይነት በሚገኘው ልዩ መብት ነው (ቍ 27-29፤ ማቴ 5፥17 እና ክርስቲያን ከሕጉ ጋር ባለው ግንኙነት ላይ የተጻፈውን ማብራሪያ ይመ፤ በገጽ 144 ላይ፣ "*የብሉይ ኪዳን ሕግ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**3፥28 በወንድና በሴት፤** ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ባለው መንፈሳዊ ግንኙነት ስላለ፣ የጐሣ፣ የዘር፣ የብሔር፣ የኀብረተ ሰብና የጾታ ልዩነት ማድረግ እንደማይገባ ጳውሎስ ያሳስባል። ሁሉም በክርስቶስ "የሕይወትን በረከት" (1ጴጥ 3፥7)፣ የመንፈስን ተስፋ (ቍ 14፤ 4፥6) እንዲሁም የፈጣሪን መልክ መምሰልን (ቈላ 3፥10-11) እኩል አብረው ይወርሳሉ። በሌላ አንጻር በመንፈሳዊ እኩልነት ዐውድ ውስጥ ወንድ ወንድነቱ፣ ሴትም ሴትነቷ የተጠበቀ ነው (ዘፍ 1፥27)፤ በጋብቻና በኀብረተ ሰብ ውስጥ እያንዳንዳቸው ሊፈጽሙት የሚገባቸው ከአምላካቸው የተሰጣቸው ልዩ ኀላፊነትና ተግባር አልተለወጠም (1ጴጥ 3፥1-4 ይመ፤ ኤፌ 5፥22-23 እና ማብ፤ 1ጢሞ 2፥13:15 እና ማብ ይመ)።

**4፥2 አባቱ እስከወሰነለት ጊዜ ድረስ ... በሞግዚቶች ሥር ነው፤** ከዚህ ላይ ጳውሎስ የሚናገረው የአንድን አማኝ ሁኔታ በብሉይ ኪዳን ተስፋ ሥር ምን እንደሚመስል ለመግለጽ ቢሆንም፣ ፈሪሀ እግዚአብሔር ያላቸው ወላጆች ለልጆቻቸው የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር ብዙውን ጊዜ በበላይ ሆነው ቍጥጥር ያደርጉ እንደ ነበር ያመለክታል (ዘዳ 6፥7 እና ማብ ይመ)። ልጆች በቤት ውስጥ በሚሰጣቸው ትምህርትም ሆነ በክርስቲያን አስተማሪዎቻቸው እግር ሥር ሆነው በሚማሩበት ጊዜ እንደዚህ ዐይነቱን ቍጥጥር ማድረግ አስፈላጊ ነው። ልጆች ከእግዚአብሔር ካልሆነ የዓለም ፍልስፍናና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካልሆኑ መረሖች ተጠብቀው፣ ቅዱስ የሆነና ክርስቶስን የመምሰል ትምህርት እንዲያገኙ ወላጆች አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ እንዳለባቸው መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምራል (ሉቃ 1፥17 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1894 ላይ፣ "*ወላጆችና ልጆች*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**4፥6 «አባ አባት» ብሎ የሚጮኽ ሯ መንፈስ፤** ከመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች አንዱ፣ እግዚአብሔር አባታቸው እንደ ሆነ እንዲያውቁ የሚያደርገውን የልጅነት ፍቅር በእግዚአብሔር ልጆች ውስጥ መፍጠር ነው። -1? "አባ" የሚለው ቃል የአረማይስጥ ቃል ሲሆን፣ ትርጒሙ "አባት" ማለት ነው። ይህም ኢየሱስ ስለ አባቱ ስለ አብ ሲናገር የተጠቀመበት ቃል ነው። "አባ" የሚለው የአረማይስጡ ቃል አባትን ከሚያመለክተው፣ ከግሪኩ ቃል "ከተር" ጋር ሲጣመር፣ መንፈስ ቅዱስ ወደ

አባት" ብሎ የሚጮኽ የልጁን መንፈስ ወደ
ልባችን ላከ።
7ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ ነህ እንጂ
ባሪያ አይደለህም፤ ልጅም ስለ ሆንህ፣
እግዚአብሔር ወራሽ አድርጎሃል።

## ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች ማሰቡ

8እግዚአብሔርን ከማወቃችሁ በፊት፤
በባሕርያቸው አማልክት ላልሆኑት ባሪያዎች
ነበራችሁ፤ 9አሁን ግን እግዚአብሔርን ዐውቃ
ችሁታል፤ ይልቁን ደግሞ በእግዚአብሔር
ታውቃችኋል። ታዲያ እንደ ገና ወደ
ደካማና ወደማይጠቅም ትምህርት እንዴት
ትመለሳላችሁ? ዳግም በእርሱ በባርነት
ለመጠመድ ትፈልጋላችሁን? 10ልዩ የሆኑ
ቀኖችን፣ ወሮችን፣ ወቅቶችንና ዓመታትን
ታከብራላችሁ። 11ስለ እናንተ በከንቱ
የደከምሁ እየመሰለኝ እፈራላችኋለሁ።
12ወንድሞች ሆይ፤ እለምናችኋለሁ፤ እኔ
እናንተን እንደ መሰልሁ እናንተም እኔን
ምሰሉ። እናንተ አንዳች አልበደላችሁኝም።
13እንደምታውቁት በመጀመሪያ ለእናንተ
ወንጌልን የሰበክሁት፣ በሕመም ምክንያት
ነበር።
14ሕመሜ ለእናንተ ፈተና ሆኖባችሁም
እንኳ፣ አልሰለቻችሁኝም፤ ወይም
አልተጸየፋችሁኝም፤ ነገር ግን እንደ
እግዚአብሔር መልአክ፣ እንዲያውም እንደ
ራሱ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ አድርጋችሁ
ተቀበላችሁኝ። 15ለመሆኑ ያ ሁሉ ደስታችሁ
የት ደረሰ? ቢቻላችሁ ዐይናችሁን ቢሆን
እንኳ አውጥታችሁ የምትሰጡኝ እንደ
ነበራችሁ እመሰክራለሁ። 16እውነቱን ስለ
ነገርኋችሁ ጠላት ሆንሁባችሁን?
17እነዚያ ሰዎች ወደራሳቸው
ሊወስዱችሁ ይተጋሉ፤ ለበጎ ግን
አይደለም፤ የሚፈልጉት እናንተን ከእኛ
ነጥለው የራሳቸው ሊያደርጓችሁ ነው።
18ለበጎ እስከ ሆነ ድረስ ተቈርቋሪ መሆን
መልካም ነው፤ ይህም መሆን የሚገባው
ዘወትር እንጂ እኔ ከእናንተ ጋር ሳለሁ
ብቻ አይደለም። 19የምወዳችሁ ልጆቼ ሆይ፤
ክርስቶስ በውስጣችሁ እስኪቀረጽ ድረስ
ስለ እናንተ እንደ ገና ምጥ ይዞኛል፤ 20ስለ
እናንተ ግራ በመጋባት ተጨንቄአለሁና፤
አሁን በመካከላችሁ ተገኝቼ ለየት ባለ ቋንቋ
ልናገራችሁ ምን ያህል በወደድሁ!

## አጋርና ሣራ ምሳሌ መሆናቸው

21እናንት ከኦሪት ሕግ በታች ለመኖር
የምትሹ እስቲ ንገሩኝ፤ ሕግ ምን እንደሚል
አልሰማችሁምን? 22አብርሃም፣ አንዱ
ከባሪያዪቱ፣ ሌላው ደግሞ ከነጻዪቱ
ሴት የሆኑ ሁለት ልጆች እንደ ነበሩት
ተጽፎአልና። 23ባሪያ ከነበረችው ሴት
የተገኘው ልጅ፣ እንደ ሥጋ ልማድ ነበር፤
ከነጻዪቱ ሴት የተወለደው ግን በተስፋው
ቃል መሠረት ነው።
24እነዚህ ሴቶች ሁለቱን ኪዳኖች
ስለሚያመለክቱ፣ ይህ ሁኔታ እንደ ምሳሌ
የሚታይ ነው። አንደኛዋ ኪዳን ከሲና
ተራራ ስትሆን፣ ለባርነት የሚሆኑ ልጆችን
የምትወልድ ናት፤ እርሷም አጋር ናት።
25እንግዲህ አጋር በዐረብ አገር ያለችው
የሲናን ተራራ በመወከል፣ አሁን ያለችውን
ኢየሩሳሌምን ትመስላለች፤ ከልጆ

4፥7 ሮሜ8፥17
4፥8 ቍ3፤ 2ዜና13፥9፤ ኢሳ37፥19፤ ኤር2፥11፤ 5፥7፤ 16፥20፤ ሮሜ1፥28፤ 1ቆሮ1፥21፤ 8፥4:5፤ 15፥34
4፥9 ቍ3፤ 8፥3፤ ቈላ2፥20
4፥12 ሮሜ7፥1፤ ገላ6፥18
4፥13 1ቆሮ2፥3
4፥14 ማቴ10፥40
4፥16 አሞ5፥10
4፥17 ገላ2፥4:12
4፥18 ቍ13:14
4፥19 ሮሜ8፥29፤ ኤፌ4፥13፤ 1ተሰ2፥11
4፥21 ሮሜ2፥12
4፥22 ዘፍ16፥15፤ 21፥2
4፥23 ቍ28:29፤ ዘፍ 17፥16-21፤ 18፥10-14፤ 21፥1፤ ሮሜ9፥7:8፤ ዕብ11፥11

---

እግዚአብሔር እንድንጮኽ የሚያደርግበትን ጥልቅ የሆነ ወዳጅነትን፣ ጥልቅ ስሜትን፣ ቍምነገረኛነትን፣ ደስ መሰኘትንና እምነትን የሚገልጽ ነው -ከማር 14ኽ36፤ ከሮሜ 8ኽ15:26-27 ጋር ያነጻጽሩ?:: መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን እየሠራ እንደ ሆነ የሚያረጋግጡልን ሁለት ምልክቶች አሉ፤ እነርሱም ወደ እግዚአብሔር፣ "አባ" ብለን እንድንጮኽ፣ ኢየሱስንም "ጌታ ነው" እንድንልና እንድንታዘዘው የሚያደርጉን ሁኔታዎች ናቸው -1ቆሮ 12ኽ3 እና ማብ ይመ?::

(2) እኛ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን እንዲልክ ስላደረገው፣ በዚህ ክፍል ጳውሎስ በይበልጥ የሚያተኵረው በመንፈስ ቅዱስ ስለ መጠመቅና ባለማቋረጥም በመንፈስ ቅዱስ ስለ መሞላት ሊሆን ይችላል (ከሐሥ 1፥5፤ 2፥4፤ ከኤፌ 5፥18 ጋር ያነጻጽሩ):: በክርስቶስ አምነን የእግዚአብሔር "ልጆች" ስለ ሆንን፣ እግዚአብሔር መንፈሱ በልባችን ውስጥ እንዲፈስ ያደርጋል:: የልጁ መንፈስ ከሙላኩ በፊት (3፥5 እና ማብ ይመ)፣ "ሙሉ የልጅነት መብት" (ቍ 5) ተቀብለናል::

**4፥13 በሕመም፤** ይህም ሕመም የዐይን መታወክ (6፥11)፣ ወባ፣ የሥጋው መውጊያ ወይም በድንጋይ ከመወገሩ የተነሣ የደረሰበት አካለ ጐደሎነት ሊሆን ይችላል:: ሕመሙ ምንም ይሁን ምን፣ ጳውሎስ አንድ ዐይነት የአካል ጉዳት የደረሰበት ይመስላል:: የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽሙና በክርስቲያናዊ አገልግሎታቸው የሚተጉ ታማኝ ክርስቲያኖች የጤና ችግር፣ የሕመም ስሜት ወይም ድካም አይደርስባቸውም ማለት አይቻልም::

**4፥19 ምጥ፤** ይህ ቃል (በግሪክ ቋንቋ፣ ዑኦዲኖጸ) ከክርስቶስ የተለዩትና ከጸጋው የራቁት (5፥4) ይድኑ ዘንድ በመመኘት ጳውሎስ በልቡ ውስጥ የሚሰማውን ሐዘን፣ ጭንቀትና ናፍቆት ይገልጻል:: ክርስቶስ እንደ ገና በልባቸው ውስጥ ይሣል ዘንድ ዳግመኛ መንፈሳዊ ልደት እንደሚያስፈልጋቸው፣ ይህም እስከሚሆን ድረስ ራሱን ምጥ እንደ ያዛት ሴት በጭንቀ ውስጥ እንዳለ አድርጎ ያቀርባል::

**4፥22 አብርሃም ... ሁለት ልጆች እንደ ነበሩት፤** ጳውሎስ በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን መካከል ያለውን ልዩነት ለማሳየት፣ አንድ ምሳሌ ይጠቀማል:: አጋር በሲና ተራራ የተመሠረተውን ብሉይ ኪዳንን የምትወክል ስትሆን (ቍ 25)፣ አሁንም ልጆቿ በዚህ ኪዳን ሥር ይኖራሉ፤ "የተወለዱትም እንደ ሥጋ ልማድ" (ቍ 23) ማለትም መንፈስ ቅዱስ የሌላቸው ናቸው:: ሣራ ሌላዪቱ የአብርሃም ሚስት ስትሆን፣ እርሷም አዲስ ኪዳንን የምትወክል ናት፤ ልጆቿ ማለትም በክርስቶስ የሚያምኑ፣ መንፈስ ቅዱስ ያላቸውና በ"መንፈስ ኀይል የተወለዱ" (ቍ 29 እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው በገጽ 321 ላይ፣ "*እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር የገባው ኪዳን*" በሚልና በገጽ 1970 ላይ፣ "*የቀደመው ኪዳንና አዲሱ ኪዳን*" በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኵረት ጽሑፎች ይመ)::

ጋር በባርነት ናትና። 26ከላይ የሆነችው
ኢየሩሳሌም ግን በነጻነት ትኖራለች፤
እርሷም እናታችን ናት። 27እንዲህ ተብሎ
ተጽፎአልና፤

"አንቺ የማትወልጂ መካን ሆይ፤
  ደስ ይበልሽ፤
አንቺ አምጠሽ የማታውቂ፣
  በእልልታ ጩኺ፤
ባል ካላት ይልቅ፣
  የብቸኛዪቱ ልጆች በዝተዋልና።"

28እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ እናንተም
እንደ ይስሐቅ የተስፋው ቃል ልጆች ናችሁ።
29በዚያን ጊዜ እንደ ሥጋ ልማድ የተወለደው፣
ልጅ በመንፈስ ኀይል የተወለደውን
አሳደደው፤ አሁንም እንደዚያው ነው። 30ነገር
ግን መጽሐፍ ምን ይላል? "ባሪያዪቱን
ከልጇ ጋር አስወግዳት፤ የባሪያዪቱ ልጅ
ከነጻዪቱ ልጅ ጋር አይወርስምና" ይላል።
31ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፤ እኛ የነጻዪቱ
እንጂ የባሪያዪቱ ልጆች አይደለንም።

5 ክርስቶስ ነጻ ያወጣን በነጻነት እንድንኖር
ነው። ስለዚህ ጸንታችሁ ቁሙ፤ ዳግመኛም
በባርነት ቀንበር አትጠመዱ። 2የምለውን
አስተውሉ፤ ትገረዙ ዘንድ ብትፈልጉ፣
ክርስቶስ ፈጽሞ ለእናንተ እንደማ ይበጃችሁ
እኔ ጳውሎስ እነግራችኋለሁ። 3መገረዝ
ለሚፈልግ ሁሉ ሕግን በሙሉ የመፈጸም
ግዴታ እንዳለበት እንደ ገና ለእ ያንዳንዱ
በግልጽ እናገራለሁ። 4በሕግ ለመጽደቅ
የምትጥሩ፣ ከክርስቶስ ተለይታችኋል፤ ከጸጋ
ርቃችኋል። 5እኛ ግን ተስፋ የምናደርገውን
ጽድቅ፣ በመንፈስ አማካይነት በእምነት
ሆነን በናፍቆት እንጠባበቃለን። 6በክርስቶስ
ኢየሱስ ከሆኑ፣ መገረዝ ወይም አለመገረዝ
አይጠቅምምና፤ የሚጠቅመውስ
በፍቅር የሚገለጽ እምነት ብቻ ነው።

7ሩጫችሁ መልካም ነበር፤ ታዲያ
ያሰናከላችሁ፣ ለእውነትስ እንዳትታዘዙ
የከለከላችሁ ማን ነው? 8እንዲህ ያለው
ማባበል ከሚጠራችሁ የመጣ አይደለም፤
9"ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ ያቦካል።"
10የተለየ ሐሳብ እንደማይኖራችሁ በጌታ
እታመናለሁ። ግራ የሚያጋባችሁ ማንም
ይሁን ማን፣ ፍርዱን ይቀበላል።

11ወንድሞች ሆይ፤ እስከ ዛሬ ስለ መገረዝ
የምሰብክ ከሆነ፣ ታዲያ እስካሁን ለምን
ያሳድዱኛል? እንደዚያማ ቢሆን ኖሮ፣ መስ
ቀል ዕንቅፋት መሆን በቀረ ነበር። 12ግራ
የሚያጋቡአችሁ ሰዎች የራሳቸውን መግረዝ
ብቻ ሳይሆን ይኰንድሉ! 13ወንድሞቼ
ሆይ፤ ነጻ እንድትሆኑ ተጠርታችኋል፤
ነጻነታችሁን ግን ሥጋዊ ምኞታችሁን*
መፈጸሚያ አታድርጉት፤ ይልቁንም አንዱ
ሌላውን በፍቅር ያገልግል።

4፥26 ዕብ12፥22፣ ራእ3፥12፣ 21፥2፡10
4፥27 ኢሳ 54፥1
4፥28 ቍ23፣ ገላ3፥16
4፥29 ቍ23፣ ዘፍ21፥9
4፥30 ዘፍ21፥10
4፥31 ቍ22፣ ሮሜ7፥4
5፥1 ቍ13፣ ማቴ23፥4፣ ዮሐ8፥32፣ ሮሜ7፥4፣ 1ቆሮ16፥13፣ ገላ2፥4
5፥2 ቍ3፡6፡11፡12፣ ሐሥ15፥1
5፥3 ሮሜ2፥25፣ ገላ3፥10፣ ያዕ2፥10
5፥4 ሮሜ3፥28 ዕብ12፥15፣ 2ጴጥ3፥17
5፥5 ሮሜ8፥23፡24
5፥6 ሮሜ16፥3፣ 1ቆሮ7፥19፣ 1ተሰ1፥3፣ ያዕ2፥22
5፥7 1ቆሮ9፥24፣ ገላ3፥1
5፥8 ሮሜ8፥28
5፥9 1ቆሮ5፥6
5፥10 ቍ12፣ 2ቆሮ2፥3፣ ገላ1፥7፣ ፊል3፥15 5፥11 ሉቃ2፥34፣ ገላ4፥29፣ 6፥12 5፥12 ቍ10 5፥13 ቍ1፡24፣ 1ቆሮ8፥9፣ 9፥19፣ 2ቆሮ4፥5፣ ኤፌ5፥21፣ 1ጴጥ2፥16

*5፥13 ወይም ኀጢአተኛ ተፈጥሮአችሁን፤ እንዲሁም ቍ 16፡17፡19 እና 24 ይመ።

5፥4 **ከጸጋ ርቃችኋል፤** አንዳንድ የገላትያ ሰዎች በክርስቶስ የነበራቸውን እምነት ትተው፣ ሕግን ሁሉ ወደ መፈጸም ግዴታ ውስጥ ገብተዋል (1፥6-7፤ 5፥3)። ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህ ሰዎች ከጸጋ የራቁ መሆናቸውን ይናገራል። ከጸጋ መራቅ ከክርስቶስ መለየት (ከዮሐ 15፥4-6 ጋር ያነጻጽሩ) እንዲሁም ሕይወትንና ድነትን የሚያስገኘውን የእግዚአብሔርን ጸጋ መርሕ መተው ማለት ነው። ይኸውም ከክርስቶስ ጋር ያለውን ኅብረት ዋጋ ቢስ ማድረግና ከእንግዲህ "በክርስቶስ" መኖርን ማቆም ነው (ዮሐ 15፥6 እና ማብ፣ 2ጴጥ 2፥15፡20-22 ይመ፤ በገጽ 1746 ላይ፣ "እምነትና ጸጋ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

5፥6 **በፍቅር የሚገለጽ እምነት፤** ሰው የሚድነው በእምነት እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ አበክሮ ይገልጻል (2፥15-16፣ ሮሜ 3፥22፤ ኤፌ 2፥8-9)። (1) በዚህ ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ የዚህ እምነት ትክክለኛ ባሕርይ ምን እንደ ሆነ ይገልጻል። የሚያድን እምነት በፍቅር የሚገለጽ በጎ ተግባር የማይለየው፣ እጅግ አስፈላጊ የሆነ በሕያው አዳኝ ላይ ያለ ሕያው እምነት ነው፤ (2) ክርስቶስን በፍጹም ልብ መውደድና መታዘዝ የሌለበት (ከ1ዮሐ 2፥3፤ 5፥3 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት ሥራ ግድ የማይለው (ከማቴ 12፥28 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ኀጢአትንና ዓለምን አጥብቆ የማይቃወም (ቍ 16-17) እምነት፣ የሚያድን እምነት ተብሎ ሊቈጠር አይችልም (ከያዕ 2፥14-16 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1746 ላይ፣ "እምነትና ጸጋ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

5፥7 **ለእውነትስ እንዳትታዘዙ የከለከላችሁ፤** የስሕተት ትምህርት አንድም በክርስትና እምነት ውስጥ የሚገኘውን ዐቢይ የሆነውን እውነት በመካድ መልክ (1፥9 እና ማብ ይመ) አሊያም አንድ አማኝ እውነተኛና ፍጹም ክርስቲያን ይሆን ዘንድ፣ በአዲስ ኪዳን ላይ ከተጻፈው (ከ1፥6፤ 2፥16፤ 5፥2፡6 ጋር ያነጻጽሩ) ውጪ ሌላ ተጨማሪ ነገር ማድረግ እንደሚያስፈልገው በመግለጽ ሊመጣ ይችላል፤ (1) ክርስቲያናዊ ትምህርት ሁሉ ሐዋርያት ባስተማሩት እውነት መመዘን አለበት፤ ማለትም ትምህርቱ በአዲስ ኪዳን ከሚገኘው ከመጀመሪያው የክርስቶስ መልእክትና የሐዋርያት ትምህርት ጋር ይስማማል ወይ? ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል (ከ1፥11-12፤ 2፥1-2፡7-9 ጋር ያነጻጽሩ፤ ኤፌ 2፥20 እና ማብ ይመ)። "ትምህርቱ ከሐዋርያት መልእክት የጐደለ ነገር ይዞአልን? የሐዋርያትን መልእክት እየተቀበለ በሌላ በኩል እውነትን የሚያፋልስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የሆነ የሚጨምረው ሌላ ነገር አለን?" ብለን መጠየቅ አለብን። (2) የአንድን ትምህርት ትክክለኛነት የምንለካው ከስሜት፣ ከተመክሮ፣ ከውጤት፣ ከሚፈጸመው ታምር ወይም ሌሎች ከሚናገሩት አንጻር ብቻ መሆን የለበትም፤ እውነትን ለመመዘን የመጨረሻው ከፍተኛ መለኪያ አዲስ ኪዳን ነው። (3) በክርስቶስ ከፍ ወዳለ የእድገት ደረጃ ለመድረስ የእግዚአብሔር ቃል በቂ እንዳልሆነ በመቍጠር፣ ቤተ ክርስቲያን ዘመናዊ ዕውቀት፣ ሳይንስ፣ ፍልስፍና፣ የሥነ ልቦና ትምህርትና አዲስ መገለጥ እንደሚያስፈልጋት ከሚያስተምር ማንኛውም ትምህርት መጠንቀቅ ይኖርብናል።

5፥13 **ነጻ እንድትሆኑ ተጠርታችኋል፤** 2ቆሮ 3፥17 እና የክርስቲያን ነጻነት በሚለው ላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

14ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ተጠቃሎአል፤
ይኸውም፣ "ባልንጀራህን እንደ ራስህ
ውደድ" የሚል ነው። 15ነገር ግን እርስ
በርሳችሁ የምትነካከሱና የምትበላሉ ከሆነ፣
እርስ በርሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ።

## በመንፈስ መመላለስ

16እንግዲህ በመንፈስ ኑሩ እላለሁ፤
የሥጋንም ምኞት አትፈጽሙም። 17ሥጋ
መንፈስ የማይፈልገውን፣ መንፈስም ሥጋ
የማይፈልገውን ይመኛልና፤ እነዚህ እርስ
በርሳቸው ስለሚጋጩ፣ የምትፈልጉትን
አታደርጉም። 18በመንፈስ ብትመሩ ግን፣
10 ከሕግ በታች አይደላችሁም።

19የሥጋ ሥራ ግልጽ ነው፦ ይኸውም
ዝሙት፣ ርኵሰት፣ መዳራት፣ 20ጣዖትን
ማምለክ፣ ሟርት፣ ጥላቻ፣ ጠብ፣ ቅናት፣
ቍጣ፣ ራስ ወዳድነት፣ መለያየት፣
አድመኛነት፤ 21ምቀኝነት፣ስካር፣ዘፋኝነት፣
እንዲሁምእነዚህንየመሰለውነው።አስቀድሜ
እንዳልሁ፣ አሁንም አስጠነቅቃችኋለሁ፤
በእንዲህ ሁኔታ የሚኖሩ ሁሉ
የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።

22የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣
ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣
ታማኝነት፣ 23ገርነት፣ ራስን መግዛት
ነው። እንደነዚህ ያሉትን ግን የሚከለክል ኤፌ 3፥17-21
ሕግ የለም። 24የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት
ሥጋን ከክፉ ምኞቱና መሻቱ ጋር
ሰቅለውታል። 25በመንፈስ የምንኖር ከሆን፣
በመንፈስ እንመላለስ። 26እርስ በርሳችን
እየተነካነታተልንና እየተቀናናን በከንቱ
ውዳሴ አንመካ።

## ለሰው ሁሉ በጎ ማድረግ

6 ወንድሞች ሆይ፤ አንድ ሰው በኀጢአት
ውስጥ ገብቶ ቢገኝ፣ መንፈሳውያን
የሆናችሁ እናንተ በገርነት ልትመልሱት
ይገባል። ነገር ግን አንተም እንዳትፈተን
ራስህን ጠብቅ። 2አንዱ የሌላውን ከባድ
ሸክም ይሸከም፤ በዚህም ሁኔታ የክርስቶስን
ሕግ ትፈጽማላችሁ። 3አንድ ሰው ምንም
ሳይሆን ትልቅ የሆነ ቢመስለው ራሱን
ያታልላል። 4እያንዳንዱ የራሱን ተግባር
ይመርምር፤ ከዚያም በኋላ፣ ከሌላ ሰው ጋር
ራሱን ሳያወዳድር፣ ስለ ራሱ የሚመካበትን
ያገኛል፤ 5እያንዳንዱ የራሱን ሸክም ሊሸከም
ይገባዋልና።

5፥14 ዘሌ19፥18፤ ማቴ5፥43፤ ገላ6፥2
5፥16 ቍ18፡24፡25፤ ሮሜ8፡2፡4-6፡ 9፡14፤ 2ቆሮ5፥17
5፥17 ሮሜ7፥15-23፤ 8፥5-8
5፥18 ቍ16፤ ሮሜ2፥12፤ 1ጢሞ1፥9
5፥19 1ቆሮ 6፥18
5፥21 ማቴ15፥19፤ 25፥32፤ ሮሜ13፥13
5፥22 ሚል2፥6፤ ማቴ7፥16-20፤ ኤፌ5፥9፤ ቆላ3፥12-15
5፥23 ቍ18፤ ሐሥ24፥25
5፥24 ቍ13፡16-21፤ 16፡17፤ ሮሜ6፥6፤ 7፥5፡18፤ 8፥3-5፡8፡9፤ 12፡13፤ 13፥14፤ ገላ6፥8፤ ቆላ2፥11
5፥25 ቍ16
5፥26 ፊል2፥3
6፥1 ማቴ18፥15፤ 1ቆሮ2፥15፤ 3፥1፤ 2ቆሮ2፥7 6፥2 1ቆሮ9፥21፤ ያዕ2፥8 6፥3 ሮሜ12፥3፤ 1ቆሮ3፥18፤ 8፥2
6፥4 2ቆሮ10፥12፤ 13፥15 6፥5 ቍ2፤ ኤር31፥30

**5፥17 ሥጋ ... መንፈስም፤** በአማኞች ውስጥ በሥጋና በመንፈስ መካከል የሚደረግ መንፈሳዊ ግጭት አካልን ሁሉ የሚመለከት ነው፤ ትግሉም ለሥጋ ፍላጎት በመሸነፍ በኀጢአት ቍጥጥር ሥር በመሆንና የመንፈስ ቅዱስን ፈቃድ በመፈጸም በክርስቶስ አገዛዝ ሥር በመሆን (ቍ 16፤ ሮሜ 8፥4-14) መካከል የሚደረግ ነው:: የጦርነቱ ሜዳ ክርስቲያኖች ራሳቸው ናቸው፤ በመጨረሻም ከክርስቶስ ጋር መግዛት ያለባቸው ከሆነም፣ ግጭቱ በምድር የሕይወት ዘመናቸው ሁሉ መቀጠሉ አይቀርም (ሮሜ 7፥7-25፤ 2ጢሞ 2፥12፤ ራእ 12፥11፤ ኤፌ 6፥11 እና ማብ ይመ)::

**5፥19 የሥጋ ሥራ፤** የሥጋ ሥራ ምን እንደሚመስል ለመረዳት በገጽ 1853 ላይ፣ *"የኀጢአተኛ ተፈጥሮ ሥራዎችና የመንፈስ ፍሬ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ::

**5፥21 የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም፤** ሐዋርያው ጳውሎስ ሕግን በመፈጸም የእግዚአብሔርን መንግሥት መውረስ እንደማይቻል ቢገልጽም (2፥16፤ 5፥4)፣ ኀጢአት መሥራት ግን ከእግዚአብሔር መንግሥት እንደሚያስወጣ ያስተምራል (1ቆሮ 6፥9 እና ማብ ይመ፤ ከማቴ 25፥41-46፤ ከኤፌ 5፥7-11 ጋር ያነጻጽሩ)::

**5፥22-23 የመንፈስ ፍሬ፤** በተለያየ መንገድ በመንፈስ ፍሬ ላይ የተሰጠውን አስተያየት ለመገንዘብ በገጽ 1853 ላይ፣ *"የኀጢአተኛ ተፈጥሮ ሥራዎችና የመንፈስ ፍሬ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ::

**6፥1 በገርነት ልትመልሱት ይገባል፤** *"መመለስ"* (በግሪክ ቋንቋ፣ *"ካታርቲዞ"*) የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ የዓሣ ማጥመጃ መረብ ማበጀትን (መጠገንን) ወይም የሰውን ባሕርይ ማስተካከልን (2ቆሮ 13፥11) ያመለክታል:: ስለዚህ ሰውን መመለስ ማለት ወደ እውነተኛ ንስሓ፣ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስና ወደ መንገዱ ሙሉ በሙሉ እንዲመለስ ማድረግ ማለት ነው:: ይህም "በገርነት" የሚወሰድ የሥነ ሥርዐት ርምጃን (ማቴ 13፥30 እና ማብ ይመ) ሊጨምር ይችላል::

(1) ከዚህ ላይ ጳውሎስ ይህን የተናገረው በምእመናን ሁሉ ላይ አሳፋሪ ሁኔታን የሚፈጥሩትን ከባድ በደሎች በማሰብ አይደለም (ከ1ቆሮ 5፥5 ጋር ያነጻጽሩ)፤ እንደዚህ ያሉ በደሎች ሲፈጸሙ፣ ሰውዬውን ከማቅናት በፊት ለጊዜው ከኅብረት ማግለልን ሊጠይቅ ይችላል (1ቆ 5፥11)::

(2) ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ መመለስ ሲናገር፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወዳለው የመሪነት ሥልጣን ወይም የማስተማር ኀላፊነት መመለስ ማለቱ አይደለም:: በአገልግሎት ውስጥ ኀላፊነት ስፍራ ላይ ሆነው ማገልገል የሚፈልጉ አማኞች፣ ሊኖራቸው የሚገባ መንፈሳዊ ብቃትና ደረጃ አሁን ካሉበት መንፈሳዊ ደረጃ የላቀ መሆን አለበት:: በአማኞች ዘንድ ጥሩ ምሳሌነት ያላቸው ይሆኑ ዘንድ ወደ ጽድቅ የሚያደርሰውን የእግዚአብሔርን መርሕ በታማኝነት ጸንተው መከተላቸውን የሚያሳይ ታሪክ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል (1ጢሞ 4፥12 ይመ፤ በገጽ 1925 ላይ፣ *"የመሪዎች መንፈሳዊ ብቃት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

**6፥2 አንዱ የሌላውን ከባድ ሸክም ይሸከም፤** "አንዱ የሌላውን ከባድ ሸክም ይሸከም" የሚለው ሐሳብ በሕመማቸው፣ በሐዘናቸውና የገንዘብ ችግር በሚያጋጥማቸው ጊዜ ችግረኞችን መርዳትንም ያካትታል:: ጳውሎስ ይህን የተናገረው፣ ሚስዮናውያንንና አስተማሪዎችን መርዳት እንደሚያስፈልግ በማሰብ ሊሆን ይችላል (ቍ 6 እና ማብ ይመ፤ ከሮሜ 15፥1፤ ከ1ቆሮ 9፥14 ጋር ያነጻጽሩ):: የሌላውን ከባድ ሸክም የመሸከም ብቃትና ችሎታ ከመለኮታዊ ኀይል ብቻ የሚገኝ ነው (መዝ 55፥22፤ 1ጴጥ 5፥7)::

6ማንም ቃሉን የሚማር፣ መልካም
የሆነውን ነገር ሁሉ ከመምህሩ ጋር
ይካፈል።
7አትታለሉ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም።
ሰው የሚዘራውን ያንኑ ያጭዳል። 8ሥጋዊ
ምኞቱን ለማርካት የሚዘራ፣ ከሥጋው[n]
ጥፋትን ያጭዳል፤ መንፈስን ለማስደሰት
የሚዘራ ግን ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት
ያጭዳል። 9በጎ ነገር ከማድረግ አንታክት፤
ተስፋ ካልቈረጥን ጊዜው ሲደርስ መከሩን
እናጭዳለን። 10ስለዚህ ዕድሉ ካለን ለሰው
ሁሉ፣ በተለይም ለእምነት ቤተ ሰቦች
መልካም እናድርግ።

## አዲስ ፍጥረት መሆን

11እንዴት ባሉ ታላላቅ ፊደላት በእጄ
እንደ ጻፍሁላችሁ ተመልከቱ።
12ውጫዊ በሆነ ነገር ለመታየት የሚፈልጉ
ሰዎች ትገረዙ ዘንድ ሊያስገድዷችሁ
ይጥራሉ፤ ይህንም የሚያደርጉት ስለ
ክርስቶስ መስቀል እንዳይሰደዱ ነው።
13እነርሱ በሥጋችሁ ለመመካት ሲሉ
እንድትገረዙ ፈለጉ እንጂ፣ የተገረዙት
ራሳቸው እንኳ ሕግን የሚጠብቁ አይደሉም።
14ነገር ግን ዓለም ለእኔ ከተሰቀለበት፣ እኔም
ለዓለም ከተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ
ክርስቶስ መስ ቀል በቀር፣ ሌላው ትምክሕት
ከእኔ የራቀ ይሁን። 15መገረዝም ሆነ አለ
መገረዝ አይጠቅምም፤ የሚጠቅመው አዲስ
ፍጥረት መሆን ነው። 16ይህን ትእዛዝ
በሚከተሉ ሁሉ፣ የእግዚአብሔር በሆነው
እስራኤልም ላይ ሰላምና ምሕረት ይሁን።
17እኔ የኢየሱስን ምልክት በሥጋዬ
ተሸክሜአለሁና፣ ከእንግዲህ ወዲህ ማንም
አያስቸግረኝ። 18ወንድሞች ሆይ፤ የጌታችን
የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመንፈሳችሁ ጋር
ይሁን፤ አሜን።

6፥6 1ቆሮ9፥11፡14፤ 1ጢሞ5፥17፡18
6፥8 ኢዮ4፥8፤ ሆሴ8፥7፤ ሮሜ6፥23፤ ያዕ3፥18
6፥9 ኢዮ42፥12፤ መዝ126፥5፤ 1ቆሮ15፥58፤ 2ቆሮ4፥1፤ ዕብ12፥3፤ ራእ2፥10
6፥10 ምሳ3፥27፤ ኤፌ2፥19፤ ቲቶ2፥14፤ 1ጴጥ4፥17
6፥11 1ቆሮ16፥21
6፥12 ማቴ23፥25፡26፤ ሐሥ15፥1፤ ገላ5፥11
6፥15 1ቆሮ7፥19፤ 2ቆሮ5፥17
6፥17 ኢሳ44፥5፤ 2ቆሮ1፥5፤ 11፥23
6፥18 ሮሜ16፥20፤ ፊል4፥23፤ 2ጢሞ4፥22፤ ፊሞ1፥25

*[n]6፥8 ወይም ኀጢአተኛ ተፈጥሮ ለማርካት የሚዘራ፣ ከዚሁ ተፈጥሮ*

6፥6-10 **መልካም የሆነውን ነገር ሁሉ ... ይካፈል፤** ወንጌል የሚስተምሩትን ሰዎች ለኑሮ በሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ መርዳት፣ የእግዚአብሔርን ቃል የተማሩ ሰዎች ሁሉ ኀላፊነት ነው (1ቆ 9፥14፡ 1ጢሞ 5፥18)። ርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ሲባል ታማኝ መጋቢዎችን፣ ሠራተኞችን፣ አስተማሪዎችንና ወንጌላውያንን ያካትታል (1ቆሮ 9፥14፡ 3ዮሐ 1፥6-8)። መርዳት እየተቻለ ሊረዱ የሚገባቸውን ሰዎች አለመርዳት፣ ራስ ወዳድነትን ዘርቶ ጥፋትን ማጨድ ነው (ቍ 7-9)። በቃሉ የሚያገለግሉ ሰዎችን መርዳት፣ ለእምነት ቤተ ሰቦች ማድረግ ከሚገባን መልካም ነገር አንዱ ነው (ቍ 10)፤ ሽልማትንና (ማቴ 10፥41-42) የዘላለምን ሕይወት (ቍ 8) ሁለቱንም "ጊዜው ሲደርስ ... እናጭዳለን" (ቍ 9)።

6፥7 **እግዚአብሔር አይዘበትበትም፤** ዳግም የተወለዱና በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ የክርስቶስ ተከታዮች እንደ ሆኑ የሚናገሩ ሰዎች (ቍ 3)፣ በሌላ በኩል ግን ሥጋቸውን ደስ ለማሰኘት ሆን ብለው የኀጢአትን ዘር የሚዘሩ ከሆነ (5፥19-21)፣ በእግዚአብሔር ላይ እየዘበቱበትና እየናቁት ናቸው። በፍጹም አትታለሉ፤ እንደነዚህ ዐይነት ሰዎች መጨረሻቸው ጥፋትና (ቍ 8) ሞት ነው እንጂ (ሮሜ 6፥20-23፤ 1ቆሮ 6፥9 እና ማብ ይመ) "የዘላለም ሕይወት" አይደለም።

6፥14 **ዓለም ለእኔ ከተሰቀለበት፤** ለእኛ ዘላለማዊ ድነት ይሆን ዘንድ አዳኙ በአሠቃቂ ሁኔታ እንደ ሞተ የሚያመለክተው የክርስቶስ መስቀል ዓለምን ከእኛ፣ እኛንም ከዓለም የሚለይ ዐጥር (ግድግዳ) ነው። "ዓለም" ማለት እግዚአብሔርን፣ መንግሥቱንና ጽድቁን የሚቃወም ማንኛውም ሥርዐት ነው (ከ4፥3፤ ከ1ቆሮ 2፥12፤ 3፥19፤ ከ1ዮሐ 2፥15-17 ጋር ያነጻጽሩ)። (1) ሕይወታቸውና ትምክሕታቸው መስቀሉ እንዲሆን ያደረጉ ሰዎች የዓለምን ደንብ፣ የምትሰጠውን ጥቅም፤ ሐሳብና ክብር እንዲሁም የምትከተለውን የአኗኗር ዘይቤ ሁሉ ጨምሮ ዓለምን ራሷን አጥብቀው የሚጠሉ ናቸው። (2) የእኛ "ከክርስቶስ ጋር መሰቀላችን" (2፥20)፣ ለዓለም የተሰቀልን መሆናችንን ይጨምራል። ከክርስቶስና ከእርሱ ሀልዎት ልባችን እንዲርቅ ለሚያደርግ ምድራዊ ደስታ ሁሉ ጀርባችንን ሳንሰጥ፣ በክርስቶስ መስቀል ከሚገኘው ድነትና ክብር ተካፋይ መሆን አንችልም።

6፥16 **የእግዚአብሔር በሆነው እስራኤልም፤** ይህ ሐረግ በአዲስ ኪዳን ሥር ያሉትን፣ ማለትም ከአይሁድና ከአሕዛብ ወገን የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑትን ሁሉ የሚመለከት ነው። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ለዓለም የተሰቀሉና (ቍ 14) "አዲስ ፍጥረት" የሆኑ ሁሉ (ቍ 15) እውነተኛ የእግዚአብሔር እስራኤል መባል ይችላሉ (ከሮሜ 2፥28-29፤ 9፥7-8፤ ከኤፌ 2፥14-22፤ ከፊል 3፥3፤ ከ1ጴጥ 2፥9 ጋር ያነጻጽሩ)።

# የኀጢአተኛ ተፈጥሮ ሥራዎችና የመንፈስ ፍሬ

*ገላ 5፥22-23 "የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት ራስን መግዛት ነው:: እንደነዚህ ያሉትንም የሚከለክል ሕግ የለም::"*

---

በመንፈስ ቅዱስ በተሞላ አማኝ የአኗኗር ዘይቤና የሥጋን ሥራ በሚፈጽም ሰው የአኗኗር ዘይቤ መካከል ያለውን ልዩነት በግልጽ የሚያሳይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ገላትያ 5፥16-26 ያለ ክፍል የለም:: ጳውሎስ በአጽንዖት የሚናገረው፣ መንፈስና ሥጋ ሁልጊዜ እርስ በርስ እንደሚጋጩ በመግለጽ በአጠቃላይ የአኗኗር ዘይቤ ላይ ያለውን ልዩነት ብቻ ሳይሆን፣ የሥጋ ሥራና የመንፈስ ፍሬ ምን ምን እንደ ሆኑ የሚያመለክቱ ዝርዝር ጉዳዮችንም ይጨምራል::

የሥጋ ሥራ፤ "ኀጢአተኛ ተፈጥሮ" (በግሪክ ቋንቋ፣ ሳርክስ) የሚለው ሐረግ ብልሹ ምኞቱን ጨምሮ የሰውን ተፈጥሮ የሚያሳይ ነው:: በክርስቶስ አምነው ከዳኑ በኋላም በክርስቲያኖች ውስጥ የኀጢአተኛ ተፈጥሮ ቅሪት ሊኖር ይችላል፤ ይህም አደገኛ ጠላታቸው ነው (ሮሜ 8፥6-8:13፤ ገላ 5፥17:21):: የሥጋን ሥራ አዘወትረው የሚፈጽሙ ሁሉ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም (ገላ 5፥21):: ስለዚህ አማኙ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል የማያቋርጥ ጦርነት በማድረግ፣ ኀጢአተኛ ተፈጥሮን መቃወምና መግደል አለበት (ሮሜ 8፥4-14 እንዲሁም ገላ 5፥17 እና ማብ ይመ):: የሥጋ ሥራ የሚከተሉትን ያካትታል (ገላ 5፥19-21):

(1) ከሥነ ምግባር ውጭ የሆነ ወሲባዊ ግንኙነትን (በግሪክ ቋንቋ፣ ፓርኒያ)፣ ይኸውም ኢግብረገባዊ የሆነ የወሲብ ልማድና የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሲሆን፣ ወሲባዊ ግንኙነትን የሚያሳዩ ሥዕሎችንና ፊልሞችን በማየት ወይም ስለዚህ የተጻፉ ጽሑፎችን በማንበብ መደሰትን ያካትታል (ከዘፀ 20፥14፤ ከማቴ 5፥31-32፤ 19፥9፤ ከሐሥ 15፥20:29፤ 21፥25፤ ከ1ቆሮ 5፥1 ጋር ያነጻጽሩ)፤

(2) "ርኩሰትን" (በግሪክ ቋንቋ፣ አካታርሲያ)፣ ይኸውም የዝሙት ኀጢአትን፣ ክፉ ድርጊትን፣ መጥፎ ልማድን፣ ክፉ የልብ ሐሳብንና ምኞትን ይጨምራል (ኤፌ 5፥3፤ ቈላ 3፥5)::

(3) ከመጠን በላይ ከመብላት፣ ከመጠጣትና ከመጨፈር ጋር የተያያዘ ኢግብረ ገባዊ ወሲብን (በግሪክ ቋንቋ፣ አሴልጂያ)፣ ይኸውም ዓለማዊነትን፣ በአደባባይ ኀፍረትን እስከማጣትና መልካም ምግባርን እስከ መጣል ድረስ የራስን ስሜትና ፍላጎት መከተል ነው (2ቆሮ 12፥21)፤

(4) "ጣዖት ማምለክን" (በግሪክ ቋንቋ፣ ኢዶሎላተሪያ) ይኸውም መናፍስትን፣ ሰዎችን ወይም የተቀረጹ ምስሎችን ማምለክ እንዲሁም ከእግዚአብሔርና ከቃሉ ጋር እኩል ወይም ከዚያ በላይ ሥልጣን እንዳለው ቈጥሮ በማንኛውም ሰው፣ ተቋም ወይም ነገር ላይ መታመን ነው (ቈላ 3፥5)፤

(5) "ሟርትን"፤ (በግሪክ ቋንቋ፣ ፋርማኪያ) ይኸውም መተትንና አስማት ማድረግን፣ መናፍስት መጥራትን፣ አጋንንትን ማምለክንና መድኀኒትን መቀመም "መናፍስታዊ" ልምምዶችን ማድረግን የሚመለከት ነው (ዘፀ 7፥11:22፤ 8፥18፤ ራእ 9፥21፤ 18፥23)፤

(6) "ጥላቻን"፤ (በግሪክ ቋንቋ፣ ኤክትራ) ይህም፣ ከባድ የጠላትነት ስሜትና ድርጊት፣ ከፍተኛ ጥላቻ ወይም ጠላትነት ነው፤

(7) "ጠብን" (በግሪክ ቋንቋ፣ ኤሪስ)፣ ይኸውም መጣላት፣ መቃወም፣ ከሌላው በልጠ ለመገኘት ትግል ማድረግ ነው (ሮሜ 1፥29፤ 1ቆሮ 1፥11፤ 3፥3)፤

(8) "ቅናትን" (በግሪክ ቋንቋ፣ ዜሎስ)፣ ይኸውም ደስ አለመሰኘትና በሌላው ስኬት መቅናት ነው (ሮሜ 13፥13፤ 1ቆሮ 3፥3)፤

(9) "ቍጣን" (በግሪክ ቋንቋ፣ ቱሞስ)፣ ይኸውም ከባድ በሆነ ቃል ወይም ድርጊት የሚገለጽ፣ የሚገነፍልና እንደ እሳት የሚለበልብ ቍጣ ነው (ቈላ 3፥8)፤

(10) "ራስ ወዳድነትን" (በግሪክ ቋንቋ፣ ኤሪቲያ)፣ ይህም ሥልጣንን መፈለግ ነው (2ቆሮ 12፥20፤ ፊል 1፥16-17)፤

(11) "መለያየትን" (በግሪክ ቋንቋ፣ ዲኮስታሲያ)፣ ይኸውም የሚከፋፍለውንና የእግዚአብሔር ቃል የማይደግፈውን ትምህርት ማስተማር ማለት ነው (ሮሜ 16፥17)፤

(12) "ዐድመኝነትን" (በግሪክ ቋንቋ፣ ሄሬሲስ)፤ ይኸውም የቤተ ክርስቲያንን አንድነት የሚያጠፉ፣ የግል ፍላጎትና ግንኙነት ባላቸው ሰዎች በምእመናን መካከል የሚፈጠር መለያየት

ነው (1ቆሮ 11፥19)፡
(13) "ምቀኝነትን" (በግሪክ ቋንቋ፣ ፍቶኖስ)፣ አንድ ሰው የሚፈልገውን ነገር ይዞ የሚገኘውን ሌላውን ሰው አጥብቆ መጥላት ወይም መቃወም ማለት ነው።
(14) "ስካርን" (በግሪክ ቋንቋ፣ ማቴ) ይኸውም የአንድን ሰው አእምሮ ወይም የአካል እንቅስቃሴ በአልኮል መጠጥ በማድከምና በመጕዳት በተገቢው ሁኔታ እንዳይሠራ ማድረግ ነው፤
(15) "ዘፋኝነትን" (በግሪክ ቋንቋ፣ ኮሞስ)፥ ይኸውም ከመጠን ያለፈ ግብዣና ፈንጠዝያን፣ እንዲሁም አልኮልን፣ ሱስ የሚያሲዝ ዕፅን፣ ዝሙትንና የመሳሰሉትን ያካተተ ነው፤
ሐዋርያው ጳውሎስ በሥጋ ሥራ ላይ የሚሰጠው የመጨረሻ አስተያየት ከባድና ኀይለኛ ነው፤ ክርስቲያን ተብለው የሚጠሩ ሰዎች ሁሉ በእንደዚህ ዐይነቱ የሥጋ ሥራ ውስጥ ተዘፍቀው የሚኖሩ ከሆነ፣ እነርሱ ከእግዚአብሔር መንግሥት ውጭ ናቸው፤ ይኸውም የዘላለምን ሕይወት አይወርሱም ማለት ነው (ገላ 5፥21፤ 1ቆሮ 6፥9 እና ማብ ይመ)።

የመንፈስ ፍሬ፤ የሥጋ ሥራ ተቃራኒ የሆነው "የመንፈስ ፍሬ" አንድ ቋሚ ያለው የኑሮ ዘይቤ ነው። ይህ የመንፈስ ፍሬ በእግዚአብሔር ልጆች ሕይወት ውስጥ የሚታየው፣ የኀጢአትን ኀይል በተለይም የሥጋን ሥራ አስወግደው በመንፈስ ቅዱስ ለመመራትና በእርሱ ቍጥጥር ሥር ለመሆን እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ለማድረግ ፈቃደኞች ሆነው ሲገኙ ነው (ሮሜ 8፥5-14 እና ማብ፤ 8፥14 እና ማብ ይመ፤ ከ2ቆሮ 6፥6፤ ከኤፌ 4፥2-3፤ 5፥9፤ ከቈላ 3፥12-15፤ ከ2ጴጥ 1፥4-9 ጋር ያነጻጽሩ)፤ የመንፈስ ፍሬ የሚከተሉትን ያካትታል፦
(1) "ፍቅርን" (በግሪክ ቋንቋ፣ አጋፔ)፤ ይኸውም የግል ጥቅም ፍላጎት ሳይኖርበት ለሌላው እጅግ መልካም ይሆን ዘንድ ማሰብና ማድረግ ነው (ሮሜ 5፥5፤ 1ቆሮ 13፤ ኤፌ 5፥2፤ ቈላ 3፥14)፤
(2) "ደስታን" (በግሪክ ቋንቋ፣ ካራ)፤ ይኸውም በክርስቶስ ለሚያምኑት የሚሰጠውን ፍቅር፣ ጸጋ፣ በረከት፣ ተስፋና የእግዚአብሔር ቅርቡነት መሠረት በማድረግ በልብ ውስጥ የሚፈጠር የደስታ ስሜት ነው (መዝ 119፥16፤ 2ቆሮ 6፥10፤ 12፥9፤ 1ጴጥ 1፥8 እንዲሁም ፊል 1፥14 እና ማብ ይመ)፤
(3) "ሰላምን" (በግሪክ ቋንቋ፣ ኢሬኔ)፣ ይኸውም በአማኙና በሰማያዊ አባቱ መካከል ያለው ግንኙነት ሁሉ መልካም መሆኑን በማወቅ ላይ የተመሠረተ የልብና የአእምሮ ሰላም ወይም ዕረፍት ነው (ሮሜ 15፥33፤ ፊል 4፥7፤ 1ተሰ 5፥23፤ ዕብ 13፥20)፤
(4) "ትዕግሥትን"(በግሪክ ቋንቋ፣ ማክሮቱሚያ)፣ ይኸውም መጽናት፣ መከራን መታገሥ፣ ለቍጣ መዘግየት ወይም ተስፋ አለመቍረጥ ማለት ነው (ኤፌ 4፥2፤ 2ጢሞ 3፥10፤ ዕብ 12፥1)፤
(5) "ቸርነትን" (በግሪክ ቋንቋ፣ ክሬስቶቴስ)፤ ይህም ማንንም ለመጕዳት አለመፈለግ ወይም ማንንም ለሥቃይ አለመዳረግ ማለት ነው (ኤፌ 4፥32፤ ቈላ 3፥12፤ 1ጴጥ 2፥3)፤
(6) "በጎነትን" (በግሪክ ቋንቋ፣ አጋቶሱኔ)፤ ይኸውም ክፉን መጥላት፣ ለእውነትና ለጽድቅ መቅናት ማለት ነው፤ ይህም የቸርነት ሥራ በማድረግ (ሉቃ 7፥37-50) ወይም ክፉ አድራጊውን በመገሠጽና በማቅናት ሊገለጽ ይችላል (ማቴ 21፥12-13)፤
(7) "ታማኝነትን" (በግሪክ ቋንቋ፣ ጲስቲስ)፤ ይኸውም አንድ ሰው በቃል ኪዳን፣ በእውነተኛነትና በመተማመን ከእርሱ ጋር አንድነትን መሥርቶ ለሚገኘው ሌላው ሰው የሚገልጸው ጽኑና እውነተኛ አቋም ነው (ማቴ 23፥23፤ ሮሜ 3፥3፤ 1ጢሞ 6፥12፤ 2ጢሞ 2፥2፤ 4፥7፤ ቲቶ 2፥10)፤
(8) "ገርነትን" (በግሪክ ቋንቋ፣ ፕሮቴስ)፤ ይኸውም ስሜትን ከመቈጣጠር ጋር ጥንካሬንና ድፍረትን አጣምሮ መያዝን፣ ቍጣ በሚያስፈልግበት ጊዜ መቈጣትን፣ ትሕትና በሚያስፈልግበትም ሁኔታ ራስን ዝቅ ማድረግ መቻልን ይገልጻል (2ጢሞ 2፥25፤ 1ጴጥ 3፥15 ይመ፤ የጌታ ኢየሱስን ገርነት በሚመለከት ማቴ 11፥29ን ከማቴ 23 እና ከማር 3፥5 ጋር ያነጻጽሩ፤ የጳውሎስን ገርነት በሚመለከት 2ቆሮ 10፥1ን ከ10፥4-6 እና ከገላ 1፥9 ጋር ያነጻጽሩ፣ የሙሴን ገርነት በሚመለከት ዘኍ 12፥3ን ከዘፀ 32፥19-20 ጋር ያነጻጽሩ)፤
(9) "ራስን መግዛትን" (በግሪክ ቋንቋ፣ ኤግክራቴያ)፤ ይኸውም የጋብቻ ቃል ኪዳንን በታማኝነት መጠበቅን ጨምሮ፣ የራስን ፍላጎትንና ስሜትን መቈጣጠር፣ ራስንም በንጽሕና መጠበቅ ማለት ነው (1ቆሮ 7፥9፤ 9፥25፤ ቲቶ 1፥8፤ 2፥5)።
ጳውሎስ የመንፈስን ፍሬ በሚመለከት የሰጠው የመጨረሻ አስተያየት፣ እዚህ ላይ በተጠቀሰው የአኗኗር ዘይቤ ላይ ብቻ የተገደበ እንዳልሆነ ያመለክታል። አማኞች እነዚህ ክርስቲያናዊ ምግባሮች ሳይቋረጡ በሕይወታቸው እንዲታዩ መትጋት አለባቸው። በእነዚህ መርሖች መሠረት እንዳይኖሩ የሚከለክላቸው ምንም ሕግ የለምና።

# የሐዋሪያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ኤፌሶን ሰዎች

*አስተዋፅኦ*

*ክርስቲያናዊ ሰላምታ* (1፥1-2)

I. *ኀይል ያለው አስተምህሮ - የአማኙ መቤዠት* (1፥3—3፥21)

(ሀ) በቤዛነት የክርስቶስ የላቀ ሚና (1፥3-14)

1. በአብ ዕቅድ ውስጥ የክርስቶስ የላቀ ሚና (1፥3-6)
2. በአማኙ ተሳትፎ የክርስቶስ የላቀ ሚና (1፥7-12)
3. መንፈስ ቅዱስ ሥራውን ሲሠራ የክርስቶስ የላቀ ሚና (1፥13-14)

ጸሎት፤ አማኙ መንፈሳዊ ብርሃን እንዲያገኝ (1፥15-23)

(ለ) በክርስቶስ እውን የሆነው ቤዛነት የሚያስገኘው ውጤት (2፥1—3፥21)

1. ከኀጢአትና ከሞት ነጻ አውጥቶ በክርስቶስ እውን ወደ ሆነው አዲስ ሕይወት ያሸጋግረናል (2፥1-10)
2. በመዳን ላይ ከሚገኙት ከሌሎች ጋር ያስታርቀናል (2፥11-15)
3. በክርስቶስ አንድ በማድረግ አንድ ቤተ ሰብ እንድንሆን ያበቃናል (2፥16-22)
4. የእግዚአብሔርን ጥበብ በቤተ ክርስቲያን በኩል ይገልጣል (3፥1-13)

ጸሎት፤ አማኙ መንፈሳዊ ብቃት ላይ እንዲደርስ (3፥14-21)

II. ተግባራዊ ትምህርት - የአማኙ ሕይወት (4፥1—6፥20)

(ሀ) የአማኙ አዲስ ሕይወት (4፥1—5፥21)

1. እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ካለው ዕቅድ ጋር ስምሙ መሆን (4፥1-16)
2. ንጽሕና ያለው አዲስ ሕይወት (4፥17—5፥7)
3. እንደ ብርሃን ልጆች መኖር (5፥8-14)
4. ጥንቃቄ ያለበትና በመንፈስ የተሞላ ነው (5፥15-21)

(ለ) የአማኙ ቤተ ሰባዊ ግንኙነት (5፥22—6፥9)

1. ሚስቶችና ባሎች (5፥22-23)
2. ልጆችና ወላጆች (6፥1-4)
3. ባሮችና ጌቶች (6፥5-9)

(ሐ) የአማኙ መንፈሳዊ ጦርነት (6፥10-20)

1. ዐጋሮችን (ረዳታችን) - እግዚአብሔር (6፥10-11ሀ)
2. ጠላታችን - ሰይጣንና ሰራዊቱ (6፥11ሀ-12)
3. መሣሪችን - የእግዚአብሔር ሙሉ የጦር ዕቃ (6፥13-20)

*መደምደሚያ* (6፥21-24)

**ጸሐፊው፤** *ጳውሎስ*

**ዋና ሐሳብ፤** *ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያን*

**የተጻፈበት ጊዜ፤** *በ62 ዓ.ም. ሳይሆን አይቀርም*

*ታሪካዊ ዳራ*

የኤፌሶን መልእክት በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መገለጥ ውስጥ ከፍተኛ እመርታ ላይ ከደረሱት

ጽሑፎች አንዱ ሲሆን፣ ከጳውሎስ መልእክቶች መካከል ልዩ ስፍራ አለው። የኤፌሶን መልእክት በብዙዎች ሌሎች የጳውሎስ መልእክቶች እንደ ታየው፣ በአስተምህሮ የእስጥ አገባ ክርክር ብረት ከመቀጥቀጥ ፈንታ ወይም በመልእክታተ ምጋቤ ችግሮች ላይ ብቻ ከማተኰር ይልቅ፣ ጕልሕ አድርጎ ያሳየው ከጳውሎስ የግል የጸሎት ሕይወት ውስጥ አድጎ የወጣውን የመገለጥ ብልጽግና ሐሳብ ነው፤ ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው ስለ ክርስቶስ እስረኛ በነበረበት ጊዜ (3፥1፤ 4፥1፤ 6፥20) ምናልባትም በሮም ከተማ እያለ ሳይሆን አይቀርም። የኤፌሶን መልእክት ከቈላስይስ መልእክት ጋር አያሌ ትስስር ያለው ሲሆን፣ ምናልባትም ከቈላስይስ መልእክት ቀጥሎ ወዲያውኑ የተጻፈ ሳይሆን አይቀርም። ሁለቱም መልእክቶች የጳውሎስ አጋር በሆነው በቲኪቆስ እጅ ወደየ አድራሻቸው በአንድ ጊዜ ሳይላኩ አልቀረም (6፥21 ይመ፤ ከቈላ 4፥7 ጋር ያነጻጽሩ)።

ጳውሎስ የኤፌሶንን መልእክት ሲጽፍ የመልእክቱ ተደራሲ (ተቀባዩ) ያደረገው የኤፌሶንን ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን፣ ከኤፌሶን ከተማ ሕዝብ ከፍ ያለ ቍጥር የነበረውን ኅብረተ ሰብ እንደ ሆነ በአብዛኛው ይታመናል፤ ምናልባትም በእስያ አገር ለነበሩ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ተዘዋዋሪ ደብዳቤ ሆኖ ሳይጻፍ አልቀረም። ከመጀመሪያውኑ በትንሹ እስያ የምትገኝ እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን በ1፥1 ላይ የየራሷን ስም ሳታስገባ አልቀረችም፤ ይህም ለእውነተኛዋ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መልእክቱ የቱን ያህል ጥልቀት እንዳለው የሚያረጋግጥ ነበር። ይህን መልእክት በትኵረት ያዩ ብዙዎች፣ የኤፌሶን መልእክት፣ ጳውሎስ በቈላስይስ 4፥16 ላይ፣ "በሎዶቅያ ያለችውን መልእክት አንብቡ" በማለት ያሳሰበው ነው ይላሉ።

### ዐላማ

ሐዋርያው ጳውሎስ የኤፌሶንን መልእክት ለምን እንደ ጻፈ ሲያመለክት፣ የቅርብ ዐላማው በእንድምታ መልክ በ1፥15-17 ላይ ተገልጾአል። አንባቢዎቹ በእምነት፣ በፍቅር፣ በጥ በብም ያድጉ ዘንድና የክብር አባት መገለጥም እውን ይሆንላቸው ዘንድ በጸሎት መንፈስ ይናፍቃል። ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብርም ብቃት ያለው ሕይወት ይኖሩ ዘንድ ከልብ ፈለገ (ለምሳሌ 4፥1-3፤ 5፥1-2)፤ ስለዚህ ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያንና (1፥22-23፤ 2፥11-22፤ 3፥21፤ 4፥11-16፤ 5፥25-27) ለእያንዳንዱ ግለሰብ (1፥15-21፤ 2፥1-10፤ 3፥16-20፤ 4፥1-3:17-32፤ 5፥1—6፥20) በክርስቶስ እውን የሆነውን የእግዚአብሔርን የቤዛነት ዘላለማዊ ዐላማ ሙሉ በሙሉ በመግለጥ (1፥3-14፤ 3፥10-12) እምነታቸውንና መንፈሳዊ መሠ ረታቸውን ለማጠንከር ፈለገ።

### ቅኝት

በእጅጉ ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለት መሠረታዊ የሆኑ ዋና ዋና ሐሳቦች ይገኛሉ፤ እነርሱም (1) እግዚአብሔር እንዴት እንደ ቤዠን እና (2) የተቤዠን እንደ መሆናችን መጠን እኛ እንዴት መኖር እንዳለብን ናቸው። ከምዕ 1-3 ያለው ክፍል በመጀመሪያው ዋና ሐሳብ ላይ የሚተኵር ሲሆን፣ ከምዕ 4—6 ያለው ክፍል ደግሞ በሁለተኛው ዋና ሐሳብ ላይ አጽንዖት ያደርጋል።

(1) ምዕ 1—3 ከአንባቢ ጋር የሚተዋወቁት መግቢያ (በር ከፋች) በሆነ አንቀጽ ሲሆን፣ ይህ ክፍል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥልቅ የሆነ ምስጢር ካላቸው ምንባቦች አንዱ ነው (1፥3-14)። አስደናቂ የሆነው ይህ የቤዛነት ውዳሴ አብ ስለ መረጠን፣ አስቀድሞ ስለ ወሰነን፣ ልጆቹም ስላደረገን (1፥3-6)፣ ወልድም በደሙ ስለ ተቤዠን (1፥7-12)፣ መንፈስ ቅዱስ የርስታችን ማኅተምና የቅድሚያ ዐረቦናችን በመሆኑ ምስጋና ያቀርባል (1፥13-14)። በእነዚህ ምዕራፎች ላይ ጳውሎስ በቤዛነት፣ በእምነት በሆነው ጸጋ እግዚአብሔር ከራሱና (2፥1-10) በመዳን ላይ ከሚገኙት ጋር (2፥11-15) እያስታረቀን ነው፤ በክርስቶስም ወደ አንድ አካል ማለትም ወደ ቤተ ክርስቲያን አንድ እያደረገን ነው (2፥16-22)። የቤዛነት ዐላማም፣ "በሰማይም በምድርም ያሉትን ነገሮች ሁሉ ራስ በሆነው በክርስቶስ ሥር ለመጠ ቅለል ነው" (1፥10)።

(2) ከ4—6 ያሉት ምዕራፎች እውን የሆነልን ቤዛነት፣ በግለሰብ ደረጃም ይሁን በኅብረት ያለብንን ግዴታ አስመልክቶ፣ ለቤተ ክርስቲያን ተግባራዊ የሆነውን ትምህርት በአብዛኛው ዐቅፈው ይገኛሉ። የተቤዡት እንዴት መኖር እንዳለባቸው በኤፌሶን መልእክት ላይ ከተሰጡት 35 መመሪያዎች ውስጥ፣ ሦስት መጠነ ሰፊ ዘርፎች አጽንዖት ተሰጥቷቸዋል፤ (1) አማኞች ንጹሕና ከዓለም የተለየ አዲስ ሕይወት እንዲኖራቸው ተጠርተዋል። "በፊቱ ቅዱሳንና ነውር አልባ" (1፥4) እንዲሆኑ፣ "ቅዱስ ቤተ መቅደስ" (2፥21)፣ ለተቀበሉት ጥሪ

"የሚገባ ኑሮ" እንዲኖሩ (4፥1)፣ "ሙሉ ሰው" እንዲሆኑ (4፥13)፣ "እውነተኛ በሆነው ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና" እንዲኖሩ (4፥24)፣ "በፍቅር" እንዲመላለሱ (5፥2 ይመ፤ ከ3፥17-19 ጋር ያነጻጽሩ)፣ "በቃሉ አማካይነት" እንዲቀደሱ (5፥26) ተጠርተዋል፤ ይኸውም ክርስቶስ፣ "አንዳች እንከን ሳይገኝባት ቅድስትና ነውር አልባ የሆነች ክብርት ቤተ ክርስቲያን" እንዲኖረው ነው (5፥27)። (2) አማኞች በቤተሰባዊና በሙያዊ ግንኙነታቸው ረገድ አዲስ የሕይወት ዘይቤ እንዲኖራቸው ተጠርተዋል (5፥22—6፥9)። እነዚህ ግንኙነቶችም ከሚኖሩበት ዓለማዊ ኅብረተ ሰብ መርሖች በተለዩ መርሖች መመራት አለባቸው። (3) በመጨረሻም አማኞች ማንኛውንም የሰይጣን ተንኰል እንዲቋቋሙ እንዲሁም፣ "በሰማያዊ ስፍራ ካሉ ከርኩሳን መናፍስት ሰራዊት" ጋር በጽናት እንዲዋጉ ተጠርተዋል (6፥10-20)።

## ልዩ ገጽታ

የኤፌሶንን መልእክት ልዩ የሚያደርጉት አምስት ዋና ዋና ገጽታዎች ናቸው፤ (1) በምዕ 1—3 ላይ ቅልብጭ ብሎ የቀረበው ታላቅ መለኮታዊ እውነት፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ኀያል በሆኑ ሁለት ሐዋርያዊ ጸሎቶች ጣልቃ ገብነት እንዲገታ ተደርጎአል፤ ከጸሎቶቹ አንዱ እግዚአብሔርን በማወቅ ረገድ ጥበብና መገለጥ ይሰጠው ዘንድ ልመና ያቀርባል (1፥15-23)፤ ሌላው የእግዚአብሔርን ፍቅር፣ ኀይልና ክብር በማወቅ ላይ ያተኵራል (3፥14-21)። (2) "በክርስቶስ" የሚለው ክብደት ያለው የጳውሎስ አገላለጽ (በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ 160 ጊዜ) በኤፌሶን መልእክት ውስጥ በተለይ ጕልሕ የሆነ ሚና አለው (በግምት 36 ጊዜ)። ማንኛውም መንፈሳዊ ስጦታና ማንኛውም ተግባራዊ የሕይወት ፍሬ፣ "በክርስቶስ" ከመሆን ጋር ግንኙነት አለው። (3) ለቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድና ዐላማ በኤፌሶን መልእክት ላይ አጽንዖት ተሰጥቶታል። (4) በክርስቲያን ሕይወት ላይ የመንፈስ ቅዱስ ሚና ምን እንደ ሆነ ፈርጀ ብዙ አጽንዖት ተሰጥቶታል (1፥13-14፡17፤ 2፥18፤ 3፥5፡16፡20፤ 4፥3-4፡30፤ 5፥18፤ 6፥17-18)። (5) አንዳንድ ጊዜ የኤፌሶን መልእክት ከቈላስይስ መልእክት ጋር፣ "መንትያ መልእክት" ተብሎ ይታሰባል፤ ምክንያቱም ሁለቱም በይዘት ረገድ በተወሰነ ደረጃ ተመሳሳይነት አላቸው፤ የተጻፉትም ከሞላ ጎደል በተመሳሳይ ወቅት ነው (የሁለቱን መልእክቶች አስተዋፅኦዎች ያነጻጽሩ)።

## የኤፌሶን መልእክትን ማንበብ

ሙሉውን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ የኤፌሶን መልእክት ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በዘጠኝ ቀን መነበብ ይኖርበታል፤

❑ 1፥1-14 ❑ 1፥15—2፥10 ❑ 2፥11-22 ❑ 3 ❑ 4፥1-16 ❑ 4፥17—5፥2 ❑ 5፥3-21 ❑ 5፥22—6፥9 ❑ 6፥10-24

### ማስታወሻ

1 በእግዚአብሔር ፈቃድ የክርስቶስ ኢየሱስ
ሐዋርያ ከሆነው ከጳውሎስ፤ በክርስቶስ
ኢየሱስ ላሉ፣ ለታመኑ፣[ሀ] በኤፌሶን[ለ]
ለሚገኙ ቅዱሳን፤
2ከእግዚአብሔር ከአባታችን፣ ከጌታም
ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ
ይሁን።

## በክርስቶስ የሚገኝ መንፈሳዊ በረከት

3በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት
ሁሉ በክርስቶስ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ
ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፤ 4በፊቱ
ቅዱሳንና ነውር አልባ እንድንሆን ዓለም
ከመፈጠሩ አስቀድሞ በእርሱ መርጦናልና።
በፍቅር፣ 5በኢየሱስ ክርስቶስ ልጆቹ እንሆን
ዘንድ፣ እንደ በጎ ፈቃዱ አስቀድሞ ወሰነን፤
ኤፌ. 6ይኸውም፣ በሚወደው በእርሱ በኩል በነጻ
1፥19- የተሰጠን ክቡር የሆነው ጸጋው እንዲመሰገን
20 ነው። 7በእርሱም እንደ እግዚአብሔር ጸጋ
ባለጠግነት መጠን፣ በደሙ በተደረገ ቤዛነት፣
የኀጢአትን ይቅርታ አገኘን፤ 8ጸጋውንም
በጥበብና በማስተዋል[ሐ] ሁሉ አበዛልን።
9በክርስቶስ ያቀደውንም የፈቃዱን ምስጢር
እንደ በጎ ሐሳቡ እንድናውቅ[ሐ] አደረገ።
10በዘመን ፍጻሜ ይሆን ዘንድ ያለው ሐሳቡ
በሰማይም በምድርም ያሉትን ነገሮች ሁሉ ራስ
በሆነው በክርስቶስ ሥር ለመጠቅለል ነው።
11ሁሉን በፈቃዱ ምክር መሠረት
እንደሚሠራው እንደ እርሱ ዕቅድ
አስቀድሞ የተወሰንን እኛ ደግሞ በእርሱ
ተመርጠናል፤[መ] 12ይኸውም በክርስቶስ
ተስፋ በማድረግ የመጀመሪያ የሆንነው
እኛ ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው።
13እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል ይህም

1፥1 ሐሥ9፥13፤ 18፥19፤ 1ቆሮ1፥1፤ 2ቆሮ1፥1፤ ቈላ1፥2
1፥2 ሮሜ1፥7
1፥3 ቍ20፤ 2ቆሮ1፥3፤ ኤፌ2፥6፤ 3፥10፤ 6፥12፤ 1ጴጥ1፥3
1፥4 ዘሌ11፥44፤ 20፥7፤ 2ሳሙ22፥24፤ መዝ15፥2፤ ማቴ25፥34፤ ኤፌ4፥2፡15፡16፤ 5፥27፤ ቈላ1፥22፤ 2ተሰ2፥13
1፥5 ቍ11፤ ሉቃ12፥32፤ ሮሜ8፥14፡15፡29፡30፤ 1ቆሮ1፥21፤ ቈላ1፥19
1፥6 ቍ12፡14፤ ማቴ3፥17
1፥7 ቍ14፤ ሮሜ2፥4፤ 3፥24፡25
1፥9 ቍ11፤ ሮሜ16፥25 1፥10 ማር1፥15፤ ሮሜ 5፥6፤ ገላ4፥4፤ ቈላ1፥20 1፥11 ቍ5፡9፤ ሮሜ8፥28፡29፡30፤ ኤፌ3፥11፤ ዕብ6፥17 1፥12 ቍ6፡14 1፥13 ዮሐ14፥16፡17፤ ሮሜ16፥3፤ ኤፌ4፥21፡30፤ ቈላ1፥5

*[ሀ]1፥1 ወይም ለሚያምኑ*
*[ለ]1፥1 አንዳንድ የጥንት ቅጆች በኤፌሶን ለሚገኙት የሚለው ሐረግ የላቸውም።*
*[ሐ]1፥8-9 ወይም ጸጋውን አበዛልን በጥበብና በአእምሮ ሁሉ፣ 9… አሳወቀን*
*[መ]1፥11 ወይም ወራሾች ሆነናል*

1፥1 **በክርስቶስ ኢየሱስ፤** *ማንኛውም "ታማኝ" የሆነ አማኝ ትርጒም ያለው ሕይወት የሚኖረው፣ "በክርስቶስ ኢየሱስ" ብቻ ነው፤* (1) "በክርስቶስ ኢየሱስ"፣ "በጌታ"፣ "በእርሱ" ወዘተ የሚሉት አገላለጾች በጳውሎስ መልእክቶች 160 ጊዜ ይገኛሉ (በኤፌሶን መልእክት ላይ 36 ጊዜ ይገኛሉ)። "በክርስቶስ" ሲባል፣ አማኙ አሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ዐውድ ውስጥ ይኖራል፤ ይንቀሳቀሳልም ማለት ነው። ከክርስቶስ ጋር ያለ አንድነት፣ ቤዛነትን ያገኘው ክርስቲያን አዲስ አካባቢ ወይም ዐውድ ነው። "በክርስቶስ" አማኞች ከጌታ ጋር ሆነ ብለው የያዙት ኅብረት አላቸው፤ በዚህ ኅብረትም የውስጥ ሕይወታቸው፣ በእነርሱ ውስጥ እንዳለው የክርስቶስ ሕይወት ይታያል (ገላ 2፥20 እና ማብ ይመ)። ይህ ግላዊ ኅብረት በክርስትና ተመክሮ ውስጥ ዐቢይ ጒዳይ ነው። ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆን የሚመጣው በእምነት ሲሆን፣ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው።

(2) *መጽሐፍ ቅዱስ*፣ "በክርስቶስ" እውን የሆነልንን አዲስ ሕይወት ቅድመ ዳግም ልደት "በአዳም" ከነበረው አሮጌው ሕይወታችን ጋር ያነጻጽረዋል። አሮጌው ሕይወት ዐመፅ፣ ኀጢአት፣ ፍርድና ሞት ዐይነተኛ ባሕርያቱ ሲሆኑ፣ "በክርስቶስ" ያን አዲሱ ሕይወታችን ግን በድነት፣ በመንፈስ ቅዱስ በሆነ ሕይወት፣ በተትረፈረፈ ጸጋ፣ በጽድቅና በዘላለም ሕይወት ተለይቶ ይታወቃል (ሮሜ 5፥12-21፤ 6፥8፤ 14፥17-19፤ 1ቆሮ 15፥21-22፡ 45-49፤ ፊል 2፥1-5፤ 4፥6-9፤ በገጽ 1746 ላይ፣ ***"እምነትና ጸጋ"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

1፥4 ***መርጦናልና፤*** በገጽ 1860 ላይ፣ ***"ምርጫና አስቀድሞ መወሰን"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

1፥5 **አስቀድሞ ወሰነን፤** በገጽ 1860 ላይ፣ ***"ምርጫና አስቀድሞ መወሰን"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

1፥5 **ልጆቹ እንሆን ዘንድ፤** 1ዮሐ 3፥1 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

1፥13 ***በመንፈስ ቅዱስ ማኅተም፤*** *መንፈስ ቅዱስ ማኅተም በመሆን ለአማኞች የእግዚአብሔር ባለቤትነት ምልክት ሆኖ ተሰጥቷቸዋል። መንፈስ ቅዱስን በመስጠት እግዚአብሔር የራሱ ሀብት አድርጎ ለይቶናል* (2ቆሮ 1፥22)። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ሲገኝ፣ የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆናችንና መቤዠታችንም እውነት ለመሆኑ ማረጋገጫ አለን (ቍ 5)። መንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደት ሲሰጠንና አዲስ ሰዎች ሲያደርገን (ዮሐ 1፥12-13፤ 3፥3-6)፣ ከኀጢአት ኀይል ሲታደገን (ሮሜ 8፥1-17፤ ገላ 5፥16-25)፣ እግዚአብሔር አባታችን መሆኑን እንድናውቅ ሲያደርገንና (ቍ 5፤ ሮሜ 8፥15፤ ገላ 4፥6)፣ ለእርሱ እንድንመሰክር በኀይል ሲሞላን፣ በእውነት የእግዚአብሔር መሆናችንን ልናውቅ እንችላለን (ሐሥ 1፥8፤ 2፥4)።

1፥13 **በመንፈስ ቅዱስ፤** *መንፈስ ቅዱስንና በአማኙ መቤዠት የእርሱ ድርሻ ምን እንደ ሆነ ማሳየት የኤፌሶን መልእክት ዋና ትኩረት ነው።* በዚሁ መጽሐፍ የመንፈስ ቅዱስ ማንነትና ተግባር እንደሚከተለው ተገልጾአል፤ (1) የእግዚአብሔር ባለቤትነት ማረጋገጫ ምልክት ወይም ማኅተም ነው (ቍ 13)፤ (2) የአማኙ ርስት የመጀመሪያ ዐረቦን ነው (ቍ 14)፤ (3) የጥበብና የመገለጥ መንፈስ ነው (ቍ 17)፤ (4) አማኙ ወደ እግዚአብሔር በቀረበ ቍጥር ይረዳዋል (2፥18)፤ (5) የአማኞችን አካል ቅዱስ ቤተ መቅደስ አድርጎ ያንጻል (2፥21-22)፤ (6) የክርስቶስን ምስጢር ይገልጣል (3፥4-5)፤ (7) በውስጥ ሰውነቱ ኀይል እንዲኖረው አማኙን ያጠነክረዋል (3፥16)፤ (8) በክርስቶስ ፍጽምና ልክ በክርስትና እምነት ውስጥ አንድነት እንዲኖር ያነሣሣል (4፥3፡ 13-14)፤ (9) በአማኙ ሕይወት ዘንድ ኀጢአት ሲገኝ ያዝናል (4፥30)፤ (10) አማኙን በተደጋጋሚ ለመሙላትና ኀይል ለመስጠት ይፈልጋል (5፥18)፤ (11) በጸሎትና በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ያግዛል (6፥18)።

1፥13-14 **በመንፈስ ቅዱስ … መያዣ፤** *መንፈስ ቅዱስ፣ "መያዣ ነው፤" ይኸውም ርስታችንን አስተማማኝ የሚያደርግ የመጀመሪያ ክፍያ ወይም ዐረቦን ነው።* በዚህ ዘመን መንፈስ ቅዱስ ወደፊት ለአማኞች በሙላት ለሚለገሰን ጸጋ ዐረቦን በመሆን ይሰጠናል። በሕይወታችን ውስጥ የእርሱ ሥራና ሀልዎት ለሚመጣው ርስታችን ዋስትና ነው (ከሮሜ 8፥23፤ ከ2ቆሮ 1፥22፤ 5፥5 ጋር ያነጻጽሩ)።

የድነታችሁን ወንጌል በሰማችሁ ጊዜ ወደ
ክርስቶስ ተጨምራችኋል፤ አምናችሁም፣
በእርሱ በመሆን ተስፋ ሆኖ በተሰጠው
በመንፈስ ቅዱስ ማኅተም ታትማችኋል።
14ለክብሩ ምስጋና ለመሆን የእግዚአብሔር
የሆኑት እስኪዋጁ ድረስ፣ እርሱ ለርስታችን
ዋስትና የሚሆን መያዣ ነው።

## የምስጋናና የልመና ጸሎት

15ስለዚህ በጌታ ኢየሱስ ስላላችሁ
እምነት፣ ለቅዱሳንም ሁሉ ስላላችሁ ፍቅር
ከሰማሁበት ጊዜ አንሥቶ፣ 16በጸሎቴ
እያስታወስኋችሁ ስለ እናንተ ምስጋና
ማቅረብን አላቋረጥሁም። 17የክብር አባት
የሆነውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን
አምላክ ይበልጥ እንድታውቁት፣ የጥበብና
የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ
ያለማቋረጥ እለምናለሁ። 18እንዲሁም
በእርሱ የተጠራችሁለት ተስፋ፣ ይህም
በቅዱሳኑ ዘንድ ያለውን ክቡር የሆነውን
የርስቱን ባለጠግነት ምን እንደ ሆነ ታውቁ
ዘንድ የልባችሁ ዐይኖች እንዲበሩ 19ለእኛ
ለምናምነውም ከሁሉ በላይ ታላቅ የሆነውን
ኀይሉን እንድታውቁ እጸልያለሁ። ይህም
ኀይል እንደ እርሱ ታላቅ ብርታት አሠራር፣
20ክርስቶስን ከሙታን ሲያስነሣውና
በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሲያስቀምጠው
የታየው ነው። 21የተቀመጠውም ከግዛትና
ከሥልጣን፣ ከኀይልና ከጌትነት እንዲሁም
በአሁኑ ዘመን ብቻ ሳይሆን በሚመጣውም
ዘመን ቢሆን ሊሰየም ከሚቻለው ስም
ሁሉ በላይ ነው። 22እግዚአብሔርም ሁሉን
ከእግሩ በታች አስገዛለት፤ በቤተ
ክርስቲያንም፣ በማንኛውም ነገር ላይ
ራስ አድርጎ ሾመው። 23እርሷም ሁሉን
ነገር በሁሉም ረገድ የሚሞላው፣
የእርሱ ሙላት የሆነች አካሉ ናት።

## በክርስቶስ ሕያው መሆን

2 እናንተ በበደላችሁና በኀጢአታችሁ
ምክንያት ሙታን ነበራችሁ፤ 2በዚህም፣
የዓለምን ክፉ መንገድ ተከትላችሁ፣ በአየር
ላይ ላሉት መንፈሳውያን ኀይላት ገዥ
ለሆነውና አሁንም በእግዚአብሔር በማይታዘዙት
ሰዎች ላይ ለሚሠራው መንፈስ እየታዘዛችሁ
ትኖሩ ነበር። 3እኛ ሁላችን በአንድ ወቅት
የሥጋችንን ምኞት* እያረካን፣ መንገዱንም
እየተከተልን በመካከላቸው እንኖር ነበር፤
እንደ ሌሎቹም የቍጣ ልጆች ነበርን። 4ነገር
ግን በምሕረቱ ባለ ጠጋ የሆነ እግዚአብሔር
ለእኛ ካለው ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ፣
5በበደላችን ሙታን ሆነን ሳለ፣ በክርስቶስ
ሕያዋን አደረገን፤ የዳናችሁት በጸጋ ነው።
6እግዚአብሔርም ከክርስቶስ ጋር አስነሣን፤
በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ
ጋር አስቀመጠን፤ 7ይኸውም በሚመጣው
ዘመን በክርስቶስ ኢየሱስ በቸርነቱ
የገለጠልንን ወደር የሌለውን የጸጋውን
ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ ነው፤ 8በእምነት፣
በጸጋ ድናችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ
ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ 9ማንም

1፥14 ቈላ6:7:12፤
ሐሥ20፥32፤
ሮሜ3፥24፤
2ቆሮ5፥5
1፥15 ሐሥ20፥21፤
ቈላ1፥4
1፥16 ሮሜ1፥8:10
1፥17 ዘፀ28፥3፤
ኢሳ11፥2፤
ዮሐ20፥17፤
ሮሜ15፥6፤
ፊል1፥9፤ ቈላ1፥9፤
ራእ1፥6
1፥18 ቈላ7:11፤
ኢዮ42፥5፤
ሮሜ2፥4፤ 8፥28፤
2ቆሮ4፥6፤
ቈላ1፥12፤ ዕብ6፥4
1፥19 ኢሳ40፥26፤
ኤፌ3:7፤ 6፥10፤
ቈላ1፥29
1፥20 ቈላ3፤
ማር16፥19፤
ሐሥ2:24
1፥21 ማቴ12፥32፤
ኤፌ3፥10፤
ፊል2፥9:10፤
ቈላ1፥16
1፥22 ማቴ22፥44፤
28፥18፤
1ቆሮ11፥3፤
ኤፌ4፥15፤ 5፥23፤
ቈላ1፥18፤ 2፥19
1፥23 ዮሐ1፥16፤
1ቆሮ12፥27፤
ኤፌ3፥19፤ 4፥10
2፥1 ቈላ5፤
ቈላ2፥13
2፥2 ቈላ3:11-13፤
ዮሐ12፥31፤
ሮሜ11፥30፤

2፥2 ሮሜ12፥2፤ 1ቆሮ5፥8፤ 6፥11፤ ኤፌ5፥6፤ ቈላ3፥7፤
ቲቶ3፥3፤ 1ጴጥ4፥3 2፥3 ቈላ2፤ ገላ5፥24 2፥4 ዮሐ3፥16
2፥5 ቈላ1:8፤ መዝ103፥12፤ ዮሐ5፥24፤ ሐሥ15፥11
2፥6 ሮሜ6፥5፤ ኤፌ1፥3:20 2፥7 ሮሜ2፥4፤ ቲቶ3፥4
2፥8 ቈላ5፤ ሮሜ3፥24፤ 9፥30 2፥9 ዘዳ9፥5፤ ሮሜ4፥2፤
1ቆሮ1፥29፤ 2ጢሞ1፥9፤ ቲቶ3፥5

*2፥3 ወይም *የአሮጌውን ባሕርይ ፈቃድ*

**1፥16-20 በጸሎቴ፤** ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች የጸለየው ጸሎት በክርስቶስ ለሚያምነው አማኝ ሁሉ እግዚአብሔር ያለውን ከፍተኛ ፍላጎት ያሳያል። መንፈስ ቅዱስ በሕይወታቸው በሙላት እንዲሠራ ጸለየ (ከ3፥16 ጋር ያነጻጽሩ)። መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ሕይወት የበለጠ ስፍራ እንዲኖረው የተደረገበት ምክንያት ስለ አሁኑና ስለሚመጣው የእግዚአብሔር የመቤዠት ዐላማ (ቍ 17-18)፣ አማኞች የላቀ ጥበብ፣ የላቀ መገለጥና የላቀ ዕውቀት እንዲያገኙ ነው፤ ከዚሁም ጋር አማኞች በሕይወታቸው የመንፈስ ቅዱስን የላቀና የተትረፈረፈ ኀይል እንዲለማመዱ ነው (ቍ 19-20)።

**1፥19 ኀይሉን፤** አማኞች ጸጋ እንዲበዛላቸው፣ በሰይጣንና በኀጢአት ላይ ድልን እንዲቀዳጁ፣ ውጤታማ በሆነ መልኩ ስለ ክርስቶስ እንዲመሰክሩ፣ የመጨረሻውንም ድነት እንዲያገኙ፣ ወደ እነርሱ የሚንቀሳቀሰውን የእግዚአብሔርን ኀይል ማግኘት አለባቸው (ከ1ጴጥ 1፥5 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ ኀይል መንፈስ ቅዱስ በእውነተኛ አማኞች ሕይወት ውስጥ የሚያደርገው እንቅስቃሴ፣ መገለጥና ብርታት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን ያስነሣውና በእግዚአብሔ ር ቀኝ ያስቀመጠው ይህ ኀይልና መንፈስ ቅዱስ ነው (ቍ 20፤ ሮሜ 8፥11፥16:26-27፤ ገላ 5፥22-25)።

**2፥2 በማይታዘዙት ሰዎች፤** ከቍ 1-4 ያለው ክፍል፣ አሁንም በመተላለፍና በኀጢአት ለሚኖሩት ሰዎች፣ ክርስቲያኖች ታላቅ ርኅራኄና ቸርነት ለምን ማሳየት እንዳለባቸው ዐቢይ ምክንያትን ያሳያል። (1) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታቸው ያልሆነ ሰዎች በሰይጣን ማለትም፣ “በአየር ላይ ላሉት መንፈሳውያን ኀይላት ገዥ” በሆነው ቍጥጥር ሥር ናቸው (ቍ 2)። የእግዚአብሔርን እውነት እንዳያስተውሉ አእምሯቸው በሰይጣን ታውሯል (ቍ 2፤ 2ቆሮ 4፥3-4)። የኀጢአትና የኀጢአታዊ ተፈጥሮ ባሮች ሆነዋል (ቍ 3፤ ሉቃ 4፥18)። (2) ዳግም ልደትን ያላገኙት ሰዎች ካሉበት መንፈሳዊ ሁኔታ የተነሣ፣ የእግዚአብሔርን ጸጋ ካላገኙ በቀር እውነቱን ሊያስተውሉ ወይም ሊቀበሉ አይችሉም (ቍ 5:8፤ 1ቆሮ 1፥18፤ ቲቶ 2፥11-14)። (3) ክርስቲያኖች ማንንም ሰው ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ እይታ አንጻር ማየት አለባቸው። በኢግብረገባዊነትና በትዕቢት ራሳቸውን የዘፈቁት የኀጢአትና የሰይጣን ባሮች ናቸውና ሊታዘንላቸው ይገባል (ቍ 1-3 ይመ፤ ከዮሐ 3፥16 ጋር ያነጻጽሩ)። (4) ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታቸው ያላደረጉት ሁሉ ለፈጸሙት በደል ኀላፊነት አለባቸው፤ እያንዳንዱ የሰው ዘር በክርስቶስ በማመን፣ እግዚአብሔ ርን እንዲፈልግና ከኀጢአት እስራት ነጻ እንዲወጣ፣ እግዚአብሔር አስፈላጊውን ብርሃንና ጸጋ ለሰው ዘር ሰጥቶታልና (ዮሐ 1፥9፤ ሮሜ 1፥18-32፤ 2፥1-16)።

**2፥8 በእምነት፣ በጸጋ፤** በገጽ 1746 ላይ፣ “እምነትና ጸጋ” የሚለውንት የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**2፥9 በሥራ አይደለም፤** ማንም ቢሆን በሥራ፣ የፍቅር መግለጫ በሆነ መልካም ሥራ ወይም

# ምርጫና አስቀድሞ መወሰን

*ኤፌ 1፥4-5 "በፊቱ ቅዱሳንና ነውር አልባ እንድንሆን ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ በእርሱ መርጦናልና። በፍቅር፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ልጆቹ እንሆን ዘንድ፣ እንደ በጎ ፈቃዱ አስቀድሞ ወሰነን።"*

---

**ምርጫ፤** በክርስቶስ የሚያምኑትን፣ እግዚአብሔር መምረጡ ለሐዋርያው ጳውሎስ ዐቢይ የሆነ አስተምህሮ ነው (ሮሜ 8፥29-33፤ 9፥6-26፤ 11፥5፡7፡28፤ ቈላ 3፥12፤ 1ተሰ 1፥4፤ 2ተሰ2፥13፤ ቲቶ 1፥1)። ምርጫ (በግሪክ፣ ኤክሌጎ) ሲባል እግዚአብሔር በክርስቶስ ሰዎችን መምረጡን ያመለክታል፤ ይኸውም የተመረጡት በፊቱ ቅዱሳንና ያለነውር እንዲሆኑ ነው (ከ2ተሰ 2፥13 ጋር ያነጻጽሩ)። ልጁን ኢየሱስን የተቀበሉትን ሁሉ እግዚአብሔር የራሱ አድርጎ ሲቀበላቸው፣ ጳውሎስ ይህንኑ ምርጫ የእግዚአብሔርን ፍቅር እንደሚገልጽ አድርጎ ይመለከተዋል (ዮሐ 1፥12)። የምርጫ አስተምህሮ የሚከተሉትን እውነቶች ያጠቃልላል።

(1) ምርጫ ክርስቶስን ያማከለ ነው፤ የሰዎች መመረጥ እውን ሊሆን የሚችለው ከክርስቶስ ጋር አንድነት ሲኖር ብቻ ነው፤ "በእርሱ መርጦናልና" (ኤፌ 1፥4 ይመ፤ 1፥1 እና ማብ ይመ)። ጌታ ኢየሱስ ራሱ ከሁሉ አስቀድሞ የእግዚአብሔር ምርጥ ነው። እግዚአብሔር ስለ ጌታ ኢየሱስ፣ "እነሆ፤ የመረጥሁት ... አገልጋዬ" ይላል (ማቴ 12፥18 ይመ፤ ከኢሳ 42፥1፡6፤ ከ1ጴጥ 2፥4 ጋር ያነጻጽሩ)። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተመረጠ እንደ መሆኑ መጠን፣ የመመረጣችን መሠረት ነው። እኛ ከተመረጡት ውስጥ አባላት ሆነን መቈጠር የምንችለው ከክርስቶስ ጋር አንድነት ሲኖረን ብቻ ነው (ኤፌ 1፥4፡6-7፡9-10፡12-13)። በእምነት አማካይነት ከክርስቶስ ጋር አንድነት የሌለው ምርጥ መሆን አይችልም።

(2) ምርጫ እውን የሚሆነው፣ "በእርሱ ... በደሙ በተደረገ ቤዛነት" ነው (ኤፌ 1፥7)። እግዚአብሔር ዓለም ከመፈጠሩ በፊት (ኤፌ 1፥4) በክርስቶስ የመስቀል ላይ ቤዛዊ ሞት ሰውን አዲስ አድርጎ ለመፍጠር ዐቀደ። ስለዚህ፣ ምርጫ የተመሠረተው እኛን ከኀጢአታችን ለማዳን በተከፈለው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የመሥዋዕት ሞት ነው (ሐሥ 20፥28፤ ሮሜ 3፥24-26)።

(3) በክርስቶስ መመረጥ በመሠረቱ የሚመለከተው አንድነት ያለውን አካል ነው፤ ይኸውም የሰዎች መመረጥ ማለት ነው (ኤፌ 1፥4-5፡7፡9)። የተመረጡት፣ "የክርስቶስ አካል" (4፥12)፣ "ቤተ ክርስቲያኔ" (ማቴ 16፥18)፣ "እግዚአብሔር ለራሱ የለያችሁ ሕዝብ" (1ጴጥ 2፥9) እንዲሁም የክርስቶስ፣ "ሙሽራ" (ራእ 19፥7) ይባላሉ። ስለዚህ ምርጫ ኅብረት ተኰር ነው፤ ግለሰቦችን አካቶ የሚይዘውም ከክርስቶስ አካል ማለትም ከእውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ጋር ራሳቸውን አንድ አድርገው እስከ ቈጠሩ ድረስ ነው (ኤፌ 1፥22-23 ይመ)፤ ይህም በብሉይ ኪዳን በእስራኤላውያን ዘንድ ከዚህ ቀደም ተግባራዊ ሆኖ ታይቶአል (ዘዳ 29፥18-21 እና ማብ፤ 2ነገ 21፥14 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 321 ላይ፣ "እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር የገባው ኪዳን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

(4) የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ለድነትና ለቅድስና መመረጧ ምንጊዜም ርግጥ ነው። ግለሰቦች ግን መመረጣቸው ርግጥ የሚሆነው በግል ሕይወታቸው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕያው የሆነ እምነት ሲኖራቸውና ከእርሱ ጋር ያላቸውን አንድነት በጽናት ሲጠብቁ ነው። ጳውሎስ ይህንኑ ጒዳይ እንደሚከተለው የሳያል፤ (ሀ) የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ ለቤተ ክርስቲያን፣ "በፊቱ ቅዱሳንና ነውር አልባ እንድንሆን" ነው (ኤፌ 1፥4)። ይህም ከኀጢአት ይቅር የመባልንና (1፥7) እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንን መቀደስና ቅድስና ያመለክታል፤ የእግዚአብሔር ምርጦች የሆኑት ሰዎች ወደ መቀደስና ወደ ቅድስና በመንፈስ ቅዱስ ይመራሉ (ሮሜ 8፥14፤ ገላ 5፥16-25)። ሐዋርያው፣ በዚህ የላቀውን የእግዚአብሔርን ዕቅድ በተደጋጋሚ አጽንዖት ያደርጋል (ኤፌ 2፥10፤ 3፥14-19፤ 4፥1-3፡13-24፤ 5፥1-18 ይመ)። (ለ) አንድ አካል ለሆነችው ቤተ ክርስቲያን ይህ ዕቅድ ተፈጻሚ እንደሚሆን ርግጥ ነው፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ "ቅድስትና ነውር አልባ የሆነች ክብርት ቤተ ክርስቲያን አድርጎ ለራሱ ሊያቀርባት ነው" (ኤፌ 5፥27)። (ሐ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግለሰቦችን በተመለከተ የዚህ ዕቅድ ፍጻሜ ላይ መድረስ ነገር ከወዲሁ መሟላት ባለባቸው ጒዳዮች ላይ የተመሠረተ ነው፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ "በፊቱ ቅዱሳንና ነውር አልባ እንድንሆን" (ኤፌ 1፥4) የሚያደርገን፣ በእምነት እስከ ጸናን ድረስ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ጒዳይ ቊልጭ አድርጎ እንደሚከተለው ይገልጸዋል፤ "ነውርና ነቀፋ የሌለባችሁ ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ሊያቀርባችሁ ... ይህም የሚሆነው በእምነታችሁ

ተመሥርታችሁና ተደላድላችሁ በመቆም ከሰማችሁት የወንጌል ተስፋ ሳትናወጡ ጸንታችሁ ብትኖሩ ነው” (ቈላ 1፥22-23)።

(5) በክርስቶስ ድነት ይገኝ ዘንድ ምርጫ የቀረበው ለሁሉም ነው (ዮሐ 3፥16-17፤ 1ጢሞ 2፥4-6፤ ቲቶ 2፥11፤ ዕብ 2፥9)፤ ይህም ለተወሰኑ ሰዎች ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው፣ በክርስቶስ እውን የሆነውን የእግዚአብሔርን የድነት ስጦታ ሲቀበሉ በሚገቡት ንስሐና ባላቸው እምነት መሠረት ነው (ኤፌ 2፥8፤ 3፥17 ይመ፤ ከሐሥ 20፥21፤ ከሮሜ 1፥16፤ 4፥16 ጋር ያነጻጽሩ)። አንድ ምእመን በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነትና ጌትነት ሲያምን፣ በመንፈስ ቅዱስ የክርስቶስ ምርጥ አካል፣ የእውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን አባል ይሆናል (1ቆሮ 12፥13)፤ በዚህም ከምርጦቹ አንዱ ይሆናል። ስለዚህ እግዚአብሔርና ሰው በምርጫ ረገድ የየራሳቸው ድርሻ አላቸው (ሮሜ 8፥29 እና ማብ፤ 2ጴጥ 1፥1-11 ይመ)።

**አስቀድሞ መወሰን፤** አስቀድሞ መወሰን (በግሪክ ፑፕሩረዘጸ ማለት ነው)፣ ማለት “አስቀድሞ መለየት” ማለት ነው። ይህም በምርጫ ውስጥ የተካተተውን የእግዚአብሔርን ዕቅድ ይመለከታል። ምርጫ እግዚአብሔር ለራሱ ይሆኑ ዘንድ “በክርስቶስ” በኩል ያደረገውን የሰዎችን (የእውነተኛዋን ቤተ ክርስቲያን) መለየት ያመለክታል። አስቀድሞ መወሰን ለእግዚአብሔር ሕዝብ (በክርስቶስ በትክክል ለሚያምኑት ሁሉ) ምን እንደሚሆንላቸው ያመለክታል።

(1) እግዚአብሔር ምርጦቹን አስቀድሞ የሚወስነው የሚከተሉት በምርጦቹ ሕይወት እውን እንዲሆኑ ነው፤ (ሀ) የተጠሩ እንዲሆኑ (ሮሜ 8፥30)፤ (ለ) እንዲጸድቁ (ሮሜ 3፥24፤ 8፥30)፤ (ሐ) እንዲከብሩ (ሮሜ 8፥30)፤ (መ) የልጁን መልክ እንዲመስሉ (ሮሜ 8፥29)፤ (ሠ) ቅዱሳንና ነውር አልባ እንዲሆኑ (ኤፌ 1፥4)፤ (ረ) የእግዚአብሔር ልጆች እንዲሆኑ (1፥5)፤ (ሰ) ቤዛነት እንዲያገኙ (1፥7)፤ (ሸ) ርስትን እንዲወርሱ (1፥14)፤ (ቀ) ለክብሩ ውዳሴ እንዲሆኑ (ኤፌ 1፥12፤ 1ጴጥ 2፥9)፤ (በ) የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ እንዲቀበሉ (ኤፌ 1፥13፤ ገላ 3፥14)፤ እና (ተ) መልካምን ሥራ ለመሥራት በክርስቶስ የተፈጠሩ እንዲሆኑ (ኤፌ 2፥10) ነው።

(2) አስቀድሞ መወሰን፣ እንደ ምርጫ ሁሉ የሚመለከተው አንድነት ያለውን የክርስቶስን አካል (ይኸውም እውነተኛዋን መንፈሳዊት ቤተ ክርስቲያን) ነው፤ ግለሰቦችን ዐቅፎ የሚይዘውም ከዚህ አካል ጋር ኅብረት ሲፈጥሩ ብቻ ሲሆን፣ እነርሱ በዚህ የሚታቀፉትም የሚያዙትም በክርስቶስ ኢየሱስ ሕያው የሆነ እምነት ሲኖራቸው ብቻ ነው (ኤፌ 1፥5፡7፡13 ይመ፤ ከሐሥ 2፥38-41፤ 16፥31 ጋር ያነጻጽሩ)።

**ማጠቃለያ፤** ምርጫንና አስቀድሞ መወሰንን በተመለከተ ወደ መንግሥተ ሰማይ በመጓዝ ላይ የምትገኝን ታላቅ መርከብ ምስስሎሽን የሐሳብ ማጉያ መሣሪያ አድርገን ልንጠቀም እንችላለን። መረከቧ (ቤተ ክርስቲያን) ጀልባው እንድትሆን በራሱ በእግዚአብሔር ተመርጣለች። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የመርከቧ ካፒቴንና አንቀሳቃሽ ነው። የዚህች የተመረጠችው መርከብና የካፒቴኗ አካል ለመሆን የሚፈልጉ ሁሉ፣ ወደ መርከቧ በሚሳፈሩበት በኢየሱስ ክርስቶስ ባላቸው ሕያው እምነት መምጣት ይችላሉ። በተመረጡት መካከል የሚቈጠሩትም ከመርከቧ ካፒቴን እስካልተለዩና በመርከቧ ውስጥ እስካሉ ድረስ ነው። መርከቧንና ካፒቴኑን ለመተው ከመረጡ ግን በተመረጡት መካከል መቈጠራቸው ይቀራል። ምርጫ ምንጊዜም ከካፒቴኑና ከመርከቡ ጋር ባለው አንድነት ላይ የተመሠረተ ነው። አስቀድሞ መወሰን ስለ መርከቧ የመጨረሻ መድረሻና በእርሷ ውስጥ ጸንተው ለሚቈዩት እግዚአብሔር ምን እንዳዘጋጀላቸው ይነግረናል። ሁሉም ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ አምኖ ወደ ተመረጠችዋ መርከብ እንዲሳፈር እግዚአብሔር ጥሪ ያቀርባል።

1ተሰ 8-10 እንዳይመካ በሥራ አይደለም፤
[10]ምክንያቱም፣ እግዚአብሔር አስቀድሞ
ያዘጋጀልንን መልካም ሥራ እንድንሠራ
ኤፌ 1-15 በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርን የእግዚአብሔር
እጅ ሥራዎች ነን።

## በክርስቶስ አንድ መሆን

[11]ስለዚህ እናንተ ቀድሞ በትውልድ
አሕዛብ የሆናችሁ፣ በአካል ላይ በሰው እጅ
ከተደረገው የተነሣ፣ ራሳቸውን "ተገርዘናል"
በሚሉት፣ "ያልተገረዙ" የተባላችሁ ያን
አስታውሱ፤ [12]በዚያን ዘመን ከክርስቶስ
ተለይታችሁ፣ ከእስራኤል ወገንነት
ርቃችሁ፣ ለኪዳኑም ተስፋ ባዕዳን ሆናችሁ፣
በዓለም ላይ ያለ ተስፋና ያለ እግዚአብሔር
እንደ ነበራችሁ አስታውሱ። [13]አሁን ግን
እናንተ ቀድሞ ርቃችሁ የነበራችሁ፣
በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም
አማካይነት ቀርባችኋል።
[14]ሁለቱን አንድ ያደረገ፣ የሚለያየውንም

2፥10 ኢሳ29፥23፤ 43፥7፤ 60፥21፤ ኤፌ4፥24፤ ቲቶ2፥14
2፥11 ቆላ2፥11
2፥12 ኢሳ14፥1፤ 65፥1፤ ገላ3፥17፤ 1ተሰ4፥13
2፥13 ቁ2፡17፤ ቈላ1፥20
2፥14 ቍ15፤ ዮሐ14፥27፤ 1ቆሮ12፥13፤ ኤፌ3፥6
2፥15 ገላ3፥28፤ ቈላ1፥21፡22፤ 2፥14
2፥16 2ቆሮ5፥18፤ ቈላ1፥20፡22
2፥17 ቍ13፤ ኢሳ57፥19፤ መዝ148፥14፤ ሉቃ2፥14

የጥል ግድግዳ ያፈረሰ ሰላማችን እርሱ
ራሱ ነውና፤ [15]ሕግንም፣ ከትእዛዛቱና
ከሥርዐቱ ጋር በሥጋው ሻረ። ዐላማውም
ከሁለቱ አንድን አዲስ ሰው በራሱ ፈጥሮ
ሰላምን ለማድረግ ነው። [16]ጥልን በገደለበት
በመስቀሉም ሁለቱን በዚህ በአንድ አካል
ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ። [17]መጥቶም
ርቃችሁ ለነበራችሁት ለእናንተ፣ ቀርበው
ለነበሩትም ለእነርሱ ሰላምን ሰበከ፤
[18]ሁላችንም በእርሱ አማካይነት በአንዱ
መንፈስ ወደ አብ መቅረብ እንችላለንና።
[19]ከዚህ የተነሣ እናንተ ከቅዱሳን ጋር
የአንድ አገር ዜጋ፣ የእግዚአብሔርም ቤተ
ሰብ አባል ናችሁ እንጂ፣ ከእንግዲህ ወዲህ
መጻተኞችና እንግዶች አይደላችሁም።
[20]በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ

2፥18 1ቆሮ12፥13፤ ኤፌ3፥12፤ 4፥4፤ ቈላ1፥12
2፥19 ቍ12፤ ገላ6፥10፤ ፊል3፥20 2፥20 ማቴ16፥18፤ ሐሥ4፥11፤ 1ቆሮ3፥9፡10፡11፤ ኤፌ4፥11፤ 1ጴጥ2፥4-8፤ ራእ21፥14

---

የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመፈጸም በሚካሄድ ብርቱ ጥረት ሊድን አይችልም። ሰውን ሁሉ የሚያድነው የእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነው፤ ለዚህም ምክንያቶቹ የሚከተሉት ናቸው፤ (1) ያልዳኑት ሁሉ በመንፈሳዊ ረገድ ሙት ናቸው (ቍ 1)፤ በሰይጣን ግዛት ሥር ናቸው (ቍ 2)፤ የኀጢአት ባሮች ናቸው (ቍ 3)፤ በእግዚአብሔር የቍጣ ፍርድ ሥር ናቸው (ቍ 3)።

(2) አንድ ሰው ይድን ዘንድ እግዚአብሔር በቸርነቱ እንዲሁ የለገሰውን ድነት መቀበል አለበት (ቍ 4-5)፤ የኀጢአትን ይቅርታ ማግኘት አለበት (ሮሜ 4፥7-8)፤ በመንፈሳዊ ረገድ ሕያው መሆን አለበት (ቈላ 1፥13)፤ ከሰይጣንና ከኀጢአት ኀይል ነጻ መውጣት አለበት (ቈላ 1፥13)፤ አዲስ ፍጥረት መሆን አለበት (ቍ 10፤ 2ቆሮ 5፥17)፤ መንፈስ ቅዱስንም መቀበል አለበት (ዮሐ 7፥37-39፤ 20፥22)። ምንም ዐይነት የግል ጥረት ከላይ የተዘረዘሩትን እውን ሊያደርግ አይችልም።

(3) ድነትን የሚያስገኘው በእምነት የእግዚአብሔር ጸጋ ነው (ቍ 5፡8)፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ የሚከተሉትን ያካትታል፤ (ሀ) በመጀመሪያ የንስሓና የእምነት ጥሪ ይመጣል (ሐሥ 2፥38)። ከዚህም ጥሪ ጋር ለእግዚአብሔር ጥሪ ምላሽ የመስጠት ኀይልንና ችሎታን በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ የሚያስገኝ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ይመጣል። (ለ) በማመንና ንስሓ በመግባት ምላሽ የሚሰጡት እንዲሁም ክርስቶስን ጌታና አዳኝ አድርገው የሚቀበሉት በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደትን ለማግኘት ወይም ዳግም ለመወለድ (በገጽ 1606 ላይ፣ *"ዳግም ልደት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ) እና በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት ተጨማሪ ጸጋን ያገኛሉ (ሐሥ 1፥8፤ 2፥38፤ ኤፌ 5፥18)። (ሐ) በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት የሆኑት ክርስቲያናዊ ሕይወትን ለመኖር፣ ኀጢአትን ለመቃወምና እግዚአብሔርን ለማገልገል ቀጣይነት ያለውን ጸጋ ይቀበላሉ (ሮሜ 8፥13-14፤ 2ቆሮ 9፥8)። አማኞች በእነርሱ ውስጥ በሚሠራው ጸጋ ለእግዚአብሔር ለመኖር ጥረት ያደርጋሉ (1ቆሮ 15፥10)። እንደ እግዚአብሔር መልካም ዕቅድ ፈቃደኞች ሆነው እንዲያገለግሉ ራሳቸውን አሳልፈው በሰጡ ክርስቲያኖች ሕይወት የእግዚአብሔር ጸጋ ይሠራል (ፊል 2፥12-13)። ድነት ከመጀመሪያው አንሥቶ እስከ መጨረሻ ድረስ እውን የሚሆነው በእግዚአብሔር ጸጋ ነው (በገጽ 1746 ላይ፣ *"እምነትና ጸጋ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**2፥18 ወደ አብ መቅረብ፤** ወደ እግዚአብሔር አብ መቅረብ የሚቻለው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በመንፈስ ቅዱስ ነው። *"መቅረብ"* ማለት እኛ በክርስቶስ የምናምን ሁሉ በአብ ፊት ተቀባይነት እንደምናገኝ፣ እንደምንወደድና ሰማያዊ በር እንደሚከፈትልን በመተማመን፣ ወደ ሰማያዊ አባታችን ልባችንን ለማቅናትና ጸሎታችንን ለማሰማት ነጻነትና መብት አለን ማለት ነው። (1) ይህ የመቅረብ መብት የተገኘውም በክርስቶስ ሲሆን፣ ይኸውም በመስቀል ላይ በፈሰሰው ደሙና (ቍ 13፤ ሮሜ 5፥1-2)፤ ወደ እርሱ ለሚመጡት ሁሉ በሚያደርገው ሰማያዊ ምልጃ እውን የሆነ ነው (ዕብ 7፥25 ይመ፤ ከ4፥14-16 ጋር ያነጻጽሩ)። (2) ወደ አብ መቅረብ የመንፈስ ቅዱስን ርዳታ ይጠይቃል። መንፈስ ቅዱስ በልብ ውስጥ የማደሩ ኀይል፣ ጸሎት እንድናቀርብና እንደ እግዚአብሔር ዕቅድና ዐላማ ወደ እርሱ ጩኸታችንን እንድናሰማ ያስችለናል (ዮሐ 14፥16-17፤ 16፥13-14፤ ሮሜ 8፥15-16፡26-27)።

**2፥20 በሐዋርያትና ... መሠረት፤** ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን ልትሆን የምትችለው፣ ለመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት በተሰጠው ሕጸጽ አልባና እስትንፋሰ ክርስቶስ በሆነው መገለጥ ላይ የተመሠረተች ከሆነ ነው። (1) የአዲስ ኪዳን ሐዋርያት ቀዳሚ መልእክተኞች፣ ምስክሮች እንደዚሁም የተሰቀለውና ከሞት የተነሣው ጌታ ባለሙሉ ሥልጣን ቀዳሚ ተወካዮችም ናቸው። እነርሱ የቤተ ክርስቲያን የመሠረት ድንጋዮች ነበሩ፤ መልእክታቸውም ቀዳሚ መልእክት ሲሆን፣ ይኸውም ለክርስቶስ ወንጌል መሠረታዊ ምስክር፣ ለየትኛውም ዘመን ጠቃሚ በመሆን በአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ላይ ተጽፎ የሚገኝ ነው።

(2) አማኞችና አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍና በሐዋርያት ሲጻፍ እስትንፋሰ እግዚአብሔርን ባገኘው ቃል፣ መልእክትና እምነት ላይ እምነታቸውን የመሠረቱ ናቸው። የእነርሱ ሥልጣን በአዲስ ኪዳን ላይ ተጽፎ ይገኛል፤ ከዚህ በኋላ የተገኘው የቤተ ክርስቲያን ትውልድም ለሐዋርያዊ መገለጥ የመታዘዝና የተገለጠውንም እውነት የመመስከር ግዴታ

ታንጻችኋል፤ የማእዘኑ ራስ ድንጋይም
ክርስቶስ ኢየሱስ ራሱ ነው፤ 21በእርሱ ሕንጻ
ሁሉ አንድ ላይ ተገጣጥሞ በጌታ ቅዱስ ቤተ
መቅደስ እንዲሆን ያድጋል። 22እናንተም ደግሞ
እግዚአብሔር በመንፈሱ የሚኖርበት ማደሪያ
ትሆኑ ዘንድ አብራችሁ እየተገነባችሁ ነው።

## ለአሕዛብ ሐዋርያ የሆነው ጳውሎስ

3 በዚህም ምክንያት እኔ ጳውሎስ ለእናንተ
ለአሕዛብ የክርስቶስ ኢየሱስ እስረኛ
ሆኛለሁ።
2ለእናንተ ጥቅም ሲባል ስለ ተሰጠኝ
የእግዚአብሔር ጸጋ መጋቢነት በርግጥ
ሰምታችኋል፤ 3ቀደም ሲል በአጭሩ እንደ
ጻፍሁት፣ በመገለጥ እንዳውቀው የተደረገው
ምስጢር ይህ ነው። 4እንግዲህ ይህን
ስታነቡ፣ የክርስቶስን ምስጢር እንዴት
እንደ ማስተውል ለመረዳት ትችላላችሁ።
5ይህም ምስጢር አሁን ለቅዱሳኑ ሐዋርያትና
ነቢያት የተገለ ጠውን ያህል ባለፉት ዘመናት
ለነበሩ ሰዎች አልተገለጠም ነበር። 6ይህም
ምስጢር አሕዛብ በወንጌል አማካይነት
ከእስራኤል ጋር አብረው ወራሾች፣ አብረው
የአንዱ አካል ብልቶች እንዲሁም በክርስቶስ
ኢየሱስ በሆነው ተስፋ አብረው ተካፋይ
መሆናቸው ነው።
7እኔም በኀይሉ አሠራር በተሰጠኝ

2፥21
1ቆሮ3፥16:17
2፥22 1ቆሮ3፥16
3፥1 ሐሥ23፥18፤
ኤፌ4፥1፤
2ጢሞ1፥8፤
ፊሞ1:9
3፥2 ቈላ1፥25
3፥3 ሮሜ16፥25፤
1ቆሮ2፥10
3፥4 2ቆሮ11፥6
3፥5 ሮሜ16፥26፤
ኤፌ4፥11
3፥6 ሕዝ47፥22፤
ሮሜ8፥17፤
ኤፌ2፥15:16
3፥7 ሮሜ12፥3፤
1ቆሮ3፥5፤
ኤፌ1፥19፤
ቈላ1፥29
3፥8 ሐሥ9፥15፤
ሮሜ2፥4፤
1ቆሮ15፥9
3፥9 ሮሜ16፥25
3፥10 ሮሜ11፥33፤
1ቆሮ2፥7፤
ኤፌ1፥3:21፤
6፥12፤
ቈላ2፥10:15፤
1ጴጥ1፥12
3፥11 ኤፌ1፥11
3፥12 2ቆሮ3፥4፤
ኤፌ2፥18፤
ዕብ3፥14፤ 4፥16፤

በእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ የዚህ ወንጌል
አገልጋይ ሆኛለሁ። 8ምንም እንኳ ከቅዱሳን
ሁሉ ያነስሁ ብሆንም፣ የማይመረመረውን
የክርስቶስን ባለጠግነት ለአሕዛብ እሰብክ
ዘንድ ይህ ጸጋ ለእኔ ተሰጠኝ። 9እንዲሁም
ሁሉን በፈጠረ በእግዚአብሔር ላለፉት
ዘመናት የተሰወረውን የዚህን ምስጢር
አሠራር ለሁሉም እገልጥ ዘንድ ተሰጠኝ።
10አሳቡም በአሁኑ ዘመን በቤተ ክርስቲያን
አማካይነት ብዙ ገጽታ ያለው የእግዚአብሔር
ጥበብ በሰማያዊ ስፍራ ላሉት አለቆችና
ባለሥልጣናት ይታወቅ ዘንድ ነው፤ 11ይህም
በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን በፈጸመው
ዘላለማዊ ዕቅዱ መሠረት ነው። 12በእርሱና
በእርሱ ላይ ባለን እምነት አማካይነት፣
በነጻነትና በልበ ሙሉነት ወደ እግዚአብሔር
መቅረብ እንችላለን። 13ስለዚህ ክብራችሁ
በሆነው ስለ እናንተ በደረሰብኝ መከራ
ተስፋ እንዳትቈርጡ ዐደራ እላችኋለሁ።

## ለኤፌሶን ክርስቲያኖች የተደረገ ጸሎት

14በዚህም ምክንያት በአብ ፊት
እንበረከካለሁ፤ 15ከእርሱም በሰማይና
በምድር ያለ ቤተ ሰብ ሁሉ ስየሜ[a] ያገኛል።
16በውስጥ ሰውነታችሁ እንድትጠነክሩ፣

3፥12 ዕብ10፥19:35፤ 1ዮሐ2:28፤ 3፥21፤ 4፥17 3፥14 ፊል2፥10 3፥16 ቍ8፤ ሮሜ2፥4፤ 7፥22፤ ፊል4፥13

[a]3፥15 *ወይም አባትነት ሁሉ*

---

አለበት። በመንፈስ ቅዱስ ለአዲስ ኪዳን ሐዋርያት የተሰጠው ወንጌል ለሕይወት፣ ለእውነትና ለቤተ ክርስቲያን አመራር ዘላቂ የሆነ ምንጭ ነው።

(3) አማኞችና አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እውነተኛ አማኞችና እውነተኛ አብያተ ክርስቲያናት የሚሆኑት የሚከተሉትን እስካደረጉ ድረስ ነው። (ሀ) በአዲስ ኪዳን ላይ ከሚገኘው የወንጌል ቃል ይኸውም ከሐዋርያት ወጥ ትምህርትና መገለጥ ጋር ለመስማማትና ልባዊ በሆነ ሁኔታ ለመከተል ጥረት ማድረግ አለባቸው (ሐሥ 2፥42)። የሐዋርያትን ትምህርት መካድ ማለት ጌታን ራሱን መካድ ማለት ነው (ዮሐ 16፥13-15፤ 1ቆሮ 14፥36-38፤ ገላ 1፥9-11)። (ለ) በታማኝነት በሚታወጀውና በመንፈስ ቅዱስ ኀይል በሚቀርበው ማስተማር አማካይነት ሐዋርያዊ መልእክትን አዲስ አድርገው ለዓለምና ለቤተ ክርስቲያን በማስተላለፍ ሐዋርያዊውን ተልእኮ መቀጠል አለባቸው (ሐሥ 1፥8፤ 2ጢሞ 1፥8-14፤ ቲቶ 1፥7-9)። (ሐ) ሐዋርያዊ መልእክትን ማመን ብቻ ሳይሆን ከማንኛቸውም ዐይነት የማጣመም ወይም የመለወጥ ተግባር መጠበቅና መከላከል አለባቸው። በአዲስ ኪዳን ላይ ሰፍሮ የሚገኘው የሐዋርያት ወጥ ወይም ቀዳሚ መገለጥ ከጊዜ በኋላ በተከሠተ መገለጥ፣ ምስክርነት ወይም ትንቢት ከቶ ሊተካ ወይም ከአገልግሎት ውጭ ሊደረግ አይገባም (ሐሥ 20፥27-31፤ 1ጢሞ 6፥20)።

**3፥4 የክርስቶስን ምስጢር፤** ጳውሎስ ለዘመናት እግዚአብሔር ራሱ ምስጢር አድርጎ ይዞት ስለነበረው (ቍ 9)፣ አሁ ግን በመንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያትና ለነቢያት (ቍ 5) በመገለጥ እንዲታወቅ ስለተደረገው (ቍ 3)፣ "የክርስቶስ ምስጢር" ይናገራል። ምስጢሩ የእግዚአብሔር ዐላማ ሲሆን፣ ይኸውም፣ "በሰማይም በምድርም ያሉትን ነገሮች ሁሉ ራስ በሆነው በክርስቶስ ሥር ለመጠቅለል ነው" (1፥10)፤ እንዲሁም ከየነገዱ ሁሉ ሰዎችን በሕይወትና በድነት ተስፋ ለማካተት (ለመጨመር) ነው (ቍ 6፤ ሮሜ 16፥25-26፤ 2ጢሞ 1፥1)። እግዚአብሔር ከአይሁድና ከአሕዛብ ወገን፣ "በክርስቶስ ኢየሱስ" (ቍ 6) ለራሱ አዲስ ሕዝብን ፈጠረ (1፥4-6፤ 2፥16፤ 4፥4:16፤ ማቴ 16፥18፤ ቈላ 1፥24-28፤ 1ጴጥ 2፥9-10)።

**3፥7 በእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ፤** የእግዚአብሔር ጸጋ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ለእያንዳንዱ አማኝ የተሰጠ፣ ከሞት ከተነሣው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘ፣ በአማኙ ልብ ውስጥ በሚያድረው መንፈስ ቅዱስ በኩል የሚሠራና ብርታትን የሚሰጥ ኀይል ነው (1፥19፤ 4፥7፤ ሐሥ 6፥8፤ 11፥23፤ 14፥26፤ 1ቆሮ 15፥10፤ 2ቆሮ 12፥9፤ ፊል 2፥13፤ ቈላ 1፥29፤ ቲቶ 2፥11-13 ይመ፤ በገጽ 1746 ላይ፣ *"እምነትና ጸጋ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**3፥10 አለቆችና ባለ ሥልጣናት፤** ይህን ጥቅስ በተመለከተ ሊሆኑ ይችላሉ የተባሉ ሁለት ትርጓሜዎች አሉ፤ (1) "በሰማያዊ ስፍራ ላሉት አለቆችና ባለሥልጣናት" ሲባል መላእክትን ሊያመለክት ይችላል (ከቈላ 1፥16 ጋር ያነጻጽሩ)። እግዚአብሔር ያን ጥበብ በቤተ ክርስቲያን በኩል ሲያሳይ የእግዚአብሔርን አስደናቂ ጥበብ ያያሉ (1ጴጥ 1፥10-12)። (2) "በሰማያዊ ስፍራ ላሉት አለቆችና ባለ ሥልጣናት" ሲባል በመንፈሳዊ ዓለም ያሉትን የጨለማው ገዥዎችን ሊያመለክት ይችላል (ከ6፥12፤ ከዳን 10፥13:20-21 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ለእነርሱም የእግዚአብሔር "ዘላለማዊ ዕቅድ" (ቍ 11) ቤተ ክርስቲያን ድነትን በምታውጅበት ዐዋጅና ከሰይጣንና ከኀይላቱ ጋር በምታካሂደው መንፈሳዊ ጦርነት እንዲታወቅ ሆኗል (ከ6፥12-18፤ ከዳን 9፥2-23፤ ከ10፥12-13፤ ከ2ቆሮ 10፥4-5 ጋር ያነጻጽሩ)።

**3፥16-19 በውስጥ ሰውነታችሁ እንድትጠነክሩ፤**

ከክብሩ ባለ ጠግነት በመንፈሱ በኩል ኀይል
እንዲሰጣችሁ እጸልያለሁ፤ [17]ይኸውም
በእምነት ክርስቶስ በልባችሁ እንዲያድር
ነው። ደግሞም ሥር ሰዳችሁ፣ በፍቅር
ታንጻችሁ፣ [18]የክርስቶስ ፍቅር ስፋቱ፣
ርዝመቱ፣ ከፍታውና ጥልቀቱ ምን ያህል
እንደ ሆነ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር የመገንዘብ
ኀይልን እንድታገኙ ነው። [19]እስከ እግዚአብሔር
ሙላት ሁሉ ልክ ደርሳችሁ እንድትሞሉ፣
ከመታወቅ በላይ የሆነውን የክርስቶስን
ፍቅር ታውቁም ዘንድ ነው።

[20]እንግዲህ በእኛ ውስጥ እንደሚሠራው
እንደ ኀይሉ መጠን፣ ከምንለምነው ወይም
ከምናስበው ሁሉ በላይ እጅግ አብልጦ
ማድረግ ለሚቻለው፣ [21]በቤተ ክርስቲያን
እንዲሁም በክርስቶስ ኢየሱስ፣ በዘመናት
ቈላ ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ለእርሱ ክብር
1፥6-8 ይሁን፤ አሜን።

## በክርስቶስ አካል ያለ አንድነት

4 እንግዲህ በጌታ እስረኛ የሆንሁ እኔ፣
ለተቀበላችሁት ጥሪ የሚገባ ኑሮ ትኖሩ
ዘንድ እለምናችኋለሁ። [2]ፍጹም ትሑታንና
ገሮች ሁኑ፤ እርስ በርሳችሁም በፍቅር እየተ
ቻቻላችሁ ትዕግሥተኞች ሁኑ። [3]በሰላም
ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ
ትጉ። [4]በተጠራችሁ ጊዜ ወደ አንድ ተስፋ
እንደ ተጠራችሁ ሁሉ አንድ አካልና አንድ
መንፈስ አለ፤ [5]አንድ ጌታ፣ አንድ እምነትና
አንድ ጥምቀት አለ፤ [6]ከሁሉም በላይ የሆነ፣
በሁሉም የሚሠራ፣ በሁሉ የሚኖር የሁሉም
አባት የሆነ አንድ አምላክ አለ።

[7]ነገር ግን ክርስቶስ በወሰነው መጠን
ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጥቶናል። [8]ስለዚህም
እንዲህ ይላል፤

"ወደ ላይ በወጣ ጊዜ፣
ምርኮ ማረከ፤
ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ።"

[9]ታዲያ፣ "ወደ ላይ ወጣ" ማለት ደግሞ
ወደ ምድር ታችኛው ክፍል[a] ወረደ ማለት
ካልሆነ በቀር ምን ማለት ነው? [10]ወደ ታች
የወረደውም፣ መላውን ፍጥረተ ዓለም ይሞላ
ዘንድ ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣው እርሱ ራሱ
ነው። [11]አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣ አንዳንዶቹ
ነቢያት፣ አንዳንዶቹም ወንጌል ሰባኪዎች፣
ሌሎቹ ደግሞ እረኞችና አስተማሪዎች ይሆኑ
ዘንድ የሰጠ እርሱ ነው፤ [12]ይኸውም የክርስቶስ
አካል ይገነባ ዘንድ፣ ቅዱሳንን ለአገልግሎት
ሥራ ለማዘጋጀት ሲሆን፣ [13]ይህም
የሚሆነው፣ ሁላችንም የእግዚአብሔርን ልጅ

3፥17 ሮሜ8፥10፤ ቈላ2፥7
3፥18 ኢዮ11፥8:9፤ መዝ103፥11፤ ኤፌ1፥15
3፥19 ኤፌ1፥23፤ ፊል4፥7፤ ቈላ2፥10
3፥20 ቍ7፤ 1ነገ 3፥13፤ ሮሜ16፥25፤ 2ቆሮ9፥8
3፥21 ሮሜ11፥36
4፥1 ሮሜ8፥28፤ ኤፌ3፥1፤ ፊል1፥27፤ ቈላ1፥10፤ 1ተሰ2፥12
4፥2 ቍ15:16፤ ኤፌ1፥4፤ ቈላ3፥12:13
4፥3 ሮሜ15፥5፤ ቈላ3፥15
4፥4 ሮሜ8፥28፤ 12፥5፤ 1ቆሮ12፥13፤ ኤፌ2፥18
4፥5 1ቆሮ8፥6
4፥6 ዘዳ6፥4፤ ዘካ14፥9፤ ሮሜ11፥36
4፥7 ሮሜ3፥24፤ 12፥3፤ 1ቆሮ12:7:11
4፥8 መዝ68፥18፤ ቈላ2፥15

4፥10 ምሳ30፥4፤ ኤፌ1፥23 4፥11 ቍ8፤ ሐሥ11፥27፤ 13፥1፤ 21፥8፤ ሮሜ12፥6:7፤ 1ቆሮ12፥10:28፤ 13፥2:8፤ 14፥1:26:39፤ ኤፌ2፥20፤ 3፥5፤ 1ጢሞ1፥7፤ 2ጢሞ4፥5፤ 2ጴጥ3፥2፤ ያዕ3፥1፤ ይሁ1፥17 4፥12 ሮሜ14፥19፤ 1ቆሮ12፥27 4፥13 ቍ3:5፤ ዮሐ1፥16፤ 1ቆሮ2፥6፤ ኤፌ1፥23፤ 3፥19፤ ፊል3፥8፤ ቈላ1፥28

[a] 4፥9 ወይም ወደ ምድር ጥልቀት

በመንፈስ ቅዱስ፣ "በውስጥ ሰውነት" መጠንከር ማለት፣ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ላይ በይበልጥ ኀይሉን እንዲገልጥ ስሜታችንን፣ ሐሳባችንንና ዕቅዳችንን እያደር አብዝተን በቍጥጥሩና በምሪቱ ሥር ማድረግ ማለት ነው:: የዚህ ጥንካሬ ዐላማም አራት ዘርፍ አለው፤ (1) ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ህልዎቱን በልባችን ላይ እንዲመሠርት (16-17 ይመ፤ ከሮሜ 8፥9-10 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (2) ለእግዚአብሔር፣ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና ለሌሎች ስንል፣ ልባዊ በሆነ ፍቅር ላይ እንድንመሠረት፤ (3) ክርስቶስ ለእኛ ያለውን ፍቅር በአእምሯችን እንድናስተውል፣ በሕይወታችንም እንድንለማመደው (ቍ 18-19)፣ (4) "እስከ እግዚአብሔር ሙላት ሁሉ ልክ" (ቍ 19) እንድንደርስ፤ ይኸውም የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ባሕርይና ሙላት በውስጥ ሰውነታችን እስኪንጸባረቅ ድረስ (ከ4፥13:15:22-24 ጋር ያነጻጽሩ) የእግዚአብሔር ህልዎት እንዲሞላን ነው::

**3፥20 እጅግ አብልጦ ማድረግ፤** እግዚአብሔር ለእኛ የሚያደርገው በጸሎት ከጠየቅነውና ከምንፈልገው በላይ ብቻ ሳይሆን፣ ከምናስበውም በላይ ነው:: ይህም ተስፋ በሕይወታችን ላይ መንፈስ ቅዱስ ህልዎቱን፣ ኀይሉንና ጸጋውን በሚለግሰው ልግስና ልክ የተመሠረተና ከዚሁም ጋር የተሳሰረ ነው (1፥19፤ 3፥16-19፤ ኢሳ 65፥24፤ ዮሐ 15፥7፤ ፊል 2፥13 ይመ)::

**4፥3 አንድነት ለመጠበቅ፤** "የመንፈስ አንድነት" በማንም ሰው ዘንድ ሊገኝ አይችልም፤ ሐዋርያው ከምዕ 1-3 ባለው ክፍል ጕልሕ አድርጎ እንደ ገለጸው እውነቱን ላመኑና ክርስቶስንም ለተቀበሉ ሁሉ ይህ የመንፈስ አንድነት እውን ሆኖ የሚገኝ ነው:: የኤፌሶን ክርስቲያኖች ያን አንድነት መጠበቅ ያለባቸው በሰው ጥረት ወይም ሰው ሠራሽ በሆነ ድርጅት አማካይነት ሳይሆን፣ ለተቀበሉት "ጥሪ የሚገባ ኑሮ" በመኖር ነው (ቍ 1):: የመንፈስ አንድነት የሚጠበቀው ለእውነት ታማኝ በመሆንና የመንፈስ ቅዱስን ምሪት በመከተል ነው (ቍ 1-3:14-15፤ ገላ 5፥22-26)፤ ይህም አንድነት በሰው ጥረት ሊሳካ አይችልም (ገላ 3፥3)::

**4፥5 አንድ ጌታ፤** ለክርስቲያናዊ እምነትና አንድነት እጅግ አስፈላጊ የሆነው፣ "አንድ ጌታ" ብቻ አለ የሚለው የእምነት መግለጫ ነው:: (1) "አንድ ጌታ" ብቻ አለ ማለት የጌታ ኢየሱስ የመቤዠት ሥራ ፍጹምና በቂ ስለ ሆነ፣ ለአማኙ ፍጹም የሆነ ድነትን ለመስጠት ሌላ ቤዛ ወይም አምላክ አያስፈልግም ማለት ነው (1ጢሞ 2፥5-6፤ ዕብ 9፥15)፤ አማኙ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ያለበት በክርስቶስ ብቻ ነው (ዕብ 7፥25)::

(2) ደግሞም "አንድ ጌታ" ሲባል እግዚአብሔር በክርስቶስና እስትንፋሰ እግዚአብሔርን ባገኘው ቃሉ ከተገለጠው በቀር ለሌላ የሥልጣን ባለቤት ለሚባል ተተካካይ ወይም የላቀ ታማኝነትን መግለጽ (ዓለማዊ ወይም ሃይማኖታዊ ለሆን)፣ ራስን ከክርስቶስ ጌትነት ማግለልና ብሎም በእርሱ ብቻ እውን ከሚሆነው እምነት መራቅ ማለት ነው:: አንድ አማኝ ጌታ ኢየሱስ የመጨረሻው ኀያል ባለሥልጣን እንደ ሆነና ሥልጣኑም የተገለጠው በተጻፈው በእግዚአብሔር ቃል መሆኑን በእምነት ካላረጋገጠ በቀር፣ የክርስቶስ ጌትነት ወይም "የመንፈስ አንድነት" (ቍ 3) በሕይወቱ ሊኖር አይችልም::

**4፥11 የሰጠ እርሱ ነው፤** በገጽ 1866 ላይ፣ "*የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ስጦታዎች*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ::

**4፥13 በማመንና ... አንድነት፤** ጳውሎስ በምዕ 4 ላይ፣ "የመንፈስን አድነት" (ቍ 3) እና "በማመንና ... አንድነት" የተሰኙት በአማኞች ሕይወትና አንድነት

በማመንና በማወቅ ወደሚገኘው አንድነት
በመምጣትና ሙሉ ሰው በመሆን፣ በክርስቶስ
ወዳለው ፍጹምነት ደረጃ እስከምንደ ርስ
ነው።
[14]ከእንግዲህ በማዕበል ወደ ፊትና ወደ ኋላ
እየተነዳን፣ በልዩ ልዩ ዐይነት የትምህርት
ነፋስ፣ በሰዎችም ረቂቅ ተንኰልና ማታለል
ወዲያና ወዲህ እየተንገዋለልን ሕፃናት
አንሆንም። [15]ይልቁንም እውነትን በፍቅር
እየተናገርን፣ ራስ ወደ ሆነው ወደ እርሱ በነገር
ሁሉ እናድጋለን፤ እርሱም ክርስቶስ ነው፤
[16]ከእርሱም የተነሣ፣ አካል ሁሉ በሚያገናኘው
ጅማት እየተያያዘና እየተጋጠመ፣
እያንዳንዱ ክፍል የራሱን ሥራ እያከናወነ
በፍቅር ያድጋል፤ ራሱንም ያንጻል።

## እንደ ብርሃን ልጆች መኖር

[17]ስለዚህ ይህን እነግራችኋለሁ፤
በጌታም ዐደራ እላለሁ፤ በአስተሳሰባቸው
ከንቱነት እንደሚኖሩት እንደ አሕዛብ
ልትመላለሱ አይገባም። [18]እነርሱ ከልባቸው
መደንደን የተነሣ ስለማያስተውሉ
ልቦናቸው ጨልሞአል፤ ከእግዚአብሔርም
ሕይወት ተለይተዋል። [19]ኅሊናቸው ስለ
ደነዘዘ በማይረካ ምኞት፣ በርኩሰት ሁሉ
እንዳሻቸው ለመኖር ቅጥ ለሌለው ብልግና
ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል።
[20]እናንተ ግን ክርስቶስን ያወቃችሁት

4፥14 ኢሳ57፥20፤ 1ቆሮ14፥20፤ ኤፌ6፥11፤ ያዕ1፥6
4፥15 ቆላ2፡16፤ ኤፌ1፥4:22
4፥16 ቆላ2፡15፤ 1ቆሮ12፥7፤ ኤፌ1፥4፤ ቆላ2፥19
4፥17 ሮሜ1፥21፤ ኤፌ2፥2
4፥18 ዘዳ29፥4፤ ሮሜ1፥21፤ 2ቆሮ3፥14፤ ኤፌ2፥12
4፥19 ሮሜ1፥24፤ ቆላ3፥5፤ 1ጢሞ4፥2፤ 1ጴጥ4፥3
4፥22 ቆላ25:31፤ ኤር17፥9፤ ሮሜ6፥6፤ ቆላ3፥5:8:9፤ ዕብ3፥13፤ ያዕ1፥21፤ 1ጴጥ2፥1
4፥23 ሮሜ12፥2፤ ቆላ3፥10
4፥24 ሮሜ6፥4፤ 13፥14፤ ኤፌ2፥10
4፥25 ዘሌ19፥11፤ መዝ15፥2፤ ዘካ8፥16፤ ሮሜ12፥5፤

እንደዚህ ባለ መንገድ አይደለም፤ [21]በርግጥ
ስለ እርሱ ሰምታችኋል፤ በኢየሱስም
እንዳለው እውነት በእርሱ ተምራችኋል።
[22]ቀድሞ ስለ ነበራችሁበት ሕይወትም፣
በሚያታልል ምኞቱ የጎደፈውን አሮጌ
ሰውነታችሁን አውልቃችሁ እንድትጥሉ
ተምራችኋል፤ [23]ደግሞም በአእምሮአችሁ
መንፈስ እንድትታደሱ፣ [24]እውነተኛ በሆነው
ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና እግዚአብሔርን
እንዲመስል የተፈጠረውን አዲሱን ሰው
እንድትለብሱ ነው።
[25]ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ፣
እያንዳንዳችሁ ከባልንጀራችሁ ጋር
እውነትን ተነጋገሩ፤ ሁላችንም የአንድ
አካል ብልቶች ነንና። [26]ተቈጡ፤ ነገር ግን
ኀጢአት አትሥሩ፤ በቍጣችሁ ላይ ፀሓይ
አይግባ፤ [27]ለዲያብሎስም ስፍራ አትስጡት።
[28]ይሰርቅ የነበረ ከእንግዲህ አይስረቅ፤
ነገር ግን ለተቸገሩት የሚያካፍለው ነገር
እንዲኖረው በገዛ እጆቹ በጎ የሆነውን
እየሠራ ለማግኘት ይድከም።
[29]እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎችን የሚያንጽና
ሰሚዎችን የሚጠቅም ቃል እንጂ የማይረባ
ቃል ከአፋችሁ አይውጣ። [30]ለቤዛ ቀን

4፥25 ቈላ3፥9 4፥26 መዝ4፥4፤ ማቴ5፥22 4፥27 2ቆሮ2፥10:11 4፥28 ሐሥ20፥35፤ ገላ6፥10፤ 1ተሰ4፥11 4፥29 ማቴ12፥36፤ ሮሜ14፥19፤ ኤፌ5፥4፤ ቈላ3፥8 4፥30 ኢሳ63፥10፤ ሮሜ8፥23፤ 2ቆሮ1:22፤ 5፥5፤ ኤፌ1፥13፤ 1ተሰ5፥19

---

የሚጠበቁትና ፍጽምናን የሚያገኙት በሚከተሉት ዐበይት ጉዳዮች መሆኑን ያስተምራል፤ (1) የአዲስ ኪዳን ሐዋርያትን፣ ነቢያትን፣ ወንጌላውያንን፣ መጋቢዎችንና መምህራንን እምነትና መልእክት በመቀበል (ቍ 11-12)፤ (2) በጸጋ ረገድ በማደግ፣ በመንፈሳዊ ብስለት ረገድ እየላቁ በመሄድ፣ በማንኛውም መልኩ ወደ ክርስቶስ በማደግ (ቍ 15)፣ በክርስቶስና በእግዚአብሔር ሙላት ሁሉ በመሞላት (ቍ 13 ይመ፤ ከ13-19 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (3) በልዩ ልዩ ዐይነት የትምህርት ነፋስ፣ «... ወዲያ ወዲህ እየተንገዋለልን ሕፃናት አንሆንም» በተባለው መሠረት የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችን ንቆ የሚተውበትን የእውነትን ዕውቀት ይዞ በመገኘት (ቍ 14-15)፤ (4) የተገለጠውን የቅዱሳት መጻሕፍትን እውነት በፍቅር በመያዝና በማወጅ (በመስበክ) (ቍ 15)፤ (5) "እውነተኛ በሆነው ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና" ውስጥ በመኖር (ቍ 24 ይመ፤ ከቍ 17-32 ጋር ያነጻጽሩ)::

**4፥14 ከእንግዲህ ... ሕፃናት አንሆንም፤** ጳውሎስ በቍ 13-15 ላይ የክርስቶስ ፍጹምነት ያላቸውን በመንፈስ ያደጉትን ሰዎች ማንነት ይገልጻል፤ (1) በመንፈስ ማደግ ሲባል ርጋታ ቢስ፣ በሌሎች የሐሰት አስተምህሮ በቀላሉ ተታላይና እንዲሁም አሳች ለሆነ የታይታ እንቅስቃሴ የተጋለጡ ሕፃናት አለመሆን ማለት ነው:: ሰዎች ሕፃናት ሆነው የሚቀሩት ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያላቸው ግንዛቤና ለእርሱም ያላቸው መሰጠት በቂ ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር ነው (ቍ 14-15):: (2) በመንፈስ ማደግ "እውነትን በፍቅር" መናገርን ያካትታል (ቍ 15):: በአዲስ ኪዳን የተገለጠው የወንጌል እውነት በፍቅር መያዝ፣ በፍቅር መስጠት፣ በፍቅር መንፈስም መታየት (መገለጽ) አለበት:: ይህ ፍቅር በመጀመሪያ መገለጽ ያለበት ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ (ቍ 15)፣ ከዚያም ለቤተ ክርስቲያን (ቍ 16)፣ ከዚያ ደግሞ ለእርስ በርስ ነው (ቍ 32 ይመ፤ ከ1ቆሮ 16፥14 ጋር ያነጻጽሩ)::

**4፥15 እውነትን በፍቅር፤** አንድነትን በእምነት መጠበቅ (ቍ 13)፣ እርስ በርስ በመቀባበልና ለክርስቶስና ለቃሉ በመታዘዝ፣ ችግርን ለመፍታትና ልዩነትንም ለማስወገድ በሚሻ ሕያው ፍቅር ላይ መመሥረት አለበት:: ይህም ማለት የአዲስ ኪዳንን እውነት በፍቅር መያዝና መጠበቅ ሲሆን፣ ከክርስቲያናዊ ተቋማት፣ ከትውፊት፣ ከግለሰቦች ወይም በአካል ከምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን ይልቅ ለአዲስ ኪዳን እውነት ቅድሚያ መስጠት ማለት ነው:: ኅብረትን ወይም አንድነትን ለመጠበቅ ሲባል የሚደረግ ማንኛውም ሙከራ የእግዚአብሔርን ቃል ዋጋ የሚያሳጣ መሆን የለበትም፤ ወይም መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትን ችላ እንዲባል የሚያደርግ መሆን የለበትም (ቍ 14):: ለቅዱስ ቃሉ ታማኝ ሆኖ መገኘት ለክርስቶስና ለሐዋርያዊ አስተምህሮ ታማኝ ካልሆነችው፣ በአካል ከምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን መለየትን ሊያስከትል ይችላል (2፥20 እና ማብ ይመ):: ከጊዜ በኋላም መንፈስ ቅዱስ ለክርስቶስና ለቀዳሚው የአዲስ ኪዳን እውነት ታማኝ የሆነች ቤተ ክርስቲያን እንድትመሠረት ሰዎችን ያነቃቃል::

**4፥30 ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ፤** በአማኙ ልብ ውስጥ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ (ሮሜ 8፥9፤ 1ቆሮ 6፥19)፣ ጌታ ኢየሱስ ስለ ኢየሩሳሌም ሲያለቅስ ወይም በሌላ ጊዜ ሲያዝን እንደ ተሰማው ያለ ከባድ ሐዘን ወይም ጸጸት የሚሰማው ከሦስቱ አንዱ አካል ነው (ማቴ 23፥37፤ ማር 3፥5፤ ሉቃ 19፥41፤ ዮሐ 11፥35):: (1) አማኞች መንፈስ ቅዱስ እንዲያዝን የሚያደርጉት ሀልዎቱን፣ ድምፁን፣ ወይም ምሪቱን ችላ ሲሉ ነው (ሮሜ 8፥5-17፤ ገላ 5፥16-25፤ 6፥7-9):: (2) መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን፣ መንፈስ ቅዱስን

# የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ስጦታዎች

*ኤፌ 4፥11 "አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣ አንዳንዶቹ ነቢያት፣ አንዳንዶቹም ወንጌል ሰባኪዎች፣ ሌሎቹ ደግሞ እረኞችና አስተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ የሰጠ እርሱ ነው።"*

ሰጨ፣ ኤፌሶን 4፥11 ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን የአገልግሎት ስጦታዎች (ይኸውም ስጦታው ያላቸው መንፈሳዊ መሪዎችን) ይዘረዝራል። ጳውሎስ እነዚህን ስጦታዎች ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚህ በታች ለተጠቀሱት ተግባሮች እንዲሆኑ መስጠቱን ይገልጻል፣ (1) የእግዚአብሔርን ሰዎች ለአገልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት (4፥12)፣ (2) እግዚአብሔር ባቀደው መሠረት የክርስቶስን አካል በመንፈሳዊ ረገድ ለማሳደግ (4፥13-16 ይመ፣ በገጽ 1800 ላይ፣ "ለአማኞች የሚሰጡ መንፈሳዊ ስጦታዎች" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

*ሐዋርያት*፣ "ሐዋርያ" የሚለው ሹመት የተሰጠው ለተወሰኑ የአዲስ ኪዳን መሪዎች ነው፣ "አፖስቴሎ" የሚለው ግስ ትርጕሙ አንድን ሰው የላኪው ተወካይ (ምስለኔ) አድርጎ ለተለየ ተልእኮ መላክ ማለት ነው። ይህ ማዕረግ ለክርስቶስ (ዕብ 3፥1)፣ ለዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት (ማቴ 10፥2)፣ ለጳውሎስ (ሮሜ 1፥1፤ 2ቆሮ 1፥1፤ ገላ 1፥1) እና ለሌሎች ተሰጥቶአል (ሐሥ 14፥4፡14፤ ሮሜ 16፥7፤ ገላ 1፥19፤ 2፥8-9፤ 1ተሰ 2፥6-7)።

(1) በአዲስ ኪዳን ላይ፣ "ሐዋርያ" የሚለው ቃል ከአጠቃላይ ግንዛቤ አንጻር ሲታይ፣ የቤተ ክርስቲያን ተወካይ ሆኖ ለተሾመ፣ እንደ መጀመሪያዎቹ የወንጌል መልእክተኞች ለነበረ አገልጋይ እንዲውል ተደርጎ ነበር። ስለዚህ በአዲስ ኪዳን ውስጥ "ሐዋርያ" ሲባል ወንጌላዊ ሆኖ የተላከን፣ ወይም ለልዩ ኀላፊነት የተላከን ማንኛውንም መልእክተኛ ያመለክታል (ሐሥ 14፥4፡ 14፤ ሮሜ 16፥7፤ 2ቆሮ 8፥23፤ ፊል 2፥25 ይመ)። እነዚህ ወገኖች ተወዳዳሪ የሌለው ልዩ መንፈሳዊ መሪነትን ያሳዩ፣ የጨለማ ኀይላትን በቀጥታ ይቋቋሙ ዘንድና የወንጌልንም እውነት፣ ታምራትን በመሥራት ያረጋግጡ ዘንድ ኀይልን የተሞሉ፣ አብያተ ክርስቲያናትንም በሐዋርያዊ እውነትና ንጽሕና ይመሠርቱ ዘንድ ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡ ሰዎች ነበሩ። እነዚህ ተዘዋዋሪ አገልጋዮች ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስምና ለወንጌል ሥርጭት ሲሉ ሕይወታቸውን ለአደጋ አጋለጡ (ሐሥ 11፥21-26፤ 13፥50፤ 14፥19-22፤ 15፥25-26)። እነዚሁ አገልጋዮች በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ የእምነትና የጸሎት ሰዎችም ነበሩ (ሐሥ 11፥23-25፤ 13፥2-5፤ 46-52፤ 14፥1-7፡21-23 ይመ)።

(2) ሐዋርያት በዚህ አጠቃላይ እሳቤ መሠረት፣ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ላለው ዕቅድ ምንጊዜም እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው። አብያተ ክርስቲያናት በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሰዎችን መላክ ቢያቋርጡ፣ በዓለም ዙሪያ ሁሉ መካሄድ ያለበት የወንጌል ሥርጭት መሰናክል ያጋጥመዋል። በአንጻሩ ግን ቤተ ክርስቲያን እንደነዚህ ያሉትን ሰዎች እስከፈራችና እስከላከች ድረስ የተልእኮ ተግባሯን ትፈጽማለች፣ ለጌታ ታላቅ ተልእኮም ታማኝ ሆና ትኖራለች (ማቴ 28፥18-20)።

(3) በሌላም በኩል፣ "ሐዋርያ" የሚለው ቃል በተለየ መልኩ ውሎ ይገኛል፣ ይኸውም ጌታ ኢየሱስን ከትንሣኤው በኋላ ያዩትን፣ ወንጌልን ይሰብኩና ቤተ ክርስቲያንንም ይተክሉ ዘንድ ከሞት በተነሣው ጌታ በግል አደራ የተሰጣቸውን ወገኖች (ለምሳሌ፣ ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያትና ጳውሎስ) የሚያመለክት ነው። ከመለኮታዊ መገለጥና ከመጀመሪያው የወንጌል መልእክት አንጻር፣ በዘመናችን በማንም ዘንድ ከእንግዲህ ወዲያ በማይገኝ መልኩ፣ ለሐዋርያት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልዩ ሥልጣን ተሰጥቷቸው ነበር (ኤፌ 2፥20 እና ማብ ይመ)። ስለዚህ የሐዋርያት ሹመት በዚህ ልዩ በሆነው እሳቤው የተለየና ሊደገም የማይችል ነው። የመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት ተተኪ ሊኖራቸው አይችልም (1ቆሮ 15፥8 እና ማብ ይመ)።

(4) የአዲስ ኪዳን ሐዋርያት ተቀዳሚ ተግባር አብያተ ክርስቲያናትን መመሥረት ሲሆን፣ እነዚሁ አብያተ ክርስቲያናት ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና ለአዲስ ኪዳን እምነት ታማኝ ሆነው የተመሠረቱ ወይም ወደ ትክክለኛ ተልእኳቸው የተመለሱ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነበር (ከዮሐ 21፥15-17፤ ከ1ቆሮ 12፥28፤ ከ2ቆሮ 11፥2-3፤ ከኤፌ 4፥11-13፤ ከፊል 1፥17 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህም ተግባር ሁለት ዐበይት ኀላፊነቶችን ያካተተ ነው፣ (ሀ) ቤተ ክርስቲያን ንጽሕናዋን ጠብቃ እንድትጓዝ፣ ከኀጢአትና ከዓለምም ተለይታ እንድትኖር አስቸኳይ የሆነ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ፍላጎትን (1ቆሮ 5፥1-5፤ 2ቆሮ 6፥14-18፤ ያዕ 2፥14-26፤ 1ጴጥ 2፥11፤ 4፥1-5፤ 1ዮሐ 2፥1፡15-17፤ 3፥3-10)፤ (ለ) የአዲስ ኪዳንን ወንጌል ለመስበክ ከማንኛውም ዐይነት ኑፋቄ፣ እንግዳ ከሆነ ነገር መለኮታዊ አቅጣጫና

ከሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ለመከላከል የማያቋርጥ ሸክምን መሸከምን (ሮሜ 16፥17፤ 1ቆሮ 11፥2፤ 2ቆሮ 11፥3-4፡14 እና ማብራሪያዎቹን፤ ገላ 1፥9 እና ማብ ይመ፤ 2ጴጥ 2፥1-3፤ 1ዮሐ 4፥1-6፤ 2ዮሐ 1፥7-11፤ ይሁ 1፥3-4፡12-13 ይመ፤ በገጽ 1716 ላይ፣ "የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ተግባራዊ ኀላፊነታቸው" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(5) የቤተ ክርስቲያንን መሠረት የጣሉት የመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት ተተኪ ባይኖራቸውም እንኳ፣ የዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን የእነርሱን ቃል፣ መልእክትና እምነት አሁንም ቢሆን የህልውናዋ መሠረት አድርጋ ትገኛለች። ቤተ ክርስቲያን ለእነርሱ ቀዳሚ ጽሑፍ መታዘዝና ታማኝ መሆን አለባት። እስትንፋሰ እግዚአብሔር ያለበትን የሐዋርያትን መገለጥ መተው ማለት ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ ውጭ መሆን፣ ጌታ ራሱንም መካድ ማለት ነው (ዮሐ 16፥13-15፤ 1ቆሮ 14፥36-38፤ ገላ 1፥9-11)። በአንጻሩ ግን ሐዋርያዊ መልእክትን ማመን፣ ይህኑንም መታዘዝና ከማንኛውም ዐይነት ጥመት መጠበቅ ማለት ለመንፈስ ቅዱስ ታማኝ ሆኖ መገኘት ሲሆን (ሐሥ 20፥28፤ 2ጢሞ 1፥14)፣ እግዚአብሔር የሚሰጠውን የማያቋርጥ ሕይወት፣ በረከትና ህልዎት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስተማማኝ ማድረግ ማለት ነው (ኤፌ 2፥20 እና ማብ ይመ)።

ነቢያት፤ ነቢያት በእግዚአብሔር ስም በመንፈስ ቅዱስ ቀጥታ መሪነት የተናገሩ፣ ዋና ጉዳቸውም የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወትና ንጽሕና የሆነ አማኞች ነበሩ። በአዲሱ ኪዳን ውስጥም ከእግዚአብሔር ዘንድ መልእክትን ለሕዝቡ ለማምጣት በመንፈስ ቅዱስ የተሾሙና ኀይልን የተቀበሉ ነበሩ (ሐሥ 2፥17፤ 4፥8፤ 21፥4)።

(1) የጥንታዊቷን ቤተ ክርስቲያን ነቢያዊ አገልግሎት ለማስተዋል የብሉይ ኪዳን ነቢያት መሠረቶች ናቸው። ቀዳሚ ተግባራቸውም የእግዚአብሔር ሕዝብ ለኪዳናዊ ኅብረታቸው ታማኝ ሆነው እንዲዘልቁ በማበረታታት፣ የእግዚአብሔርን ቃል በመንፈስ ቅዱስ መሪነት መንገር ነበር። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ በገለጠላቸው መሠረት ስለ ወደፊቱ ተንብየው ነበር (በገጽ 1009 ላይ፣ "ነቢይ በብሉይ ኪዳን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና ሐዋርያት በአገልግሎት ረገድ የብሉይ ኪዳን አርአያ ሆነው ይታያሉ (ሐሥ 3፥22-23፤ 13፥1-2)።

(2) ነቢያት በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚከተሉት መንገዶች ሠርተዋል፤ (ሀ) በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ የእግዚአብሔር ቃል ሰባኪዎችና ተርጓሚዎች ነበሩ፤ ሕዝብን ለማስጠንቀቅ፣ ለመምከር፣ ለማጽናናትና ለማነጽ በእግዚአብሔር የተጠሩ ሰዎችም ነበሩ (ሐሥ 2፥14-36፤ 3፥12-26፤ 1ቆሮ 12፥10፤ 14፥3)። (ለ) የትንቢትን ስጦታ መለማመድ ነበረባቸው (በገጽ 1800 ላይ፣ "ለአማኞች የሚሰጡ መንፈሳዊ ስጦታዎች" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። (ሐ) የወደፊቱን የሚናገሩ (ሐሥ 11፥28፤ 21፥10-11)፣ አንዳንድ ጊዜም ባለ ራእዮች ነበሩ (1ዜና 29፥29 ያነጻጽሩ)። (መ) የአዲስ ኪዳን ነቢያት፣ እንደ ብሉይ ኪዳን ነቢያት ኀጢአትን ለማጋለጥ፣ ጽድቅን ለማወጅ፣ ስለሚመጣው ፍርድ ለማስጠንቀቅ፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ ዘንድ የሚታየውን ዓለማዊነትና ለብታነት ለመዋጋት ተጠርተው ነበር (ሉቃ 1፥14-17)። ከጽድቅ መልእክታቸው የተነሣ፣ ነቢያትና አገልግሎታቸው በለብታና በክሕደት ዘመን ውስጥ በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነትን ሊያጡ ይችላሉ።

(3) የነቢዩ ባሕርይ፣ ሸክም ፍላጎትና ችሎታ የሚከተሉትን ያካትታል፤ (ሀ) የቤተ ክርስቲያን ንጽሕና ይጠበቅ ዘንድ ከፍተኛ ቅናትን (ዮሐ 17፥15-17፤ 1ቆሮ 6፥9-11፤ ገላ 5፥22-25)፤ (ለ) ክፋትን በሩቁ የማሽተት ከፍተኛ ስጦታና ጽድቅ ያልሆነውን ነገር የመለየትና የመጥላት ችሎታን (ሮሜ 12፥9፤ ዕብ 1፥9)፤ (ሐ) የሐሰት ትምህርት የሚያስከትለውን አደጋ የቱን ያህል እንደ ሆነ የማስተዋል ልዩ ችሎታን (ማቴ 7፥15፤ 24፥11፡24፤ ገላ 1፥9፤ 2ቆሮ 11፥12-15)፤ (መ) የነቢዩ መልእክት የቱን ያህል ዋጋ እንዳለው ለመመዘን ምንጊዜም ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የመጣበቅ ችሎታን (ሉቃ 4፥17-19፤ 1ቆሮ 15፥3-4፤ 2ጢሞ 3፥16)፤ (ሠ) ለእግዚአብሔር መንግሥት መስፋፋት ማሰብንና በእግዚአብሔር ሐሳብ ውስጥ ተካፋይ ሆኖ መገኘትን (ማቴ 21፥11-13፤ 23፥37፤ ሉቃ 13፥34፤ ዮሐ 2፥14-17፤ ሐሥ 20፥27-31)።

(4) የነቢያት መልእክት ስሕተት አልባ ተደርጎ መቈጠር የለበትም፤ መልእክታቸው በቤተ ክርስቲያን፣ በሌሎች ነቢያትና በእግዚአብሔር ቃል ይመዘን ዘንድ ግድ ነው። ማኅበረ ምእመኑ መልእክታቸው ከእግዚአብሔር መሆኑንና አለመሆኑን እንዲለይና እንዲመዝን ይጠበቅበታል (1ቆሮ 14፥29-33፤ 1ዮሐ 4፥1)።

(5) ነቢያት የእግዚአብሔር ዐላማ ይሳካ ዘንድ ዛሬም ቢሆን ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊዎች ናቸው። የእግዚአብሔርን ነቢያት የማትቀበል ቤተ ክርስቲያን ወደ ዓለማዊነት የምትጓዝ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነትንም ለድርድር ለማቅረብ የምትዋልልና በመዳከም ላይ የምትገኝ ቤተ ክርስቲያንናት (1ቆሮ 14፥3 ይመ፤ ከማቴ 23፥31-38፤ ከሉቃ 11፥49፤ ከሐሥ 7፥51-52 ጋር ያነጻጽሩ)።

ነቢያት በመንፈስ ቅዱስ አነሣሽነት ያገኙትን የተግሣጽና የማስጠንቀቂያ ቃል፣ ይኸውም ኀጢአትንና ጽድቅ ያልሆነውን አካሄድ ለማጋለጥ ካልተፈቀደላቸው በቀር (ዮሐ 16፥8-11)፣ ቤተ ክርስቲያኗ ውሎ ዐድሮ የመንፈስ ቅዱስ ድምፅ የማይሰማበት ቦታ ትሆናለች። የቤተ ክርስቲያን ፖለቲካና ከዓለም የሆነው ኀይል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን ስፍራ ይይዛሉ (2ጢሞ 3፥1-9፤ 4፥3-5፤ 2ጴጥ 2፥1-3፡12-22)። በአንጻሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ከመሪዎቿ ጋር የነቢያትን ድምፅ ብትሰማ፣ ወደሚታደስ ሕይወትና ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ወደ ማድረግ የምትነሣሣ ትሆናለች፤ ኀጢአት ታንቅሮ ይተፋል፤ የመንፈስ ቅዱስ ህልዎትም ታማኝ ሆነው በሚኖሩት ዘንድ እውን ይሆናል (1ቆሮ 14፥3፤ 1ተሰ 5፥19-21፤ ራእ 3፥20-22)።

*ወንጌላውያን*፤ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ወንጌላውያን፣ ላልዳኑት የድነትን ወንጌል (ይኸውም የምሥራች ማለት ነው) እንዲሰብኩ፣ በአንድ ከተማ አዲስ ሥራ ይጀምር ዘንድ እንዲያግዙ ከእግዚአብሔር ስጦታን የተቀበሉና በእግዚአብሔር የተሾሙ ሰዎች ናቸው። ወንጌል ሲሰበክ፣ የጸጋን ስጦታና የድነትን ኀይል ምንጊዜም ከራሱ ጋር ይዞ ይመጣል (ሮሜ 1፥16-17)።

(1) "የወንጌላዊው" የፊልጶስ አገልግሎት (ሐሥ 21፥8)፣ በአዲስ ኪዳን ሥርዐት መሠረት የወንጌላዊ ሥራ ምን መሆን እንዳለበት ቍልጭ ያለ ሥዕል ይሰጣል። (ሀ) ፊልጶስ የክርስቶስን ወንጌል ሰበከ (ሐሥ 8፥4-5፡35)። (ለ) ብዙዎቹ ዳኑ፤ በውሃም ተጠመቁ (ሐሥ 8፥6፡12)። (ሐ) ምልክት፣ ታምር፣ ፈውስና ከክፉ መናፍስት ነጻ መውጣት ስብከቱን አጅበውታል (ሐሥ 8፥6-7፡13)። ፊልጶስ አዲስ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ እንዲጠመቁ ፈለገ (ሐሥ 8፥12-17 ይመ፤ ከ2፥38፤ ከ19፥1-6 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ላለው ዐላማ የአንድ ወንጌላዊ በዚያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መገኘት እጅግ አስፈላጊ ነው። የአንድን ወንጌላዊ አገልግሎት ማገዝ የተሳናት ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር በሚፈልገው መጠን አዲስ አማኞችን ማፍራት አትችልም። እድገት የማይታይባት፣ ሚስዮናዊ ተልእኮ የተለየትና ባለችበት የምትንፏቀቅ ቤተ ክርስቲያን ትሆናለች። በአንጻሩ ግን የወንጌላዊውን መንፈሳዊ ስጦታ አክብራ የምትይዝ፣ ለጠፉትም የጋለ ፍቅርን ዘወትር እየገለጸች የምትጓዝ ቤተ ክርስቲያን የድነትን መልእክት በሚያሳምንና አዳኝ በሆነ ኀይል ታውጃለች (ሐሥ 2፥14-41)።

*መጋቢዎች*፤ መጋቢዎች የአንድን ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ምእመናን መንፈሳዊ ፍለጎት የሚከታተሉና የሚጠብቁ ናቸው። "ሽማግሌዎች" እና (ሐሥ 20፥17፤ ቲቶ 1፥5) "ኤጲስ ቆጶስ"ም (1ጢሞ 3፥1፤ ቲቶ 1፥7) ተብለው ይጠራሉ።

(1) የመጋቢዎች ተግባር ጤናማ የሆነውን አስተምህሮ ማወጅ፣ ኑፋቄን ዋጋ ቢስ ማድረግ (ቲቶ 1፥9-11)፣ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማርና በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአመራር ማገልገል ነው (1ተሰ 5፥12፤ 1ጢሞ 3፥1-5)፤ እንዲሁም የቅድስናና የጤናማ አስተምህሮ አርአያ መሆን (ቲቶ 2፥7-8)፣ አማኞች ሁሉ በመለኮታዊ ጸጋ ሥር መሆናቸውንም መከታተል ነው (ዕብ 12፥15፤ 13፥17፤ 1ጴጥ 5፥2)። በሐዋርያት ሥራ 20፥28-31 ላይ የመጋቢዎች ተግባር፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊከሠት የሚችለውን የሐሰት አስተምህሮና የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችን በመለየት፣ ሐዋርያዊ እውነትንና የእግዚአብሔርን መንጋ መንከባከብ መሆኑ ተገልጸአል (በገጽ 1716 ላይ፣ "የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ተግባራዊ ኀላፊነታቸው" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። መጋቢዎች እረኞች በመሆን ያገለግላሉ፤ ለእነርሱም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመልካም እረኛነቱ አርአያቸው ነው (ዮሐ 10፥11-16፤ 1ጴጥ 2፥25፤ 5፥2-4)።

(2) በአዲስ ኪዳን ለይ የሚታየው ሥርዐት ከአንድ በላይ የሆኑ መጋቢዎች የአንድን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት ሲመሩ ያሳያል (ሐሥ 20፥28፤ ፊል 1፥1)። መጋቢዎች የተመረጡ አገልጋዮች ነበሩ፤ የተመረጡትም በፖለቲካ መንገድ ሳይሆን፣ ቤተ ክርስቲያን የዕጩ መጋቢን መንፈሳዊ ብቃት በምታጤንበት ጊዜ ለእርሷ በተሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ጥበብ ነው (በገጽ 1925 ላይ፣ "የመሪዎች መንፈሳዊ ብቃት" በሚል ርእው የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(3) መጋቢዎች፣ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ላለው ዐላማ አስፈላጊ ናቸው፤ እግዚአብሔርን የሚፈሩና ታማኝ የሆኑ መጋቢዎችን መምረጥ የተሳናት ቤተ ክርስቲያን፣ በመንፈስ ቅዱስ ሐሳብ መሠረት መገዛትን ታቆማለች (1ጢሞ 3፥1-7)። ለሰይጣን አጥፊ ኀይላትና ለዓለም የተጋለጠች ትሆናለች (ሐሥ 20፥28-31 ይመ)። የቃሉ ስብከት ከመሥመር የወጣ ይሆናል፤ የወንጌል የብቃት መለኪያም ከቤተ ክርስቲያኗ ይታጣል (2ጢሞ 1፥13-14)። የቤተ ክርስቲያኗ አባላትና ቤተ ሰቦች በእግዚአብሔር ዐለማ መሠረት እንክብካቤን አያገኙም (1ጢሞ 4፥6፡12-16፤ 6፥20-21)። ብዙዎች ከእውነት ይርቃሉ፤ ልባቸውንም ለተረት አሳልፈው ይሰጣሉ (2ጢሞ 4፥4)።

በአንጻሩ ግን እግዚአብሔርን የሚፈሩ መጋቢዎች ቢሾሙ፣ አማኞች በእምነት ቃልና በጤናማ አስተምህሮ ይኰተኰታሉ፤ ለፈሪሀ እግዚአብሔር ዐላማም ራሳቸውን ያሠለጥኑ ይሆናሉ (1ጢሞ 4፥6-7)። ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስና በሐዋርያት ትምህርት ትጸና ዘንድ ትምህርት ይሰጣታል፤ ከዚህም የተነሣ የራሷን ድነትና የሚሰሙትንም ድነት አስተማማኝ ታደርጋለች (1ጢሞ 4፥16፤ 2ጢሞ 2፥2)።

አስተማሪዎች፤ አስተማሪዎች የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ትገነባ ዘንድ የእግዚአብሔርን ቃል ግልጽ ለማድረግ፣ ለማብራራትና ለማወጅ፣ ልዩ የሆነውንና ከእግዚአብሔር የተገኘውን ስጦታ የተቀበሉ ናቸው (ኤፌ 4፥12)።

(1) የአስተማሪዎች ልዩ ተግባር ዐደራ የተሰጣቸውን ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ ከአደጋ መጠበቅ ነው (2ጢሞ 1፥11-14)። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወደ ሆነው መገለጥና ወደ ቀደመው የክርስቶስና የሐዋርያት መልእክት ቤተ ክርስቲያንን በታማኝነት ማሳየት አለባቸው፤ በዚሁ ተግባራቸውም ጸንተው መገኘት ይኖርባቸዋል።

(2) የመጽሐፍ ቅዱሳዊው ማስተማር ዐቢይ ዐላማ፣ በእግዚአብሔር ቃል ላይ በተገለጠው መሠረት የክርስቶስን አካል፣ ወላዋይነት ወደሌለበትና ፈሪሀ እግዚአብሔር ወደሚገኝበት የሕይወት ዘይቤ በመምራት እውነትን መጠበቅና ቅድስናን እውን ማድረግ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቲያናዊ ትምህርት ዐላማን እንደሚከተለው ይገልጻል፤ "ከንጹሕ ልብ፣ ከበጎ ኅሊና እንዲሁም ከእውነተኛ እምነት የሚገኝ ፍቅር ነው" (1ጢሞ 1፥5)። ስለዚህ የክርስቲያናዊ ዕውቀት ማረጋገጫ፣ "አንድ ሰው ምን ያህል ያውቃል?" የሚለው ቀርቶ፣ "እንዴት ይኖራል?" የሚለው ሲሆን፣ ይኸውም ፍቅር፣ ንጽሕና፣ እምነትና ፈሪሀ እግዚአብሔር በአንድ አማኝ ሕይወት ላይ ጐልተው መታየት ማለት ነው።

(3) አስተማሪዎች እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ ላለው ዐላማ አስፈላጊ ናቸው፤ ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ መገለጥ ታማኞች የሆኑትን፣ እነዚህኑ አስተማሪዎችና የሥነ መለኮት ሊቃውንት የማትቀበል ወይም የማትሰማ ቤተ ክርስቲያን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው መልእክት የቱን ያህል እውነት እንደ ሆነ፣ ስለ ዐይነተኛው የክርስቶስና የሐዋርያት ትምህርትም የተሰጠው ትርጓሜ የቱን ያህል ትክክል እንደ ሆነ ከማስተዋል ትዘናጋለች። ዝም ብለው የሚያልፉ አስተማሪዎችና የሥነ መለኮት ሊቃውንት ያሉባት ቤተ ክርስቲያን በእውነት ላይ ጸንታ አትቆዝም። አዲስና ከእውነት የወጣ የአስተምህሮ ነፋስም ምዘና ውስጥ ሳይገባ ተቀባይነትን ያገኛል፤ ከተገለጠው እውነት ይልቅ ሃይማኖታዊ ተመክሮና የሰው ሐሳብ ለቤተ ክርስቲያኗ አስተምህሮ፣ መመዘኛና ልምምድ የበላይ መመሪያ ይሆናሉ። በአንጻሩ ፈሪሀ እግዚአብሔር ያላቸውን አስተማሪዎችና የሥነ መለኮት ሊቃውንት የምትሰማ ቤተ ክርስቲያን፣ ትምህርቷንና ልምምዷን መሠረታዊ በሆነው የወንጌል ምስክርነት ታስመዝናለች፤ የተሳሳተ ሐሳብና አሠራር እንዲጋለጥ ታደርጋለች፤ ዐይነተኛ የሆነው የክርስቶስ መልእክትም ሳይዛባ ጥራቱ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ወደ አዲሱ ትውልድ እንዲተላለፍ ታደርጋለች። እስትንፋሰ እግዚአብሔር ያለበት የእግዚአብሔር ቃል የትምህርት ሁሉ መመዘኛ ይሆናል፤ ቤተ ክርስቲያኗም እስትንፋሰ እግዚአብሔር ያለው የመንፈስ ቅዱስ ቃል የመጨረሻው እውነትና ባለሥልጣን መሆኑን፣ ብሎም ከአብያተ ክርስቲያናትና ከተቋማቸው በላይ መሆኑን እንድትገነዘብ ትደረጋለች።

የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር
መንፈስ አታሳዝኑ። 31መራርነትን ሁሉ፣
ቍጣና ንዴትን፣ ጩቅጭቅና ስድብን
ከማንኛውም ክፋት ጋር ከእናንተ ዘንድ
አስወግዱ። 32እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር
እንዳላችሁ፣ እናንተም ይቅር ተባባሉ፤
እርስ በርሳችሁ ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ።

5 እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች
እግዚአብሔርን ምሰሉ፤ 2ክርስቶስ እንደ
ወደደን ራሱንም ስለ እኛ መልካም መዐዛ
ያለው መባና መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር
እንደ ሰጠ እናንተም በፍቅር ተመላለሱ።
3ማንኛውም የዝሙት ወይም የርኵሰት
ወይም የስስት ነገር ከቶ በመካከላችሁ
አይነሣ፤ ይህ ቅዱስ ለሆነው ለእግዚአብሔር
ሕዝብ አይገባምና። 4የሚያሳፍርና ተራ
የሆነ ንግግር፣ ዋዛ ፈዛዛም ለእናንተ
ስለማይገባ በመካከላችሁ አይኑር፤ ይልቁንስ
የምታመሰግኑ ሁኑ። 5ደግሞም ይህን
ዕወቁ፤ ማንም አመንዝራ ወይም ርኩስ
ወይም ስግብግብ ይኸውም ጣዖት አምላኪ
በክርስቶስና በእግዚአብሔር መንግሥት[a] ርስት
የለውም። 6ማንም በከንቱ ንግግር አያታላችሁ፤
ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቍጣ በማይታዘዙ
ልጆች ላይ የሚመጣው በእንደዚህ ዐይነት ነገር
ነው። 7ስለዚህ እንዲህ ካሉ ጋር አትተባበሩ።

4፥31 ቆላ3፥8፤ 1ጴጥ2፥1
4፥32 ማቴ6፥14፡15፤ ቈላ3፥12፡13፤ 1ጴጥ3፥18፤
5፥1 ማቴ5፥48፤ ሉቃ6፥36፤ ዮሐ1፥12፤
5፥2 ቈላ25፤ ዮሐ13፥34፤ ገላ1፥4፤ 2፥20፤ ዕብ7፥27፤
5፥3 1ቆሮ6፥18፤ ቈላ3፥5
5፥4 ቈላ20፤ ኤፌ4፥29
5፥5 ማቴ25፥34፤ ሐሥ20፥32፤ ቈላ3፥5
5፥6 ማር13፥5፤ ሮሜ1፥18፤ ኤፌ2፥2
5፥8 ሉቃ16፥8፤ ዮሐ8፥12፤ ሐሥ26፥18፤ ኤፌ2፥2
5፥9 ማቴ7፥16-20፤ ሮሜ15፥14፤ ገላ5፥22
5፥10 1ጢሞ5፥4

8ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁ፤ አሁን ግን
በጌታ ብርሃን ናችሁ። እንደ ብርሃን ልጆች
ኑሩ፤ 9የብርሃኑ ፍሬ በበጎነት፣ በጽድቅና
በእውነት ሁሉ ዘንድ ነውና። 10እንዲሁም
ጌታን ደስ የሚያሰኘውን ፈልጉ። 11ፍሬ
ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር ምንም ዐይነት
ግንኙነት አይኑራችሁ፤ ይልቁን ግለጡት፤
12በድብቅ የሚሠሩትን ነገር መናገር ራሱ
አሳፋሪ ነውና። 13ብርሃን የበራበት ነገር
ሁሉ ግልጽ ሆኖ ይታያል፤ 14ምክንያቱም
ሁሉን ነገር እንዲታይ የሚያደርገው ብርሃን
ነውና፤ ስለዚህም፣
"አንተ የተኛህ ንቃ፤
ከሙታን ተነሣ፤
ክርስቶስም ያበራልሃል" ተብሎአል።
15እንግዲህ ጥበብ እንደ ሌላቸው ሳይሆን
እንደ ጥበበኞች እንዴት እንደምትኖሩ
ተጠንቀቁ። 16ቀኖቹ ክፉ ናቸውና ዘመኑን
በሚገባ ዋጁ። 17ስለዚህ ሞኞች አትሁኑ፤
የጌታ ፈቃድ ምን እንደ ሆነ አስተውሉ
እንጂ። 18በመንፈስ ተሞሉ እንጂ በወይን ጠጅ

5፥11 ሮሜ13፥12፤ 2ቆሮ6፥14 5፥13 ዮሐ3፥20፡21
5፥14 ኢሳ26፥19፤ 60፥1፤ ሚል4፥2፤ ዮሐ5፥25፤
ሮሜ13፥11 5፥15 ቈላ2 5፥16 ኤፌ6፥13፤ ቈላ4፥5
5፥17 ሮሜ12፥2፤ ቈላ1፥9፤ 1ተሰ4፥3 5፥18 ዘሌ10፥9፤
ምሳ20፥1፤ ኢሳ28፥7፤ ሉቃ1፥15፤ ሮሜ13፥13

[a]5፥5 ወይም የክርስቶስና የእግዚአብሔር መንግሥት በሆነው

---

ወደ መቃወም ያመራል (ሐሥ 7፥51)፤ ይህም በበኩሉ የመንፈስ ቅዱስን እሳት ወደማዳፈን (1ተሰ 5፥19)፣ በመጨረሻም የጸጋን መንፈስ ቅዱስ ወደ መሳደብ ያደርሳል (ዕብ 10፥29)። ይህ የመጨረሻው ድርጊት የኀጢአት ይቅርታ ከማይኖረውና በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል ከመናገር ጋር አንድ ሆኖ ሊቈጠር ይችላል (ማቴ 12፥31 እና ማብ ይመ)።

**5፥5 ይህን ዕወቁ፤** ሐዋርያው ጳውሎስም ሆነ የኤፌሶን ሰዎች ኢግብረገባዊ፣ ንጽሕና የሌላቸው ወይም ስስታም (ከእግዚአብሔር ይልቅ ሀብትን የሚወዱ)፣ ሰዎች ሁሉ (በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ሆነ ውጭ) ከክርስቶስ መንግሥት የተገለሉ መሆናቸውን ያለጥርጥር ያውቃሉ። ይህም ጕዳይ በብሉይ ኪዳን ነቢያት (ኤር 8፥7 እና ማብ፤ 23፥17 እና ማብ፤ ሕዝ 13፥10 እና ማብ ይመ) በሐዋርያትና በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን (1ቆሮ 6፥9 እና ማብ፤ ገላ 5፥21 እና ማብ ይመ) በብርቱ አጽንዖት ትምህርት ተሰጥቶበታል። እንደነዚህ ያሉትን በደሎች የሚፈጽሙ ሁሉ፣ ያልዳኑ ለመሆናቸው፣ የእግዚአብሔር ሕይወት የሌላቸው ለመሆኑ፣ ከዘላለም ሕይወት የተለዩ ለመሆናቸውም ግልጽ ማስረጃን ይሰጣሉ (ዮሐ 8፥42 እና ማብ፤ 1ዮሐ 3፥15 እና ማብ ይመ)።

**5፥6 አያታላችሁ፤** አንዳንድ አስተማሪዎች የኤፌሶን ሰዎችን ስለ ኢግብረገባዊነታቸው የእግዚአብሔርን ቍጣ መፍራት የለባችሁም በማለት እንደሚነግሯቸው ጳውሎስ ዐውቆአል። ስለዚህ፣ «ማንም ... አያታላችሁ» በማለት ይመክራቸዋል። እንግዲህ አንድ ሰው ኢግብረገባዊ የሆኑና ቅድስና የሌላቸው አንዳንድ ሰዎች በክርስቶስ መንግሥት ርስት ሊኖራቸው ይችላል በማለት ሊታለል ይችላል (በገጽ 1519 ላይ፣ «*የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**5፥11 ከጨለማ ሥራ፤** የክርስቶስን ጌትነት አምነው የተቀበሉ ሁሉ ስለ «ጨለማ ሥራ» እና ስለ ኢግብረገባዊነት ደንታቢሶች ወይም ምንም የማይሰማቸው ሊሆኑ አይችሉም (ቍ 3-6)። በተለያየ መልኩ የሚከሠተውን ክፋት ለማጋለጥ፣ ለመገሠጽና ለመኰነን ምንጊዜም ዝግጁዎች መሆን አለባቸው። ትክክለኛ ስላልሆነው ነገር በቅንነት መጮኽ ማለት ኀጢአትን መጥላት ነው (ዕብ 1፥9)፤ ክፋውን በመቃወም ከእግዚአብሔር ጋር መቆም ነው (መዝ 94፥16)፤ እንዲሁም የክፋትን ሥራ ላጋለጠው ጌታ ለክርስቶስ በጽናት ታማኝ መሆን ነው (ዮሐ 7፥7፤ 15፥18-20 ይመ፤ ከሉቃ 22፥28 ጋር ያነጻጽሩ)።

**5፥18 በወይን ጠጅ፤** በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አማኞች መቀደስን ለማግኘትና የተገኘውንም መቀደስ ይጠብቁ ዘንድ ለተሰጣቸው ጸጋ ከሚያደርጉት አጸፋ ጋር የተሳሰረ ነው፤ ይኸውም አንድ ሰው የወይን ጠጅ ጠጥቶ እያለ በመንፈስ ቅዱስ ሊሞላ እንደማይችል ያሳያል። ጳውሎስ ስለ ኀጢአተኛ ተፈጥሮ ድርጊቶች አማኞችን ሁሉ ያስጠነቅቃል፤ ማለትም፣ እነዚህን የሚፈጽሙ ሁሉ፣ «የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም» ይላል (ገላ 5፥19-21 ይመ፤ ከኤፌ 5፥3-7 ጋር ያነጻጽሩ)። በተጨማሪም፣ «በእንዲህ ሁኔታ የሚኖሩ ሁሉ» (ገላ 5፥21)፣ የመንፈስ ቅዱስ ህልዎትና ሙላት ሁልጊዜ በሕይወታቸው እውን ሊሆን አይችልም፤ በሌላም አገላለጽ፣ «የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ»ን ማጣት ማለት የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ማጣት ማለት ነው (ሐሥ 8፥21 እና ማብ ይመ)።

**5፥18 በመንፈስ ተሞሉ፤** «ተሞሉ» (የአሁን ጊዜያት፣ ኢተሻጋሪ ትእዛዛዊ አንቀጽ ነው) የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ፣ «በተደጋጋሚ መሞላት» የሚለውን ትርጕም ይዞ ይገኛል። የእግዚአብሔር ልጆች በመንፈስ ቅዱስ በተደጋጋሚ በመሞላት ዘወትር ወይም በተደጋጋሚ መታደስ አለባቸው (3፥14-19፤ 4፥22-24፤ ሮሜ 12፥2)። (1) ክርስቲያኖች አዲስ ፍጥረት ከሆኑ በኋላ በመንፈስ

ተዘ፣ ቀቀ አትስከሩ፤ ይህ ብክነት ነውና። 19በመዝሙርና
በውዳሴ፣ በመንፈሳዊም ዝማሬ እርስ
በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ በልባችሁ ለጌታ
ተቀኙ፤ አዚሙም። 20በዚህም እግዚአብሔር
ቈላ 3፥16-17 አብን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም
ስለ ሁሉ ነገር ሁልጊዜ አመስግኑ።
21ለክርስቶስ ካላችሁ አክብሮታዊ ፍርሀት
የተነሣ እንዳችሁ ለአንዳችሁ ተገዙ።

## ባልና ሚስት

*5፥22—6፥9 ተዛ ምብ — ቈላ3፥18—4፥1*

22ሚስቶች ሆይ፤ ለጌታ እንደምትገዙ
ለባሎቻችሁም ተገዙ 23ክርስቶስ፣ አካሉ
ለሆነችውና አዳኟ ለሆናት ቤተ ክርስቲያን
ራስ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ባልም የሚስቱ
ራስ ነውና። 24እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን
ለክርስቶስ እንደምትገዛ፣ ሚስቶችም
ለባሎቻቸው በማንኛውም ነገር እንደዚሁ
መገዛት ይገባቸዋል።
25ባሎች ሆይ፤ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን
እንደ ወደዳትና ራሱንም ስለ እርሷ አሳልፎ
እንደ ሰጠ፣ እናንተም ሚስቶቻችሁን
ውደዱ፤ 26በቃሉ አማካይነት በውሃ አጥቦ
በማንጻት እንድትቀደስ፣ 27እንዲሁም
ጕድፍ ወይም የፊት መጨማደድ ወይም
እንዳች እንከን ሳይገኝባት ቅድስትና ነውር
አልባ የሆነች ክብርት ቤተ ክርስቲያን
አድርጎ ለራሱ ሊያቀርባት ነው።

5፥19 መዝ27፥6፤ 95፥2፤ ሐሥ16፥25፤ 1ቆሮ14፥15፡26፤ ቈላ3፥16 5፥20 ቍ4፤ ኢዮ1፥21፤ መዝ34፥1፤ ቈላ3፥17፤ ዕብ13፥15 5፥21 ገላ5፥13፤ 1ጴጥ5፥5 5፥22 ዘፍ3፥16፤ 1ቆሮ14፥34፤ ኤፌ6፥5፤ ቈላ3፥18፤ 2ጢሞ2፥12፤ ቲቶ2፥5፤ 1ጴጥ3፥1፡5፡6

5፥23 ኤፌ1፥22 5፥24 ቍ22 5፥25 ቍ2፡28፡33፤ ቈላ3፥19 5፥26 ዮሐ17፥19፤ ሐሥ22፥16፤ ዕብ2፥11፤ 10፥10፡14፤ 13፥12፤ 5፥27 2ቆሮ4፥14፤ ኤፌ1፥4

ቅዱስ መሞላት አለባቸው (ሐሥ 1፥5፤ 2፥4)፤ ይህም ሆኖ ለአምልኮ፣ ለአገልግሎትና ለምስክርነት በተደጋጋሚ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አለባቸው (ሐሥ 4፥31-33 እና ማብ ፤ 6፥3 እና ማብ ይመ)። (2) አማኞች በተደጋጋሚ በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን ተመክሮአቸው የሚያደርጉት የሚከተሉትን በመፈጸም ነው፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያላቸውን ሕያው የሆነ እምነት አጽንተው በመያዝ (ገላ 3፥5)፣ በሙላት የእግዚአብሔር ቃል ማደሪያ በመሆን (ቈላ 3፥16)፣ በመጸለይ፣ ምስጋና በማቅረብና ለጌታ በመዘመር (ቍ 19-20፤ 1ቆሮ 14፥15)፣ ሌሎችን በማገልገል (ቍ 21)፣ መንፈስ ቅዱስ የሚፈልገውን በመፈጸም (4፥30፤ ሮሜ 8፥1-14፤ ገላ 5፥16፤ 1ተሰ 5፥19)። (3) በመንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ ከሚታዩት ውጤቶች ውስጥ አንዳንዶቹ ከዚህ በታች ተጠቅሰዋል፤ (ሀ) በመዝሙር፣ በውዳሴና በመንፈሳዊ ዝማሬ ለእግዚአብሔር በሐሤት በመንገር (ቍ 19)፣ (ለ) ምስጋና ማቅረብ (ቍ 20)፣ እና (ሐ) አንዱ ለሌላው መገዛት (ቍ 21)።

**5፥19 ለጌታ ተቀኙ፤** በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ሆነ በግል የምንዘምረው መንፈሳዊ መዝሙር ሁሉ፣ የውዳሴ ወይም የምልጃ ጸሎት በመሆን ከሁሉ አስቀድሞ ለእግዚአብሔር መቅረብ አለበት (ከመዝ 40፥3፤ 77፥6 ጋር ያነጻጽሩ)። (1) የምስጋና መዝሙር ወይም ማንኛውም መንፈሳዊ መዝሙር የመንፈስ ቅዱስ ሀልዎት መግለጫ ሊሆን ይችላል (ቍ 18 እና ቀጥሎ ያሉትን፤ 1ቆሮ 14፥14 እና ቀጥሎ ያሉትን ማብ ይመ)። (2) መንፈሳዊ መዝሙር መዘመር የማነጫያ፣ የማስተማሪያ፣ ምስጋና የማቅረቢያና የመጸለያ መንገድ ነው (ቈላ 3፥16)። (3) ክርስቲያናዊ መዝሙር የደስታ መግለጫ ነው (ቍ 19)። (4) ዝማሬን የማቅረብ ወይም መንፈሳዊ መዝሙርን የመዘመር ዐላማ ለመዝናናት ወይም ግለሰብን ከፍ ከፍ ለማድረግ ሳይሆን፣ እግዚአብሔርን ለማምለክና ውዳሴን ለእርሱ ለማቅረብ ነው (ሮሜ 15፥9-11፤ ራእ 5፥9-10)።

**5፥21 አንዳችሁ ለአንዳችሁ ተገዙ፤** በክርስቶስ ሆኖ አንዱ ለአንዱ መገዛት አጠቃላይ መንፈሳዊ መርሕ ነው፤ ይህ መርሕ ከሁሉ አስቀድሞ ሥራ ላይ መዋል ያለበት በክርስቲያን ቤተ ሰብ ዘንድ ነው። ለሌላው መገዛት፣ ትሕትናን፣ ጨዋነትንና ትዕግሥትን ማሳየት እንዲሁም ተቻችሎ መኖር የእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ባሕርይ መሆን አለበት። ሚስት በቤተ ሰብ ውስጥ ባል ላለበት ኀላፊነት መገዛት አለባት (በፍቅር መገዛት ማለት ነው)፤ (የሚቀጥለውን ማብራሪያ ይመልከቱ)። ባል በፍቅርና ራስን በመስጠት መንፈስ ለሚስት ፍላጎት መገዛት አለበት (ቍ 23 እና ማብ ይመ)። ልጆች በመታዘዝ መንፈስ ለወላጆች ሥልጣን መገዛት አለባቸው (6፥1 እና ማብ ይመ)። ወላጆችም ለልጆቻቸው መሠረታዊ ፍላጎት መገዛት አለባቸው፤ በጌታ ትምህርትም ልጆቻቸውን ኰትኵተው ማሳደግ ይኖርባቸዋል (6፥4 እና ማብ ይመ)።

**5፥22 ሚስቶች ሆይ፤ ... ተገዙ፤** ለአንዲት ሚስት ከእግዚአብሔር የተሰጣት ተግባር ለባሏ ረዳት እንድትሆንና ለእርሱም እንድትገዛ ነው (ቍ 22-24)፤ ለባሏ ማሳየት ያለባት ተግባርም የሚከተሉትን ያካትታል፤ ፍቅርን (ቲቶ 2፥4)፣ አክብሮትን (ቍ 33፤ 1ጴጥ 3፥1-2)፣ ረዳት መሆንን (ዘፍ 2፥18)፣ ንጹሕ የሆነ አኗኗርን (ቲቶ 2፥5፤ 1ጴጥ 3፥2)፣ ተገዥነትን (ቍ 22፤ 1ጴጥ 3፥5)፣ የጨዋነትንና የቍምትነትን መንፈስ ማሳደግን (1ጴጥ 3፥4)፣ መልካም እናትነትንና (ቲቶ 3፥4) ጥሩ የቤት አያያዝን (1ጢሞ 2፥15፤ 5፥14፤ ቲቶ 2፥5)። አንዲት ሴት ለባሏ መገዛት፣ ለኢየሱስ እንደምትገዛ ማለትም፣ “ለጌታ እንደምትገዛ” ተብሎ በተጻፈው መሠረት ለመገዛቷ እንደ አንድ ምልክት ሆኖ በእግዚአብሔር ዘንድ ይቈጠርላታል (ገላ 3፥28 እና ማብ፤ 1ጢሞ 2፥13፡15 እና ማብራሪያዎቹን፤ ቲቶ 2፥4 እና ማብ ይመ)።

**5፥23 ባልም ... ራስ፤** እግዚአብሔር ቤተ ሰብን በኅብረተሰብ ውስጥ መሠረታዊ አሐድ አድርጎ አቁሞታል፤ እያንዳንዱ ቤተ ሰብ መሪ እንዲኖረው ያስፈልጋል፤ ስለዚህ እግዚአብሔር የሚስትና የቤተ ሰብ ራስ እንዲሆን ለባል ኀላፊነትን ሰጥቶታል (ቍ 23-33፤ 6፥4)። ባል ለሚስቱና ለቤተ ሰቡ ያለውን የበላይነት በፍቅር፣ በጨዋነትና በማስተዋል ተግባራዊ ማድረግ አለበት (ቍ 25-30፤ 6፥4)። የሚስት ራስ ይሆን ዘንድ ከእግዚአብሔር ሥልጣን የተሰጠው ባል ኀላፊነት የሚከተሉትን ያካትታል፤ (1) ለቤተ ሰቡ የሚጠቅመው መንፈሳዊና ሥጋዊ ፍላጎት ጠቃሚ የሆነውን ነገር ዝግጁ ማድረግ (ቍ 23-24፤ ዘፍ 3፥16-19፤ 1ጢሞ 5፥8)። (2) ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሁሉ ለሚስት ደኅንነት የሚሆነውን ፍቅር፣ ጥበቃና እንክብካቤ መለገስን (ቍ 25-33)፤ (3) እርሷን ማክበርን፣ ከእርሷ ጋር መግባባትን፣ እርሷን ማድነቅንና ስለ እርሷ መጨነቅን (ቈላ 3፥19፤ 1ጴጥ 3፥7)፤ (4) እግዚአብሔር ለፈቀደው የጋብቻ ጥምረት ፈጽሞ ታማኝ መሆንን (ቍ 31፤ ማቴ 5፥27-28)።

28ባሎችም እንደዚሁ ሚስቶቻቸውን እንደ
ገዛ ሥጋቸው መውደድ ይገባቸዋል።
ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል።
29የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ማንም የለም፤
ይመግበዋል፤ ይንከባከበዋል፤ ክርስቶስም
ለቤተ ክርስቲያን ያደረገው ልክ እንደዚሁ
ነው፤ 30እኛ የክርስቶስ አካል ብልቶች ነንና።
31"ስለዚህም ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፤
ከሚስቱም ጋር አንድ ይሆናል፤ ሁለቱም
አንድ ሥጋ ይሆ ናሉ"። 32ይህ ጥልቅ ምስጢር
ነው፤ እኔም ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ
ክርስቲያን እናገራለሁ። 33ሆኖም ከእናንተ
እያንዳንዱ ሚስቱን እንደ ራሱ አድርጎ
ይውደድ፤ ሚስትም ባሏን ታክብር።

## ወላጆችና ልጆች

6 ልጆች ሆይ፤ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፤
ይህ ተገቢ ነውና። 2"አባትህንና እናትህን
አክብር" በሚለው ቀዳሚ ትእዛዝ ውስጥ ያለው
ተስፋ፣ 3"መልካም እንዲሆንልህ፣ ዕድሜህም
በምድር ላይ እንዲረዝም" የሚል ነው።
4አባቶች ሆይ፤ እናንተም ልጆቻችሁን
አታስቈጧቸው፤ ነገር ግን በጌታ ምክርና
ተግሣጽ አሳድጓቸው።

5፥28 ቊ25
5፥30 ሮሜ12፥5፤ 1ቆሮ12፥27
5፥31 ዘፍ2፥24፤ ማቴ19፥5፤ 1ቆሮ6፥16
5፥33 ቊ25
6፥1 ምሳ6፥20፤ ቈላ3፥20
6፥3 ዘፀ20፥12፤ ዘዳ5፥16
6፥4 ዘፍ18፥19፤ ዘዳ6፥7፤ ምሳ13፥24፤ 22፥6፤ ቈላ3፥21
6፥5 ኤፌ5፥22፤ ቈላ3፥22፤ 1ጢሞ6፥1፤ ቲቶ2፥9፤ 1ጴጥ2፥18
6፥6 ሮሜ6፥22
6፥7 ቈላ3፥23
6፥8 ማቴ16፥27፤ ቈላ3፥24
6፥9 ኢዮ31፥13፡14፤ ሐሥ10፥34
6፥10 2ሳሙ10፥12፤ መዝ27፥14፤

## ጌቶችና ባሪያዎች

5ባሪያዎች ሆይ፤ ለክርስቶስ እንደምት
ታዘዙ፣ በምድር ጌቶቻችሁ ለሆኑት
በአክብሮትና በፍርሀት፣ በልብ ቅንነትም
ታዘዙ፤ 6ሊታይታና ከእነርሱ ሙገሳን
ለማግኘት ሳይሆን እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች
የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከልብ በመፈጸም
ታዘዟቸው። 7ሰውን ሳይሆን ጌታን
እንደምታገለግሉ ሆናችሁ በሙሉ ልብ
አገልግሉ፤ 8ምክንያቱም፣ ባሪያም ሆነ ነጻ
ሰው ለሚያደርገው በጎ ነገር ሁሉ ሽልማቱን
ከጌታ እንደሚቀበል ታውቃላችሁ።
9እናንተም ጌቶች ሆይ፤ ለባሮቻችሁ
እንዲሁ አድርጉላቸው፤ የእነርሱም፣
የእናንተም ጌታ የሆነው በሰማይ እንዳለ፣
የሰውንም ፊት አይቶ እንደማያደላ
ታውቃላችሁና አታስፈራሯቸው።

## የእግዚአብሔር ጦር ዕቃ

10በተረፈ በጌታና ብርቱ በሆነው ኀይሉ
ጠንከሩ። 11የዲያብሎስን የተንኰል ሥራ
መቋቋም ትችሉ ዘንድ፣ የእግዚአብሔርን

6፥10 ሐጌ2፥4፤ 1ቆሮ16፥13፤ ኤፌ1፥19፤ 2ጢሞ2፥1
6፥11 ቊ13፤ ሮሜ13፥12፤ 1ተሰ5፥8

**6፥1 ልጆች ሆይ፤ ... ታዘዙ፤** በመሠረቱ የአማኞች ልጆች የራሳቸውን ቤተ ሰብ እስከሚመሠርቱ ድረስ በወላጆች መሪነት ሥር መሆን አለባቸው፤ (1) ትናንሽ ልጆች በጌታ ቃልና ትምህርት ኰትኵተው በማደግ፣ ለወላጆቻቸው እንዲታዘዙና ወላጆቻቸውን እንዲያከብሩ መመሪያ ይሰጣቸው ዘንድ ያስፈልጋል (ምሳ 13፥24 እና ማብ፤ 22፥6 እና ማብ፤ ቀጥሎ ያለውን ማብ ይመ)፡፡ (2) ትላልቅ ልጆች ትዳር ከያዙ በኋላ እንኳ የወላጆቻቸውን ምክር መከተል አለባቸው (ቍ 2)፤ እንክብካቤ በማድረግና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ገንዘብ በመስጠት በሽምግልና ዘመናቸው ወላጆቻቸውን ማክበር አለባቸው (ማቴ 15፥1-6)፡፡ (3) ወላጆቻቸውን የሚያከብሩ ልጆችን እግዚአብሔር በዚህ ምድር ላይና በዘላለም ሕይወት ላይ ይባርካቸዋል (ቍ 3)፡፡

**6፥4 አባቶች ሆይ፤ ... ልጆቻችሁን፤** ወላጆች ልጆቻቸውን እንዴት ማሳደግ እንዳለባቸውና ኀላፊነታቸው የቱን ያህል እንደ ሆነ በሰፊው ተብራርቶ የሚገኘውን ክፍል ለማስተዋል፣ በገጽ 1894 ላይ፣ *«ወላጆችና ልጆች»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ፡፡

**6፥11 የዲያብሎስን የተንኰል ሥራ መቋቋም፤** ክርስቲያኖች ከክፋው ጋር መንፈሳዊ ጦርነት ገጥመው ይገኛሉ፤ ይህ መንፈሳዊ ፍልሚያ የእምነት ጦርነት ተብሎ ተገልጿል (2ቆሮ 10፥4፤ 1ጢሞ 1፥18-19፤ 6፥12)፤ ወደሚመጣው ሰማያዊ ሕይወት እስከሚገቡ ድረስ ይህ ጦርነት ይቀጥላል (2ጢሞ 4፥7-8 ይመ፤ ገላ 5፥17 እና ማብ ይመ)፡፡ (1) የአማኙ ድል አድራጊነት በክርስቶስ የመስቀል ሞት በራሱ በክርስቶስ እውን ሆኖለታል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሰይጣንን ድል አደረገ፤ የክፉ ኀይላትንና ሥልጣናትን ያለ የሌለ መሣሪያ ገፈፈ (ቈላ 2፥15 ይመ፤ ከማቴ 12፥29፤ ከሉቃ 10፥18፤ ከዮሐ 12፥31 ጋር ያነጻጽሩ)፤ በዚሁ በመስቀል ሞቱም ምርኮን ማረከ (4፥8)፤ አማኙንም የሆነውንም ከሰይጣን ኀይል ታደገው (1፥7፤ ሐሥ 26፥18፤ ሮሜ 3፥24፤ ቈላ 1፥13-14)፡፡

(2) በአሁኑ ጊዜ ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ በሚያካሂዱ መንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ ቆጠምደው ይገኛሉ (ሮሜ 8፥13)፤ የተጠመዱበትም ጦርነት የሚከተለው ነው፤ (ሀ) በራሳቸው ውስጥ ከሚገኘው ኀጢአታዊ ፍላጎት ጋር (1ጴጥ 2፥11፤ ገላ 5፥17 እና ማብ)፤ (ለ) ፈሪሀ እግዚአብሔር ከሌለበት የዚህ ዓለም ከሆነው ደስታና ከማንኛውም ዐይነት ፈተና ጋር (ማቴ 13፥22፤ ገላ 1፥4፤ ያዕ 1፥14-15፤ 1ዮሐ 2፥16)፤ (ሐ) ከሰይጣንና ከኀይላቱ ጋር (ቀጥሎ ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ)፡፡ አማኞች የዓለምን ክፋት በመጥላት (ዕብ 1፥9 ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 2022 ላይ፣ *«ክርስቲያን ከዓለም ጋር ያለው ግንኙነት»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፣ ፈተናውን በማለፍና ለፈተናው ልብን ባለመስጠት (ገላ 6፥14፤ 1ዮሐ 5፥4)፣ የራሱ የዓለም የሆነውን ኀጢአትንም በይፋ በመቃወም (ዮሐ 7፥7) ከአሁኑ የዓለም ሥርዐት ራሳቸውን ይለዩ ዘንድ ተጠርተዋል (በገጽ 1826 ላይ፣ *«የአማኞች መለየት»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፡፡

(3) የክርስቲያን ወታደሮች ማንኛውንም ዐይነት ክፋት መዋጋት ያለባቸው በራሳቸው ኀይል ሳይሆን (2ቆሮ 10፥3)፣ በመንፈሳዊ ጦር መሣሪያ ነው (ቍ 10-18 ይመ፤ ከ2ቆሮ 10፥4-5 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡

(4) ክርስቲያኖች ከእምነታቸው የተነሣ ጦርነት ውስጥ ሲገቡ ብርቱ የክርስቶስ ወታደር በመሆን የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ተጠርተዋል፤ መከራን እንዲቋቋሙ (2ጢሞ 2፥3)፣ ስለ ወንጌል መከራ እንዲቀበሉ (ማቴ 5፥10-12፤ ሮሜ 8፥17፤ 2ቆሮ 11፥23፤ 2ጢሞ 1፥8)፣ በጎውን የእምነት ጦርነት እንዲዋጉ (1ጢሞ 6፥12፤ 2ጢሞ 4፥7)፣ ጦርነት እንዲገጥሙ (2ቆሮ 10፥3)፣ እንዲጸኑ (ቍ 18)፣ እንዲያሸንፉ (ሮሜ 8፥37)፣ ድል አድራጊዎች እንዲሆኑ (1ቆሮ 15፥57)፣ እንዲያሸንፉ (2ቆሮ 2፥14)፣ ወንጌልን ከጠላት ኀይል እንዲከላከሉ (ፊል 1፥16)፣ ስለ እምነት እንዲጋደሉ (ፊል 1፥27፤

ሙሉ የጦር ዕቃ ልበሱ። [12]ምክንያቱም ተጋድሎአችን ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን ከዚህ ከጨለማ ዓለም ገዦች፣ ከሥልጣናትና ከኀይላት እንዲሁም በሰማያዊ ስፍራ ካሉ ክርኩሳን መናፍስት ሰራዊት ጋር ነው። [13]ክፉው ቀን ሲመጣ መቋቋም ትችሉ ዘንድ የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር ዕቃ ልበሱ፤ ሁሉን ከፈጸማችሁ በኋላ ጸንታችሁ መቆም ትችላላችሁና። [14]እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ዝናር ታጥቃችሁ፣ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፣ [15]በሰላም ወንጌል ዝግጁነት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ። [16]ከእነዚህም ሁሉ ጋር፣ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፤ [17]የመዳንን ራስ ቍር አድርጉ፤ የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፤ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው። [18]በሁሉ ዐይነት ጸሎትና ልመና፣ በማንኛውም ሁኔታ በመንፈስ ጸልዩ፤ ይህንም በማሰብ ንቁ፤ ስለ ቅዱሳንም ሁሉ በትጋት ልመና አቅርቡ።

[19]የወንጌልን ምስጢር ለመግለጥ አፌን በምከፍትበት ጊዜ ሁሉ በድፍረት እንድናገር ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ጸልዩልኝ። [20]በሰንሰለት የታሰረ መልእክተኛ የሆንሁት ለዚሁ ነውና። ስለዚህ መናገር የሚገባኝን ያለ ፍርሀት እንድናገር ጸልዩልኝ።

## የመጨረሻ ሰላምታ

[21]በምን ሁኔታ እንዳለሁና ምን እንደማደርግ ታውቁ ዘንድ ተወዳጅ ወንድምና በጌታ ታማኝ አገልጋይ የሆነው ቲኪቆስ ሁሉንም ነገር ይነግራችኋል። [22]የእኛን ሁኔታ እንድ ታውቁና ልባችሁን እንዲያበረታ ለዚሁ ስል ወደ እናንተ ልኬዋለሁ።

[23]ከእግዚአብሔር አብ፣ ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ሰላም፣ ፍቅርም ከእምነት ጋር ለወንድሞች ይሁን። [24]ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን በማይጠፋ ፍቅር ለሚወዱ ሁሉ ጸጋ ይሁን።

6፥12 ሮሜ8፥38፤ 1ቆሮ15፥50፤ ኤፌ1፥3፡21፤ 3፥10፤ ዕብ2፥14
6፥13 ቍ11፤ 2ቆሮ6፥7
6፥14 መዝ132፥9፤ ኢሳ11፥5፤ 59፥17፤ 1ተሰ5፥8
6፥15 ኢሳ52፥7፤ ሮሜ 10፥15
6፥16 ማቴ5፥37፤ 1ዮሐ5፥4
6፥17 ኢሳ49፥2፤ 59፥17፤ ዕብ4፥12
6፥18 ማቴ26፥41፤ ሉቃ18፥1፤ ሐሥ1፥14፤ ሮሜ8፥26፡27፤ ፊል 1፥4፤ 4፥6፤ ቈላ1፥3
6፥19 ሐሥ4፥29፤ ሮሜ16፥25፤ 1ተሰ5፥25
6፥20 ሐሥ21፥33፤ 2ቆሮ5፥20
6፥21 ሐሥ20፥4
6፥22 ቈላ2፥2፤ 4፥7-9
6፥23 ገላ6፥16፤ 2ተሰ3፥16፤ 1ጴጥ5፥14

ይሁ 1፥3)፣ በጠላትም ኀይል እንዳይሸበሩ (ፊል 1፥28)፣ የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር ዕቃ እንዲለብሱ፣ በጽናትም እንዲቆሙ (ቍ 14)፣ የሰይጣንን ምሽግ እንዲደመስሱ (2ቆሮ 10፥4)፣ ማንኛውንም ሐሳብ ከንቱ እንዲያደርጉ (2ቆሮ 10፥5)፣ እና በጦርነት የእምነት አርበኞች እንዲሆኑ ተጠርተዋል (ዕብ 11፥34)።

**6፥12 ክርኩሳን ... ሰራዊት፤** ክርስቲያኖች ከሰይጣንና ክርኩሳን መናፍስት ሰራዊት ጋር መንፈሳዊ ውጊያ ምንጊዜም እንደ ገጠሙ ነው (ስለ ሰይጣን የተገለጸውን፣ ማቴ 4፥10 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1499 ላይ፣ *«በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። (1) እነዚህ የጨለማ ኀይላት ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌላቸውን የሚያበረታቱ (2፥2)፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚቃወሙ (ዘፍ 3፥1-7፤ ዳን 10፥12-13፤ ማቴ 13፥38-39)፣ እንዲሁም ብዙውን ጊዜ የአሁኑን ዘመን አማኞች የሚወጉ (1ጴጥ 5፥8) የክፉ መንፈሳዊ ኀይላት አካላት ናቸው (ዮሐ 12፥31፤ 14፥30፤ 16፥11፤ 2ቆሮ 4፥4፤ 1ዮሐ 5፥19)። (2) እነዚህ ኀይላት አያሌ ቍጥር ያላቸው ናቸው (ራእ 12፥4፡7)፤ የክፉው ግዛት አካል ሆነውም በሥልጣን ተዋረድ በከፍተኛ ደረጃ ተደራጅተው ይገኛሉ (2፥2፤ ዮሐ 14፥30)።

**6፥17 የመንፈስንም ሰይፍ፤** «የመንፈስንም ሰይፍ» አማኙ ከክፉ ኀይል ጋር በሚያደርገው ጦርነት የሚጠቀምበት የማጥቂያ መሣሪያ ነው። በዚህ ሰይፍ፣ «ይኸውም በእግዚአብሔር ቃል» ላይ ክርስቲያን ያለውን መታመን ዋጋ ለማሳጣት ወይም ለማጥፋት ሰይጣን የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል። ቤተ ክርስቲያን በትምህርቷ ሁሉ እስትንፋሰ እግዚአብሔር ያለባቸውን ቅዱሳት መጻሕፍት፣ የእግዚአብሔር ቃል አይደሉም ከሚለው ከንቱ ሐሳብ መከላከል አለባት። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና ሐዋርያት እስትንፋሰ እግዚአብሔር ላለው ለእግዚአብሔር ቃል ያሳዩትን ታማኝነት መቀው ማለት፣ ቃሉ ለመገሠጽ ወይም ለማስተካከል፣ ለመቤዠት፣ ለመፈወስ፣ አጋንንትን ለማስወጣትና ክፋትን ሁሉ ለማሸነፍ ያለውን ኀይል ማሳጣት ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ (ቅዱሳት መጻሕፍት) ለሚሰጠው ትምህርት ሁሉ ፍጹም ትክክል መሆኑን መካድ ማለት ራሳችንን ለሰይጣን ክንድ አሳልፈን መስጠት ማለት ነው (ከ2ጴጥ 1፥21 እና ማብ፤ ከማቴ 4፥1-11 ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም በገጽ 1941 ላይ፣ *«መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ መሆኑና ያለው ሥልጣን»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**6፥18 በመንፈስ ጸልዩ፤** ክርስቲያን ከመንፈሳዊ ኀይላት ጋር የሚያደርገው ጦርነት ብርቱ ጸሎት መደረግ እንዳለበት ያሳስባል፤ ይኸውም፣ «በመንፈስ ቅዱስ ኀይል መጸለይ»፣ «በማንኛውም ጊዜ መጸለይ»፣ «በማንኛውም ዐይነት ጸሎት»፣ «ለቅዱሳን ሁሉ መጸለይ»፣ «ሁልጊዜ ጸልዩ» የሚል ዐደራና አጽንዖት ተሰጥቶት ይገኛል። ጸሎት የእውነተኛው ጦርነት አካል ሆኖ መቈጠር አለበት እንጂ ለራሳችንም ሆነ ለሌሎች ድል በተገኘልን ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር አብረን በመሥራት ላይ ሳለን፣ እንደ አንድ ሌላ የጦር መሣሪያ ተደርጎ መታየት የለበትም። በማንኛውም ሁኔታና በማንኛውም ዐይነት ጸሎት በትጋት አለመጸለይ ማለት ለጠላት ድል ተመቻችቶ መገኘት ማለት ነው (ሉቃ 18፥1፤ ሮሜ 12፥12፤ ፊል 4፥6፤ ቈላ 4፥2፤ 1ተሰ 5፥17)።

# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች

*አስተዋፅኦ*

*መግቢያ* (1፥1-11)
- (ሀ) ክርስቲያናዊ ሰላምታ (1፥1-2)
- (ለ) ስለ ፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች የቀረበ ምስጋናና ጸሎት (1፥3-11)

I. ጳውሎስ አሁን ያለበት ሁኔታ (1፥12-26)
- (ሀ) በጳውሎስ እስራት የተነሣ ወንጌል መስፋፋቱ (1፥12-14)
- (ለ) በማንኛውም መንገድ (በዚህም ሆነ በዚያ) ክርስቶስ መሰበኩ (1፥15-18)
- (ሐ) ጳውሎስ ለመኖርም ሆነ ለመሞት ዝግጁ መሆኑ (1፥19-26)

II. ቤተ ክርስቲያኒቷ ትኩረት ልታደርግባቸው የሚገቡ ጉዳዮች (1፥27—4፥9)
- (ሀ) ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች የሰጠው ምክር (1፥27—2፥18)
  1. ጸንተው እንዲቆሙ (1፥27-30)
  2. በመካከላቸው ኅብረትና አንድነት እንዲኖር (2፥1-2)
  3. በትሕትናና በአገልጋይነት መንፈስ እንዲመላለስ (2፥3-11)
  4. የሚታዘዙና ነቀፋ የሌለባቸው እንዲሆኑ (2፥12-18)
- (ለ) ወደ ቤተ ክርስቲያኒቷ የሚመጡ የጳውሎስ መልእክተኞች (2፥19-30)
  1. ጢሞቴዎስ (2፥19-24)
  2. አፍሮዲጡ (2፥25-30)
- (ሐ) የሐሰት ትምህርትን በሚመለከት ጳውሎስ የሰጠው ማስጠንቀቂያ (3፥1-21)
  1. ሐሰተኛ መገረዝ ከእውነተኛ መገረዝ ጋር መነጻጸሩ (3፥1-16)
  2. ምድራዊ አስተሳሰብ ከመንፈሳዊ አስተሳሰብ ጋር ሲነጻጸር (3፥17-21)
- (መ) የጳውሎስ ማጠቃለያ ምክር (4፥1-9)
  1. ጽናትና አንድ ልብ እንዲኖራቸው (4፥1-3)
  2. ደስ እንዲላቸውና ገሮች እንዲሆኑ (4፥4-5)
  3. ስለ ማንኛውም ነገር እንዳይጨነቁ (4፥6-7)
  4. ሐሳባቸውንና ፈቃዳቸውን እንዲቈጣጠሩ (4፥8-9)

*መደምደሚያ*፤ (4፥10-23)
- (ሀ) ጳውሎስ ለተደረገለት ችሮታ ያቀረበው ምስጋና (4፥10-20)
- (ለ) የስንብት ሰላምታና ጸሎተ ቡራኬ (4፥21-23)

**ጸሓፊው፤** *ጳውሎስ*

**ዋና ሐሳብ፤** *ለክርስቶስ በመኖር የሚገኝ ታላቅ ደስታ*

**የተጻፈበት ጊዜ፤** *በ62/63 ሳይሆን አይቀርም*

*ታሪካዊ ዳራ*

የፊልጵስዩስ ከተማ ከኤጂያን ባሕር 16 ኪሎ ሜትር ገባ ብሎ በምሥራቅ መቄዶንያ የምትገኝ ሲሆን፣ የምትጠራውም በታላቁ እስክንድር አባት በመቄዶንያ ንጉሥ በዳግማዊ ፊልጶስ ስም ነበር። ጳውሎስ በነበረበት ዘመን ፊልጵስዩስ የታወቀችና ወታደር የሰፈረባት የሮማ ከተማ ነበረች።

የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በጳውሎስና አብረው ያገለግሉ የነበሩት ሲላስ፣ ጢሞቴዎስና ሉቃስ በሚገኙበት ቡድን ሲሆን፣ ይህም እግዚአብሔር በጢሮአዳ ለሰጠው ራእይ ምላሽ ለመስጠት፣ ጳውሎስ ሁለተኛውን ሚሲዮናዊ ጉዞ ባደረገበት ወቅት ነው (ሐሥ 16፥9-40)። በሐዋርያው ጳውሎስና በፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን መካከል ጠንካራ ወዳጅነት ተፈጠረ። ብዙ ጊዜ ቤተ ክርስቲያኗ ለጳውሎስ የገንዘብ ርዳታ አድርጋለች (2ቆሮ 11፥9፤ ፊል 4፥15-16)፤ በኢየሩሳሌም ያሉትን ችግረኞች ለመርዳት ገንዘብ በሚያሰባስብበትም ጊዜ፣ ይህች ቤተ ክርስቲያን በታላቅ ልግስና እጅዋን ዘርግታለች (ከ2ቆሮ 8—9 ጋር ያነጻጽሩ)። በሦስተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞው ወቅት ሐዋርያው ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያኗ ሁለት ጊዜ የጐበኘ ይመስላል (ሐሥ 20፥1፡3፡6)።

## ዐላማ

ጳውሎስ በሮም እስር ቤት በነበረበት ጊዜ (1፥7፡13-14)፣ ይህን መልእክት ለፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች የጻፈው፣ በቅርቡ በአፍሮዲጡ በኩል ለላኩለት የልግስና ስጦታ እነርሱን ለማመስገንና (4፥14-19) አሁን ያለበትን ሁኔታ ሊያሳውቃቸው ሳይሆን አይቀርም። በተጨማሪም ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው፣ በእስራቱ ሁሉ የእግዚአብሔር ዐላማ እንደሚፈጸም ለቤተ ክርስቲያኒቱ ምእመናን ለማረጋገጥ (1፥12-30)፣ መልእክታቸውን ይዞ ወደ እርሱ የመጣው አፍሮዲጡ በታማኝነት ኀላፊነቱን እንደ ተወጣና ወደ እነርሱ የተመለሰውም በቂ ጊዜ ቈይቶ እንደ ሆነ ለቤተ ክርስቲያኗ እንደ ገና ለማረጋገጥ (2፥25-30) እንዲሁም በአንድነት፣ በትሕትና፣ በኅብረትና በሰላም በመኖር ጌታን በሚገባ ለማወቅ ይተጉ ዘንድ እነርሱን ለማበረታታት ነው።

## ቅኝት

ከብዙዎች የጳውሎስ መልእክቶች በተለየ ሁኔታ "ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች" የተላከው መልእክት የተጻፈው፣ በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ ችግር ወይም ግጭት ተፈጥሮ አይደለም፤ የተጻፈበት መሠረታዊ ምክንያት ለቤተ ክርስቲያኒቱ ምእመናን ልባዊ የሆነ ፍቅርን ለመግለጽ፣ ሰላምታም ለማቅረብ ነው። ከሰላምታ አንሥቶ (1፥1) እስከ ጸሎተ ቡራኬ ድረስ (4፥23) መልእክቱ የሚያተኵረው፣ የክርስቲያን የመኖር ዐላማና የዘላለም ሕይወት ተስፋ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን በመግለጽ ላይ ነው።

በዚህ መልእክት ውስጥ ጳውሎስ በፊልጵስዩስ አማኞች ዘንድ ሦስት መለስተኛ ችግሮች እንደ ነበሩ ይጠቅሳል፤ (1) የእስራቱ ጊዜ እየተራዘመ በመሄዱ፣ የሚሰማቸውን የተስፋ መቍረጥ ስሜት (1፥12-26)፤ (2) ለአንድነት ጠንቅ ሊሆን የሚችለውን በቤተ ክርስቲያኒቷ ውስጥ ባሉ ሁለት ሴቶች መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት (4፥2 ይመ፤ ከ2፥2-4 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (3) የአይሁድ እምነት ቅሬታ ካላቸው ክርስቲያኖችና ምድራዊ አስተሳሰብ ካላቸው (ምዕ 3) ሰዎች የተነሣ፣ ታማኝነት በሚጐድላት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ጊዜም ቢሆን ሥጋትና ፍርሀት መኖሩ። ወደ ፊት የጐላ ችግር ሊሆኑ ከሚችሉ ከእነዚህ ሦስት ጕዳዮች ጐን፣ ቀጥሎ ባሉት ሐሳቦች ላይ የተሰጠውን የጳውሎስ የዳበረ ትምህርት እናገኛለን፤ (1) በማንኛውም የሕይወት ውጣ ውረድ ውስጥ ብንሆን ሁልጊዜ በጌታ ደስ ስለ መሰኘት (ለምሳሌ 1፥4፡12፤ 2፥17-18፤ 4፥4፡11-13)፤ (2) ስለ ክርስቲያናዊ ትሕትናና አገልግሎት (2፥1-18)፤ (3) ክርስቶስን ማወቅ ከሁሉም የሚበልጥ ጥቅም ያለው ስለ መሆኑ (ምዕ 3)።

## ልዩ ገጽታ

ይህን መልእክት አምስት ዋና ዋና ገጽታዎች ልዩ ያደርጉታል፤ (1) ጳውሎስ ከፊልጵስዩስ አማኞች ጋር ያለውን የቀረበ ግንኙነት የሚያሳይ፣ በግል ሁኔታ ላይ ያተኰረ ተወዳጅ መልእክት ነው፣ (2) በከፍተኛ ደረጃ ክርስቶስን ማእከል ያደረገና ጳውሎስ ከክርስቶስ ጋር ያለውን የቀረበ ግንኙነት የሚያሳይ ነው (ለምሳሌ 1፥21፣ 3፥7-14)፣ (3) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የአስተምህሮተ ክርስቶስ ምጡቅ ሐሳቦች የሚገኙበት መልእክት ነው (2፥5-11)፣ (4) በዋነኛነት የአዲስ ኪዳን "የደስታ መልእክት" ተብሎ የሚጠራ መልእክት ነው፤ (5) መልእክቱ በክርስትና ሕይወት ውስጥ እጅግ ከፍተኛ የሆነውን የብቃት ደረጃ የሚገልጽ ሲሆን፣ ይህም በትሕትና መመላለስንና፣ ራስን ባሪያ ማድረግን (2፥1-8)፣ ወደ ግቡ ለመድረስ በታማኝነት ወደ ፊት መገሥገሥን (3፥13-14)፣ ሁልጊዜ በጌታ ደስ መሰኘትን (4፥4)፣ ስለ ማንኛውም ነገር አለመጨነቅን (4፥6)፣ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ያለኝ ይበቃኛል ማለትን (4፥11)፣ በሚያስችለው በክርስቶስ ጸጋ ሁሉን ማድረግ መቻልን (4፥13) ይጨምራል።

## የፊልጵስዩስ መልእክትን ማንበብ

ሙሉውን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ የፊልጵስዩስ መልእክት ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በአምስት ቀን መነበብ ይኖርበታል፡

❑ 1 ❑ 2፥1-18 ❑ 2፥19—3፥11 ❑ 3፥12—4፥3 ❑ 4፥4-23

*ማስታወሻ*

1 የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋዮች የሆኑ
ጳውሎ ስና ጢሞቴዎስ፤ ከቤተ
ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶሳትና[a] ከዲያቆናት
ጋር በፊልጵስዩስ ላሉ በክርስቶስ ኢየሱስ
ቅዱሳን ለሆኑ ሁሉ፤
2ከእግዚአብሔር ከአባታችን፣ ከጌታም
ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ
ይሁን።

## ምስጋናና ጸሎት

3እናንተን ባስታወስሁ ቍጥር
አምላኬን አመሰግናለሁ። 4ዘወትር ስለ
ሁላችሁ ስጸልይ፣ በደስታ እጸልያለሁ፤
5ከመጀመሪያው ቀን አንሥቶ እስካሁን ድረስ
በወንጌል አገልግሎት ተካፋይ ሆናችኋልና።
6በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው
እርሱ እስከ ክርስቶስ ኢየሱስ ቀን ድረስ
ከፍጻሜው እንደሚያደርሰው ርግጠኛ ነኝ።
7በልቤ ስላላችሁ፣ ስለ ሁላችሁ እንዲህ
ማሰቤ ተገቢ ነው፤ በእስራቴም ሆነ ለወንጌል
ስመክትና ሳጸናው ሁላችሁም ከእኔ ጋር
የእግዚአብሔር ጸጋ ተካፋዮች ናችሁና።
8በክርስቶስ ኢየሱስ ፍቅር ሁላችሁንም ምን
ያህል እንደምናፍቃችሁ እግዚአብሔር ምስክሬ
ነው።
9ፍቅራችሁ በጥልቅ እውቀትና
በማስተዋል ሁሉ በዝቶ እንዲትረፈረፍ
እጸልያለሁ። 10ይኸውም ከሁሉ የሚሻለውን
ለይታችሁ እንድታውቁ፣ እስከ ክርስቶስም
ቀን ድረስ ንጹሓንና ነቀፋ የሌለባችሁ
እንድትሆኑ፣ 11ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና
በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሚገኘው የጽድቅ
ፍሬ እንድትሞሉ ነው።

## በጳውሎስ እስራት ወንጌል መስፋፋቱ

12አሁንም ወንድሞች ሆይ፤ በእኔ ላይ
የደረሰው ነገር ወንጌል በይበልጥ እንዲስፋፋ
መርዳቱን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ። 13ከዚህ
የተነሣ እስራቴ ስለ ክርስቶስ እንደ ሆነ፣

1፥1 ሐሥ9፥13፤ 16፥1፡12፤ 2ቆሮ1፥1፤ 1ጢሞ3፥1፡8
1፥2 ሮሜ1፥7
1፥3 ሮሜ1፥8
1፥4 ሮሜ1፥10
1፥5 ሐሥ2፥42፤ 16፡12-40፤ ፊል4፥15
1፥6 ቆላ10፤ መዝ138፥8፤ 1ቆሮ1፥8
1፥7 ቆላ13፡14፡16፡17፤ ሐሥ21፥33፤ 2ቆሮ7፥3፤ 2ጴጥ1፥13
1፥8 ሮሜ1፥9
1፥9 ኤፌ1፥17፤ 1ተሰ3፥12
1፥10 ቆላ6፤ 1ቆሮ1፥8
1፥11 ያዕ3፥18
1፥13 ቆላ7፡14፡17፤ ሐሥ21፥33

[a] *1፥1 ወይም ተመልካች ቿባቂዎች*

**1፥4 በደስታ፤** ደስታ በክርስቶስ ላገኘነው ድነት ዋና አካል ነው። ይህ ደስታ ከእግዚአብሔር አብ፣ ከእግዚአብሔር ወልድና ከእግዚአብሔር *መንፈስ ቅዱስ* ጋር ካለን ኅብረት፣ ከእነርሱም ጋር ካለን ግንኙነት የተነሣ ወደ እኛ በሚፈሰው በረከት ምክንያት እውን የሚሆን ውስጣዊ ሰላምና ሐሤት ነው (ከ2ቆሮ 13፥14 ጋር *ያነጻጽሩ*)። ስለ ደስታ የሚናገረው *መጽሐፍ ቅዱሳዊ* ትምህርት የሚከተለውን *ያካትታል*፦ (1) ደስታ እግዚአብሔር በክርስቶስ አማካይነት ለሰው ከሚሰጠው ድነትና (1ጴጥ 1፥3-6 *ይመ*፤ ከመዝ 5፥11፤ 9፥2፤ ከኢሳ 35፥10 ጋር *ያነጻጽሩ*) ከእግዚአብሔር ቃል ጋር (ኤር 15፥16 *ይመ*፤ ከመዝ 119፥14 ጋር *ያነጻጽሩ*) ግንኙነት አለው።

(2) ደስታ፣ ከመንፈስ ፍሬ አንዱ በመሆን ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ነው (መዝ 16፥11፤ ሮሜ 15፥13፤ ገላ 5፥22)፤ ይህም ወዲያው የሚመጣ ሳይሆን፣ ከክርስቶስ ጋር ግንኙነትን *መሥርቶ በመቈየት* የሚገኝ ነው (ዮሐ 15፥1-11)። *መንፈስ ቅዱስ* የእግዚአብሔርን ህልዎትና ቅርቡነት በሕይወታችን ውስጥ በጥልቀት እንዲሰማን ሲያደርግ፣ ደስታችን እጅግ የላቀ ይሆናል (ከዮሐ 14፥15-21 ጋር *ያነጻጽሩ*፤ 16፥14 እና *ማብ ይመ*)። ይህ ደስታ ፍጹም የመሆኑ ጒዳይ በቃሉ ከመኖራችን፣ ሌሎችን ከመውደዳችን፣ ትእዛዙን ከመጠበቃችንና (ዮሐ 15፥7፡10-11) ከዓለም ከመለየታችን (ዮሐ 17፥13-17) ጋር የተያያዘ መሆኑን ጌታ ኢየሱስ አስተምሯል።

(3) በእግዚአብሔር ቅርቡነትና የመቤዠት ስጦታ ላይ የተመሠረተ ደስታ ከሕመም፣ ከመከራ፣ ከድካም ወይም ከአስቸጋሪ ሁኔታዎች የተነሣ ሊጠፋ አይችልም (*ማቴ* 5፥12፤ ሐሥ 16፥23-25፤ 2ቆሮ 12፥9)።

**1፥6 እርግጠኛ ነኝ፤** ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ሰዎች ላይ የነበረው ትምክሕት የተመሠረተው፣ እግዚአብሔር በእነርሱ ውስጥ በሚያደርገው መልካም ሥራ ላይ ብቻ ሳይሆን፣ ለእምነታቸው ባላቸው ቅናትና *መሥዋዕትነትም* ላይ የተመሠረተ ነው (ቆላ 5፡7፤ 4፥15-18)። የእግዚአብሔር ታማኝነት ምንጊዜም ጠቃሚ ሆኖ የሚገኘው ታማኝ ለሆኑ ክርስቲያኖች ነው፤ ጸጋውን ለሚቃወሙት ሰዎች ግን ታማኝነቱ ምንም አይሠራም (2፥13 እና *ማብ*፤ 2ጢሞ 2፥13 እና *ማብ ይመ*)።

**1፥9 ፍቅራችሁ ... ዕውቀትና ... እንዲትረፈረፍ፤** ፍቅር ክርስቲያናዊ ባሕርይ እንዲኖረው ካስፈለገ፣ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ዕውቀት ላይ የተመሠረተ መሆኝ አለበት። (1) በአዲስ ኪዳን "ዕውቀት" ሲል (በግሪክ ቋንቋ፣ ኤፒግኖሲስ) እንዲሁ የአእምሮ ዕውቀት ብቻ ሳይሆን፣ በልብ ውስጥ ያለ መንፈሳዊ ዕውቀት ማለት ነው። ይህ ዕውቀት በሰው ሕይወት ላይ በተግባር ተገልጾ እንደ ታየው፣ ከእግዚአብሔር የሆነውን መገለጥ የሚያመለክት ሲሆን፣ ስለ እግዚአብሔር እውነት የሆኑ ነገሮችን ለመረዳት የአእምሮ ዕውቀትን ከማካበት ይልቅ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙነት መፍጠርን ይጨምራል (ቈላ 10-11፤ ኤፌ 3፥16-19 *ይመ*፤ በገጽ 1937 ላይ፣ ***"የክርስቲያኖች የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ *ይመ*)።

(2) ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ (ከሮሜ 7፥1 ጋር *ያነጻጽሩ*) ወይም የእግዚአብሔርን ፈቃድ መረዳት (ሐሥ 22፥14፤ ሮሜ 2፥18) ሲባል በኅብረት፣ በመታዘዝ፣ በኑሮና ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ እውን የሚሆነውን ዕውቀት ማግኘት እንደ ሆነ ያመለክታል (ዮሐ 17፥3፤ 1ዮሐ 4፥8)። *ሥነ መለኮታዊ* እውነትን *መረዳትን* (1ጢሞ 6፥3፤ ቲቶ 1፥9 *ይመ*፤ ገላ 1፥9 እና *ማብ ይመ*)፣ እግዚአብሔርን *መውደድንና* ከኀጢአት ነጻ *መሆንን* ዐላማ አድርጎ ይዞአል (ሮሜ 6፥6 *ይመ*፤ በገጽ 1937 ላይ፣ ***"የክርስቲያኖች የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ *ይመ*)። "በማስተዋል" የሚለው ሐረግ አማኙ በፍቅርና በዕውቀት *መልካሙንና ክፉውን* የሚለይ *መሆኑን ያመለክታል*።

**1፥10 ንጹሓንና ነቀፋ የሌለባችሁ፤** "ንጹሕ" ማለት "ክፋት የሌለበት" ማለት ሲሆን፣ "ነቀፋ የሌለበት" ማለት ደግሞ እግዚአብሔርንም ሆነ ሰውን "የማያስቈጣ" ማለት ነው። ከክርስቶስ በቅርብ ተመልሶ ከመምጣት አንጻር፣ እንደዚህ ዐይነቱ ቅድስና የአማኞች ሁሉ ዋና ዐላማ ሊሆን ይገባል። *መንፈስ ቅዱስ* በልባችን ውስጥ አትረፍርፎ ባፈሰሰው ፍቅርና (ሮሜ 5፥5 *ይመ*፤ ከቲቶ 3፥5-6 ጋር *ያጸጽሩ*) ለእግዚአብሔር ቃል በሚኖረን ጽኑ ታማኝነት ብቻ እስከ ክርስቶስ ቀን ድረስ ንጹሓንና ነቀፋ የሌለብን እንሆናለን።

በቤተ መንግሥት ዘበኞችና[ሀ] በሌሎችም
ሁሉ ዘንድ ታውቆአል። 14በእኔ መታሰር
ምክንያት በጌታ ካሉት ወንድሞች ብዙዎቹ
የእግዚአብሔርን ቃል ያለ ፍርሀት፣ በድፍረት
ለመናገር ብርታት አግኝተዋል። 15አንዳንዶች
ከቅናትና ከፉክክር የተነሣ፣ ሌሎች ግን
ከበጎ ፈቃድ የተነሣ ክርስቶስን ይሰብካሉ።
16እነዚህ፣ እኔ ለወንጌል ለመሟገት እዚህ
እንዳለሁ ስለሚያውቁ፣ በፍቅር ይህን
ያደርጋሉ፤ 17እነዚያ ግን በእስራቴ ላይ
ሳለሁ መከራ ሊያጸኑብኝ አስበው በቅንነት
ሳይሆን ለግል ምኞታቸው ሲሉ ክርስቶስን
ይሰብካሉ[ለ]። 18ታዲያ ችግሩ ከምን ላይ ነው?
ቁም ነገሩ በቅንነትም ይሁን በማስመሰል
በማንኛውም መንገድ ክርስቶስ መሰበኩ
ነው። በዚህም ደስ ይለኛል።
አዎን፤ ደስ ይለኛል፤ 19በእኔ ላይ
የደረሰው ነገር፣ በጸሎታችሁ አማካይነትና
ከኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ በተሰጠ ረድኤት
ለመዳኔ[ሐ] እንደሚሆን ዐውቃለሁና።
20በምንም ዐይነት መንገድ ዐፍሬ እንዳልገኝ
ጽኑ ናፍቆትና ተስፋ አለ፤ ነገር ግን እንደ
ወትሮው ሁሉ ዛሬም በሕይወትም ሆነ በሞት
ክርስቶስ በሥጋዬ እንዲከበር ሙሉ ድፍረት
ይኖረኛል። 21ለእኔ፣ መኖር ክርስቶስ ነው፤
ሞትም ማትረፍ ነው። 22በሥጋ ከቈየሁ፣
ፍሬያማ ተግባር ይኖረኛል፤ ነገር ግን
የትኛውን እንደምመርጥ አላውቅም።
23በእነዚህ በሁለቱ እጨነቃለሁ፤ ልሄድ፣
ከክርስቶስም ጋር ልሆን እናፍቃለሁ፤ ይህ
እጅግ የተሻለ ነውና። 24ነገር ግን በሥጋ
መኖሬ ለእናንተ ይበልጥ አስፈላጊ ነው።
25ይህን በማስተዋል፣ በእምነት እንድታ
ድጉና ደስ እንዲላችሁ፣ በሁላችሁ ዘንድ
እን ደምቈይና እንደምኖር ተረድቻለሁ።
26እንደገና መምጫ በእናንተ ዘንድ
በምሆንበት ጊዜ በእኔ ምክንያት በክርስቶስ
ኢየሱስ ያላችሁ ደስታ ይበዛላችኋል።
27ብቻ ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ
ኑሩ፤ ይህ ከሆነ መምጫ ባያችሁ ወይም
በርቀት ሆኜ ስለ እናንተ ብሰማ፣ ለወንጌል
እምነት እንደ አንድ ሰው ሆናችሁ በመጋደል
በአንድ መንፈስ ጸንታችሁ እንደምትቆሙ
ዐውቃለሁ። 28በማንኛውም መንገድ
በተቃዋሚ ዎቻችሁ አትሸበሩ፤ ይህ እነርሱ
እንደሚጠፉ፣ እናንተ ግን እንደምትድኑ
ከእግዚአብሔር የተሰጠ ምልክት ነው።
29በክርስቶስ እንድታምኑ ብቻ ሳይሆን ስለ
እርሱ መከራ እንድትቀበሉም ይህ ጸጋ
ተሰጥቶአችኋልና፤ 30ቀድሞ እንዳያችሁት
አሁንም በእኔ እንዳለ በምትሰሙት በዚያው
ዐይነት ተጋድሎ እናንተም እያለፋችሁ
ነውና።

## ትሕትናን ከክርስቶስ መማር

2 ከክርስቶስ ጋር ካላችሁ አንድነት የተነሣ
የትኛውም መበረታታት፣ ከፍቅር የሆነ
መጽናናት፣ የመንፈስ ኅብረት፣ ምሕረትና
ርኅራኄ ካላችሁ፣
2በአንድ ሐሳብ፣ በአንድ ፍቅር፣
በአንድ መንፈስና በአንድ ዐላማ በመሆን፣
ደስታዬን ፍጹም አድርጉልኝ። 3ሌሎች
ከእናንተ እንደሚሻሉ በትሕትና ቍጠሩ

1፥14
ቈ7፥13፡17፤
ሐሥ4፥29፤
21፥33
1፥16 ቈ7፥12
1፥17
ቈ7፥13፥14፤
ሐሥ21፥33፤
ፊል2፥3
1፥19 ሐሥ16፥7፤
2ቆሮ1፥11፤
ፊሞ1፥22
1፥20 ቍ14፤
ሮሜ8፥19፤ 14፥8፤
1ቆሮ 6፥20
1፥21 ገላ2፥20
1፥23 ዮሐ12፥26፤
2ጢሞ4፥6
1፥27
1ቆሮ16፥13፤
ኤፌ4፥1፤ ይሁ1፥3
1፥29
ማቴ5፥11፡12፤
ሐሥ5፥41፤
14፥22
1፥30 ቍ13፤
ሐሥ16፥19-
40፤ 1ተሰ2፥2፤
ዕብ10፥32
2፥1 2ቆሮ13፥14፤
ቈላ3፥12
2፥2 ዮሐ3፥29፤
ሮሜ15፥5፤
ፊል4፥2
2፥3 ሮሜ12፥10፤
ገላ5፥26፤
1ጴጥ5፥5

ሀ1፥13 ወይም በቤተ መንግሥት ሁሉ
ለ1፥16፡17 አንዳንድ ጥንታዊ ያልሆኑ ቅጆች የቍ16 እና 17 ቅደም ተከተል ለዋውጠውታል
ሐ1፥19 ወይም ለትድግናዬ

**1፥16 ለወንጌል ለመሟገት፤** በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በተገለጸው መሠረት፣ ጳውሎስ ለወንጌል እውነት ይሟገት ዘንድ እግዚአብሔር ታላቅ ኀላፊነት ሰጥቶታል:: በተመሳሳይም ሁኔታ አማኞች ሁሉ ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት እንዲቆሙና ትክክለኛውን እምነት የሚያጣምሙትን ሰዎች እንዲቃወሙ ተጠርተዋል (ቍ 27፤ ገላ 1፥9 እና ማብ፤ ይሁ ቍ 3 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1866 ላይ፣ *"የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ስጦታዎች"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ):: ለቅዱሳን አንዴና ለመጨረሻ ስለ ተሰጠው እምነት መጋደል (ይሁ 1፥3) ለማይፈልጉ በዚህ ዘመን ለሚገኙ አገልጋዮች ጳውሎስ የተናገረው ቃል እንግዳ መስሎ ሊታያቸው ይችላል::

**1፥19 ከኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ፤** በአማኝ ውስጥ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ፣ "የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ" ተብሎ ይጠራል (ከሐሥ 16፥7፤ ከሮሜ 8፥9፤ ከገላ 4፥6 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ምክንያቱም ክርስቶስን ተቀብሎ በሚድንበት ጊዜ መንፈስን ለአማኙ የሚሰጥና (በገጽ 1646 ላይ፣ *"የደቀ መዛሙርት መንፈስ ቅዱስን መቀበል"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ) ከዚያም በኋላ አማኙን በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ ክርስቶስ ስለ ሆነ ነው (ሐሥ 1፥8 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1664 ላይ፣ *"በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ):: ለዓለም ቤዛነትን ያመጣ ዘንድ ኢየሱስን የቀባው ይኸው መንፈስ ነው (ሉቃ 4፥18 ይመ፤ በገጽ 1559 ላይ፣ *"ኢየሱስና መንፈስ ቅዱስ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)::

**1፥21 ሞትም ማትረፍ ነው፤** በእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት የሚኖሩ እውነተኛ አማኞች ሞትን መፍራት የለባቸውም፤ እግዚአብሔር በሕይወታቸው ዐላማ እንዳለው ሞትም ቢሆን ጊዜውን ጠብቆ ሲመጣ ምድራዊ ተልእኮአቸው የሚያበቃበትና ከክርስቶስ ጋር እጅግ የከበረ ሕይወት መኖር የሚጀመርበት እንደ ሆነ ያውቃሉ (ቍ 20-25፤ ሮሜ 8፥28 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 765 ላይ፣ *"ሞት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)::

**1፥27 በአንድ መንፈስ ጸንታችሁ እንደምትቆሙ፤** የመንፈስ አንድነት እውነተኛ ባሕርይ በተገቢው ሁኔታ መኖርን (ከኤፌ 4፥1-3 ጋር ያነጻጽሩ)፣ በአንድ መንፈስና በአንድ ዐላማ ጸንቶ መቆምን (ከኤፌ 4፥3 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ለሐዋርያት በተገለጠው መሠረት ስለ ወንጌል መሟገትን (ቍ 16 ይመ፤ ከኤፌ 4፥13-15 ጋር ያነጻጽሩ) እንደ ተዋጊ ሰራዊት መታገልንና "የክርስቶስ መስቀል ጠላቶች" ከሆኑት (3፥18 እና ማብ ይመ) የወንጌልን እውነት መጠበቅን ያካትታል::

**2፥3 በትሕትና፤** ሰው ከውድቀቱ የተነሣ በተፈጥሮው ራስ ወዳድ በመሆኑ፣ ዓለም ለትሕትና የምትሰጠው ግምት ዝቅተኛ ነው:: ሆኖም ስለ ሰውና ስለ ድነት

እንጂ፣ በራስ ወዳድነት ምኞት ወይም
ከንቱ ውዳሴ ለማግኘት አንዳች አታድርጉ።
4እያንዳንዳችሁ ሌሎችን የሚጠቅመውንም
እንጂ፣ ራሳችሁን የሚጠቅመውን ብቻ
አትመልከቱ።
5በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረው ያ አስተሳሰብ፣
በእናንተም ዘንድ ይሁን፤
6እርሱ በባሕርዩ[ሠ] አምላክ ሆኖ ሳለ፣
ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን
ሊለቀው እንደማይገባ አድርጎ
አልቈጠረውም፤
7ነገር ግን የባሪያን መልክ[ረ] ይዞ፣
በሰውም አምሳል ተገኝቶ፣
ራሱን ባዶ አደረገ፤
8ሰው ሆኖ ተገልጦም፣
ራሱን ዝቅ አደረገ፤
እስከ ሞት፣ ያውም በመስቀል ላይ
እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ።
9ስለዚህ እግዚአብሔር እጅግ ከፍ አደረገው፤
ከስምም ሁሉ በላይ የሆነውን ስም
ሰጠው፤
10ይኸውም በሰማይና በምድር፣ ከምድርም
በታች፣
ጕልበት ሁሉ ለኢየሱስ ስም
ይንበረከክ ዘንድ፣
11ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር፣
ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ
ይመሰክር ዘንድ ነው።

## እንደ ከዋክብት ማብራት

12ስለዚህ፣ ወዳጆቼ ሆይ፤ ሁልጊዜም
ታዛዦች እንደ ነበራችሁ ሁሉ፣ አሁንም

2፥4 1ቆሮ10፥24
2፥5 ማቴ11፥29
2፥6 ዮሐ1፥1፤ 5፥18፤ 14፥9
2፥7 ማቴ20፥28፤ ዮሐ1፥14፤ ሮሜ8፥3፤ 2ቆሮ8፥9፤ ዕብ2፥17
2፥8 ማቴ26፥39፤ ዮሐ10፥18፤ ሮሜ5፥19፤ 1ቆሮ1፥23፤ ዕብ5፥8
2፥9 ኢሳ52፥13፤ 53፥12፤ ዳን7፥14፤ ሐሥ2፥33፤ ኤፌ1፥20፡21፤ ዕብ2፥9
2፥10 መዝ95፥6፤ ኢሳ45፥23፤ ማቴ28፥18፤ ሮሜ14፥11፤ ኤፌ1፥10፤ ቈላ1፥20
2፥11 ዮሐ13፥13
2፥12 2ቆሮ7፥15

[ሠ]2፥6 ወይም መልክ
[ረ]2፥7 ወይም ባሕርይ

የሚናገረው እግዚአብሔርን ማእከል ያደረገው መጽሐፍ ቅዱሳዊው እይታ፣ ለትሕትና ያለው ግምት እጅግ ከፍተኛ ነው:: (1) ትሑት መሆን ማለት ደካማነታችንን ዐውቀን፣ ባከናወንነውና በተሳካልን ነገር ሁሉ እግዚአብሔርንና ሌሎችን ማመስገን ማለት ነው (ዮሐ 3፥27፤ 5፥19፤ 14፥10፤ ያዕ 4፥6)::

(2) ከክርስቶስ ከተለየን ኀጢአተኞችና (ሉቃ 18፥9-14) ከንቱ ፍጥረቶች (ዘፍ 18፥27) በመሆናችን፣ በጌታም ካልሆን በቀር (2ቆሮ 10፥17) በማንም መመካት ስለሌለብን (ሮሜ 7፥18፤ ገላ 6፥3) ትሑት መሆን ይገባናል:: መልካም ሰው መሆንና ፍሬ ማፍራት የምንችለው በእግዚአብሔር ርዳታ እንጂ በራሳችን ኀይል አይደለም፤ ያለ እግዚአብሔርና ያለ ሌሎች ርዳታ ዘላቂ የሆነ መልካም ነገር ማከናወን አንችልምና (መዝ 8፥4-5፤ ዮሐ 15፥1-16::)

(3) እግዚአብሔር ትሑታን ከሆኑት ጋር አብሮ ይኖራል (ኢሳ 57፥15፤ ሚክ 6፥8):: እግዚአብሔር ለትሑታን ጸጋን አብዝቶ ይሰጣል፤ ትዕቢተኞችን ግን ይቃወማል (ያዕ 4፥6፤ 1ጴጥ 5፥5):: ሥራውን ለመሥራት ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው ልጆቹ "ጌታን በታላቅ ትሕትና" (ሐሥ 20፥19) ያገለግላሉ::

(4) አማኞች እንደ መሆናችን መጠን፣ ከእኛ ይልቅ ሌሎች እንደሚሻሉ በመቍጠር፣ በሌሎች ዘንድ በትሕትና መመላለስ ይገባናል (ከሮሜ 12፥3 ጋር ያነጻጽሩ)::

(5) የትሕትና ተቃራኒ ትምክሕት ወይም ትዕቢት ነው፤ ይኸውም አንድ ሰው በመልካም ሥራው፣ ከሌላው ከመብለጡና ስኬታማ ከመሆኑ የተነሣ በውስጡ የሚፈጠር ከመጠን በላይ ራስን የመካብና ለራስ ከፍተኛ ግምት የመስጠት ስሜት ነው:: የዓለምና የሰው ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ ከትሕትና ይልቅ ትምክሕትን የሚያንጸባርቅ ነው (1ዮሐ 2፥16 ይመ፤ ከኢሳ 14፥13-14፤ ከሕዝ 28፥17፤ ከ1ጢሞ 6፥17 ጋር ያነጻጽሩ)::

**2፥5 ያ አስተሳሰብ በእናንተም ዘንድ ይሁን፤** ኢየሱስ ክርስቶስ ሌሎችን ለማዳን ሲል በሰማይ የነበረውን ወደር የሌለውን ክብሩን ጥሎ የባሪያን መልክ በመያዝ፣ እስከ ሞት ድረስ እንዴት እንደ ታዘዘ ጳውሎስ በአጽንዖት ይገልጻል (ቍ 5፥8):: በክርስቶስ ዘንድ የነበረው የልብና የአእምሮ ትሕትና፣ ከራስ ወዳድነት ነጻ ሆነው ለሌሎች በማሰብ፣ መልካም በማድረግና ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ሕያው መሥዋዕት አድርገው በማቅረብ ይኖሩ ዘንድ በተጠሩት ተከታዮቹ ሕይወት መገኘት ይኖርበታል::

**2፥6 በባሕርዩ አምላክ ሆኖ ሳለ፤** ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት፣ በምድር በነበረበት ጊዜና ከዚያም በኋላ ቢሆን፣ ከእግዚአብሔር አብ ጋር በእኩል ደረጃ ያለ፣ በባሕርዩ ምንጊዜም አምላክ የሆነ ጌታ ነው (ዮሐ 1፥1፤ 8፥58፤ 17፥24፤ 20፥28 እና ማብ፤ ቈላ 1፥15፡17፣ ማር 1፥11 እና ማብ፤ ዮሐ 20፥28 እና ማብ ይመ):: ክርስቶስ፣ "ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን ሊለቀው እንደማይገባ አድርጎ አልቈጠረውም" ሲባል በምድር ያለነውን እኛን ለማዳን፣ በሰማይ የነበረውን ልዩ መብትና ክብር ተወ ማለት ነው::

**2፥7 ራሱን ባዶ አደረገ፤** በግሪክ ቋንቋም ሐሳቡ ቃል በቃል ሲተረጐም ልክ እንደዚሁ "ራሱን ባዶ አደረገ" የሚል ነው፤ ይኸውም ሰማያዊ ክብሩን (ዮሐ 17፥4)፣ ሥልጣኑን (ዮሐ 5፥30፤ ዕብ 5፥8)፣ ሀብቱን (2ቆሮ 8፥9)፣ መብቱን (ሉቃ 22፥27፤ ማቴ 20፥28)፤ እንደዚሁም የራሱን መለኮታዊ ፈቃድ ማድረግን (ዮሐ 5፥19፤ 8፥28፤ 14፥10) ተወ ማለት ነው:: "ራሱን ባዶ አደረገ" የሚለው ይህ አባባል በፈቃዱ መለኮታዊ ሥልጣኑንና ልዩ መብቱን መተዉን ብቻ ሳይሆን፣ መከራ መቀበሉን፣ ሰዎች በትክክል ሳይረዱት መቅረቱን፣ መንገላታቱን፣ መጠላቱንና በመስቀል ላይ የተረገመ ሆኖ መሰቀሉን ጭምር የሚያካትት ነው::

**2፥7 የባሪያን መልክ ይዞ፣ በሰውም አምሳል ተገኝቶ፤** ክርስቶስ የባሪያን መልክ ይዞ መምጣቱን የሚገልጹትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባቦች ለመረዳት ማር 13፥32፤ ሉቃ 2፥40-52፤ ሮሜ 8፥3፤ 2ቆሮ 8፥9፤ ዕብ 2፥7፡14 ይመልከቱ:: ክርስቶስ ፍጹም መለኮት ቢሆንም የሰውን ባሕርይ ከፈተናው፣ ከውርደቱና ከድካሙ ጋር ለበሰ፤ በዚህ ሁሉ ግን አንድም ኀጢአት አልነበረበትም (ቍ 7-8፤ ዕብ 4፥15)::

**2፥12 የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ፤** በጸጋ የዳንን አማኞች እንደ መሆናችን መጠን፣ እስከ መጨረሻ ድረስ የራሳችንን መዳን መፈጸም አለብን፤ ይህን ሳናደርግ ብንቀር፣ የተሰጠንን ድነት እናጣለን:: (1) የግል ጥረት በማድረግ ብቻ መዳናችንን መፈጸም አንችልም፤ ይህ ሊሆን የሚችለው በተሰጠን በእግዚአብሔር ጸጋና በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ነው (በገጽ 1746 ላይ፣ "እምነትና ጸጋ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

(2) የራሳችንን መዳን እንፈጽም ዘንድ፣ ኀጢአትን መቃወምና በውስጣችን የመንፈስ ቅዱስን መሻት

እኔ በአጠገባችሁ ሳለሁ ብቻ ሳይሆን፣
ይልቁንም አሁን በሌለሁበት ጊዜ በፍርሃትና
በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ፤
13እንደ በጎ ፈቃዱ መፈለግንና ማድረግን
በእናንተ ውስጥ የሚሠራ እግዚአብሔር
ነውና።
14ማንኛውንም ነገር ሳታጕረመርሙና
ሳትከራከሩ አድርጉ፤ 15ይኸውም በጠማማና
በክፉ ትውልድ መካከል ንጹሓንና ያለ
ነቀፋ፣ ነውርም የሌለባቸው የእግዚአብሔር
ልጆች ሆና ችሁ፣ እንደ ከዋክብት በዓለም
ሁሉ ታበሩ ዘንድ ነው። 16የሕይወትንም
ቃል ስታቀርቡ[a]፣ በከንቱ እንዳልሮጥሁ
ቈላ 3፥5-14 ወይም በከንቱ እንዳልደከምሁ በክርስቶስ
ቀን የምመካበት ይሆን ልኛል።
17ነገር ግን በእምነታችሁ መሥዋዕትና
አገልግሎት ላይ እንደ መጠጥ ቍርባን
ብፈስ እንኳ ከሁላችሁ ጋር ደስ ይለኛል፤
ሐሤትም አደርጋለሁ። 18እናንተም
እንደዚሁ ከእኔ ጋር ደስ ልትሰኙና ሐሤት
ልታደርጉ ይገባል።

## ጢሞቴዎስና አፍሮዲጡ

19ስለ እናንተ ሰምቼ ደስ እንዲለኝ፣
ጢሞቴዎስን ቶሎ ወደ እናንተ ልልክላችሁ
በጌታ ኢየሱስ ተስፋ አደርጋለሁ። 20ስለ
እናንተ ደኅንነት ከልቡ የሚገደው እንደ

2፥13 ዕዝ1፥5፤ 1ቆሮ 12፥6፤ 15፥10፤ ገላ2፥8፤ ኤፌ1፥5፤ ዕብ13፥21
2፥14 1ቆሮ10፥10፤ 1ጴጥ4፥9
2፥15 ማቴ5፥45:48፤ ሐሥ2፥40፤ ኤፌ5፥1፤ 1ተሰ3፥13
2፥16 1ቆሮ1፥8፤ 9፥24፤ 1ተሰ2፥19
2፥17 ሮሜ15፥16፤ 2ቆሮ6፥10፤ 12፥15፤ 2ጢሞ4፥6
2፥19 ቍ23፤ ሐሥ16፥1 2፥20 1ቆሮ16፥10

[a]2፥16 ስትይዙ

መከተል አለብን:: ክፉን ለማሸነፍና የክርስቶስን ሕይወት በኑሮአችን ለመግለጽ፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ መፈጸሚያ የሆነውን ማንኛውንም ነገር መሣሪያ አድርጎ ለመጠቀም የማያቋርጥ ጥረት ማድረግን ይጠይቃል:: ስለዚህ መዳችንን ለመፈጸም የምናከናውነው በመቀደስ አስፈላጊነት ላይ የተመሠረተ ነው (ገላ 5፥17 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1853 ላይ፣ *"የኀጢአተኛ ተፈጥሮ ሥራዎችና የመንፈስ ፍሬ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

(3) ወደ ክርስቶስ እየተጠጋን በመሄድ (ዕብ 7፥25 እና ማብ ይመ)፣ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን ነገር በማሰብና በመፈጸም (ቍ 13 እና ማብ ይመ)፣ ኀይሉንም በመቀበል መዳናችንን እንፈጽማለን:: መዳናችንን በሰማይ ፍጻሜ ላይ ለማድረስ፣ "ከእግዚአብሔር ጋር አብረን የምንሠራ ነንና" (1ቆሮ 3፥9)::

(4) መዳናችንን መፈጸም ዐቢይ ጕዳይ ስለ ሆነ፣ "በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ" (የሚቀጥለውን ማብ ይመ) እውን ልናደርገው ይገባል::

**2፥12 በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ፤** በክርስቶስ በኩል የሚፈጸመው ድነት፣ በእግዚአብሔር ፊት በፍርሀትና በመንቀጥቀጥ መሆን እንደሚገባው ጳውሎስ ያሳስባል:: የእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ ለእግዚአብሔር ቃል እንዲንቀጠቀጡና (ኢሳ 66፥2) ክፋትን ሁሉ እንዲተዉ (ምሳ 3፥7፤ 8፥13) የሚያደርግ ቅዱስ ፍርሀት በውስጣቸው ሊኖር ይገባል:: ጌታን መፍራት ሁል ጊዜ እንደሚነገረው አክብሮታዊ እምነትን ብቻ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን ኀይል፣ ቅድስናና ጻድቅ ባሕርይ መፍራትን እንዲሁም በእርሱ ላይ ኀጢአት መፈጸምንና ከዚህም የተነሣ የሚመጣውን መዘዝ ሁሉ መፍራትን ያካትታል (ከዘፀ 3፥6፤ ከመዝ 119፥120፤ ከሉቃ 12፥4-5 ጋር ያነጻጽሩ):: ይህ ዐይነቱ ፍርሀት አጥፊ ፍርሀት ሳይሆን፣ ወደ እግዚአብሔር ቅሩብነትና በረከት፣ ወደ ግብረገባዊ ንጽሕና፣ ወደ ሕይወትና ወደ ድነት ለመምራት በሥርዐት የሚያስኼድና የሚቤዥ ፍርሀት ነው (ከመዝ 5፥7፤ 85፥9፤ ከምሳ 14፥27፤ 16፥6 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 291 ላይ፣ *"እግዚአብሔርን መፍራት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

**2፥13 በእናንተ ውስጥ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና፤** ፈቃዱን ይፈጽሙ ዘንድ፣ መሻትንም ሆነ ኀይልን በመስጠት በልጆቹ ውስጥ የሚሠራው የእግዚአብሔር ጸጋ አሁንም እየሠራ ነው (በገጽ 1746 ላይ፣ *"እምነትና ጸጋ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ) :: ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ሥራ በግዴታ የሚሠራ ወይም ላይቀበሉት የማይቻል አይደለም:: በውስጣችን ያለው የጸጋ ሥራ (1፥6፤ 1ተሰ 5፥24፤ 2ጢሞ 4፥18፤ ቲቶ 3፥5-7) ሁልጊዜ ብእኛ ታማኝነትና ትብብር ላይ የተመሠረተ ነው (ቍ 12:14-16)::

**2፥15 በጠማማና በክፉ ትውልድ፤** በምንኖርበት ዓለም ውስጥ ያለው ሕዝብ የማያምንና ጠማማ ትውልድ መሆኑን (ማቴ 17፥17 ይመ፤ ከ12፥39፤ ከሐሥ 2፥40 ጋር ያነጻጽሩ) ጌታ ኢየሱስና ሐዋርያት በአጽንዖት ተናግረዋል:: በዓለም ያለው ሕዝብ አመለካከቱ የተሳሳተ፣ ፍርዱም ጠማማ ነው፤ በአኗኗሩም ኢግብረገባዊነትን የሚከተልና የእግዚአብሔርን ቃል ሥርዐት የማይቀበል ነው:: የእግዚአብሔር ልጆች የክርስቶስን አስደናቂ የመቤዠት ሥራ ለጠፋው ዓለም ለማወጅ ዓለምን ከመምሰል መራቅ፣ የማይነቀፉ፣ ንጹሓንና እንከን አልባ መሆን አለባቸው (ከ1ዮሐ 2፥15 ጋር ያነጻጽሩ)::

**2፥17 እንደ መጠጥ ቍርባን ብፈስ እንኳ፤** ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች ካለው ጽኑ ፍቅርና ጭንቀት የተነሣ በእግዚአብሔር ፊት እንደ መሥዋዕት ሆኖ ይቀርብ ዘንድ ሕይወቱን እንኳ ሳይቀር ስለ እነርሱ አሳልፎ ለመስጠት ፈቃደኛ ነበር:: (1) በክርስቶስ ያላቸው እምነትና ለእርሱ ያላቸውም ፍቅር ይጠነክርና ሥር ይሰድ ዘንድ (ከ2ጢሞ 4፥6 ጋር ያነጻጽሩ) ጳውሎስ ራሱ ተጐድቶ ስለ እነርሱ መሥዋዕት ሆኖ ቢቀርብ ደስ ይለዋል እንጂ አይጸጸትም:: (2) ጳውሎስ ለመንፈሳዊ ልጆቹ መሥዋዕት እስከ መሆን የሚያደርስ እንደዚህ ዐይነት ፍቅር ከነበረው፣ እኛስ የመንፈሳዊ ልጆቻችን እምነት እንዲጠነክር መሥዋዕትነትን ለመክፈልና መከራን ለመቀበል ምን ያህል ፈቃደኞች ነን? ልጆቻችንን በተቻለ መጠን በጌታ ፍጹማን እንዲሆኑ ለማድረግ፣ ሕይወታችንና ደማችንም እንኳ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ሆኖ እንዲፈስ የሚጠይቅ ከሆነ፣ እንደዚህ ዐይነቱን መሥዋዕትነት ለመክፈልም ዝግጁ መሆን ይገባናል (ወላጆች፣ ልጆቻቸውን እግዚአብሔርን በመፍራት ያድጉ ዘንድ ለማድረግ የሚጠቅሙ ዐሥራ አምስት ነጥቦች ያሉትን በገጽ 1894 ላይ፣ *"ወላጆችና ልጆች"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

**2፥19 ጢሞቴዎስን፤** የእግዚአብሔር አገልጋይና መልእክተኛ ሕይወቱ ምን መምሰል እንዳለበት ጢሞቴዎስ ጥሩ ምሳሌ ነበር፤ እርሱም የእግዚአብሔርን ቃል ለማወቅና ለመታዘዝ የሚተጋ ተማሪ ከመሆኑም በላይ (2ጢሞ 3፥15) ክርስቶስን ለማገልገል ብቁ የሆነ (1ተሰ 3፥2)፣ መልካም ዝና ያለው (ሐሥ 16፥2)፣ የተወደደና የታመነ (1ቆሮ 4፥17)፣ ስለ ሌሎች ከልብ የሚገደው (ቍ 20)፣ ተስፋ የሚጣልበት (2ጢሞ 4፥9:21)፣ ለወንጌልና ለጳውሎስ ራሱን ሙሉ በሙሉ የሰጠ ሰው ነበር (ቍ 22፤ ሮሜ 16፥21)::

እርሱ ያለ ማንም የለኝም፤ 21ሁሉም
የኢየሱስ ክርስቶስን ሳይሆን የራሳቸውን
ፍላጎት ለማሟላት ይሯሯጣሉና። 22ነገር
ግን እንደምታውቁት ጢሞቴዎስ ማንነቱን
አስመስክሮአል፤ ልጅ ከአባቱ ጋር
እንደሚያገለግል፣ ከእኔ ጋር በወንጌል
ሥራ አገልግሎአልና። 23እንግዲህ የራሴን
የወደ ፊት ሁኔታ እንዳጣራሁ ልልከው
ተስፋ አደርጋለሁ። 24እኔም ራሴ ቶሎ
እንደምመጣ በጌታ ታምኛለሁ። 25እንዲሁም
ወንድሜን፣ የሥራ ባልደረባዬ ንና
አብሮኝ ወታደር የሆነውን፣ በሚያስፈል
ገኝ ሁሉ እንዲንከባከበኝ የላካችሁትን፣
የእና ንተ መልእክተኛ የሆነውን
አፍሮዲጡን መልሼ እንድልክላችሁ
አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። 26እርሱ
ሁላችሁንም ይናፍቃልና፤ መታመሙን
ስለ ሰማችሁም ተጨንቆአል። 27በርግ ጥም
ታሞ ለሞት ተቃርቦ ነበር፤ እግዚአብሔር
ግን ምሕረት አደረገለት፤ በሐዘን ላይ
ሐዘን እንዳይደራረብብኝ፣ ለእኔም ጭምር
እንጂ ለእርሱ ብቻ አይደለም። 28ስለዚህ
እርሱን እንደ ገና ስታዩ ደስ እንዲላችሁና
የእኔም ጭንቀት እንዲቀል ልልከው
በጣም ጓጉቻለሁ። 29በሙሉ ደስታ በጌታ
ተቀበሉት፤ እንደ እርሱ ያሉትንም ሰዎች
አክብሯቸው። 30እርሱም እናንተ ልትሰጡኝ
ያልቻላችሁትን አገልግሎት ለማሟላት
ሲል ለሕይወቱ እንኳ ሳይሳሳ፣ ለክርስቶስ
ሥራ ከሞት አፋፍ ደርሶ ነበርና።

## በሥጋ አለመመካት

3 ከዚህ በተረፈ ወንድሞቼ ሆይ፤ በጌታ
ደስ ይበላችሁ። ያንኑ ደግሜ ብጽፍላችሁ
እኔ አይሰለቸኝም፤ ለእናንተም ይጠቅማች
ኋል። 2ከእነዚያ ውሾች ተጠንቀቁ፤ ክፋትን
ከሚያደርጉና ሥጋን ከሚቈራርጡ ሰዎች
ተጠበቁ። 3እኛ በእውነት የተገረዝን
በእግዚአብሔር መንፈስ የምናመልክ፣
በክርስቶስ ኢየሱስ የምንመካ፣ በሥጋም
የማንታመን ነንና። 4ካስፈለገ እኔም በሥጋ
የምመካበት አለኝ።
ማንም በሥጋ የሚመካበት ነገር
ያለው ቢመስለው፣ እኔ እበልጠዋለሁ፤
5በስምንተኛው ቀን የተገረዝሁ፣ ከእስራኤል
ዘር፣ ከብንያም ወገን የተወለድሁ ስሆን፣
ከዕብራውያንም ዕብራዊ ነኝ፤ ስለ ሕግ
ከተነሣ፣ ፈሪሳዊ ነበርሁ፤ 6ስለ ቅናት ከሆነ፣
የቤተ ክርስቲያን አሳዳጅ ነበርሁ፤ ሕግን
በመፈጸም ስለሚገኝ ጽድቅ ከሆነም፣ ያለ
ነቀፋ ነበርሁ።
7ነገር ግን ይጠቅመኝ የነበረውን ሁሉ
አሁን ለክርስቶስ ስል እንደ ጉድለት
ቈጥሬዋለሁ። 8ከዚህም በላይ ለእርሱ ብዬ
ሁሉን ነገር የተውሁለትን፣ ወደር የሌለውን

2፥21 1ቆሮ10፥24
2፥22 1ቆሮ4፥17፤ 1ጢሞ1፥2
2፥23 ቍ19
2፥24 ፊል1፥25
2፥25 ሮሜ16፥3፡9፡21፤ 2ቆሮ823፤ ፊል4፥3፡18፤ ፊላ4፥11 ፊሞ1፡2
2፥26 ፊል1፥8፤
2፥28 ቍ25፤
2፥29 1ቆሮ16፥18፤ 1ጢሞ5፥17
2፥30 1ቆሮ16፥17
3፥1 ፊል2፥18፤
3፥2 መዝ22፥16፡20፤ ራእ22፥15፤
3፥3 ሮሜ2፥28፡29፤ 15፥17፤ ገላ6፥14፡15፤ ፊላ2፥11
3፥4 2ቆሮ11፥21
3፥5 ሉቃ1፥59፤ ሐሥ23፥6፤ ሮሜ11፥1፤ 2ቆሮ11፥21፡22
3፥6 ቍ9፤ ሐሥ8፥3፤ 21፥20፤ ሮሜ9፥30፤ 10፥5
3፥7 ማቴ13፥44፤ ሉቃ14፥33
3፥8 ቍ10፤ መዝ73፥25፤ ኤር9፥23፡24፤ ዮሐ17፥3፤ ኤፌ4፥13፤ 2ጴጥ1፥2

**2፥21 ሁሉም … የራሳቸውን ፍላጎት ለሚሟላት ይሯሯጣሉና፤** ወንጌል እንዲስፋፋ ከልብ ገዷቸው ሳይሆን የግል ጥቅምን፣ ክብርንና ዝናን ለማግኘትና የራስ ወዳድነት ምኞትን ለማሳካት ከመፈለግ የተነሣ የሚሰብኩ፣ የሚያስተምሩና መጋቢ የሚሆኑ ወይም የሚጽፉ አገልጋዮች አሉ። እነዚህ አገልጋዮች ጌታ ኢየሱስን ደስ ለማሰኘት ከመፈለግ ይልቅ፣ ሰዎችን ደስ ለማሰኘትና በሰዎች ዘንድ ለመመስገንም ጥረት ያደርጋሉ (ቍ 20-21፣ 1፥15፤ 2ጢሞ 4፥10፡16)። እንደነዚህ ያሉ አገልጋዮች እውነተኛ የጌታ አገልጋዮች አይደሉም።

**3፥2 ከእነዚያ ውሾች … ክፋትን ከሚያደርጉና ሥጋን ከሚቈራርጡ፤** የሐዋርያው ጳውሎስ ከባዱ ፈተና የክርስቶስን ወንጌል ከሚያጣምሙ ሰዎች የተነሣ የሚሰማው የልብ ሐዘን ነበር። ጳውሎስ ለክርስቶስ፣ ለቤተ ክርስቲያንና ቤዛነት ላለበት እውነት የነበረው ፍቅር እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ፣ ንጹሑን አስተምህሮ የሚያጣምሙትን ሰዎች አጥብቆ ለመቃወምና እነርሱንም "ውሾች" እና "ክፋትን የሚያደርጉ" ብሎ ለመግለጽ አስገደደው (1፥17 እና ማብ፤ ገላ 1፥9 እና ማብ ይመ፤ ከማቴ 23 ጋር ያነጻጽሩ)። "ሥጋን የሚቈራርጡ" የሚለው ሐረግ፣ የብሉይ ኪዳን የግዝረት ምልክት ለድነት አስፈላጊ እንደ ሆነ የሚያምኑ፣ ከአይሁድ እምነት ሙሉ በሙሉ ገና ያልተላቀቁ ክርስቲያኖች የሚያስተምሩትን የግዝረት ሥርዐት ለማመልከት ሐዋርያው ጳውሎስ የተጠቀመበት አገላለጽ ነው። እውነተኛ ግዝረት የሚሆነው፣ የሰው ልብ በመንፈስ ቅዱስ ተገርዞ ከኀጢአትና ከክፋት ነጻ ሲሆን እንደ ሆነ ጳውሎስ ይናገራል (ቍ 3፤ ሮሜ 2፥25-29፤ ቈላ 2፥11)።

**3፥8-11 ክርስቶስን አገኝ ዘንድ፤** እነዚህ ጥቅሶች የሐዋርያውን ልብና የክርስትናን መሠረታዊ ይዘት ያሳያሉ። የጳውሎስ ትልቁ ናፍቆት፣ ክርስቶስን ማወቅና እጅግ የቀረበ ግንኙነት በመፍጠር ከእርሱ ጋር ያለውን ኅብረትና ወዳጅነት አጽንቶ መኖር ነው። የጳውሎስ ፍለጋ (ክትትል) የሚከተሉትን ያካትታል፦

(1) በእግዚአብሔር ቃል ላይ በተገለጸው መሠረት ክርስቶስን እንደዚሁም መንገዱን፣ ማንነቱንና ባሕርዩን በግል ማወቅን። ስለ ክርስቶስ ያለን እውነተኛ ዕውቀት ቃሉን መታዘዝን፣ መንፈሱን መከተልን፣ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ለሚሠራው በእምነት፣ በእውነትና በመታዘዝ እንዲሁም ሐሳቡንና ዐላማውን በመቀበል ምላሽ መስጠትን ያካተተ ነው።

(2) በእርሱ ዘንድ መገኘትን (ቍ 9)፣ ይኸውም በስጦታ መልክ ብቻ እግዚአብሔር የሚሰጠውን ጽድቅ ለማግኘት ከክርስቶስ ጋር አንድነትና ኅብረት መፍጠር ማለት ነው (1፥10-11፤ 1ቆሮ 1፥30 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1735 ላይ፣ "*ድነትን የሚገልጹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

(3) የትንሣኤውን ኀይል ማወቅን (ቍ 10)፤ ይኸውም የሕይወት መታደስ ማግኘትን፣ ከኀጢአት ባርነት ነጻ መውጣትን (ሮሜ 6፥4፤ ኤፌ 2፥5-6)፤ ውጤታማ ምስክርነትን፣ ፈውስንና ታምራትን የሚያስገኘውን፣ በመጨረሻም አንድን ክርስቲያን ከሙታን እንዲነሣ የሚያደርገውን የመንፈስ ቅዱስ ኀይል ማግኘት ማለት ነው (ቍ 11፤ ኤፌ 1፥18-20)።

(4) ስለ ክርስቶስና ስለ ዐላማው መከራን በመቀበል፣ ራስን በመካድና አሮጌውን ሰውነት በመስቀል፣ በክርስቶስ መከራ መካፈልን (ከ1፥29፤ ከሐሥ 9፥16፤ ከሮሜ 6፥5-6፤ ከ1ቆሮ 15፥31፣ ከ2ቆሮ 4፥10፣ ከገላ 2፥20፤ ከቈላ 1፥24፤ ከ1ጴጥ 4፥13 ጋር ያነጻጽሩ)።

ጌታዬን ክርስቶስ ኢየሱስን ከማወቅ
ታላቅነት ጋር ሳነጻጽር፣ ሁሉንም ነገር እንደ
ጕድለት እቈጥረዋለሁ፤ ለእርሱ ስል ሁሉን
አጥቻለሁ፤ ክርስቶስን አገኝ ዘንድ ሁሉን
እንደ ጕድፍ እቈጥራለሁ፤ 9ሕግ በመጠበቅ
የሚገ" የራሴ ጽድቅ ኖሮኝ ሳይሆን፣
በክርስቶስ በማመን ይኸውም ከእግዚአብሔር
የሚመጣ፣ ከእምነትም በሆነ ጽድቅ በእርሱ
ዘንድ እንድገኝ ነው። 10ክርስቶስንና
የትንሣኤውን ኀይል እንዳውቅ፣ በሥቃዩ
ተካፋይ እንድሆንና በሞቱም እርሱን
እንድመስል እመኛለሁ፤ 11ለሙታን
ትንሣኤም እንድደርስ እናፍቃለሁ።

## ወደ ግብ ለመድረስ መፋጠን

12ይህን ሁሉ አግኝቻለሁ ወይም ፍጹም
ሆኛ ለሁ ማለት አይደለም፤ ነገር ግን
ክርስቶስ ኢየሱስ እኔን የራሱ ያደረገበትን
ያን፣ እኔም የራሴ ለማድረግ እጣጣራለሁ።
13ወንድሞች ሆይ፤ እኔ ገና እንደ ያዝሁት
አድርጌ ራሴን አልቈጥርም፤ ነገር ግን
አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ ከኋላዬ ያለውን
እየረሳሁ ከፊቴ ወዳለው እዘረጋለሁ።
14እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ላይ
ስለ ጠራኝ፣ ሽልማት ለመቀዳጀት ወደ ግቡ
እፈጥናለሁ።
15እንግዲህ እኛ ብስለት ያለን ሁላችን
ነገሮችን በዚህ ሁኔታ ማየት ይኖርብናል፤
በአንዳንድ ነገር የተለያየ አስተሳሰብ
ቢኖራችሁ፣ እግዚአብሔር እርሱንም
ይገልጥላችኋል። 16ሆኖም በደረስንበት
በዚያ እንመላለስ።
17ወንድሞች ሆይ፤ የእኔን አርኣያነት
በመከተል ከሌሎች ጋር ተባበሩ፤
እኛ በሰጠናችሁ ምሳሌነት መሠረት
የሚኖሩትንም አስተውሉ። 18ምክንያቱም
ከዚህ በፊት ደጋግሜ እንደ ነገርኋችሁ፣
አሁንም እንደ ገና፣ ያውም በእንባ
እነግራችለሁ፤ ብዙዎች የክርስቶስ
መስቀል ጠላቶች ሆነው ይመላለሳሉ።
19መጨረሻቸው ጥፋት ነው፤ ሆዳቸው
አምላካቸው ነው፤ ክብራቸው በነውራቸው
ነው፤ ልባቸው ያረፈው በምድራዊ ነገር ላይ
ነው። 20እኛ ግን አገራችን በሰማይ ነው፤
ከዚያ የሚመጣውንም አዳኝ፣ ጌታ ኢየሱስ

3፥9 ቍ6፤
ኤር33፥16
3፥10 ቍ8፤
ሮሜ6፥3-5፤
2ቆሮ1፥5
3፥11 ዮሐ11፥24፤
ሮሜ6፥5፤
ራእ20፥5፡6
3፥12 ሐሥ9፥5፡6፤
1ቆሮ13፥10፤
1ጢሞ6፥12
3፥13 ሉቃ 9፡62
3፥14 ሮሜ8፥28፤
1ቆሮ9፥24፤
ዕብ6፥1
3፥15 1ቆሮ2፥6፤
ገላ5፥10፤
ኤፌ1፥17፤
1ተሰ4፥9
3፥17 1ቆሮ4፥16፤
1ጢሞ4፥12
3፥18
ሐሥ20፥31፤
ገላ6፥12
3፥19
መዝ73፥17፤
ሮሜ6፥21፤
8፥5፡6፤ 16፥18፤
ሩላ3፥2፤

3፥19 ይሁ1፥13 3፥20 1ቆሮ1፥7፤ ኤፌ2፥19፤ ሩላ3፥1፤
ዕብ12፥22

**3፥9 ከእግዚአብሔር የሚመጣ ... ጽድቅ፤** የአማኞች ጽድቅ ከሁሉም በፊት ይቅር መባልን፣ መዳንን፣ በእምነት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘትን (ሮሜ 4፥5 እና ማብ ይመ) በውስጡ ይዞአል::

(1) ይሁን እንጂ ጽድቃችን ከዚህም በላይ ነው:: ጽድቃችን በልባችን ውስጥ የሚኖረው ክርስቶስ ኢየሱስ ራሱ እንደ ሆነ የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል (ከ1፥20-21፤ ከሮሜ 8፥10፤ ከ1ቆሮ 1፥30፤ ከገላ 2፥20፤ ከኤፌ 3፥17፤ ከቈላ 3፥4 ጋር ይነጻጸሩ)፤ በብሉይ ኪዳን ውስጥ መሲሑ፣ "የጽድ ቅርንጫፍ" እንዲሁም "እግዚአብሔር ጽድቃችን" ተብሎ ተጠቅሶአል (ኤር 23፥5-6 እና ማብ ይመ):: ስለዚህ እኛ ያለን ጽድቅ የራሳችን ሳይሆን፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ እምነታችንም በእርሱ ነው (1ቆሮ 1፥30 እና ማብ፤ ገላ 2፥20 እና ማብ ይመ):: ኢየሱስ በውስጣችን በመኖሩ፣ በእርሱ "የእግዚአብሔር ጽድቅ" እንሆናለን (2ቆሮ 5፥21 እና ማብ ይመ)::

(2) የድነታችን መሠረትና የጽድቃችን ብቸኛ ተስፋ የሆነው፣ ክርስቶስ የሞተው መሥዋዕታዊ ሞት፣ ያፈሰሰው ደም (ሮሜ 3፥24፤ 4፥25፤ 5፥9፤ 8፥3-4፤ 1ቆሮ 15፥3፤ ገላ 1፥4፤ 2፥20፤ ኤፌ 1፥7፤ ዕብ 9፥14፤ 1ጴጥ 1፥18-19፤ 1ዮሐ 4፥10) እንዲሁም በልባችን ውስጥ ያለው የእርሱ የትንሣኤ ሕይወት ነው (ሮሜ 4፥25፤ 5፥9-10፤ 8፥10-11፤ ገላ 2፥20፤ ቈላ 3፥1-3፤ ሮሜ 4፥22 እና ማብ ይመ)::

**3፥13 ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤** ጳውሎስ ኀይሉን ሁሉ እየተጠቀመ ክርስቶስ ለሕይወቱ ግብ አድርጎ ያስቀመጠውን ነገር እንዳያጣ በከፍተኛ ጥንቃቄ ወደ ፊት እንደሚሮጥ በእሽቅድድም ስፍራ ላይ እንዳለ ሯጭ ራሱን ይቈጥራል (ከዕብ 12፥1 እና ማብ ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይህም የሕይወት ግብ ሐዋርያው ጳውሎስ ከክርስቶስ ጋር የሚኖረውን ፍጹም አንድነት (ቍ 8-10)፣ የመጨረሻ ድነቱንና ከሙታን መነሣቱን (ቍ 11) ያካትታል:: (1) የጳውሎስ የሕይወቱ ምኞት ይኸው ነበር:: ሰማያዊውን ክብር በውልብታ አይቶአል (2ቆሮ 12፥4)፤ ይህም በመሆኑ በእግዚአብሔር ጸጋ ወደ ፊት ለመቀጠል፣ አንድ ቀንም ወደ መንግሥት ሰማያት ለመግባትና ክርስቶስን ፊት ለፊት ለማየት ባደረገው ውሳኔ ዙሪያ ሕይወቱ ሁሉ እንዲያተኵር ቈረጠ (ከ2ጢሞ 4፥8፤ ከራእ 2፥10፤ 22፥4 ጋር ያነጻጽሩ)::

(2) ሁላችንም እንደዚህ ዐይነቱን ቈራጥ ውሳኔ ማድረግ ይኖርብናል:: በሕይወት ዘመናችን ሁሉ የኑሮ ጭንቀት፣ ሀብት፣ ክፋትና እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ ዕንቅፋቶችና ፈተናዎች ለጌታ የገባነውን ቃል እንድናጥፍ ተስፋ ሊያስቈርጡን ይሞክራሉ (ከማር 4፥19፤ ከሉቃ 8፥14 ጋር ያነጻጽሩ):: በዚህ ጊዜ ማድረግ የሚገባን አስፈላጊው ነገር፣ በኋላችን ያለውን ይኸውም ብልሹ የሆነውን ዓለምና አሮጌውን ኀጢአተኛ ሰውነታችንን (ከዘፍ 19፥17፡26፤ ከሉቃ 17፥32 ጋር ያነጻጽሩ) በመርሳት፣ በክርስቶስ ወደ ድነታችን ፍጻሜ ለመድረስ ከፊታችን ወዳለው መዘርጋት ነው::

**3፥18 የክርስቶስ መስቀል ጠላቶች፤** እነዚህ ጠላቶች፣ ኢግብረገባዊ የሆነ ኑሮ በመኖርና የሐሰት ትምህርት በማስተማር ወንጌልን የሚያጣምሙና የሚበርዙ አስመሳይ አማኞች እንደ ሆኑ መረዳቱ ይበልጥ አሳማኝ ነው:: ጳውሎስን ታላቅ ያደረገው አንዱ ዐቢይ ነገር፣ ወንጌል በሚጣመምበት ጊዜ ወይም ያገለገላቸው ሰዎች ሕይወት አደጋ ላይ በሚወድቅበት ጊዜ ፈጥኖ የሚሰማው መሆኑ ነው (ቍ 2 እና ማብ፤ ገላ 1፥9 እና ማብ፤ በገጽ 1716 ላይ፣ *"የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ተግባራዊ ኀላፊነታቸው"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)::

**3፥20 እኛ ግን አገራችን በሰማይ ነው፤** ከእንግዲህ ክርስቲያኖች የዚህ ዓለም ዜጎች አይደሉም፤ በምድር ላይ እንግዶችና መጻተኞች ናቸው (ሮሜ 8፥22-24፤ ገላ 4፥26፤ ዕብ 11፥13፤ 12፥22-23፤ 13፥14፤ 1ጴጥ 1፥17፤ 2፥11 ይመ፤ በገጽ 47 ላይ፣ *"የአብርሃም መጠራት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ):: (1) አሁን ያለን የሕይወት አካሄድ፣ ልንይዘው የሚገባ ፋይዳና አቅጣጫ ሁሉ

ክርስቶስን በናፍቆት እንጠባበቃለን፤
21እርሱም ሁሉን ለራሱ ባስገዛበት ኀይል፣
1ተሰ ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን
10 ሥጋችንን ይለውጣል።

4 ስለዚህ የምወዳችሁና የምናፍቃችሁ፣ ወንድሞቼ ደስታዬና አክሊሌ የሆናችሁ፣ እንዲሁም ወዳጆች ሆይ፤ በዚህ ሁኔታ በጌታ ጸንታችሁ ቁሙ።

## የጳውሎስ ምክር

2በጌታ አንድ ልብ እንዲኖራቸው
ኤዎድ ያንን እለምናለሁ፤ ሲንጤኪንንም
እለምናለሁ። 3አዎን፤ አንተ ታማኝ የሥራ
ባልደረባዬ ሆይ፤ ወንጌልን በማሰራጨት ረገድ ከእኔና ከቀሌምንጦስ ጋር፣ እንዲሁም ስማቸው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፋት ከሌሎች የሥራ ጓደኞቼ ጋር የተጋደሉትን እነዚህን ሴቶች እንድትረዳቸው እለምንሃለሁ።
4ምንጊዜም በጌታ ደስ ይበላችሁ፤ ደግሜ
እላለሁ ደስ ይበላችሁ። 5ገርነታችሁ በሁሉ
ዘንድ የታወቀ ይሁን፤ ጌታ ቅርብ ነው።
6በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ፣ ከምስጋናም ጋር ልመናችሁን በእግዚአብሔር ፊት አቅርቡ እንጂ ስለማንኛውም ነገር አትጨነቁ።
7ከማስተዋል በላይ የሆነው የእግዚአብሔር ሰላም፣ ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።
8በመጨረሻም ወንድሞች ሆይ፤ እውነት የሆነውን ሁሉ፣ ክቡር የሆነውን ሁሉ፣ ትክክል የሆነውን ሁሉ፣ ንጹሕ የሆነውን ሁሉ፣ ተወዳጅ የሆነውን ሁሉ፣ መልካም የሆነውን ሁሉ፣ በጎ ነት ቢሆን ወይም ምስጋና፣ እንደ እነዚህ ስላሉት ነገሮች
አስቡ። 9ከእኔ የተማራችሁትን ወይም
የተቀበላችሁትን፣ የሰማችሁትን ወይም ያያችሁትን ማናቸውንም ነገር አድርጉ፤ የሰላም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆናል።

## ላደረጉት ችሮታ የቀረበ ምስጋና

10ከብዙ ጊዜ በኋላ በአዲስ መንፈስ ስለ
እኔ ማሰብ በመጀመራችሁ፣ በጌታ እጅግ

3፥21 ሮሜ8፥29፤ 1ቆሮ15፥43-53፤ ኤፌ1፥19፤ ሩላ3፥4
4፥1 1ቆሮ16፥13፤ ፊል1፥8
4፥2 ፊል2፥2
4፥3 ፊል2፥25፤ ራእ20፥12
4፥4 መዝ85፥6፤ 97፥12፤ ዕንባ3፥18፤ ማቴ5፥12፤ ሮሜ12፥12፤ ፊል3፥1
4፥5 መዝ119፥151፤ 145፥18፤ ዕብ10፥37፤ ያዕ5፥8፡9
4፥6 ማቴ6፥25-34፤ ኤፌ6፥18፤ 1ጢሞ2፥1
4፥7 ኢሳ26፥3፤ ዮሐ14፥27፤ ኤፌ3፥19
4፥9 ሮሜ15፥33፤ 1ቆሮ4፥16
4፥10 2ቆሮ11፥9

*መንግሥተ ሰማይ የአባታችን አገር መሆኑን ከመገንዘብ አኳያ ነው፡፡ የተወለድነው ከላይ ነው (ዮሐ 3፥3)፤ ስማችንም በሕይወት መጽሐፍ ተጽፎአል (4፥3)፤ ሕይወታችን የሚመራው በሰማያዊ ሕግ ነው፤ ልዩ መብትና ርስትም በሰማይ ተጠብቆልናል፡፡*

(2) ጸሎታችን የሚያርገው ወደ ሰማይ ነው (ከ2ዜና 6፥21፤ 30፥27 ጋር ያነጻጽሩ)፤ የተስፋችንም አቅጣጫ ወደዚያው የሚያመራ ነው፡፡ ብዙ ወዳጆቻችንና የቤተሰብ አባሎቻችን አሁን በዚያ አሉ፤ እኛም ወደ እነርሱ የምንሄድበት ጊዜ ሩቅ አይደለም፡፡ ኢየሱስም ለእኛ መኖሪያ እያዘጋጀልን በዚያ ይገኛል፤ ተመልሶ እንደሚመጣ፣ ወደ ራሱም እንደሚወስደን ተስፋ ሰጥቶናል (ዮሐ 14፥2-3 እና ማብ ይመ፤ ከዮሐ 3፥3፤ 14፥1-4፤ ከሮሜ 8፥17፤ ከኤፌ 2፥6፤ ከቆላ 3፥1-3፤ ከዕብ 6፥19-20፤ 12፥22-24፤ ከ1ጴጥ 1፥4-5፤ ከራእ 7፥9-17 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡ ከዚህም የተነሣ የተሻለውን አገር እንናፍቃለን፤ ይኸውም ሰማያዊውን አገር ነው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካችን ተብሎ ሊጠራ አላፈረም፤ ዘላለማዊ ከተማንም ለእኛ አዘጋጅቶልናል (ዕብ 11፥16)፡፡

**4፥4 በጌታ ደስ ይበላችሁ፤** ክርስቲያን የጌታን ጸጋ፣ ቅሩብነትና ተስፋ እያሰበ በጌታ ደስ ሊለውና ሊበረታ ይገባል (1፥4 እና ማብ ይመ)፡፡

**4፥5 ጌታ ቅርብ ነው፤** ጌታ በማንኛውም ጊዜ ሊመጣ እንደሚችል ማመን አለብን፡፡ የጌታ መምጫ ጊዜ ቅርብ እንደ ሆነ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተገልጾአል (ሉቃ 12፥35-40 እና ማብ ይመ)፤ ስለዚህ ሁልጊዜ ጌታን እያገለገልንና ነቅተን እየጠበቅን ዝግጁ ሆነን መገኘት አለብን (ማቴ 24፥36፤ 25፥1-13፤ ሮሜ 13፥12-14)፡፡

**4፥6 ስለ ማንኛውም ነገር አትጨነቁ፤** ከጭንቀት ለመዳን ትልቁ መፍትሔ ጸሎት ነው፤ ይህም የሚሆነው ከሚከተሉት ምክንያቶች የተነሣ ነው፡- (1) በጸሎት ጭንቀታችንና ችግራችንን ሁሉ ስለ እኛ በሚያስበው ታማኝ በሆነው ጌታ ላይ በመጣል፣ ያለንን እምነት እናድሳለን (ማቴ 6፥25-34፤ 1ጴጥ 5፥7)፡፡ (2) ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር ካለን ኅብረት የተነሣ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችንና ሐሳባችንን ለመጠበቅ ይመጣል (ቁ 6-7፤ ኢሳ 26፥3፤ ቆላ 3፥15)፡፡ (3) እግዚአብሔር እኛ እንድናደርገው የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ማድረግ እንድንችል፣ ኀይልን ይሰጠናል (ቁ 13፤ 3፥20 እና ማብ፤ ኤፌ 3፥16 ይመ)፡፡ (4) በሚያስፈልገን ጊዜ ምሕረትን፣ ጸጋንና ርዳታን ከእርሱ እንቀበላለን (ዕብ 4፥16)፡፡ (5) በነገር ሁሉ እግዚአብሔር ለእኛ መልካም ይሆን ዘንድ እንደሚሠራ ርግጠኞች ነን (ቁ 11 እና ማብ፤ ሮሜ 8፥28 እና ማብ ይመ)፡፡

**4፥7 የእግዚአብሔር ሰላም፣ ልባችሁንና … ይጠብቃል፤** በክርስቶስና በቃሉ በሚኖር እውነተኛ ልብ ወደ እግዚአብሔር በምንጸልይበት ጊዜ (ዮሐ 15፥7)፣ የተጨነቀችው ነፍሳችን በእግዚአብሔር ሰላም ትሞላለች፡፡ (1) ይህ ሰላም መንፈስ ቅዱስ የሚፈጥረው ውስጣዊ ጸጥታ ነው (ሮሜ 8፥15-16)፡፡ ይህም ኢየሱስ ቅርብ እንደ ሆነ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር በሕይወታችን ውስጥ ለእኛ በበጎነት እንደሚሠራ ጽኑ እምነትን የያዘ ነው (ሮሜ 8፥28፡32 ይመ፤ ከኢሳ 26፥3 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡ (2) ችግራችንን በጸሎት ወደ እግዚአብሔር በምናቀርብበት ጊዜ፣ በጭንቀትና በሐዘን ሕይወታችን እንዳይናወጥና በክርስቶስ ያለን ተስፋ እየሟሸሸ እንዳይሄድ ይህ ሰላም ልባችንንና ሐሳባችንን ይጠብቃል (ቁ 6፤ ኢሳ 26፥3-4፡12፤ 37፥1-7፤ ሮሜ 8፥35-39፤ 1ጴጥ 5፥7)፡፡ (3) ፍርሀትና ጭንቀት ቢመለሱብን፣ ጸሎት፣ ምስጋናና ምልጃ ልባችንን በሚጠብቀው በእግዚአብሔር ሰላም ውስጥ እንድንሆን ያደርጉናል፤ አሁንም በምንም ሁኔታ እንሁንም፤ በጌታም ደስ ይለናል (ቁ 4 ይመ፤ በገጽ 1150 ላይ፣ *«የእግዚአብሔር ሰላም»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፡፡

**4፥8 ንጹሕ የሆነውን ሁሉ፤** በመጨነቅ ፈንታ እግዚአብሔር የሚሰጠውን ሰላምና ነጻነት ለማግኘት፣ አማኞች እውነት የሆነውን ሁሉ፣ ክቡር የሆነውን ሁሉ፣ ትክክል የሆነውን ሁሉ፣ ንጹሕ የሆነውን ሁሉ … አጥብቀው ማሰብና መፈለግ አለባቸው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህን ነገሮች ብታደርጉ፣ «የሰላም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆናል» (ቁ 9) ይላል፡፡ ርኩስ የሆነውን የዓለም ነገር ብናስብ፣ ውጤቱ የእግዚአብሔርን ደስታ፣ ሰላሙንና ከእርሱ ጋር ያለንን ቅርበት ማጣት ይሆናል፤ ልባችንም በእርሱ የተጠበቀ አይሆንም፡፡

ደስ ይለኛል፤ በርግጥ በተግባር ለመግለጽ
ዕድሉ አልነበራችሁም እንጂ ማሰቡንስ
ታስቡልኝ ነበር። [11]ይህን የምለው ስለቸገረኝ
አይደለም፤ ምክንያቱም በማንኛውም ሁኔታ
ውስጥ ያለኝ ይበቃኛል ማለትን፣ [12]ማጣትን
ዐውቀዋለሁ፤ ማግኘትንም ዐውቀዋለሁ።
ብጠግብም ሆነ ብራብም፣ ባገኝም ሆነ ባጣ
በማንኛውም ሆነ በየትኛውም ሁኔታ ያለኝ
ይበቃኛል የማለትን ምስጢር ተምሬአለሁ።
[13]ኀይልን በሚሰጠኝ በእርሱ ሁሉን ማድረግ
እችላለሁ።

[14]ሆኖም የመከራዬ ተካፋይ ስለ ሆናችሁ
መልካም አድርጋችኋል። [15]ከዚህም በላይ፣
እናንተ የፊልጵስዩስ ሰዎች ራሳችሁ እንደ
ምታውቁት፣ በመጀመሪያ ወንጌልን
በተቀበላችሁ ጊዜ ከመቄዶንያ ስነሣ፣
ከእናንተ በቀር በመስጠትና በመቀበል
የትኛውም ቤተ ክርስቲያን አልተባበረም።
[16]በተሰሎንቄ በነበርሁበት ጊዜ እንኳ፣ በችግሬ
ወቅት ደጋግማችሁ ርዳታ ልካችሁልኛልና።
[17]ይኸውም ትርፉ ለእናንተ እየበዛ እንዲሄድ
እንጂ ስጦታውን ንፌቼ አይደለም።

4፥11
1ጢሞ6፥6፡8፤
ዕብ13፥5
4፥12 1ቆሮ
4፥11፤ 2ቆሮ11፥9
4፥13 2ቆሮ12፥9፤
ኤፌ3፥16፤
ቈላ1፥11፤
1ጢሞ1፥12፤
2ጢሞ4፥17
4፥14 ፊል1፥7
4፥15 ሐሥ16፥9፤
2ቆሮ11፥8፡9፤
ፊል1፥5
4፥16 ሐሥ17፥1፤
1ተሰ2፥9
4፥17
1ቆሮ9፥11፡12
4፥18 2ቆሮ2፥14፤
ፊል2፥25
4፥19 መዝ23፥1፤
ሮሜ2፥4፤
2ቆሮ9፥8
4፥20
ሮሜ11፥36፤
ገላ1፥4፤
1ተሰ1፥3፤
3፥11፡13

[18]የሚያስፈልገኝን ሁሉ፣ ከሚያስፈልገኝም
በላይ ተቀብያለሁ፤ የላካችሁትንም ስጦታ
ከአፍሮዲጡ እጅ ተቀብዬ ተሞልቻለሁ፤
ይህም መዐዛው የጣፈጠ፣ በእግዚአብሔር
ዘንድ ተቀባይነት ያለውና ደስ የሚያሰኝ
መሥዋዕት ነው። [19]አምላኬም እንደ ታላቅ
ባለጠግነቱ መጠን የሚያስፈልጋችሁን
ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ይሞላባችኋል።
[20]ለአምላካችንና ለአባታችን ከዘላለም እስከ
ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።

## የስንብት ሰላምታ

[21]ለቅዱሳን ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ
ሰላምታ አቅርቡልኝ። ከእኔ ጋር ያሉት
ወንድሞችም ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። [22]
ቅዱሳን ሁሉ፣ በተለይም ከቄሳር ቤተ ሰው
የሆኑት ወገኖች ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።
[23]የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ
ከመንፈሳችሁ ጋር ይሁን፤ አሜን[a]።

4፥21 ገላ1፥2 4፥22 ሐሥ9፥13 4፥23 ሮሜ16፥20፤ ገላ6፥18

[a]*4፥23 አንዳንድ ቅጆች አሜን የሚለው የላቸውም*

**4፥11-12 ያለኝ ይበቃኛል ማለትን ... ዐውቀዋለሁ፤** ለመርካት መሠረታዊው ነገር፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ድል አድራጊ ሆነን ብንኖር፣ የሚያስፈልገንን ነገር ሁሉ አሁን ባለንበት ሁኔታ እግዚአብሔር የሰጠን መሆኑን ማስተዋል ነው (1ቆሮ 15፥57፤ 2ቆሮ 2፥14፤ 1ዮሐ 5፥4)። በዚህ ተለዋዋጭ ዓለም ውስጥ አሸናፊዎች ሆነን ለመኖር የሚያስችለን በእኛ ውስጥ የሚፈስው የክርስቶስ ኀይል ነው (ቊ 13፤ 1ጢሞ 6፥8 እና ማብ ይመ)። ይህ ችሎታ በተፈጥሮ አይገኝም፤ የሚገኘው ግን በክርስቶስ ላይ በመደገፍ ብቻ ነው።

**4፥13 ኀይልን በሚሰጠኝ በእርሱ ሁሉን ማድረግ እችላለሁ፤** እንዲፈጽሙ የሚጠበቅባቸውን ነገር ሁሉ ማድረግ ይችሉ ዘንድ፣ የክርስቶስ ኀይልና ጸጋ በአማኞች ውስጥ እውን ሆኖ ይገኛል (በገጽ 1746 ላይ፣ “እምነትና ጸጋ” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**4፥16 ደጋግማችሁ ርዳታ ልካችሁልኛልና፤** የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያው ጳውሎስን በጒዞው ወቅት በሚያስፈልገው ነገር ሁሉ በመርዳት፣ የወንጌልን ተልእኮ የምትደግፍ ቤተ ክርስቲያን ነበረች (ቊ 15-17፤ 1፥4-5)። ለወንጌል ተልእኮ ርዳታ ማድረግ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለውና እርሱን ደስ የሚያሰኝ ነው፤ ይህም መዐዛው እንደሚጣፍጥ፣ በእግዚአብሔርም ዘንድ ተቀባይነት እንዳለውና ደስ እንደሚያሰኝ መሥዋዕት ነው (ቊ 18)። ስለዚህ ታማኝ የሆነውን የወንጌል አገልጋይ ለመርዳት የምናደርገው፣ በእግዚአብሔር ፊት እንደሚቀርብ መሥዋዕት ይቈጠራል። ከእነዚህ አነስተኛ ከሆኑት ወንድሞቻችን ለአንዱ የሚደረገው ነገር ለጌታ እንደ ተደረገ ይቈጠራል (ማቴ 25፥40)።

**4፥19 የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ... ይሞላባችኋል፤** እግዚአብሔር አብ ለልጆቹ የሚያደርገውን የፍቅር እንክብካቤ ጳውሎስ ከዚህ ላይ በአጽንዖት ይገልጻል። በሚያስፈልገን ነገር ሁሉ (መንፈሳዊም ቍሳዊም በሆነው) እግዚአብሔርን ከለመንነው፣ የሚያስፈልገንን ነገር ሁሉ ይሞላልናል። በክርስቶስ ኢየሱስ ሁሉንም ያሳካልናል። ከክርስቶስ ጋር አንድ በመሆንና ኅብረት በመፍጠር ብቻ፣ የእግዚአብሔርን መግቦት መቀበል እንችላለን። እግዚአብሔር የሚያደርገውን ጥንቃቄና ርዳታ በተመለከተ፣ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ተስፋን ከሚሰጡና መጽናናትን ከሚያስገኙ ከብዙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፤ ዘፍ 28፥15፤ 50፥20፤ ዘፀ 33፥14፤ ዘዳ 2፥7፤ 32፥7-14፤ 33፥27፤ ኢሱ 1፥9፤ 1ሳሙ 7፥12፤ 1ነገ 17፥6፡16፤ 2ዜና 20፥17፤ መዝ 18፥35፤ 23፤ 121፤ ኢሳ 25፥4፤ 32፥2፤ 40፥11፤ 41፥10፤ 43፥1-2፤ 46፥3-4፤ ኢል 2፥21-27፤ ሚል 3፥10፤ ማቴ 6፥25-34፤ 14፥20፤ 23፥37፤ ሉቃ 6፥38፤ 12፥7፤ 22፥35፤ ዮሐ 10፥27-28፤ 17፥11፤ ሮሜ 8፥28፡31-39፤ 2ጢሞ 1፥12፤ 4፥18፤ 1ጴጥ 5፥7 ይመ፤ በገጽ 100 ላይ፤ “መግቦተ እግዚአብሔር” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ቈላስይስ ሰዎች

*አስተዋፅኦ*

*መግቢያ* (1፥1-12)

(ሀ) ክርስቲያናዊ ሰላምታ (1፥1-21)

(ለ) የቈላስይስ ምእመናን ስላላቸው እምነት፣ ፍቅርና ተስፋ የቀረበ ምስጋና (1፥3-8)

(ሐ) ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው ማደግ የሚደረግ ጸሎት (1፥9-12)

I. ታላቅ አስተምህሮ፤ የአማኝ መዋጀት (1፥13—2፥23)

(ሀ) የክርስቶስ ፍጹም ታላቅነት (1፥13-23)

1. በእኛ ፈንታ መከራን የተቀበለ አዳኝ (1፥13-14 ይመ፤ ከ1፥20:22 ጋር ያነጻጽሩ)
2. የፍጥረት ሁሉ ጌታ (1፥15-17)
3. የቤተ ክርስቲያን ራስ (1፥18)
4. ሁሉንም ነገር ከእግዚአብሔር ጋር ያስታረቀ (1፥19-20)
5. የቈላስይስን ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያስታረቀ (1፥21-23)

(ለ) ጳውሎስ በክርስቶስ የተገለጠውን የእግዚአብሔር ምስጢር ማገልገሉ (1፥24—2፥7)

1. የክርስቶስ መከራ ተካፋይ በመሆን የጐደለውን መሙላት (1፥24-25)
2. አማኞችን በክርስቶስ ፍጹማን ማድረግ (1፥26—2፥7)

(ሐ) የሐሰት ትምህርትን በመቃወም የተሰጠ ማስጠንቀቂያ (2፥8-23)

1. ችግር፤ በክርስቶስ ላይ ያልተመሠረተ ትምህርትን ማስተማር (2፥8) መፍትሔ፤ በክርስቶስ ፍጹም መሆን (2፥9-15)
2. ችግር፤ በክርስቶስ ላይ ያልተመሠረተ ሃይማኖታዊ ልምምድ (2፥16-20) መፍትሔ፤ ከክርስቶስ ጋር መሞታችን (2፥20)

II. ተግባራዊ መመሪያዎች፤ የአማኙ ሕይወት (3፥1—4፥6)

(ሀ) የአማኙ የግል ጠባይ (3፥1-17)

1. ክርስቶስ ሕይወታችን በሚሆንበት ጊዜ (3፥1-4)
2. አሮጌውን በኀጢአት የመመላለስ ሕይወት መተው (3፥5-9)
3. በክርስቶስ አዲሱን ሰው መልበስ (3፥10-17)

(ለ) የአማኙ ቤተ ሰባዊ ግንኙነት (3፥18—4፥1)

1. ሚስቶችና ባሎች (3፥18-19)
2. ልጆችና ወላጆች (3፥20-21)
3. ባሮችና ጌቶች (3፥22—4፥1)

(ሐ) የአማኙ መንፈሳዊ ምሳሌነት (4፥2-6)

1. በጸሎት የተጠመደ ሕይወት (4፥2-4)
2. በውጭ ካሉት ሰዎች ጋር በጥበብ መመላለስ (4፥5)
3. በጸጋ የተሞላ ቃልን መናገር (4፥6)

*መደምደሚያ* (4፥7-18)

**ጸሐፊው፤** *ጳውሎስ*

**ዋና ሐሳብ፤** *የክርስቶስ የበላይነት*

**የተጻፈበት ጊዜ፤** *በ62 ዓ.ም. ሳይሆን አይቀርም*

### ታሪካዊ ዳራ

የቈላስይስ ከተማ በቀጥታ ከኤፌሶን በስተምሥራቅ 160 ኪሎ ሜትር በመራቅ፣ በትንሹ እስያ ደቡብ ምዕራብ ክፍል ከሎዶቅያ አጠገብ (ከ4፥16 ጋር ያነጻጽሩ) ትገኝ ነበር። የቈላስይስ ቤተ ክርስቲያን መመሥረት፣ ጳውሎስ በኤፌሶን ከተማ ለሦስት ዓመት የነበረው ስኬታማ የሆነ የተለየ አገልግሎት (ሐሥ 20፥31) ውጤት ነው፤ ይህም አገልግሎት ታላቅና እጅግ የተደነቀ በመሆኑ፣ በእስያ አውራጃ ይኖሩ የነበሩት የአይሁድና የግሪክ ሰዎች ሁሉ የጌታን ቃል ለመስማት ቻሉ (ሐሥ 19፥10)። ጳውሎስ በአካል ወደ ቈላስይስ ከተማ ሄዶ ባያውቅም (2፥1)፣ ከመንፈሳዊ ልጆቹ አንዱ በሆነውና በሥራው በመጠመድም አብሮት ያገለግል በነበረው በቈላስይስ ሰው በኤጳፍራ አማካይነት ከቤተ ክርስቲያኒቱ ጋር ግንኙነት ነበረው (1፥7፤ 4፥12)።

ይህን መልእክት ለመጻፍ ሐዋርያው ጳውሎስን ያነሣሣው፣ የቈላስይስን ቤተ ክርስቲያን የወደፊት መንፈሳዊ ሁኔታ አደጋ ላይ የሚጥሉ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ብቅ ማለት ነበር (2፥8)። የቈላስይስ ቤተ ክርስቲያን መሪና ምናልባትም መሥራች የሆነው ኤጳፍራ፣ ጳውሎስን ለመጐብኘትና በቈላስይስ ያለውን ሁኔታም ሊነግረው ወደ እርሱ በሄደ ጊዜ (1፥8፤ 4፥12)፣ ጳውሎስ ሐሳቡን የገለጸው ይህን መልእክት በመጻፍ ነበር። ጳውሎስ በዚህ ጊዜ እስረኛ ነበር (4፥3፡10፡18)፤ ምናልባትም በዚህ ጊዜ በሮም እስር ቤት ሆኖ (ሐሥ 28፥16-31) ወደ ቄሣር ይግባኝ በማለት ውጤቱን ይጠባበቅ ነበር (ሐሥ 25፥11-12)። ጳውሎስን በመወከል ይህን መልእክት ለቈላስይስ ቤተ ክርስቲያን ወስዶ ያስረከበው፣ ከጳውሎስ ጋር አብሮ ያገለግል የነበረው ቲኪቆስ ነው (4፥7)።

በቈላስይስ የነበረው የኑፋቄ ትምህርት ትክክለኛ ሁኔታ በመልእክቱ ውስጥ ግልጽ ሆኖ ያልተጠቀሰው መልእክቱ የተጻፈላቸው የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ጉዳዩን በሚገባ ስለሚያውቁት ነው። የሐሰት ትምህርትን በመቃወም ጳውሎስ ከተናገረው ቃል እንደምንረዳው፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ማእከላዊነት የሚያጣጥለውና በሌላም ነገር የሚተካው ይህ የኑፋቄ ትምህርት ከክርስትና ትምህርት ጋር የተደባለቀ እንግዳ ትምህርት ነው፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭም የሆነውን የአይሁድን ወግና የአረማውያንን ፍልስፍና የያዘ ሲሆን፣ በዚህ ዘመን ከሚገኘው ድብልቅ ከሆነው የጣዖት አምልኮ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው።

### ዐላማ

ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው፣ (1) በፍጥረት ውስጥ፣ በተገለጠው እውነት በድነትና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን የክርስቶስን ማእከላዊነትና የበላይነት ገፍቶ በማስወጣት፣ ሌላ ነገር የሚያስገባውን በቈላስይስ የነበረውን አደገኛ የሐሰት ትምህርት ለመዋጋት፣ (2) በክርስቶስ የሚገኘው አዲስ ሕይወት ትክክለኛ ባሕርይ ምን እንደሚመስልና ከአማኙ የሚፈለገው ምን እንደ ሆነ በአጽንዖት ለመግለጽ ነው።

### ቅኝት

ሐዋርያው ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያን ሰላምታ ካቀረበና በዚያ የሚገኙትን ቅዱሳን ስላላቸው እምነት፣ ፍቅር፣ ተስፋና እድገት ካመሰገነ በኋላ በሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ያተኵራል፤ እነዚህም ትክክለኛ አስተምህሮና (1፥13—2፥23) ተግባራዊ ምክር ናቸው (3፥1—4፥6)። ጳውሎስ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እውነተኛ ባሕርይና ክብር ከሥነ መለኮት አንጻር ይገልጻል። እርሱ የማይታየው አምላክ አምሳል ነው (1፥15)፤ የመለኮት ሙላት ሁሉ በአካል በእርሱ ይኖራል (2፥9)፤ ሁሉ በእርሱ ተፈጥሮአል (1፥16-17)፤ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው (1፥18) እንዲሁም ፍጹም የሆነ የድነታችን ምንጭ ነው (1፥14፡20-22)። ክርስቶስ ድነትን ለማስገኘት ፍጹም የሆነ ብቃት አለው፤ በቈላስይስ የነበረው የኑፋቄ ትምህርት ግን ፈጽሞ ድነትን የሚያስገኝ አልነበረም፤ ይህም ትምህርት ባዶ ከመሆኑ ባሻገር ማታለል ያለበትና የሰው ፈጠራ ነው (2፥8)፤ መንፈሳዊነት የጐደለውና ትዕቢትን ያዘለ ከመሆኑም በላይ፣ ልቅ የሆነ ሥጋዊ ፍላጎትን ለመቈጣጠር ኀይል አልነበረውም (2፥23)።

በዚህ ልባዊ ምክሩ በክርስትና ሕይወት ለማደግ ብቸኛው መንገድ በክርስቶስ ፍጹም ብቃት ላይ የተመሠረተ ሕይወት መሆኑን ጳውሎስ አጥብቆ ያሳስባል። ክርስቶስ በውስጣችን የመኖሩ እውነታ (1፥27) በክርስቲያናዊ ጠባይ (3፥1-17)፣ በቤተ ሰብ ውስጥ ባለ ግንኙነት (3፥18—4፥1) እና መንፈሳዊ ሥነ ሥርዐትን በማሳየት ረገድ መገለጽ አለበት (4፥2-6)።

### ልዩ ገጽታ

ይህን መልእክት ሦስት ዋና ዋና ገጽታዎች ልዩ ያደርጉታል፤ (1) ከሌሎች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ይልቅ፣ የቈላስይስ መልእክት በክርስቶስ የበላይነትና አማኝ በእርሱ ውስጥ ባለው ፍጹምነት ጣምራ እውነት ላይ ያተኵራል። (2) ክርስቶስ ፍጹም መለኮት እንደ ሆነ አጠንክሮ የሚገልጽ ሲሆን (2፥9)፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ክብሩን በተመለከተ ከሚጠቀሱት ዋና ዋና ክፍሎች አንዱ የሚገኘው በዚህ መልእክት ውስጥ ነው (1፥15-23)። (3) የቈላስይስ መልእክት ይዘቱ ከኤፌሶን መልእክት ጋር ስለሚመሳሰልና ሁለቱም የተጻፉበት ጊዜ ተመሳሳይ ስለ ሆነ፣ አንዳንድ ጊዜ "ተወራራሽ ሁለት መልእክቶች" በመባል ይታወቃሉ (ከሁለቱ መልእክቶች አስተዋፅኦ ጋር ያነጻጽሩ)።

### ቈላስይስን ማንበብ

ሙሉውን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ የቈላስይስ መልእክት ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በአምስት ቀን ውስጥ መነበብ አለበት፦

❑ 1፥1-23 ❑ 1፥24—2፥5 ❑ 2፥6-23 ❑ 3፥1—4፥1 ❑ 4፥2-18

*ማስታወሻ*

1 በእግዚአብሔር ፈቃድ የክርስቶስ
ኢየሱስ ሐዋርያ ከሆነው ከጳውሎስና
ከወንድማችን ከጢሞቴዎስ፤
2በቈላስይስ ለሚኖሩ፣ በክርስቶስ ለሆኑ
ቅዱሳንና ታማኝ[ሀ] ወንድሞች፤
ከእግዚአብሔር ከአባታችን[ለ] ጸጋና ሰላም
ለእናንተ ይሁን።

## ምስጋናና ጸሎት

3ስለ እናንተ በምንጸልይበት ጊዜ
የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት
እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እናመሰግናለን፤
4ምክንያቱም በክርስቶስ ኢየሱስ ስላላችሁ
እምነትና ለቅዱሳን ሁሉ ስላላችሁ ፍቅር
ሰምተናል፤ 5ይህም የሆነው በሰማይ
ተዘጋጅቶ ከተቀመጠላችሁ ተስፋ የተነሣ
ነው፤ ስለዚህ ተስፋ በወንጌል የእውነት
ቃል አስቀድማችሁ ሰማችሁ፤ 6ይህም
ወደ እናንተ ደርሶአል። ይህንም ወንጌል
ከሰማችሁበትና የእግዚአብሔርን ጸጋ በእውነት
ከተረዳችሁበት ቀን ጀምሮ በዓለም ዙሪያ
እየሠራ እንዳለ ሁሉ በእናንተም ዘንድ
ፍሬ እያፈራና እያደገ ነው። 7ይህንም ስለ
እኛ[ሐ] የክርስቶስ ታማኝ አገልጋይ የሆነው፣
አብሮንም በአገልግሎት የተጠመደው
ተወዳጁ ኤጳፍራ አስተማራችሁ፤ 8ደግሞም
በመንፈስ ስላላችሁ ፍቅር ነገረን።
9ከዚህ የተነሣ እኛ ደግሞ ይህን
ከሰማንበት ቀን ጀምሮ እግዚአብሔር የፈቃዱን
ዕውቀት በመንፈሳዊ ጥበብና መረዳት ሁሉ
ይሞላችሁ ዘንድ ስለ እናንተ መጸለይና
መለመን አላቋረጥንም፤ 10የምንጸልየውም
ለጌታ እንደሚገባ እንድትኖሩና በሁሉም
ደስ እንድታሰኙት ነው፤ ይኸውም
በመልካም ሥራ ሁሉ ፍሬ እያፈራችሁ
እግዚአብሔርን በማወቅ እያደጋችሁ፣
11ታላቅ ጽናትና ትዕግሥት ይኖራችሁ
ዘንድ፣ እንደ ክቡር ጕልበቱ መጠን በኀይል
ሁሉ እየበረታችሁ፣ ደስ እየተሰኛችሁ፣
12በቅዱሳን ርስት በብርሃን ተካፋዮች ለመሆን
ያበቃንን[መ] አብን እንድታመሰግኑ ነው።

1፥1 ሐሥ16፥1፤ 1ቆሮ1፥1፤ 2ቆሮ1፥1
1፥2 ሮሜ1፥7፤ ቈላ4፥18
1፥3 ሮሜ1፥8
1፥4 ሐሥ9፥13፤ ገላ5፥6፤ ኤፌ1፥15፤ ፊሞ1፥5
1፥5 ቍ23፤ 1ተሰ5፥8፤ 2ጢሞ2፥15፤ ቲቶ1፥2፤ 1ጴጥ1፥4
1፥6 ቍ23፤ ዮሐ15፥16፤ ሮሜ10፥18
1፥7 ቈላ4፥7፡12፤ ፊሞ1፥23
1፥8 ሮሜ15፥30
1፥9 ቍ4፤ ሮሜ1፥10፤ ኤፌ1፥15፡17፤ 5፥17
1፥10 ቍ6፤ 2ቆሮ5፥9፤ ኤፌ4፥1
1፥11 ኤፌ4፥2፤
1፥11 ፊል4፥13 1፥12 ሐሥ20፥32፤ 26፥18፤ 2ጴጥ1፥11

*[ሀ]1፥2 ወይም የሚያምኑ*
*[ለ]1፥2 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ከአባትና ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ*
*[ሐ]1፥7 አንዳንድ የጥንት ቅጆች እናንተ ይላሉ።*
*[መ]1፥12 ወይም ያበቃችሁን*

**1፥2 በቈላስይስ ለሚኖሩ ... ታማኝ ወንድሞች፤** ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን መልእክት ለቈላስይስ ሰዎች የጻፈው፣ ለክርስቶስ ሙሉ በሙሉ ራስን አሳልፎ መስጠትና የሐዋርያትን አስተምህሮ መከተል ሙሉ ድነትን ለማግኘት የሚያበቃ አይደለም ብለው የሚያስተምሩ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች፣ ቀስ በቀስ ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ሠርገው እየገቡ ስለ ነበር ነው። ይህ የሐሰት ትምህርት የሰውን ፍልስፍናና ባህል ከወንጌል ጋር አደባልቆ የያዘ ሲሆን (2፥8)፣ መላእክት በእግዚአብሔር ፊት ሰውን እንደሚያማልዱ በመቍጠር፣ መላእክት እንዲመለኩ ያሳስባል (2፥18)፤ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች በአይሁድ ሃይማኖታዊ ሥርዐት መሠረት የተደነገጉ ደንቦች እንዲከበሩ አዘዙ (2፥16፡21-23)፤ በራእይ አገኘነው ለሚሉት መገለጥ ስፍራ በመስጠት (2፥18)፣ ስሕተታቸውን ለማለባበስ ሞከሩ። (1) ከዚህ ስሕተት በስተጀርባ የሚገኘው ዋና ፍልስፍና ዛሬ እየተንጸባረቀ የሚገኘው ኢየሱስ ክርስቶስና የመጀመሪያው የአዲስ ኪዳን ወንጌል መንፈሳዊ ፍላጎታችንን ለማርካት በቂ አይደሉም በሚለው ትምህርት በኩል ነው (2ጴጥ 1፥3 እና ማብ ይመ)።

(2) ክርስቶስ አዳኝ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን ራስና የፍጥረተ ዓለም ሁሉ ጌታ መሆኑን በማመልከት ጳውሎስ ይህን የኑፋቄ ትምህርት ለማፍረስ ቈርጦ ተነሥቶአል። ስለዚህ የሚቤዠንና የዘላለም ሕይወት የሚሰጠን የሰው ፍልስፍናና ጥበብ ሳይሆን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲሁም የእርሱ ኀይል በውስጣችን መሆኑ ነው። አማላጆች አስፈላጊ አይደሉም፤ ወደ እርሱ በቀጥታ መቅረብ ይገባናል።

(3) አማኝ መሆን ማለት፣ በክርስቶስና በወንጌሉ ማመን፣ በእርሱ መታመን፣ እርሱን መውደድና በእርሱ ህልዎት ውስጥ መኖር ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ምንም ነገር መጨመር አያስፈልግም፤ ዘመናዊና ሰባዊ ጥበብ ወይም ፍልስፍና መቀላቀል የለበትም።

**1፥9 የፈቃዱን ዕውቀት፤** የእግዚአብሔር የፍቃዱ ዕውቀት የሚገኘው በጸሎት በመትጋትና ለቃሉ ታማኝ በመሆን፣ ከእርሱም ጋር ኅብረት በማድረግ ነው። መንፈሳዊ ጥበብንና መረዳትን የሚሰጠን፣ ልባችንንና ሕይወታችንን የሚለውጥልን፣ እንደዚህ ዐይነቱ ዕውቀት ብቻ ነው።

**1፥9-12 ስለ እናንተ መጸለይና መለመን አላቋረጥንም፤** በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጳውሎስ ከጸለያቸው አራት ታላላቅ ሐዋርያዊ ጸሎቶች መካከል ይህኛው አንዱ ሲሆን፣ የተናገረውም በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ነው (ሌሎቹ ሦስቱ የሚገኙት በኤፌ 1፥16-19፤ 3፥14-19 እና በፊል 1፥9-11 ነው)። ከዚህ ጸሎት ለልጆቻችን፣ ለክርስቲያን ወገኖች፣ ለሚሲዮናውያን፣ ለመጋቢያን ወዘተ እንዴት መጸለይ እንደሚገባን እንማራለን። መጸለይ ያለብንም የሚከተሉት እውን እንዲሆኑ ነው፦ (1) የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲያውቁ፣ (2) መንፈሳዊ ጥበብን እንዲያገኙ፣ (3) ጌታን ደስ የሚያሰኝ ቅዱስ ኑሮ እንዲኖሩ፣ (4) ለክርስቶስ ፍሬ እንዲያፈሩ፣ (5) በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በመንፈስ ቅዱስ እንዲጠነክሩ፣ (6) በእምነትና በጽድቅ እንዲጸኑ፣ (7) እግዚአብሔር አብን እንዲያመሰግኑ፣ (8) ሰማያዊውን ነገር ተስፋ ማድረጋቸውን እንዲቀጥሉ፣ (9) የክርስቶስ ቅሩብነት በሕይወታቸው እንዲታይ፣ (10) የክርስቶስን ፍቅር እንዲያውቁ፣ (11) በእግዚአብሔር ሙላት እንዲሞሉ፣ (12) ፍቅርንና ምሕረትን ለሌሎች እንዲገልጹ፣ (13) ክፋውን እንዲለዩ፣ (14) ቅንና ነቀፋ የሌለባቸው ሆነው እንዲገኙ እንዲሁም (15) የጌታን ዳግም ምጽአት በናፍቆት እንዲጠባበቁ።

**1፥11 እንደ ክቡር ጕልበቱ መጠን በኀይል ሁሉ እየበረታችሁ፤** ለጌታ እንደሚገባ ለመኖር (ቍ 10) በኀይሉ መጠንከር ይገባል። ይህ ኀይል ከእግዚአብሔር ከራሱ ሕይወት ሳይቋረጥ የምንቀበለው ነው። ከዚህ ሌላ ኀጢአትን፣ ሰይጣንና ዓለምን ለማሸነፍ የሚያስችለን ምንም ነገር የለም (ከፊል 4፥13 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1746 ላይ፣ “እምነትና ጸጋ” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

[13]እርሱ ከጨለማ አገዛዝ ታደገን፤
ወደሚወደው ልጁ መንግሥትም አሻገረን፤
[14]በእርሱም መዋጀትን በደሙ[ሀ] አግኝተናል፤
ይህም የኀጢአት ይቅርታ ነው።

## ክርስቶስ ከሁሉ በላይ

[15]እርሱ የማይታየው አምላክ አምሳል ነው፤
ከፍጥረት ሁሉ በፊት[ለ] በኵር ነው፤ [16]ሁሉ
ነገር በእርሱ ተፈጥሮአል፤ በሰማይና በምድር
ያሉ፣ የሚታዩና የማይታዩ፣ ዙፋናት ቢሆኑ
ወይም ኀይላት፣ ገገሮች ቢሆኑ ወይም ባለ
ሥልጣናት፣ ሁሉም ነገር በእርሱና ለእርሱ
ተፈጥሮአል። [17]እርሱ ከሁሉ በፊት ነው፤
ሁሉም ነገር በአንድ ላይ ተያይዞ የጸናው
በእርሱ ነው። [18]እርሱ አካሉ የሆነችው የቤተ
ክርስቲያን ራስ ነው፤ በሁሉ ነገር የበላይነት
ይኖረው ዘንድ እርሱ የመጀመሪያ፣ ከሙታን
መካከልም በኵር ነው። [19]እግዚአብሔርም
ሙላቱ ሁሉ በእርሱ ይሆን ዘንድ ወዶአልና፤
[20]በመስቀሉ ላይ በፈሰሰው ደሙ ሰላምን በማ
ድረግ በምድርም ሆነ በሰማይ ያለውን ነገር
ሁሉ በእርሱ በኩል ከራሱ ጋር አስታረቀ።
[21]ከክፉ ባሕርያችሁ የተነሣ[ሐ] ቀድሞ
ከእግዚአብሔር የተለያችሁ በአሳባችሁም
ጠላቶች ነበራችሁ። [22]አሁን ግን ነውርና
ነቀፋ የሌ ለባችሁ ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ
ፊት ሊያቀርባችሁ፣ በክርስቶስ ሥጋ
በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ፤ [23]ይህም
የሚሆነው በእምነታችሁ ተመሥርታችሁና
ተደላድላችሁ በመቆም ከሰማችሁት የወንጌል
ተስፋ ሳትናወጡ ጸንታችሁ ብትኖሩ ነው።
እናንተ የሰማችሁትና ከሰማይ በታች ላለ
ፍጥረት ሁሉ የተሰበከውም ወንጌል ይኸው
ነው፤ እኔም ጳውሎስ ለዚህ ወንጌል አገልጋይ
ሆንሁ።

## ጳውሎስ ስለ ቤተ ክርስቲያን ያሳየው ትጋት

[24]ስለ እናንተ በተቀበልሁት መከራ አሁንም

1፥13 ማቴ3፥17፤ ሐሥ26፥18፤ 2ጴጥ1፥11
1፥14 ሮሜ3፥24፤ ኤፌ1፥7
1፥15 ቍ18፤ ዮሐ1፥18፤ 14፥9፤ 1ጢሞ1፥17፤ ዕብ11፥27
1፥16 ዮሐ1፥3፤ ሮሜ11፥36፤ ኤፌ1፥20:21
1፥17 ዮሐ1፥2
1፥18 ቍ 15:24፤ መዝ89፥27፤ ሐሥ26፥23፤ ሮሜ8፥29፤ 1ቆሮ12፥27፤ ኤፌ1፥22 ዕብ1፥6፤ ራእ1፥5
1፥19 ዮሐ1፥16፤ ኤፌ1፥5
1፥20 ሉቃ2፥14፤ ሮሜ5፥10፤ ኤፌ1፥10፤ 2፥13
1፥21 ሮሜ5፥10፤ ኤፌ2፥3
1፥22 ቍ20፤ ሮሜ5፥10፤ 7፥4፤ 2ቆሮ4፥14፤ ኤፌ1፥4፤ 5፥27
1፥23 ቍ5:6:25፤ ሮሜ10፥18፤ 11፥22፤ 1ቆሮ3፥5፤ ኤፌ3፥17 1፥24 1ቆሮ12፥27፤ 2ቆሮ1፥5፤ 6፥10

*ሀ1፥14 አንዳንድ ቅጆች በደሙ የሚለው ቃል የላቸውም*
*ለ1፥15 ወይም በላይ*
*ሐ1፥21 ወይም በክፉ ባሕርያችሁ እንደሚታየው*

1፥13 **ከጨለማ ግዛት፤** ከጨለማ ግዛትና ኀይል ማለትም ከሰይጣን ኀይል (ማቴ 4፥8-11፤ ሉቃ 22፥52-53፤ ኤፌ 2፥2፤ 6፥12) ነጻ መውጣት በድነት ውስጥ የተከናወነ ዐቢይ ጕዳይ ነው። አሁን ግን በክርስቶስ መንግሥት ውስጥ ነን፤ በእርሱም አገዛዝ ሥር እንገኛለን (ሮሜ 6፥17-22፤ ሐሥ 26፥18 እና ማብ ይመ)።

1፥15 **ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር፤** የዚህ ሐረግ ሐሳብ ክርስቶስ ፍጡር ነበር የሚል ለማለት አይደለም፤ ነገር ግን "በኵር" በመሠረቱ የብሉይ ኪዳን ቃል ሲሆን፣ ከዚህ የተለየ ሌላ ትርጕም አለው፤ ይኸውም "ቀዳሚ ስፍራን የሚይዝ"፣ "ወራሽ" ወይም "ከፍተኛ" ማለት ነው (ዘፀ 4፥22፤ ኤር 31፥9፤ ምንም እንኳ ዳዊት በኵር ልጅ ባይሆንም፣ ገዥነቱን የሚያሳየውን በመዝ 89፥27 ላይ ይመልከቱ)። ክርስቶስ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ልጅ እንደ መሆኑ መጠን፣ የፍጥረት ሁሉ ወራሽና ገዥ ነው (ከቍ 18፤ ከዕብ 1፥1-2 ጋር ያነጻጽሩ)።

1፥16 **ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሮአል፤** ጳውሎስ የክርስቶስን የመፍጠር ሥራ ለማረጋገጥ ይናገራል። (1) ቍሳዊና መንፈሳዊ የሆነው ነገር ሁሉ ሊኖር የቻለው ክርስቶስ በመፍጠር ሥራ ውስጥ ከነበረው ጥልሕ ሚና የነተሣ ነው (ዮሐ 1፥3፤ ዕብ 1፥2)። (2) ሁሉም ነገር በአንድ ላይ የተያያዘውና የጸናው በእርሱ ነው (ቍ 17፤ ዕብ 1፥3 ይመ፤ በገጽ 26 ላይ፣ "*ፍጥረት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

1፥18 **ከሙታንም መካከል በኵር፤** ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈሳዊና በማይሞት አካል ከሙታን መካከል በመነሣት ቀዳሚ ነው (1ቆሮ 15፥20)። በትንሣኤው ቀን ኢየሱስ የቤተ ክርስቲያን ራስ ሆኖአል። የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ጅማሬ ኢየሱስ ከሙታን በነተሣበትና ደቀ መዛሙርት መንፈስ ቅዱስን በተቀበሉበት ጊዜ ነው (በገጽ 1646 ላይ፣ "*የደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን መቀበል*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። ክርስቶስ "ከሙታን መካከል በኵር" መሆኑ፣ ከዚህ በኋላ እርሱ የሞተላቸው ሁሉ ትንሣኤ እንደሚያገኙ ያመለክታል።

1፥19 **ሙላቱ ሁሉ በእርሱ ይሆን ዘንድ፤** ጳውሎስ የክርስቶስን አምላክነት በጣም ግልጽ በሆነ ቃል ይናገራል። የመለኮት ሙላትና ፍጹምነት ከነይሉና ከባሕርዩ ሁሉ ጋር በክርስቶስ ይኖራል (2፥9 ይመ፤ ከዕብ 1፥8 ጋር ያነጻጽሩ)።

1፥20 **ነገር ሁሉ … ከራሱ ጋር አስታረቀ፤** ሰውና በፍጥረተ ዓለም ያለው ነገር ሁሉ ወደ አንድነትና ወደ ስምምነት ሊመጣ የቻለው በክርስቶስ ነው (ከቍ 16-18 ጋር ያነጻጽሩ)። እንዲህም ሲባል ሰዎች ሁሉ ከፈቃዳቸው ውጭ ታርቀዋል ማለት አይደለም። በክርስቶስ የተገኘውን ዕርቅ የማይቀበል ሰው የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖ ይኖራል (ሮሜ 2፥4-10)።

1፥23 **በእምነታችሁ … ጸንታችሁ ብትኖሩ፤** ክርስቲያኖች በመጨረሻ ነውርና ነቀፋ የሌለባቸው ቅዱሳን ሆነው በክርስቶስ ፊት ለመቅረብ (ቍ 22) ጳውሎስ እንደሚናገረው ከሰው በኩል የሚጠበቀውን ኀላፊነት ተወጥተውና ሥራቸውን አከናውነው መገኘታቸው እጅግ አስፈላጊ ነው፤ በመሆኑም ክርስቲያኖች (1) በእምነታቸው ማለትም ኢየሱስ ጌታና አዳኝ እንደ ሆነ በማመን ጸንተው መቆም (በገጽ 1746 ላይ፣ "*እምነትና ጸጋ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)፤ (2) በክርስቶስና በሐዋርያት ትምህርት መመሥረትና ተደላድለው መቆም፤ (3) ከሰሙት የወንጌል ተስፋ ሳይናወጡ ማለትም ቀድሞ ወደ ነበሩበት ተስፋ ወደሌለውና የሕይወት መጥፋት ወደሚታይበት ሁኔታ ሳይመለሱ ጸንተው መኖር ይገባቸዋል (3፥5-11፤ ዕብ 10፥38 እና ማብ ይመ)።

1፥24 **ስለ እናንተ በተቀበልሁት መከራ፤** ክርስቶስ አሁንም መከራ እየተቀበለ እንደ ሆነ ጳውሎስ ተረድቶአል፤ መከራ እየተቀበለ ያለውም ለድነታችን ሳይሆን፣ ሕዝቡ ወደ ጠፉት ሰዎች ወንጌልን ይዘው በሚሄዱበት ጊዜ በሚገጥማቸው መከራ ጌታም ከሕዝቡ ጋር ካለው ግንኙነት የተነሣ የመከራቸው ተካፋይ በመሆኑ ነው (ከሐሥ 9፥4 ጋር ያነጻጽሩ)። በክርስቶስ መከራ ይካፈል ዘንድ ስለ ተፈቀደለት ጳውሎስ ሐሤት ያደርጋል (የጳውሎስን መከራ በሚመለከት ፊል 3፥10 ይመ፤ ከ2ቆሮ 1፥4-5 እና ማብ፤ 4፥7 እና ማብ፤ 11፥23 እና ማብ ጋር ያነጻጽሩ)።

ደስ ይለኛል፤ ክርስቶስ ስለ አካሉ ስለ ቤተ
ክርስቲያን ከተቀበለው መከራ የጐደለውን
በሥጋዬ አሟላለሁ። 25የእግዚአብሔርን ቃል
በሙላት እንዳቀርብላችሁ ከእግዚአብሔር
በተሰጠኝ ዐደራ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ
ሆኛለሁ፤ 26ይህም ቃል ከዘመናትና
ከትውልዶች ተሰውሮ ምስጢር ሆኖ ቈይቶ
ነበር፤ አሁን ግን ለቅዱሳኑ ተገልጦአል።
27ለእነርሱም እግዚአብሔር የዚህ ምስጢር
ክብር ባለ ጠግነት በአሕዛብ መካከል ምን
ያህል እንደ ሆነ ለማሳወቅ መረጠ፤ እርሱም
የክብር ተስፋ የሆነው በእናንተ ውስጥ
ያለው ክርስቶስ ነው።
28እኛም እያንዳንዱን ሰው በክርስቶስ
ፍጹም አድርገን ማቅረብ እንችል ዘንድ፣
ሰውን ሁሉ በጥበብ ሁሉ እየመከርንና
እያስተማርን እርሱን እንሰብካለን፤ 29እኔም
በብርታት በውስጤ በሚሠራው በእርሱ ኀይል
ሁሉ እየታገልሁ ለዚህ ዐላማ እጥራለሁ።
2 ስለ እናንተና በሎዶቅያ ስላሉት
እንዲሁም በአካል አይተውኝ ስለማያውቁ
ሁሉ ምን ያህል እየተጋደልሁ እንደ ሆነ
እንድታውቁ እፈልጋለሁ፤ 2ደግሞም ልባቸው
እንዲጽናናና በፍቅር እንዲተሳሰሩ፣ ፍጹም
የሆነውን የመረዳት ብልጥግና አግኝተው
የእግዚአብሔር ምስጢር የሆነውን ክርስቶስን
እንዲያውቁ እተጋለሁ፤ 3የተሰወረ የጥበብና
የዕውቀት ሀብት ሁሉ የሚገኘው በእርሱ
ዘንድ ነውና።* 4ማንም ንግግር በማሳመር
እንዳያታልላችሁ ይህን እነግራችኋለሁ።
5ምንም በሥጋ ከእናንተ ርቄ ብገኝ
በመንፈስ ከእናንተ ጋር ነኝና በሥርዐት
መኖራችሁንና በክርስቶስ ያላችሁን ጽኑ
እምነት እያየሁ ደስ ይለኛል።

## ከሰው ሠራሽ ሥርዐት በክርስቶስ ነጻ መሆን

6እንግዲህ ጌታ ክርስቶስ ኢየሱስን
እንደ ተቀበላችሁት እንዲሁ በእርሱ
ኑሩ፤ 7በእርሱ ተተክላችሁና ታንጻችሁ፣
እንደ ተማራችሁት በእምነት ጸንታችሁ፣
የተትረፈረፈ ምስጋና እያቀረባችሁ ኑሩ።
8በክርስቶስ ላይ ሳይሆን፣ በሰዎች
ልማድና በዚህ ዓለም መሠረታዊ ሕግጋት
ላይ በተመሠረተ ፍልስፍናና ከንቱ
ማግባቢያ ማንም ማርኮ እንዳይወስዳችሁ
ተጠንቀቁ።
9የመለኮት ሙላት ሁሉ በአካል በእርሱ

1፥25 ቍ23፤ 1ቆሮ3፥5፤ ኤፌ3፥2፤ ዕብ4፥12
1፥26 ሮሜ16፥25
1፥27 ማቴ13፥11፤ ሮሜ2፥4፤ 8፥10
2፥1 ቈላ1፥29፤ 4፥12፡13፡15፡16፤ ራእ1፥11፤ 3፥14
2፥2 ሮሜ16፥25፤ ኤፌ6፥22፤ ቈላ4፥8
2፥3 ኢሳ11፥2፤ ኤር23፥5፤ ሮሜ11፥33፤ 1ቆሮ1፥24፡30
2፥4 ሮሜ16፥18
2፥5 ሐሥ20፥21፤ 1ቆሮ5፥4፤ 14፥40፤ 1ተሰ2፥17፤ 1ጴጥ5፥9
2፥6 ዮሐ13፥13፤ ቈላ1፥10
2፥7 ኤፌ3፥17፤ 4፥21
2፥8 ቍ20፤ ገላ4፥3፤ 1ጢሞ6፥20
2፥9 ዮሐ1፥16

**1፥27 የክብር ተስፋ የሆነው በእናንተ ውስጥ ያለው ክርስቶስ፤** ክርስቶስ በእኛ ውስጥ መኖሩ ወደፊት ለምንቀበለው ክብርና የዘላለም ሕይወት ዋስትና ነው። የእርሱ በውስጣችን መኖርና ከእርሱ ጋር ያለን የቀረበ ግንኙነት ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመግባት ያለንን ጥርጥር ሁሉ ጨርሰው ሊያስወግዱልን ይችላሉ። እርሱን ማግኘት ሕይወትን ማግኘት ነው (ከሮሜ 8፥11፤ ከኤፌ 1፥13-14፤ ከ1ዮሐ 5፥11-12 ጋር ያነጻጽሩ)።

**2፥8 በክርስቶስ ላይ ሳይሆን ... ፍልስፍናና ከንቱ ማግባቢያ፤** ከእግዚአብሔርና ከተጻፈው ቃሉ ወጥቶ፣ የሰውን ሥራ የሚያጐላ ፍልስፍናን፣ ሃይማኖትንና ወግን አጥብቀን እንድንቃወም ጳውሎስ ያስጠነቅቀናል። ዛሬ በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ የተመሠረተውን ክርስትና ከሚፈታተኑት ታላላቅ ፍልስፍናዎች አንዱ በሰው ምድራዊ ማንነት ላይ የሚያተኵረው አስተሳሰብ ነው። ይህ አመለካከት በአጠቃላይ በዓለማዊ ትምህርት፣ አስተዳደርና ኅብረተ ሰብ ውስጥ ዋና ፍልስፍናና ተቀባይነትን ያገኘ ሃይማኖት ሆኖአል፤ በዓለም ሁሉ በሚገኙ ብዙ ጋዜጦችና መዝናኛ ፕሮግራሞች ላይም ትኵረትን የሳበ ጕዳይ መሆን ችሎአል።

(1) በሰው ምድራዊ ማንነት ላይ የተመሠረተው ፍልስፍና የሚያስተምረው የሚከተለውን ነው፦ (ሀ) የሰው ዘር፣ ፍጥረተ ዓለምና በውስጡ ያሉት ነገሮች ሁሉ ቍስንና ኀይልን ብቻ በማካተት አሁን ያላቸውን ቅርጽ ይዘው የተገኙት በማንም ሳይሆን በአጋጣሚ እንደ ሆነ ያስተምራል፤ (ለ) ሰዎች የተፈጠሩት በእግዚአብሔር ሳይሆን፣ በአዝጋሚ ለውጥ ሂደት ውስጥ የተገኙ መሆናቸውን ያስተምራል፤ (ሐ) ማንነቱ በሚታወቀውና ወሰን በሌለው አምላክ ማመንን ካለመደገፉም በላይ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ለሰው ዘር የተሰጠ ከእግዚአብሔር የመጣና እስትንፋሰ እግዚአብሔር መሆኑን አይቀበልም፤ (መ) ሰው ተመራምሮ ከሚደርስበት ግኝት ውጭ ዕውቀት ሊኖር እንደማይችልና ሰባዊ አመክንዮ በአንድ ኅብረተ ሰብ ውስጥ ትክክለኛ ሥነ ምግባር ይኖር ዘንድ ወሳኝነት እንዳለው ያስተምራል፤ ይህም ሰውን የመጨረሻው ከፍተኛ ሥልጣን ያለው ያደርገዋል፤ (ሠ) በትምህርት፣ ምጣኔ ሀብትን በተገቢው ሁኔታ በማከፋፈል፣ ዘመናዊ የሥነ ልቦና ትምህርትን ወይም የሰውን ጥበብ በመጠቀም የሰውን ጠባይና ሁኔታ ለመለወጥ ጥረት ያደርጋል፤ (ረ) የሥነ ምግባር መመዘኛዎች ፍጹምነት ያላቸው ሳይሆኑ፣ ሰዎችን ደስ ከማሰኘታቸው፣ ለሰዎች ደስታን ከማስገኘታቸው ወይም በመሪዎች ዕቅድ መሠረት ለኅብረተ ሰቡ የሚበጁ ከመሆናቸው አንጻር እንደ ሁኔታው የሚታዩ መሆናቸውን ያስተምራል፤ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን መመዘኛና ግብረገብ አይቀበልም፤ (ሰ) ሰው ማንኛውንም ነገር በራሱ ጥበብ መፈጸሙ፣ የሚያገኘው ርካታና ደስታ በሕይወት ውስጥ እጅግ ከፍተኛው መልካም ነገር እንደ ሆነ ያስገነዝባል፤ (ሸ) ሰዎች በእግዚአብሔር ሳያምኑና በእርሱም ላይ ሳይደገፉ፣ በሞትና በችግር ያላቸውን አመለካከት ለመለወጥና ራሳቸውን ከዚያ ጋር ለማለማመድ መሞከር አለባቸው የሚል አቋም አለው።

(2) የሰውን ታላቅነት አጕልቶ የሚያሳየው ፍልስፍና የተጀመረው በሰይጣን ነው፤ ይህም ሰው እንደ እግዚአብሔር ሊሆን ይችላል በማለት በሐሰት ከተናገረው የመነጨ አስተሳሰብ ነው (ዘፍ 3፥5)። የዚህ ፍልስፍና አራማጆች "የእግዚአብሔርን እውነት በሐሰት እንደለወጡ፣ በፈጣሪም ፈንታ ፍጡርን እንዳመለኩና እንዳገለገሉ" መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል (ሮሜ 1፥25)።

(3) ክርስቲያን መሪዎች፣ መጋቢዎችና ወላጆች ሁሉ ወንድና ሴት ልጆቻቸው በዚህ ሰው ሠራሽ በሆነው ትምህርት ከመጠመድ እንዲጠበቁ የተቻላቸውን ማድረግ ይገባቸዋል። ይህ ዐይነቱ ትምህርት ልጆችን ለስሕተት አሠራር እንዲጋለጡ፣ ከእግዚአብሔር የሆነውን መልካም ነገር እንዲንቁና ከዚህም የተነሣ እንዲጠፉ ያደርጋልና (ሮሜ 1፥20-32፤ 2ቆሮ 10፥4-5፤ 2ጢሞ 3፥1-10፤ ይሁ 1፥4-20፤ 1ቆሮ 1፥20 እና ማብ፤ 2ጴጥ 2፥19 እና ማብ ይመ)።

ይኖራልና፤ 10እናንተም የገዥነትና
የሥልጣን ሁሉ ራስ በሆነው በክርስቶስ
ሙሉ ሆናችኋል። 11በእርሱ ሆናችሁ በእጅ
ባልተደረገመገረዝተገረዛችሁ፤በክርስቶስም
መገረዝ የሥጋን ኀጢአታዊ ባሕርይ
አስወገዳችሁ፤ 12በጥምቀትም ከእርሱ ጋር
ተቀብራችሁ፣ እርሱን ከሙታን ባስነሣው
በእግዚአብሔር ኀይል በማመን ከእርሱ ጋር
ደግሞ ተነሣችሁ።
13እናንተም በበደላችሁና የሥጋችሁን
ኀጢአታዊ ባሕርይ ባለ መገረዝ ሙታን
ሳላችሁ፣ እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር
ሕያዋን አደረጋችሁ[a]፤ ኀጢአታችንንም
ሁሉ ይቅር አለን፤ 14ሲቃወመንና ሲጻረረን
የነበረውን የዕዳ ጽሕፈት ከነሕግጋቱ
በመደምሰስ፣ በመስቀል ላይ ቸንክሮ
ከመንገድ አስወገደው። 15የአለቆችንና
የባለ ሥልጣናትንም ማዕረግ በመግፈፍ
በመስቀሉ[†] ድል ነሥቶ በአደባባይ
እያዞራቸው እንዲታዩ አደረገ።
16እንግዲህ በምትበሉትም ሆነ
በምትጠጡት ወይም በዓልን፣ ወር
መባቻንና ሰንበትን በማክበር ነገር ማንም
አይፍረድባችሁ፤ 17እነዚህሊመጡላሉነገሮች
ጥላ ናቸውና፤ አካሉ ግን የክርስቶስ ነው።
18ዐጕል ትሕትናንና የመላእክትን አምልኮ
የሚወድ ማንም ሰው እንዳያደናቅፋችሁ
ተጠንቀቁ። እንደዚህ ያለ ሰው ስላየው
ራእይ ከመጠን በላይ ራሱን እየካበ በሥጋዊ
አእምሮው ከንቱ ሐሳብ ተሞልቶ ይታበያል፤

2፥10 ማቴ28፥18፤ ኤፌ1፥22
2፥11 ሮሜ2፥29፤ ገላ5፥24፤ ፊል3፥3
2፥12 ማቴ28፥19፤ ሐሥ2፥24፤ ሮሜ6፥5
2፥13 ኤፌ2፥1፡5፤ 4፥32
2፥14 ኤፌ2፥15፤ 1ጴጥ2፥24
2፥15 ቍ10፤ ማቴ12፥29፤ ሉቃ10፥18፤ ዮሐ12፥31፤ ኤፌ6፥12
2፥16 ዘሌ23፥2፤ 1ዜና23፥31፤ ማር2፥27፡28፤ 7፥19፤ ሮሜ14፥3፤ ሮሜ4፡5፤ 17፤ ገላ4፥10
2፥17 ዕብ8፥5፤ 10፥1
2፥18 ቍ23፤ 1ቆሮ9፥24፤ ፊል3፥14

[a]2፥13 አንዳንድ የጥንት ቅጆች አደረገን ይላሉ።
[†]2፥15 ወይም በእርሱ

**2፥11 በክርስቶስም መገረዝ፤** በብሉይ ኪዳን መገረዝ እያንዳንዱ እስራኤላዊ ከእግዚአብሔር ጋር በተደረገው ኪዳናዊ ግንኙነት ላይ ለመቆሙ ምልክት ነበር (ዘፍ 17፥11 እና ማብ ይመ)። ይህም ከኀጢአትና በዓለም ውስጥ ካለው ርኩስ ነገር ሁሉ ጋር እስራኤላውያን ያላቸውን ግንኙነት እንዲያቋርጡና ከዚያም እንዲለዩ የሚያመለክት ትእምርት ነው። በአዲስ ኪዳን ያሉ አማኞች በመንፈሳዊ ግዝረት ሥርዐት ውስጥ ዐልፈዋል፤ ይኸውም ኀጢአተኛ ተፈጥሯቸውን አውልቀው በመጣላቸው እውን ሆኖ ይታያል። እንደዚህ ዐይነቱ ግዝረት መንፈሳ ድርጊት ሲሆን፣ ዳግም ያልተወለደውንና በእግዚአብሔር ላይ የሚያምፀውን አሮጌ ተፈጥሯችንን ክርስቶስ ከእኛ ቈርጦ የሚጥልበት ከመሆኑም በላይ፣ መንፈሳዊ ሕይወትን ወይም የክርስቶስን የትንሣኤ ሕይወት ለእኛ የሚያስተላልፍበት መንገድ ነው (ቍ 12-13)፤ ይህም የልብ መገረዝ ነው (ዘዳ 10፥16፤ 30፥6፤ ኤር 4፥4፤ 9፥26፤ ሮሜ 2፥29)።

**2፥14 የዕዳ ጽሕፈት ከነሕግጋቱ፤** ይህ የሚያመለክተው የሙሴ ሕግ ሲሆን፣ ትክክለኛው ባሕርይ እንዲኖር የሚናገሩትን፣ ነገር ግን ሕይወት የማይሰጡትንና እግዚአብሔርን ለመታዘዝ የሚያስችል ኀይል የሌላቸውን ትእዛዛት ያሳያል (ገላ 3፥21)። ብሉይ ኪዳን ወደ ድነት የሚያደርስ መንገድ በመሆን ይሰጠው የነበረው አገልግሎት በመስቀል ላይ ተጠርቆ ተወገደ፤ እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል በመንፈሱ የተሻለውን ኪዳን መሠረተ (2ቆሮ 3፥6-9፤ ዕብ 8፥6-13፤ 10፥16-17፡29፤ 12፥24 ይመል፤ በገጽ 1970 ላይ፣ "*የቀደመው ኪዳንና አዲሱ ኪዳን*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

**2፥15 የአለቆችንና የባለ ሥልጣናትንም ማዕረግ በመግፈፍ፤** ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቱ አማካይነት በዓለም ላይ ባሉ ጋኔናዊ ኀይላትና ሰይጣናዊ ሥልጣናት ሁሉ ላይ ድል ተቀዳጀ (ከኤፌ 6፥12 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ወንዶችና ሴቶች ከፈቃዳቸው ውጭ በክፉ ግዛት ውስጥ እስረኛ ሆነው እንዲቈዩ ማድረግ የሚችሉበትን ሥልጣን ገፈፋቸው (ከ1፥13፤ ከማቴ 12፥29፤ ከሉቃ 10፥18፤ 11፥20-22፤ ከዕብ 2፥14 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1499 ላይ፣ "*በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሁሉ የዚህ ድል ባለቤት ነው። በዓለምና በሚደርስብን ፈተና ላይ ድል መቀዳጀታችን ብቻ ሳይሆን (1ዮሐ 4፥4)፣ ከክፉ መንፈሳዊ ኀይላት ጋር የምንዋጋበት ብርቱ መሣሪያም ጭምር አለን (ኤፌ 6፥12 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1527 ላይ፣ "*አማኞች የሚከተሏቸው መንፈሳዊ ምልክቶች*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

**2፥16 በምትበሉትም ሆነ በምትጠጡት … ሰንበትን፤** ለድነት አስፈላጊ እንደ ሆነ ተቈጥሮ የቈላስይስ ክርስቲያኖች እንዲፈጽሙት የተጫነባቸው ልዩ የአመጋገብ ሥርዐት ሰውነትን ለማጕሳቈል ሲባል የሚደረገውን የአይሁድ የአመጋገብ ልምድ ሳይመለከት አይቀርም (ከቍ 17 ጋር ያነጻጽሩ)። "የሃይማኖት በዓል፣ የወር መባቻ በዓል ወይም የሰንበት ቀን" የሚለው፣ በአይሁድ የቀን መቍጠሪያ መሠረት አስፈላጊ የሆኑ አንዳንድ የታወቁ በዓላትን የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም። ክርስቲያን እንደዚህ ካለው ሕግና የበዐል አከባበር ግዴታ ውስጥ ገብቶ ከመታሰር ነጻ የወጣ መሆኑን ጳውሎስ ያስተምራል (ገላ 4፥4-11፤ 5፥1 ይመ፤ እንደዚሁም በማቴ 12፥1 ላይ ስለ ሰንበት የቀረበውን ማብራሪያ፤ በማርቆስ 7፥6 ላይ ደግሞ ስለ ሕግ አክራሪነት የቀረበውን ማብ ይመ)።

**2፥18 የመላእክትን አምልኮ፤** ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ሰዎች መላእክትን አማላጅ በማድረግ ወደ እነርሱ ልመናን ማቅረብና እነርሱንም ማምለክ እንደሚገባቸው የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ያስተምሩ ነበር። ለጳውሎስ ወደ መላእክት ልመናን ማቅረብ ማለት ልዑልና ምሉእ የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነውን የኢየሱስ ክርስቶስን ቦታ እንደ መስጠት ይቈጠራል (ቍ 19)፤ ከዚህም የተነሣ ይህ ዐይነቱ አምልኮ እንዳይፈጸም ጳውሎስ በጥብቅ ያስጠነቅቃል። ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ብቸኛ አስታራቂ አይደለም የሚለው እምነት፣ የሞቱ ቅዱሳንን ጠባቂና አማላጅ አድርጎ በመቍጠር ለእነርሱ በሚደረገው አምልኮና በሚቀርበው ጸሎት ልምምድ ዛሬም ሲገለጽ ይታያል። እንዲህ ዐይነቱ ልምምድ የክርስቶስን የበላይነትና በእግዚአብሔር የመቤዠት ዕቅድ ውስጥ ያለውን ማእከላዊነት ዋጋ ያሳጣል። ለእግዚአብሔር አብ፣ ለእግዚአብሔር ወልድና ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር ለሰው የሚደረግ አምልኮና ወደ ሰው የሚቀርብ ልመና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስላልሆነ፣ ሊወገድ ይገባዋል (1፥2 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 713 ላይ፣ "*አምልኮተ እግዚአብሔር*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

[19]ይህ ሰው፣ አካል ሁሉ በጅማትና በማሰሪያ
እየተጋጠመ ምግብንም እየተቀበለ
እግዚአብሔር በሚሰጠው ማደግ ከሚያድግበት
ራስ ከሆነው ጋር ግንኙነት የለውም።
[20]ለዚህ ዓለም መርሕ ከክርስቶስ ጋር
ከሞታችሁ ታዲያ ለምን እንደዚህ ዓለም ሰው
ለሕጎቹ ተገዥ ትሆናላችሁ? [21]"አትያዝ!
አትቅመስ! አትንካ!" እንደሚሉት ዐይነት፣
[22]እነዚህ ሁሉ በሰው ትእዛዝና ትምህርት
ላይ የተመሠረቱ ስለ ሆኑ በተግባር ላይ
ሲውሉ ጠፊ ናቸው። [23]እነዚህ ነገሮች በገዛ
ራስ ላይ ከሚፈጥሩት የአምልኮ ስሜት፣
ከሀሰት ትሕትናና ሰውነትን ከመጨቈን
አንጻር በርግጥ ጥበብ ያለባቸው ይመስላሉ፤
ነገር ግን የሥጋን ልቅነት ለመቈጣጠር
አንዳች ፋይዳ የላቸውም።

## የቅድስና ሕይወት መመሪያ

3 እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፣
ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ በተቀመጠበት
በላይ ያሉ ነገሮችን እሹ፤ [2]አሳባችሁም
በላይ ባለው ላይ እንጂ በምድራዊ ነገር ላይ
አይሁን። [3]ሞታችኋልና፤ ሕይወታችሁም
ከክርስቶስ ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ
ተሰውሯልና፤ [4]ሕይወታችሁ[a] የሆነው
ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ እናንተም በዚያን
ጊዜ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ።
[5]ስለዚህ ምድራዊ ምኞቶቻችሁን ግደሉ፤
እነዚህም:- ዝሙት፣ ርኵሰት፣ ፍትወት፣
ክፉ ምኞትና አምልኮተ ጣዖት የሆነው
መጐምጀት ናቸው። [6]በእነዚህም ምክንያት
የእግዚአብሔር ቍጣ በማይታዘዙት[†] ላይ
ይመጣል፤ [7]እናንተም ቀድሞ በኖራችሁበት
ሕይወት በእነዚህ ትመላለሱ ነበር፤ [8]አሁን
ግን ቍጣን፣ ንዴትን፣ ስድብን፣ ሐሜትንና
አሳፋሪ ንግግርን የመሳሰሉትንም ሁሉ
አስወግዱ፤ [9]እርጌውን ሰው ከሥራው ጋር
አውልቃችሁ ስለ ጣላችሁ እርስ በርሳችሁ
ውሸት አትነጋገሩ። [10]የፈጣሪውን መልክ
እንዲመስል በዕውቀት የሚታደሰውን
አዲሱን ሰው ለብሳችኋል፤ [11]በዚያ ግሪክ
ወይም ይሁዲ፣ የተገረዘ ወይም ያልተገረዘ፣
አረማዊ ወይም እስኩቴስ፣ ባሪያ ወይም
ጌታ ብሎ ልዩነት የለም፤ ነገር ግን ክርስቶስ
ሁሉም ነው፤ በሁሉም ነው።
[12]እንግዲህ የተቀደሳችሁና የተወደዳችሁ
የእግዚአብሔር ምርጦች እንደ መሆናችሁ
ርኅራኄን፣ ቸርነትን፣ ትሕትናን፣
ጨዋነትንና ትዕግሥትን ልበሱ፤ [13]እርስ
በርሳችሁ ተቻቻሉ፤ ከእናንተ አንዱ በሌላው
ላይ ቅር የተሰኘበት ነገር ቢኖር ይቅር
ተባባሉ፤ ጌታ ይቅር እንዳላችሁ እናንተም
ሌላውን ይቅር በሉ። [14]በእነዚህ ሁሉ ላይ
ሁሉን በፍጹም አንድነት የሚያስተሳስረውን
ፍቅርን ልበሱት።
[15]እንደ አንድ አካል ሆናችሁ የተጠራችሁበት የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይንገሥ፤
የምታመሰግኑም ሁኑ። [16]የክርስቶስ ቃል
በሙላት ይኑርባችሁ፤ እርስ በርሳችሁ በጥበብ

2፥19 1ቆሮ12፥27፤ ኤፌ1፥22፤ ኤፌ4፥16
2፥20 ቍ8፥14፥16፤ ሮሜ6፥6፤ ገላ4፥3፥9
2፥22 ኢሳ29፥13፤ ማቴ15፥9፤ 1ቆሮ6፥13፤ ቲቶ1፥14
2፥23 ቍ18
2፥28 ማቴ5፥48፤ 1ቆሮ2፥6፥7፤ ኤፌ5፥27፤ ቈላ3፥16
2፥29 1ቆሮ15፥10፤ 2ቆሮ11፥23፤ ኤፌ1፥19፤ 3፥7፤ ቈላ15፥10
3፥1 ማር16፥19፤ ሮሜ6፥5
3፥2 ፊል3፥19፥20
3፥3 ሮሜ6፥2፤ 2ቆሮ5፥14
3፥4 1ቆሮ1፥7፤ ገላ2፥20፤ 1ጴጥ1፥13፤ 1ዮሐ3፥2
3፥5 ሮሜ6፥2፤ 1ቆሮ6፥18፤ ገላ5፥19፤ 21፥24፤ ኤፌ4፥22፤ 5፥3፥5
3፥6 ሮሜ1፥18
3፥7 ኤፌ2፥2
3፥8 ኤፌ4፥22፤ 29፥31
3፥9 ሮሜ6፥6፤ ኤፌ4፥25
3፥10 ሮሜ6፥4፤ 12፥2፤ 13፥14፤ 2ቆሮ4፥16፤

3፥8 ኤፌ2፥10፤ 4፥23 3፥11 ሮሜ10፥12፤ 1ቆሮ7፥19፤ 12፥13፤ ገላ3፥28፤ ኤፌ1፥23 3፥12 ቍ10፤ 2ቆሮ6፥6፤ ገላ5፥22፤ 23፤ ኤፌ4፥2፤ ፊል2፥3 3፥13 ኤፌ4፥2፥32 3፥14 ሮሜ15፥5፤ 1ቆሮ13፥1፥13 3፥15 ዮሐ14፥27፤ ሮሜ12፥5፤ 14፥19 3፥16 መዝ47፥7፤ ሮሜ10፥17፤ ኤፌ5፥19፤ ቈላ1፥28

[a]3፥4 አንዳንድ የጥንት ቅጆች የኛ ሕይወት
[†]3፥6 በማይታዘዙት ላይ የሚለው ሐረግ በአንዳንድ የጥንት ቅጆች ላይ ብቻ የሚገኝ ነው

**3፥2 አሳባችሁም በላይ ባለው እንጂ ... አይሁን፤** ሕይወታችን ከክርስቶስ ጋር በሰማይ ስለ ሆነ (ቍ 3)፣ ልባችን በዚያ ላይ ያረፈና አስተሳሰባችንም ሁሉ ከላይ ባሉ ነገሮች የተገዛ መሆን ይገባዋል:: ለማንኛውም ነገር ዋጋ፣ ግምትና ፍርድ የምንሰጠው ከዘላለማዊና ከሰማያዊ እይታ አንጻር መሆን አለበት:: ግቦቻችንና ክትትላችን መንፈሳዊ ነገሮችን ለማግኘት (ቍ 1-4)፣ ኀጢአትን ለመቃወም (ቍ 5-11) እንዲሁም የክርስቶስን ባሕርይ ለመልበስ (ቍ 12-17) ሊሆን ይገባል:: መንፈሳዊ ጸጋዎች፣ ኀይል፣ ልምምዶችና በረከቶች ሁሉ የሚገኙት በክርስቶስ ዘንድ በሰማይ ነው:: እነዚህን ነገሮች በቅንነት ለሚጠይቁ፣ በትጋት ለሚፈልጉና ያለማቋረጥ እያንኳኩ ለሚለምኑ ሁሉ አትረፍርፎ ያፈስላቸዋል (ሉቃ 11፥1-13፤ 1ቆሮ 12፥11፤ ኤፌ 1፥3፤ 4፥7-8)::

**3፥4 ሕይወታችሁ የሆነው ክርስቶስ፤** ትክክለኛ አስተምህሮ (2ጢሞ 1፥13-14) እና ቅዱስ ሕይወት (3፥5-17፤ ዮሐ 14፥15፥21) በክርስቶስ ለሚገኘው ድነት አስፈላጊ ነገሮች ቢሆኑም፣ ምንጊዜም በዋነኛነት መጠበቅ ያለበት ግን ከክርስቶስ ጋር ያለን ኅብረትና ለእርሱም ያለን ፍቅር ነው (ከሮሜ 3፥22 ጋር ያነጻጽሩ):: በዚህ መልእክት ውስጥ አንድ አማኝ በግል ከክርስቶስ ጋር ስላለው ኅብረት ትኩረት የተሰጠ ስለ መሆኑ ልብ ይበሉ (1፥27፤ 2፥6-7፥10፥20፤ 3፥1፥3-4)::

**3፥5 አምልኮተ ጣዖት የሆነው መጐምጀት፤** ጣዖት ማምለክ ምንድን ነው? (1) በእግዚአብሔር ማመንንና በእርሱም ላይ መደገፍን ያስጥላል፤ የሰው ምኞት፣ ትምክሕትና ዋጋ አሰጣጥ በምድራዊ ነገሮች ላይ ብቻ እንዲያተኵር ያደርጋል (ከዘፀ 20፥3-6፤ ከዘዳ 7፥25-26፤ ከኢሳ 40፥18-23 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 428 ላይ፣ *"የጣዖት አምልኮ ባሕርይ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ):: ከዚህም የተነሣ መጐምጀት አምልኮተ ጣዖት ተብሎአል:: (2) አምልኮተ ጣዖት በምድር ላሉ ሰዎች፣ ተቋሞች፣ ባህሎች ወይም ባለሥልጣኖች ተመጣጣኝ ወይም የበለጠ ታማኝነትን እያሳየ፣ በሌላ በኩል ግን ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ታማኝ የመሆንን ሐሳብ ሊያካትት ይችላል:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ተገለጸው ሰው ከእግዚአብሔርና ከቃሉ ጋር ከሚኖረው እውነተኛ ግንኙነት በላይ ምንም ነገር ማስቀመጥ የለበትም (ሮሜ 1፥22-23፤ ኤፌ 5፥5)::

**3፥16 የክርስቶስ ቃል ... ይኑርባችሁ፤** የክርስቶስን ቃል ማለትም መጽሐፍ ቅዱስን ያለማቋረጥ ማንበብ፣ ማጥናትና ማሰላሰል እንዲሁም ቃሉ በውስጣችን በሙላት እስከሚኖር ድረስ መጸለይ ያስፈልጋል:: ይህን የዘወትር ልምምዳችን ስናደርገው አስተሳሰባችን፣ ንግግራችን፣ ተግባራችንና ፍላጎታችን የተለወጠና ክርስቶስ የሚቈጣጠረው ይሆናል (መዝ 119፥11፤ ዮሐ 15፥7፤ 1ቆሮ 15፥2 እና ማብ ይመ):: መዝሙር፣ ማሕሌትና መንፈሳዊ ቅኔ የሚቀርቡት ቃሉን ለማስተማር እንዲሁም ክርስቶስን በመታዘዝ ይኖሩ ዘንድ አማኞችን

ሁሉ ተማማሩ፤ ተመካከሩ፤ በመዝሙርና
በማሕሌት፣ በመንፈሳዊም ቅኔ በማመስገን
በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ። 17በእርሱ በኩል
ለእግዚአብሔር አብ ምስጋና እያቀረ ባችሁ፣
ዕብ በቃልም ሆነ በተግባር የምታደርጉትን
፥15 ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት።

## የክርስቲያናዊ ቤተ ሰብ መመሪያ

18ሚስቶች ሆይ፤ በጌታ ዘንድ ተገቢ
በመሆኑ ለባሎቻችሁ ታዘዙ።
19ባሎች ሆይ፤ ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤
መራራም አትሁኑባቸው።
20ልጆች ሆይ፤ ይህ ጌታን ደስ የሚያሰኝ
በመሆኑ ለወላጆቻችሁ በሁሉም ነገር
ታዘዙ፤
21አባቶች ሆይ፤ ተስፋ እንዳይቈርጡ
ልጆቻችሁን አታስመርሯቸው።
22ባሮች ሆይ፤ ሰውን ለማስደሰትና
ለታይታ ብላችሁ ሳይሆን በቅን ልብ ጌታን
በመፍራት ለምድራዊ ጌቶቻችሁ በሁሉ
ነገር ታዘዙ። 23የምታደርጉትን ሁሉ ለሰው
ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉት ቈጥራችሁ
በሙሉ ልባችሁ አድርጉት፤ 24ከጌታ ዘንድ
እንደ ብድራት የምትቀበሉት ርስት እንዳለ
ታውቃላችሁና፤ የምታገለግሉት ጌታ
ክርስቶስን ነው። 25በደለኛውም የእጁን
ያገኛል፤ አድልዎም የለም።
4 ጌቶች ሆይ፤ እናንተም በሰማይ
ጌታ እንዳላችሁ ስለምታውቁ
አገልጋዮቻችሁን በፍትሕና በቅንነት
አስተዳድሯቸው።

3፥17
1ቆሮ10፥31፤
ኤፌ5፥20
3፥18 ኤፌ5፥22
3፥24
ማቴ16፥27፤
ሐሥ20፥32
3፥25 ሐሥ10፥34
4፥1
ዘሌ25፥43፡53

---

ለመምከርና ለመገሠጽ መሆን አለበት (በኤፌ 5፥19 ላይ *መንፈሳዊ ቅኔን በተመለከተ የቀረበውን ማብ ይመ*)::

**3፥17 በቃልም ሆነ በተግባር የምታደርጉትን ሁሉ፤** በመንፈስ ቅዱስ የሚመሩ አማኞች በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በግልጽ ያልተወሱ ተግባሮች ትክክል መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን መለየት የሚያስችሏቸውን አጠቃላይ መርሖች መጽሐፍ ቅዱስ ይሰጣል:: በምንናገረው፣ በምናደርገው በምናስበው ወይም ደስ በምንሰኝበት በማንኛውም ነገር ሁሉ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ አለብን: (1) የሚደረገው ነገር ለእግዚብሔር ክብር ሊሆን ይችላልን (1ቆሮ 10፥31)? (2) የሚደረገውን እርሱ ይባርከው ዘንድ በመለመን "በጌታ በኢየሱስ ስም" ሊከናወን ይችላልን (ዮሐ 14፥13 እና ሚብ ይመ)? (3) ለእግዚአብሔር ከልብ የሆነ ምስጋና በማቅረብ ሊደረግ የሚችል ነውን? (4) የክርስቶስን ምሳሌነት በመከተል የሚደረግ ነውን (1ዮሐ 2፥6)? (5) የሌሎችን ጽኑ እምነት ያዳክም ይሆን (1ቆሮ 8፥1 እና ማብ ይመ)? (6) ለመንፈሳዊ ነገሮች ማለትም ለእግዚአብሔር ቃልና ለጸሎት ያለኝን ፍላጎት የሚቀንስ ነውን (ሉቃ 8፥14፤ ማቴ 5፥6 እና ማብ ይመ)? (7) ለክርስቶስ ስል የምሰጠውን ምስክርነት የሚያዳክምና የሚያበላሽ ነው (ማቴ 5፥13-16)?

**3፥18-19 ሚስቶች ሆይ፤ ... ለባሎቻችሁ ታዘዙ፤** ኤፌ 5፥21-23 እና ማብ ይመ፤ በ1ጢሞ 2፥13-15 ላይ ደግሞ በቤተ ሰብ ግንኙነት ውስጥ የሚስቶችንና የባሎችን ኀላፊነት በሚመለከት የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ::

**3፥20 ልጆች ሆይ፤ ... ለወላጆቻችሁ በሁሉም ነገር ታዘዙ፤** በኤፌ 6፥1 ላይ በቤተ ሰብ ግንኙነት ውስጥ የልጆችን ኀላፊነት አስመልክቶ የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ::

**3፥21 አባቶች ሆይ፤ ... ልጆቻችሁን አታስመርሯቸው፤** ወላጆች ልጆቻቸውን እንዴት ወደ ክርስቶስ መምራት እንዳለባቸው የሚገልጹ ዐሥራ አምስት ነጥቦችን ጨምሮ በዚህ ክፍል ከተጠቀሰው ሐሳብ ጋር በተያያዘ፣ በገጽ 1894 ላይ፣ "*ወላጆችና ልጆች*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ::

**3፥22 ባሮች ሆይ፤ ... ለምድራዊ ጌቶቻችሁ በሁሉ ነገር ታዘዙ፤** ባሮች ኑሯቸው መከራና ሥቃይ የበዛበት ቢሆንም እንኳ፤ ክርስቲያናዊ የሆነውን መንገድ እንዴት መከተል እንዳለባቸው ሐዋርያው ጳውሎስ መመሪያ ይሰጣል:: የጌታና የባሪያ ግንኙነት እግዚአብሔር ያጸደቀውና በዘላቂነትም መቀጠል ያለበት እንደ ሆነ ጳውሎስ ከቶ አይናገርም፤ ይልቁንም በፊልሞና 10፡14-17፡21 ላይ ሥርዐት ይደመሰስ ዘንድ አስተዋፅኦ የሚያደርገውን ዘር ይዘራል፤ በዚያውም ለጌቶችና ለባሮች ለሁለቱም ጠቃሚ የሆነውን ነገር ለማድረግ ይፈልጋል (ኤፌ 6፥5-9፤ 1ጢሞ 6፥1-2፤ ቲቶ 2፥9-10 ይመ፤ ከ1ጴጥ 2፥18-19 ጋር ያነጻጽሩ)::

**3፥23 ለጌታ እንደምታደርጉት ቈጥራችሁ፤** ክርስቲያኖች የሚሠሩትን ነገር ሁሉ ጌታን ለማገልገል እንዳደረጉት ይቈጥሩት ዘንድ ሐዋርያው ጳውሎስ አጥብቆ ይመክራል፤ አንድን ተግባር ስናከናውን፣ ሥራውን የሚያሠራው ክርስቶስ እንደ ሆነ በመቍጠርና ለእርሱም ብለን የምናደርገው ነገር አንድ ቀን ሽልማት የሚያስገኝ መሆኑን በመገንዘብ መሆን አለበት (ቍ 24 ይመ፤ ከኤፌ 6፥6-8 ጋር ያነጻጽሩ)::

**3፥25 በደለኛውም፤** በቤተ ሰብ፣ በቤተ ክርስቲያን፣ በአሠሪና በሠራተኛ ግንኙነት ውስጥ (ቍ 12-25) ፍቅር፣ ትክክለኛ ፍርድና ቅንነት ያለበት ነገር እንዲደረግ ጳውሎስ ዘወትር የሚያሳስበው ጉዳይ ነው:: በእነዚህ ጥቅሶች ላይ ያለው ሐሳብ በትኩረት ቢታይና ተግባራዊ ቢደረግ፣ በቤታችንና በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ በሌሎች ላይ የምናደርገውን ፍቅርና ፍትሕ የጐደለውን ሁኔታ ማስወገድ እንችላለን:: ከዚህ አቅጣጫ የምንማረው ትምህርት፣ (1) ክርስቲያኖች ሆነን ሳለ በሌሎች ላይ የማይገባውን ማድረጋችን ወደ ፊት በመንግሥተ ሰማይ የሚኖረንን ክብር የሚያጐድፍ እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ መሆኑን (ከ2ቆሮ 5፥10 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (ሀ) በአንጻሩ ለሌሎች ፍቅርና በጎነት ያለበት ነገር የሚያደርጉ ከጌታ ሽልማት ይቀበላሉ (ቍ 24፤ ኤፌ 6፥8)፤ (ለ) በሌላው አማኝ ላይ አግባብ ያልሆነውን የሚያደርግና በደል የሚፈጽም ማንኛውም ሰው ላደረገው ክፉ ነገር የእጁን ያገኛል:: በደለኛው በደሉን ለፍርድ ቀን ተሸክሞት ይኼዳል፤ በመጨረሻም ልዩነት ሳይደረግ የእጁን ያገኛል (ዘዳ 10፥17፤ 2ዜና 19፥7፤ ሐሥ 10፥34፤ ሮሜ 2፥11)::

(2) ወደ ፊት በእግዚአብሔር ፊት ያለብን የተጠያቂነት ሁኔታ ሰዎችን ሁሉ በፍቅር፣ በደግነትና በርኅራኄ ዐይን እንድናያቸው ሊያደርገን የሚገባ መሆኑን፤ አማኞች ሁሉ እርስ በርስ ስላሳዩት እንክብካቤ፣ እግዚአብሔር ተጠያቂ እንደሚያደርጋቸው መዘንጋት የለባቸውም (ገላ 6፥7፤ ማቴ 22፥37፡39 እና ማብ፤ ዮሐ 13፥34 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1822 ላይ፣ "*በአማኞች ላይ የሚሰጥ የተለየ ፍርድ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

# ወላጆችና ልጆች

*ቈላ 3፥21 "አባቶች ሆይ፥ ተስፋ እንዳይቈርጡ ልጆቻችሁን አታስመርሯቸው።"*

ልጆቻቸው ክርስቲያናዊ አስተዳደግ ይዘው እንዲያድጉ ማስተማርና መምከር የወላጆች ከፍተኛ ኀላፊነት ነው (በግሪክ ቋንቋ፣ "ቴር" ብዙ ቍጥሩ "ቴርስ" የሚለው ቃል ትርጕም "አባቶች" ወይም "አባትና እናት" ሊሆን ይችላል)። ወላጆች ከሥራቸው ይልቅ፣ ከሙያቸውም፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካላቸው አገልግሎት ወይም በኅብረተ ሰብ ውስጥ ካላቸው ቦታም የበለጠ፣ ለልጆቻቸው ድነት ትኵረት በመስጠት ክርስቲያናዊ ሕይወትንና ባሕርይን በማሳየት መልካም ምሳሌ ሊሆኗቸው ይገባል (ከመዝ 127፥3 ጋር ያነጻጽሩ)።

(1) በኤፌ 6፥4 እና በቈላ 3፥21 ላይ ጳውሎስ እንደ ተናገረው፣ በብዙ የብሉይ ኪዳን ክፍሎችም እግዚአብሔር በሰጠው ትእዛዝ ላይ እንደ ተጠቀሰው ሁሉ (ዘፍ 18፥19 እና ማብ፤ ዘዳ 6፥7 እና ማብ፤ መዝ 78፥5 እና ማብ፤ ምሳ 4፥1-4 እና ማብ፤ 6፥20 እና ማብ ይመ)፣ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት ይኖራቸው ዘንድ፣ ልጆቻቸው በመልካም ሁኔታ እንዲያድጉ ማድረግ የወላጆች ኀላፊነት ነው። ልጆችን መጽሐፍ ቅዱሳዊና መንፈሳዊ በሆነው መንገድ ቀርጾ የማሳደጉ ኀላፊነት፣ የቤተ ክርስቲያን ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኘው ት/ቤት ሳይሆን፣ የቤተ ሰብ ነው። ቤተ ክርስቲያንና በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የሚገኘው ት/ቤት ወላጆች ለልጆቻቸው በሚያደርጉት ሥልጠና ለማገዝ የቆሙ ናቸው።

(2) የልጆቹን ልብ አዳኝ ወደ ሆነው ልብ ለመመለስ፣ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆቻቸው ልብ መመለስ ይገባል፤ ይህም ለክርስቲያናዊ አስተዳደግ መሠረታዊ የሆነው ነገር ነው (ሉቃ 1፥17 እና ማብ ይመ)።

(3) ወላጆች ልጆቻቸውን በሚያሳድጉበት ጊዜ አድልዎ ማድረግ የለባቸውም፤ ማበረታታት ብቻ ሳይሆን፣ ሆን ብለው ስሕተት ሲፈጽሙም መቅጣት ይኖርባቸዋል፤ ርኅራኄን፣ ደግነትን፣ ትሕትናን፣ ጨዋነትንና ትዕግሥትን እያሳዩ ሕይወታቸውን በፍቅር ለልጆቻቸው አሳልፈው መስጠት ይገባቸዋል (ቈላ 3፥12-14፡21)።

(4) ወላጆች እንደ ወላጅነታቸው ልጆቻቸው በክርስቶስ ሆነው እግዚአብሔርን በመፍራት እንዲያድጉ ለማድረግ የሚያስችሏቸው ዐሥራ አምስት ነጥቦች ቀጥሎ የተዘረዘሩት ናቸው፡

(ሀ) ልጆቻችሁን ገና በልጅነታቸው ለእግዚአብሔር አስረክቡ (1ሳሙ 1፥28፤ ሉቃ 2፥22)።

(ለ) እግዚአብሔርን እንዲፈሩና ከኀጢአት እንዲርቁ፣ ጽድቅን እንዲወዱ ኀጢአ ትን እንዲጠሉ አስተምሩ። እግዚአብሔር ኀጢአትን እንደሚጠላና በኀጢአትም ላይ እንደሚፈርድ በየጊዜው አስገንዝቡ (ዕብ 1፥9 እና ማብ ይመ)።

(ሐ) መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነው ሥነ ሥርዐት ልጆቻችሁ እንዲታዘዟችሁ አስተምሩ (ዘዳ 8፥5፤ ምሳ 3፥11-12፤ 13፥24፤ 23፥13-14፤ 29፥15፡17፤ ዕብ 12፥7)።

(መ) ዓለማዊ በሆነ ነገር እንዲሳቡና በክፉ ጓደኝነት እንዲጠመዱ በማድረግ ሰይጣን የልጆቻችሁን መንፈሳዊ ሕይወት ለማበላሸት ያለውን ዕቅድ በመገንዘብ፣ ልጆቻችሁ ፈሪሀ እግዚአብሔር ከሌለበት ሁኔታ እንዲጠበቁ አድርጉ (ምሳ 13፥20፤ 28፥7፤ 1ዮሐ 2፥15-17)።

(ሠ) እግዚአብሔር ልጆቻችሁ የሚያደርጉትን፣ የሚያስቡትንና የሚናገሩትን እግዚአብሔር ሁልጊዜ እንደሚያይና እንደሚመዝን አስገንዝቧቸው (መዝ 139፥1-12)።

(ረ) ልጆቻችሁ በልጅነታቸው በግል ክርስቶስን እንዲያምኑ፣ ከኀጢአታቸው ንስሓ እንዲገቡና የውሃ ጥምቀት እንዲጠመቁ አድርጉ (ማቴ 19፥14)።

(ሰ) መንፈስ ቅዱስ የሚሠራበት፣ ቅዱስ ትእዛዙ የሚከበርበትና ቃሉ በሙላት የሚሰበክበት ቤተ ክርስቲያን አባል እንዲሆኑ አድርጉ፤ "እኔ ለሚፈሩህ ሁሉ፣ ሥርዐትህንም ለሚጠብቁ ባልንጀራ ነኝ" የሚለውን የሕይወት መመሪያም እንዲከተሉ አስተምሩ (መዝ 119፥63፤ ሐሥ 12፥5 እና ማብ ይመ)።

(ሸ) ልጆቻችሁ ከዓለማዊ ነገር ጋር ያላቸውን ግንኙነት ጨርሶ እንዲያቋርጡና በአንጻሩም ስለ ^ግዚአብሔር እንዲመሰክሩና እርሱን እንዲያገለግሉ አደፋፍሩ (2ቆሮ 6፥14—7፥1፤ ያዕ 4፥4)።

` ምድር እንግዶችና መጻተኞች እንደ ሆኑ (ዕብ 11፥13-16)፣ እውነተኛ ቤታቸውና ዜ ~ም ከክርስቶስ ጋር በሰማይ መሆኑን አስተምሯቸው (ፊል 3፥20፤ ቈላ 3፥1-3)።

ንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አስፈላጊ መሆኑን እንዲያውቁ ልጆቻችሁን አስተምሩ +-5፡8፤ 2፥4፡39)።

(በ) እግዚአብሔር እንደሚወዳቸውና ለሕይወታቸው ዐላማ እንዳለው ልጆቻችሁን አስተምሩ (ሉቃ 1፥13-17፤ ሮሜ 8፥30፤ 1ጴጥ 1፥3-9)።
(ተ) በውይይት ጊዜም ሆነ በቤተ ሰብ የጥሞና ጊዜ ልጆቻችሁን በየቀኑ በእግዚአብሔር ቃል ምሩ (ዘዳ 4፥9፤ 6፥5-7፤ 1ጢሞ 4፥6፤ 2ጢሞ 3፥15)።
(ቸ) ምሳሌ በመሆንና ከልብ በመምከር ልጆቻችሁ ለጸሎት የተሰጠ ሕይወት እንዲኖራቸው አደፋፍሩ (ሐሥ 6፥4፤ ሮሜ 12፥12፤ ኤፌ 6፥18፤ ያዕ 5፥16)።
(ኀ) ስለ ጽድቅ የሚመጣውን ስደት ለመቀበልና በትዕግሥት ለማሳለፍ እንዲችሉ ልጆቻችሁን አዘጋጁ (ማቴ 5፥10-12)፤ "በክርስቶስ ኢየሱስ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት መኖር የሚወዱ ሁሉ" እንደሚሰደዱ (2ጢሞ 3፥12) ማወቅ አለባቸው።
(ነ) ስለ ልጆቻችሁ በእግዚአብሔር ፊት የማያቋርጥና ልባዊ የሆነ ጸልዩ (ኤፌ 6፥18፤ ያዕ 5፥16-18)፤ ወላጆች ለልጆቻቸው መጸለይ እንደሚገባቸው ምሳሌ ሊሆን የሚችለውን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ የጸለየውን የምልጃ ጸሎት በሚመለከት የተሰጠውን ማብራሪያ በ17፥1 ላይ ተመልከቱ።
(ኘ) ልጆቻችሁ በእምነታቸው ሥር እንዲሰዱና በጌታ ፊት ሊኖራቸው የሚገባውን መልካም ሕይወት እንዲይዙ፣ ሕይወታቸው እንደ መጠጥ ቍርባን ሆኖ በጌታ ፊት እስከሚፈስ ድረስ ታማኞች እንዲሆኑ፣ ወላጆች ለልጆቻችሁ ጽኑ ፍቅርና ኀላፊነት ይኑራችሁ (ፊል 2፥17 እና ማብ ይመ)።

## ሌሎች ምክሮች

2ከማመስገን ጋር ነቅታችሁ በትጋት
ጸልዩ። 3እኔ እስረኛ የሆንሁለትን የክርስቶስን
ምስጢር ማወጅ እንድንችል፣ እግዚአብሔር
የቃሉን በር እንዲከፍትልን ስለ እኛ ደግሞ
ጸልዩ፤ 4ደግሞም መናገር እንደሚገባኝ
ቃሉን በግልጽ እንድናገር ጸልዩልኝ።
5በውጭ ካሉት ሰዎች ጋር ባላችሁ ግንኙነት
በጥበብ ተመላለሱ፤ በተገኘውም ዕድል ሁሉ
ተጠቀሙ። 6ለእያንዳንዱ ሰው እንዴት
መልስ መስጠት እንደሚገባችሁ ታውቁ
ዘንድ ንግግራችሁ በጨው እንደ ተቀመመ
ሁልጊዜ በጸጋ የተሞላ ይሁን።

## የስንብት ሰላምታ

7ቲኪቆስ ስላለሁበት ሁኔታ በሙሉ
ይነግራችኋል፤ እርሱ የተወደደ ወንድምና
ታማኝ አገልጋይ፣ በጌታም አብሮኝ ሎሌ
ነው። 8ስላለንበት* ሁኔታ እንድታውቁና
ልባችሁንም እንዲያጽናና ለዚህ ጕዳይ ወደ
እናንተ እልከዋለሁ፤ 9እርሱም ከእናንተ
ወገን ከሆ ነው ከታማኙና ከተወዳጁ
ወንድማችን ከአናሲሞስ ጋር ወደ እናንተ
ይመጣል፤ እነርሱም እዚህ ስላለው ሁኔታ
ሁሉ ይነግሯችኋል።
10አብሮኝ የታሰረው አርስጥሮኮስና
የበርናባስ የአክስቱ ልጅ ማርቆስ ሰላምታ
ያቀርቡላችኋል፤ ስለ ማርቆስ መመሪያ
ደርሶአችኋል፤ እንግዲህ ወደ እናንተ ሲመጣ
ተቀበሉት። 11ኢዮስጦስ የተባለው ኢያሱም
ሰላምታ ያቀርብላችኋል። ከተገረዙት
መካከል ስለእግዚአብሔር መንግሥት አብረውኝ
የሚሠሩት እኔንም ያጽናኑኝ እነዚህ
ብቻ ናቸው፤ እነርሱም አጽናንተውናል።
12ከእናንተ ወገን የሆነው የክርስቶስ ኢየሱስ
አገልጋይ ኤጳፍራ ሰላምታ ያቀርብላችኋል፤
እርሱም ፍጹም ጠንክራችሁና ሙሉ በሙሉ
ተረጋግታችሁ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉ
ጸንታችሁ እንድትቆሙ ዘወትር ስለ እናንተ
በጸሎት እየተጋደለ ነው። 13ደግሞም ስለ
እናንተ እንዲሁም በሎዶቅያና በኢያራ
ከተሞች ስላሉት ተግቶ እንደሚሠራ
እኔ እመሰክርለታለሁ። 14የተወደደው
ሐኪሙ ሉቃስ እንዲሁም ዴማስ ሰላምታ
ያቀርቡላችኋል። 15በሎዶቅያ ላሉት
ወንድሞች፣ ለንምፉን፣ በቤቷም ላለች ቤተ
ክርስቲያን ሰላምታ አቅርቡልኝ።
16ይህች መልእክት ከተነበበችላችሁ በኋላ
በሎዶቅያ ላለችው ቤተ ክርስቲያን ደግሞ
እንድትነበብ አድርጉ፤ እናንተም ደግሞ
በሎዶቅያ ያለችውን መልእክት አንብቡ።
17ለአክሪጳም፣ "በጌታ የተቀበልኸውን

4፥2 ሉቃ18፥1
4፥3 ሐዋ14፥27፤ 21፥33፤ ሮሜ16፥25
4፥5 ማር4፥11፤ ኤፌ5:15:16
4፥6 ማር9፥50፤ ኤፌ4፥29፤ 1ጴጥ3፥15
4፥7 ሐዋ20፥4፤ ኤፌ6፥21:22፤ ቆላ1፥7
4፥8 ኤፌ6፥21:22፤ ቆላ2፥2
4፥9 ቍ12፤ ፊሞ1፥10
4፥10 ሐዋ4፥36፤ 12፥12፤ 19፥29
4፥11 ፊል2፥25
4፥12 ቍ9፤ ሮሜ15፥30፤ 1ቆሮ2፥6፤ ቆላ1፥7፤ ፊሞ1፥23
4፥13 ቆላ2፥1
4፥14 2ጢሞ4፥10:11፤ ፊሞ1፥24
4፥15 ሮሜ16፥5፤ ቆላ2፥1
4፥16 1ተሰ3፥14፤ 1ጢሞ4፥13
4፥17 2ጢሞ4፥5፤ ፊሞ1፥2

*4፥8 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ስለእናንተ ... የውቅ ዘንድ

**4፥2 ነቅታችሁ በትጋት ጸልዩ፤** “በትጋት” (በግሪክ ቋንቋ፣ ፕሮስካርቴርዮ) ሲል “ጸንቶ መቆም”፣ “ተስፋ ባለመቍረጥ መቀጠል” ማለት ሲሆን፣ በታላቅ ፍላጎትና ስሜት በሐሳብ መጽናትን፣ ያለማሰለስ መጸለይን ያመለክታል። “ነቅታችሁ” (በግሪክ ቋንቋ፣ ግሬጎሬዮ) ሲል “በመንፈሳዊ ሕይወት ጥንቁቅና ዝግጁ ሆኖ መገኘት” ማለት ነው፤ (1) በጸሎት የተጠመደ ሕይወት እንዲኖረን፣ ከዚህ ዐላማ ፈቀቅ ሊያደርጉ የሚችሉ ብዙ ነገሮችን ነቅተን መጠበቅ አለብን። ሰይጣንና የሰባዊ ተፈጥሯችን ደካማነት ጸሎትን ችላ እንድንል ወይም በምንጸልይበት ጊዜ ሐሳባችን እንዲዛባና እንዲከፋፈል ለማድረግ ይሞክራሉ። ለክርስቲያናዊ ድል የሚያበቃ የጸሎት ሕይወት እንዲኖረን ራሳችንን በሥርዐት ማስሄድ አለብን። (2) ይህ በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁ በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩ ክርስቲያኖች ያደርጉት የነበረ አስፈላጊ የሆነ ልምምድ ነው፤ “እነርሱም ... በጸሎት ይተጉ ነበር” (ሐዋ 2፥42)፤ በትጋት የሚቀርበው ይህ ጸሎት፣ ጌታ ኢየሱስ ለእኛ ስላደረገው ነገር ምስጋና የሚቀርብበት መሆን አለበት።

**4፥3 በር እንዲከፍትልን፤** ሕይወቱንና አገልግሎቱን ለመምራት በር በመክፈትም ሆነ በመዝጋት የሚሠራው እግዚአብሔር ለመሆኑ ጳውሎስ ርግጠኛ ነበር። በሕይወታችንና በምስክርነታችን ፍሬያማ መሆን የምንችለው፣ በችሮታውና በቀጥታ በጕዳያችን ጣልቃ ከመግባቱ የተነሣ ነው። የአገልግሎት በር እንዲከፍትልንና የት ማገልገል እንዳለብን ምሪት እንድናገኝ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ አለብን (ከሐዋ 16፥6-10 ጋር ያነጻጽሩ)።

**4፥6 ንግግራችሁ ... በጸጋ የተሞላ ይሁን፤** የአንድ አማኝ ንግግር ደስ የሚያሰኝ፣ ውበት ያለው፣ በጎ የሆነና በጸጋ የተሞላ መሆን አለበት። ንግግራችን፣ የእግዚአብሔር ጸጋ በልባችን በሚሠራው ነገር ተሟሽቶ የወጣና እውነትን በፍቅር የሚገልጽ ንግግር መሆን ይገባዋል (ኤፌ 4፥15)። “በጨው እንደ ተቀመመ” ሲል ተገቢ የሆነ፣ ንጽሕና ያለውና ብልሹ ያልሆነ ማለት ሊሆን ይችላል (ከኤፌ 4፥29 ጋር ያነጻጽሩ)። በጸጋ የተሞላ ንግግር መናገር፣ የመስቀሉ ጠላቶች የሆኑ ሐሰተኛ አማኞችን መቃወም በሚያስፈልግበት ጊዜ፣ ጠንካራና የቍጣ ቃልን ከመናገር የሚያግድ አይደለም (ማቴ 23፤ ሐዋ 15፥1-2፤ ገላ 1፥9 ይመ)።

**4፥12 ዘወትር ስለ እናንተ በጸሎት እየተጋደለ፤** “እየተጋደለ” (በግሪክ ቋንቋ፣ አጎኒዞ) የሚለው ቃል ጥልቅ ፍላጎትንና በጸሎት እጅግ ከፍተኛ ጥረት ማድረግን ያመለክታል። በአዲስ ኪዳን ብዙ ታማኝ ክርስቲያኖች በትጋት መጸለይ ብቻ ሳይሆን (ቍ 2)፣ አጥብቀው በመጸለይ ከፍተኛ ትግል አድርገዋል። የቤተ ሰቦቻችን፣ የአብያተ ክርስቲያናትና የዓለም ፍላጎት ምን እንደሚመስል ካስተዋልን፣ ከዚህ ባላነሰ ሁኔታ በጸሎት እንድንቃትት እንጂ ያላንዳች ጭንቀት እንድንጸልይ አያደርግም። በጸሎት ትግላችን ውስጥ የክርስቶስ ኀይል በእኛ ውስጥ የሚሠራ መሆኑንና (ከ1፥29 ጋር ያነጻጽሩ) ዐላማውም በሌሎች አማካይነት የሚፈጸም እንደ ሆነ በመረዳት፣ በትጋት መጸለይ አለብን።

**4፥16 ይህች መልእክት ከተነበበችላችሁ በኋላ፤** የጳውሎስ መልእክቶች ከፍ ባለ ድምፅ በግልጽ የሚነበቡት ምእመናን ለአምልኮ በሚሰበሰቡበት ጊዜ ነበር። የቈላስይስ ክርስቲያኖች ይህን መልእክት ከተቀበሉ በኋላ፣ ለራሳቸው ገልብጠው በማስቀረት በአቅራቢያ ለምትገኘው ለሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ሳይልኩት አልቀረም። “በሎዶቅያ ያለችውን መልእክት” ሲባል ምናልባት ወደ ኤፌሶን የተላከውን መልእክት ማመልከት ሊሆን ይችላል (የኤፌሶንን መልእክት መግቢያ ይመ)።

አገልግሎት ከፍጻሜ ለማድረስ ተጠንቀቅ" በሉልኝ።
[18]ይህን ሰላምታ በገዛ እጄ የጻፍሁት እኔ ጳውሎስ ነኝ። እስራቴን አስቡ። ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።

4፥18 ሐሥ21፥33፤ 1ቆሮ16፥21፤

4፥18 1ጢሞ6፥21፤ ዕብ13፥3

**4፥18 እስራቴን አስቡ፤** ጳውሎስ በመጀመሪያ በሮም ታስሮ በነበረበት ጊዜ የጻፋቸው መልእክቶች የቈላስይስ፣ የፊልሞና፣ የኤፌሶንና የፊልጵስዩስ መልእክቶች ናቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ ለአራት ዓመት ወይም ከዚህም በላይ ያለአግባብ ታስሮ ቢቈይም እንኳ፣ መልእክቶቹ ግን በ“ምስጋና” (1፥3፡12፤ 2፥7፤ 3፥15፤ 4፥2)፣ በ“ጸጋ” (ኤፌ 1፥2፡6-7፤ 2፥5፤ 3፥2፤ 4፥7፤ 6፥24)፣ በ“ደስታ” (ፊል 1፥4፡18፤ 2፥2፤ 3፥1፤ 4፥1፡4) እና በ“ፍቅር” (ፊሞ 1፥5፡7፡9) ቃል ምን ያህል የተሞሉ እንደ ሆነ ያስተውሉ።